የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት



አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣የመጻሕፍተ መነኮሳትና የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ መምህር)

ሐምሌ ፳፫፣ ፳ ፻ ፲ ፯ ዓ.ም

መግቢያ

ይህ ስስ ቅጂ (Soft copy) የብሉይ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ስንማማር ከእያንዳንዱ ምዕራፍ የያዝኩት ማስታዎሻ ነው። ምናልባት ማስታዎሻውን በዚህ መልኩ ስጽፍ የገደፍኩት ፊደል፣ የተሳሳትኩት ቃል ካለ አንባቢ እያረመ እንዲያነበው አስቀድሜ አሳስባለሁ።

© በትረ ማርያም አበባው ካሣ

- የቴሌግራም ቻናሌ፡- በትረማርያም አበባው Betremariam Abebaw https://t.me/betremariyamabebaw ነው።

- ✓ የዩቲዩብ ቻናሌ:- We belong to Christ ንሕነ ዘክርስቶስ https://youtube.com/@edenawizechristos?si=6V4y-73OM3LTzhAf ነው።

- የፌስቡክ ገጼ፡- Betremariam Abebaw https://www.facebook.com/profile.php?id=100075547015721 ነው።

ማውጫ

፩. ኦሪት ዘፍጥረት.....6

፪. ኦሪት ዘፀአት.....13

፫. ኦሪት ዘሌዋውያን.....22

፬. ኦሪት ዘኍልቊ.....25

፭. ኦሪት ዘዳግም.....32

፮. መጽሐፈ ኢያሱ.....37

፯. መጽሐፈ መሳፍንት.....39

፰. መጽሐፈ ሩት.....43

፱. አንደኛ መጽሐፈ ሳሙኤል.....44

፲. ሁለተኛ መጽሐፈ ሳሙኤል.....48

፲፩. አንደኛ መጽሐፈ ነገሥት.....50

፲፪. ሁለተኛ መጽሐፈ ነገሥት.....54

፲፫. አንደኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል.....57

፲፬. ሁለተኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል.....59

፲፭. መጽሐፈ ኩፋሌ.....61

፲፮. መጽሐፈ ሄኖክ.....66

፲፯. መጽሐፈ ዕዝራ.....68

፲፰. መጽሐፈ ነህምያ.....69

፲፱. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል.....70

፳. መጽሐፈ ዕዝራ ካልእ.....71

፳፩. መጽሐፈ ጦቢት.....72

፳፪. መጽሐፈ ዮዲት.....73

፳፫. መጽሐፈ አስቴር.....74

፸፬. አንደኛ መጽሐፈ መቃብያን.....76

፸፭. ሁለተኛ መጽሐፈ መቃብያን.....79

፸፮. ሦስተኛ መጽሐፈ መቃብያን.....81

፸፯. መጽሐፈ ኢዮብ.....82

፸፰. መዝሙረ ዳዊት.....86

፸፱. መጽሐፈ ምሳሌ.....98

፹. መጽሐፈ ተግሣጽ.....105

፹፩. መጽሐፈ ጥበብ.....106

፹፪. መጽሐፈ መክብብ.....108

፹፫. መሓልየ መሓልይ.....109

፹፬. መጽሐፈ ሲራክ.....109

፹፭. ትንቢተ ኢሳይያስ.....120

፹፮. ትንቢተ ኤርምያስ.....126

፹፯. መጽሐፈ ባሮክ.....131

፹፰. ሰቆቃወ ኤርምያስና ተረፈ ኤርምያስ.....131

፹፱. ተረፈ ባሮክ.....132

፺. ትንቢተ ሕዝቅኤል.....133

፺፩. ትንቢተ ዳንኤል.....138

፺፪. ትንቢተ ሆሴዕ.....140

፺፫. ትንቢተ አሞጽ.....141

፺፬. ትንቢተ ሚክያስ.....142

፺፭. ትንቢተ ኢዩኤል.....143

፺፮. ትንቢተ ዮናስና ትንቢተ ናሆም.....143

፺፯. ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስና ትንቢተ ሐጌ.....144

፵፮. ትንቢተ ዘካርያስ.....145

፵፱. ትንቢተ ሚልክያስ.....146

የሐዲስ ኪዳን ማውጫ

፩. የማቴዎስ ወንጌል.....146

፭፩. የማርቆስ ወንጌል.....151

፭፪. የሉቃስ ወንጌል.....153

፭፫. የዮሐንስ ወንጌል.....156

፭፬. የሐዋርያት ሥራ.....159

፭፭. የሮሜ መልእክት.....163

፭፮. አንደኛ ቆሮንቶስ.....165

፭፯. ሁለተኛ ቆሮንቶስ.....168

፭፰. ገላትያ.....169

፭፱. ኤፌሶን.....170

፮. ፊልጵስዩስ.....172

፮፩. ቈላስይስ.....172

፮፪. አንደኛ ተሰሎንቄ.....173

፮፫. ሁለተኛ ተሰሎንቄ.....174

፮፬. አንደኛ ጢሞቴዎስ.....174

፮፭. ሁለተኛ ጢሞቴዎስ.....176

፮፮. ቲቶና ፊልሞና.....176

፮፯. ዕብራውያን.....177

፮፰. አንደኛ ጴጥሮስ.....180

፮፱. ሁለተኛ ጴጥሮስ.....181

፸. አንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዮሐንስ.....182

፳፩. የያዕቆብ መልእክትና የይሁዳ መልእክት.....183

፳፪. ራእየ ዮሐንስ.....184

አሪት ዘፍጥረት

ምዕራፍ 1-ፍጥረታትን ሁለ እግዚአብሔር እንደፈጠረ

-የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ መልካም እንደሆነ

-ፍጥረታት የተፈጠሩት ለእኛ ለሰው ልጆች ጥቅም እንደሆነ

-እግዚአብሔር ሰውን በአርዓያውና በመልኩ እንደፈጠረው

-ሰው ፍጥረታትን ይገዛ ዘንድ ከእግዚአብሔር ሥልጣን እንደተሰጠው

ምዕራፍ 2-እግዚአብሔር ሰባተኛዋን ቀን (ቅዳሜን) እንደባረካት

-እግዚአብሔር አዳምን በኤደን ገነት እንዳኖረው

-ከኤደን ገነት የሚወጡ ወንዞች አራት (ኤፌሶን፣ ግዮን፣ ጤግሮስ፣ኤፍራጥስ) እንደሆኑ

-አዳም ዕፀ በለስን እንዳይበላ በእግዚአብሔር መታዘዙ

-ከአዳም የጎን አጥንት ሔዋን መገኘቷ

ምዕራፍ 3-ሰይጣን በእባብ አድሮ አዳምና ሔዋንን ማሳሳቱ

-በአዳም በሔዋን በእባብ እርግማን መተላለፉ

-እግዚአብሔር ገነትን በኪሩቤል ማስጠበቁ

ምዕራፍ 4-አዳምና ሔዋን ልጆችን እንደወለዱ

-እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋት መቀበሉ የቃኤልን መሥዋዕት ግን አለመቀበሉ

-ቃኤል አቤልን መግደሉ በዚህም ምክንያት ተቅበዝባዥ መሆኑ

ምዕራፍ 5-ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ መሠወሩን

-የዐበይት አባቶችን የትውልድ ሀረግ

-ከአዳም እስከ ማየ አይኅ መጨረሻ 2254 ዓመት አካባቢ እንደሆነ (ደምሬ ያገኘሁት)።

ምዕራፍ 6-የሰው ልጆች በደልን ማብዛታቸው

-ኖኅ ግን ጻድቅ ሰው እንደነበረ

ምዕራፍ 7-የጥፋት ውሃ ምድርን ሁሉ ማጥፋቱ፣ -ኖኅና ቤተሰቦቹ ከጥፋት ውሃ እንደዳኑ

ምዕራፍ 8-የውሃውን መጉደል እንዲያይ ኖኅ ቁራን ቢልከው ቁራ አለመመለሱ፣

-ርግብን ቢልካት ግን የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ መመለሷ

- ኖኅ መሥዋዕትን እንዳቀረበ

ምዕራፍ 9-እግዚአብሔር ምድርን ዳግመኛ በማየ አይኅ እንደማያጠፋት ለኖኅ ቃል

-ኪዳን መግባቱና የቃል ኪዳኑ ምልክትም ቀስተ ደመና እንደሆነ።

-ከነዓን መረገሙ

-መስከር እንደማይገባ

ምዕራፍ 10-የኖኅ ልጆች የሴም፣ የያፌት፣ የካም የትውልድ ሐረጎች መጠቀሳቸውን።

ምዕራፍ 11-የዓለም ቋንቋ ሁሉ አንድ እንደነበረ

-በኋላ እግዚአብሔር የዓለምን ቋንቋ እንደለያየ

ምዕራፍ 12-እግዚአብሔር አብርሃምን ከዘመዶቹና ከአባቱ ተለይቶ እንዲወጣ ማድረጉ

-እግዚአብሔርም አብርሃምን እንደሚባርከው ታላቅ ሕዝብም እንደሚያደርገው መንገሩ፣ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ እንዳለው፣ አብርሃም መሠዊያ ሠርቶ የእግዚአብሔርን ስም እንደጠራ፣ ረኃብ ተከሥቶ አብርሃም ወደ ግብጽ ሀገር መሄዱ፣ ሣራ ሚስቱ ለማድረግ ያሰበ ፈርዖን መቅሠፍት እንደደረሰበት።

ምዕራፍ 13-አብርሃም ባዕለ ጸጋ እንደሆነ

-አብርሃም በከነዓን ምድር እንደኖረ

-እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩን እንደ ምድር አሸዋ እንደሚያበዛለት መንገሩ

ምዕራፍ 14-ሎጥ እንደተማረከና አብርሃም 318 ሰዎችን አስከትሎ ኖኅን ከምርኮ እንዳዳነው

-መልከጼዴቅ የልዑል እግዚአብሔር ካህን እንደሆነ

-መልከ ጼዴቅ አብርሃምን እንደባረከውና አብርሃም ለመልከጼዴቅ አሥራትን

እንደሰጠው

ምዕራፍ 15-እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘርህ እንደሰማይ ከዋክብት ይሆናሉ እንዳለው

-አብርሃም በእግዚአብሔር ማመኑና ይህ ጽድቅ ሆኖ እንደተቆጠረለት

- እግዚአብሔር ለአብርሃም አምላክህ እኔ ነኝ እንዳለው

ምዕራፍ 16-አብርሃም ከአጋር ይስማኤልን እንደወለደ

-ባሪያዋ አጋር በእመቤቷ በሣራ እንደኮራችባት

-መልአኩ አጋርን ለሣራ ዝቅ እንድትል መንገሩ

ምዕራፍ 17-ግዝረት በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ለተደረገ ቃል ኪዳን ምልክት መሆኑ

-አብርሃምና ሣራ ፈጽመው ካረጁ በኋላ ይስሐቅን መውለዳቸው።

-ይስማኤል በ13 ዓመቱ መገረዙ

ምዕራፍ 18-እግዚአብሔር ለአብርሃም በመምሬ ዛፍ ሥር እንደተገለጠለት

-አብርሃም ለሰዶም እንደማለደ

ምዕራፍ 19-ሎጥ መላእክትን በእንግድነት መቀበሉ

-ሎጥ ከነቤተሰቦቹ ከሰዶም እንደወጣ

-የሰዶምና የገሞራ በእሳት መጥፋት

-የሎጥ ሚስት ትእዛዝ አፍርሳ ወደኋላ በመመልከቷ የጨው ሐውልት ሆና መቅረቷን

ምዕራፍ 20-አብርሃም ጸልዮ አቤሜሌክን እንዳዳነው

ምዕራፍ 21-አሮጊቱ ሣራ ፀንሳ ይስሐቅን እንደወለደች

-እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘሩ በይስሐቅ እንደሚጠራለት መንገሩ

-በዐዘቅተ መሓላ አብርሃምና አቤሜሌክ እንደተማማሉ

-አብርሃም የእግዚአብሔርን ስም እንደጠራ

ምዕራፍ 22-አብርሃም በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ይስሐቅን ለመሥዋዕት ማቅረቡ

-በይስሐቅ ፈንታ እግዚአብሔር አንድ በግ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ መምጣቱና አብርሃም በይስሐቅ ፈንታ በጉን መሠዋቱ

-እግዚአብሔር አብርሃምን እንደባረከው

ምዕራፍ 23-አብርሃም ለሣራ መቃብር ድርብ ክፍል ያላትን የእርሻ ቦታ መግዛቱ

ምዕራፍ 24-ይስሐቅ ርብቃን እንዳገባትና ከእናቱ ሞት ኀዘን እንደተጽናና

ምዕራፍ 25-አብርሃም ከኬጡራ ልጆችን እንደወለደ

-አብርሃም ገንዘቡን ሁሉ ለይስሐቅ እንዳወረሰ

-አብርሃም ሸምግሎ በ175 ዓመቱ እንዳረፈ

-ይስሐቅ ከርብቃ ኤሳውንና ያዕቆብን መውለዱ

-ዔሳው ብኩርናውን በምስር ንፍሮ እንደሸጠ

ምዕራፍ 26-ረኃብ በምድር ላይ መከሠቱ

-ይስሐቅ ወደ ፍልስጥኤም ንጉሥ ወደአቤሜሌክ ወደ ጌራራ መሄዱ

-በውሃ ጉድጓድ ምክንያት የጌራራ እረኞችና የይስሐቅ እረኞች መጣላታቸው

-እግዚአብሔር ለይስሐቅ በዐዘቅተ መሐላ እንደተገለጠለት

-እግዚአብሔር ይስሐቅን ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ እንዳለው

-እግዚአብሔር ይስሐቅን ስለአባትህ ስለአብርሃም ብየ ዘርህን አበዛዋለሁ እንዳለው

-ይስሐቅ መሠዊያን ሠርቶ የእግዚአብሔርን ስም እንደጠራ።

-በጌራራ ሰዎችና በይስሐቅ መካከል ስምምነት እንደተደረገ

ምዕራፍ 27-ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው (እንደመረቀው)

-ያዕቆብ የዔሳውን ምርቃት መውሰዱ

ምዕራፍ 28-ያዕቆብ ወደ ላባ እንደሄደ

-ያዕቆብ በራእይ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ደርሶ እንዳየ

-ያዕቆብ ራእይ ያየበትን ቦታ የእግዚአብሔር ቤት (ቤቴል) እንዳለው፣ ያ ቦታ ቀድሞ ሎዛ ይባል እንደነበር

-ያዕቆብ ራእይ ካየበት ቦታ ሐውልት እንዳቆመ

ምዕራፍ 29-ያዕቆብ የእነራሔል በጎች ውሃን ይጠጡ ዘንድ የውሃውን ጉድጓድ ድንጋይ እንዳነሣው

-ያዕቆብ ራሔልን ለማግባት ስለራሔል ሰባት ዓመት ለአባቷ ማገልገሉ

-የራሔል አባት ያዕቆብ ሰባት ዓመት ካገለገለው በኋላ ልያን እንደሰጠው

-ያዕቆብ እንደገና ሰባት ዓመት አገልግሎ ራሔልን እንዳገባ

-ልያ ሮቤልን፣ ስምዖንን፣ ሌዊን፣ ይሁዳን እንደወለደች

ምዕራፍ 30-ያዕቆብ ከራሔል አገልጋይ ከባላ ዳንን፣ ንፍታሌምን እንደወለደ

-ያዕቆብ ከልያ አገልጋይ ከዘለፋ ጋድን፣ አሴርን እንደወለደ

-ልያ ይሳኮርን፣ ዛብሎንን፣ ዲናን እንደወለደች

-ራሔል ዮሴፍን እንደወለደች

ምዕራፍ 31-ያዕቆብ ከላባ ተለይቶ ልጆቹን ሚስቶቹን ይዞ ቀድሞ ራእይ ወዳየበት ቦታ መመለሱን

-ራሔል የአባቷን ጣዖት እንደሰረቀች

-ያዕቆብና ላባ እንደተስማሙ የስምምነታቸውን ምስክርም የድንጋይ ክምር አድርገው ወግረ ስምዕ እንዳሉት

-ያዕቆብ በተራራ ላይ መሥዋዕትን እንደሠዋ

ምዕራፍ 32-ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከትመው እንዳየ፣ ያየበትን ቦታም ተዓይን እንዳለው

-ያዕቆብ ከዔሳው ጋር በሰላም ለመገናኘት አስቀድሞ እጅ መንሻ መስደዱ

-ያዕቆብ በራእይ ከአንድ ሰው ጋር ትግል እንደገጠመ፣ ያንን ሰውም ካልባረከኝ አልለቅህም እንዳለው፣ ያም በሰው አምሳል የተገለጠው እግዚአብሔር እንደሆነና ስሜ መንክር (ድንቅ) ነው እንዳለው

ምዕራፍ 33-ያዕቆብ ከዔሳው ጋር በሰላም እንደተገናኘ

-ያዕቆብ መሠዊያ ሠርቶ የእስራኤልን አምላክ እንደጠራ

ምዕራፍ 34-የያዕቆብን ልጅ ዲናን ሴኬም እንዳስነወራት

-ለዲና ወንድሞቿ ስምዖንና ሌዊ እንደተበቀሉላት

ምዕራፍ 35-እግዚአብሔር ያዕቆብን እስራኤል እንዳለው

-እግዚአብሔር ያዕቆብን ነገሥታት ከጉልበትህ ይወጣሉ እንዳለው

-ራሔል ብንያምን ስትወልድ በወሊድ ሞክንያት እንደሞተች

-ያዕቆብ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ከመሥራቱ በፊት ጣዖታትን ከዛፍ በታች እንደቀበራቸው

ምዕራፍ 36-የዔሳውን የትውልድ ሐረግ

ምዕራፍ 37-ያዕቆብ ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ አብልጦ ይወደው እንደነበረ

-በዮሴፍ ወንድሞቹ እንደቀኑበት

-ዮሴፍ ሕልም እንዳየ

-ዮሴፍን ይገድሉት ዘንድ ወንድሞቹ እንደተማከሩ፣ ነገር ግን ሳይገድሉት ልብሱን ገፈው ለይስማኤላውያን እንደሸጡት፣ ይስማኤላውያን ደግሞ ለጲጥፋራ እንደሸጡት

-የዮሴፍ ወንድሞች ልብሱን በደም ነክረው ለያዕቆብ አሳይተው ዮሴፍ ሞተ እንዳሉት፣ በዚህም ያዕቆብ በጣም እንዳዘነ

ምዕራፍ 38-የይሁዳ ልጅ ዔር በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንደነበረና እግዚአብሔርም እንደቀሠፈው

-አውናን ለወንድሙ ዘር እንዳይተካ ዘሩን በምድር ያፈስሰው እንደነበረ

-ይሁዳ ሳያውቅ ከልጁ ሚስት ከትእማር እንደደረሰ

-ትእማር ከይሁዳ ዛራንና ፋሬስን እንደወለደች

ምዕራፍ 39-እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበረ የዮሴፍ ሥራው ሁሉ እንደተከናወነለት

-ጲጥፋራ ዮሴፍን በገንዘቡ ላይ ሁሉ እንደሾመው

-የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ለዝሙት እንደፈለገችውና ዮሴፍ ግን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ ብሎ እንቢ እንዳላት፣ በዚህም ምክንያት ሊደፍረኝ ነበር ብላ ዋሽታ እስር ቤት እንዳሳሰረችው

-ዮሴፍ በእስር ቤት ሳለ የግዞት ቤቱ ጠባቂ አለቃ ዮሴፍን እንደሾመው

ምዕራፍ 40-ዮሴፍ እስር ቤት ሳለ የሁለት ሰዎችን ሕልም እንደተረጎመ

-ዮሴፍ ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር የሰጠው እንደሆነ መናገሩ

ምዕራፍ 41-ፈርዖን ሕልም እንዳየ፣ የግብጽ ሕልም ተርጓሚዎችም የፈርዖንን ሕልም መተርጎም እንዳቃታቸው

-ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም እንደተረጎመለት

-ዮሴፍ እግዚአብሔር ከገለጸለት ሰው በቀር ሕልምን መተርጎም የሚችል እንደሌለ ለፈርዖን መንገሩን

-ፈርዖን ዮሴፍን ከእርሱ በታች ያለ የግብፅ አዛዥ አድርጎ እንደሾመው

-ዮሴፍ አስኔትን አግብቶ ምናሴንና ኤፍሬምን እንደወለደ

-በምድር ላይ ረኀብ ጸንቶ ስለነበር ሀገሮች ሁሉ ከግብፅ እህልን ይገዙ ዘንድ ወደ ግብፅ መሄዳቸው

ምዕራፍ 42-በከነዓን ሀገር ረኃብ ስለሆነ የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመሸመት ወደ ግብፅ መሄዳቸውን

-የዮሴፍ ወንድሞች ለዮሴፍ እንደሰገዱለት

-ወንድሞቹ ዮሴፍ እንደሞተ ለዮሴፍ እንደነገሩት

ምዕራፍ 43-የዮሴፍ ወንድሞች ብንያምን ይዘውት እንደመጡ

-ስለአባቱ ስለያዕቆብ ደኅንነት መጠየቁን

-ዮሴፍ አፍቅሮ ጸላእትን እንዳስተማረን

ምዕራፍ 44-ዮሴፍ ወንድሞቹን እንደፈተናቸው

ምዕራፍ 45-ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ እንደገለጠ

-የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍ እንደሆነ ሲያውቁ እንደደነገጡ

-አባቱን ያዕቆብን ይዘውት እንዲመጡ መጠየቁ

-ያዕቆብ የዮሴፍን በሕይወት መኖር ሰምቶ ደስ እንዳለው

ምዕራፍ 46-ያዕቆብ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንደሠዋ

-ያዕቆብ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ግብፅ መሄዱ

-ዮሴፍ አባቱን ባየው ጊዜ ደስ ብሎት እንዳቀፈው

ምዕራፍ 47-ዮሴፍ የዘመዶቹን መምጣት ለፈርዖን መናገሩ

-ፈርዖን የያዕቆብን እድሜውን እንደጠየቀው

-ፈርዖን የራምሴ ምድርን ለነያዕቆብ ርስት አድርጎ እንደሰጣቸው

-በዮሴፍ መልካም አመራር ግብፃውያን ከረኀብ እንደዳኑ

ምዕራፍ 48-ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ኤፍሬምንና ምናሴን እንደባረከ

ምዕራፍ 49-ያዕቆብ ልጆቹን እንደመረቃቸው

-ያዕቆብ ልጆቹን ስሞት በአባቶቼ መቃብር ከአባቶቼ ጋር ቅበሩኝ ማለቱ

ምዕራፍ 50-በያዕቆብ ሞት ልጆቹ እንዳለቀሱ

-ዮሴፍ የልጅ ልጅ አይቶ መሞቱን

-ዮሴፍ ከግብፅ ስትወጡ አጥንቴን ከእናንተ ጋር ይዛችሁ ውጡ እንዳለ

ኦሪት ዘፀአት

ምዕራፍ 1 -ያዕቆብና 70 የሚደርሱ ከእርሱ የሚወለዱ ቤተሰቦቹ (ልጆቹ የልጅ ልጆቹ) ወደ ግብፅ እንደሄዱ

-የያዕቆብ ዘሮች በግብፅ ሀገር እንደበዙ

-የዮሴፍን ውለታ የዘነጋ ሌላ ፈርዖን በግብፅ መንገሡ

-ግብጻውያን እስራኤላውያንን ይጸየፏቸው እንደነበረ

-ግብጻውያን እስራኤላውያንን በባርነት እንደገዟቸውና ያስመርሯቸው እንደነበረ

- ፈርዖን ሲፓራና ፎሓ የሚባሉ አዋላጆችን ዕብራውያት ሴቶችን ሲያዋልዱ ወንድ ከሆነ እንዲገሉት ማዘዙን

-ሲፓራና ፎሓ እግዚአብሔርን ፈርተው የግብጽ ንጉሥ እንዳዘዛቸው አለማድረጋቸው በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለአዋላጆች መልካም እንዳደረገላቸው

ምዕራፍ 2-እንበረም ከሌዊ ወገን ከምትሆን ሴት ወንድ ልጅን (ሙሴን) እንደወለደ

-ሕፃኑ ሙሴ እንዳይገደል ፈርታ እናቱ በደንገል ሣጥን አድርጋ ወንዝ ዳር እንዳስቀመጠችውና የሙሴ እኅት ትጎበኘው እንደነበረ

- የፈርዖን ልጅ ሕፃን በወንዝ ዳር ሲያለቅስ ሰምታ እንዳስመጣችውና ልጇ እንዳደረገችው

-የሙሴ እናት እናቱ መሆኗን ለፈርዖን ልጅ ሳታስታውቅ ታጠባው እንደነበረ

- ሙሴን ከውሃ አገኘሁት ስትል የፈርዖን ልጅ ሙሴ እንዳለችው

- ሙሴ አድጎ የእስራኤላውያንን መከራ እንደተመለከተ

- ሙሴ አንድ ግብጻዊ አንዱን ዕብራዊ ሲመታ ባየው ጊዜ ለዕብራዊው አብሮ ግብፃዊውን እንደገደለው

- ሙሴ ሁለት ዕብራውያን ሲገጥሙ ባየ ጊዜ ተዉ እንዳላቸው፣ በዚህ ጊዜ አንደኛው ዕብራዊ እንደ ግብጻዊው ልትቀብረኝ ነው ወይ ማለቱና ሙሴም ነገሩ ተሰምቶብኛልን ብሎ ፈርቶ ኮብልሎ ወደ ምድያም መሄዱ

-ፈርያን ሙሴን ሊገድለው እንደፈለገ

- ሙሴ የዮቶርን ልጆች ከእረኞች እንዳዳናቸው

-ሙሴ ከራጉኤል ጋር እንደኖረና ራጉኤልም ልጁን ሲፓራን ለሙሴ እንዳጋባው

-የእስራኤል ልጆች ከባርነት የተነሣ እንደጮሁና ጩኸታቸውንም እግዚአብሔር እንደሰማ

-እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ የገባውን ቃል ኪዳን እንዳሰበና የእስራኤልን ልጆች እንደጎበኛቸው

ምዕራፍ 3- ሙሴ የአማቱን የዮቶርን በጎች ይጠብቅ እንደነበረ

-ሙሴ ወደእግዚአብሔር ተራራ ወደኮሬብ እንደሄደ

-የእግዚአብሔር መልአክ ለሙሴ በእሳት ነበልባል በቁጥቋጦ መካከል እንደታየው

-ሙሴ ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል እንዳየ

-እግዚአብሔር ሙሴን የቆምክባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን አውልቅ እንዳለው

-እግዚአብሔር የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ እንደሆነ ለሙሴ መንገሩ

-ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት እንዲያድናቸውና ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደ ከነዓን እንዲያስገባቸው በእግዚአብሔር መላኩን

-እግዚአብሔር ሙሴን እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ እንዳለው

-እግዚአብሔር ያለና የሚኖር መሆኑን ለሙሴ መናገሩ

ምዕራፍ 4-እግዚአብሔር ለሙሴ በትሩን እባብ አድርጎ እንዳሳየው እንደገና በትር አድርጎ ማሳየቱ

-ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እጁን ወደ ብብቱ ሲያስገባ እጁ ለምጽ እንደሆነና መልሶ ሲያስገባ እንደዳነ

-እግዚአብሔር ለሙሴ እኒህን ሁለት ምልክቶችን አድርጎ ዕብራውያንን እንዲያሳምናቸው ማድረጉ

-ሙሴ እግዚአብሔርን አፈ ኮልታፋ ስለሆነ መናገር የሚችል የምትልከው ሌላ ሰው ፈልግ እንዳለው

-እግዚአብሔር ለሙሴ አሮን ይናገርልህ እንዳለው

-ሙሴ ወደአማቱ ዮቶር ሄዶ ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ወደ ግብጽ እንደሄደ

-ሙሴ ያችን የእግዚአብሔር በትር ይዞ ወደ ግብጽ እንደሄደ

-የእግዚአብሔር መልአክ ሙሴን ሊገድለው እንደፈለገና የሙሴ ሚስት ሲፓራ ልጆቿን ስትገዝር መዓቱ እንደራቀለት

- እግዚአብሔር አሮን ሙሴን በምድረ በዳ እንዲያገኘው መንገሩ

-ሕዝቡ ተአምራቱን አይተው እንዳመኑ

ምዕራፍ 5-ሙሴና አሮን ወደፈርዖን ገብተው በምድረ በዳ በዓል ያደርግልኝ ዘንድ ሕዝቤን ልቀቅ ብሎሀል እግዚአብሔር እንዳሉት

-ፈርዖን እግዚአብሔርን አላውቅም እስራኤልንም አልለቅም ማለቱ

-ፈርዖን በእስራኤላውያን ላይ ሥራ እንዳከበደባቸው

ምዕራፍ 6 -እግዚአብሔር ለሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጻውያን ተገገርነት አወጣችኋለሁ ከባርነታችሁም አድናችኋለሁ በተዘረጋ ክንድ፣ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ ለእኔም ሕዝብ እንድትሆኑ እቀበላችኋለሁ ብሏችኋል በላቸው እንዳለው

-እስራኤላውያን ከሰውነታቸው መጨነቅ የተነሣ ከሥራቸው ክብደት የተነሣ የሙሴን ቃሉን እንዳልሰሙት

-የሙሴና የአሮን ትውልድ

-የሙሴ እናት ዮካብድ እንደምትባል

-እግዚአብሔር የምነግርህን ሁሉ ለፈርዖን ንገረው ብሎ ለሙሴ መንገሩ

ምዕራፍ 7-እግዚአብሔር ሙሴን ለፈርዖን አምላክ አድርጌሀለሁ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሀል እንዳለው

-እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አጸናለሁ፣ ድንቅ ተአምራትንም በግብጽ ላይ አደርጋለሁ እንዳለ

-ሙሴና አሮን ፈርዖንን በተናገሩት ጊዜ የሙሴ 80 ዓመት የአሮን 83 ዓመት ሆኗቸው እንደነበረ

-ሙሴ በትሩን በተአምራት እባብ እንዳደረጋትና የግብጽ ጠንቋዮችም እያንዳንዳቸው በትራቸውን እባብ እንዳደረጉ

-የሙሴ በትር እባብ ሆና የጠንቋዮችን የምትሐት እባብ እንደዋጠቻቸው

-ሙሴ በበትሩ የወንዙን ውሃ ወደ ደም እንደለወጠውና በዚህም ምክንያት በወንዙ የነበሩ ዓሣዎች እንደሞቱ፣ የግብጽ ጠንቋዮችም በአስማታቸው እንዲሁ እንዳደረጉ

ምዕራፍ 8-ሙሴ በበትሩ በወንዞቹ፣ በመስኖዎቹና በውሃ ማከማቻዎቹም ላይ እጁን ዘርግቶ ጓጉንቸሮችን እንዳወጣ፣ የግብጽ ጠንቋዮችም በአስማታቸው እንዲሁ እንዳደረጉ

-ፈርዖን መዓቱ እንዲርቅለት እነሙሴን መጠየቁና ሕዝበ እስራኤልንም እለቃለሁ እንዳለ።

-ሙሴ ጸልዮ መዓቱን እንዳራቀውና ፈርዖን ግን መልሶ ልቡ በክፋት እንደጸና

-ሙሴ በትሩን ሲዘረጋ ቅማል በግብጽ ሀገር በሰው በእንስሳ ላይ እንደወጣ፣ የግብጽ ጠንቋዮች ግን በአስማታቸው ይህንን ለማድረግ ሲሞክሩ ማድረግ እንዳልቻሉ

-ጠንቋዮች የቅማሉን መቅሠፍት የእግዚአብሔር ጣት እንዳሉት

-እግዚአብሔር በግብጽ ላይ ተናካሽ የውሻ ዝንብ እንዳመጣ

ምዕራፍ 9-እግዚአብሔር የግብጽ ከብቶች ሁሉ እንዲሞቱ ማድረጉ፣ የእስራኤላውያን ከብቶች ግን እንዳልጠፉ

-ሙሴ አመድ በፈርዖን ፊት ወስዶ እንደበተነና በሰውና በእንስሳት ላይም ቁስልን እንዳመጣ

-እግዚአብሔር በግብጽ ላይ በረዶ ነጎድጓድና እሳት አውርዶ በሜዳ ያለው ሰውንና እንስሳን ሁሉ እንደመታ፣ የእስራኤል ልጆች በነበሩባት ሀገር ግን ይህ እንዳልሆነ

-ፈርዖን በደልኩ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው እኔና ሕዝቤ ኃጢአተኞች ነን ማለቱ። እነሙሴ ጸልየው መቅሠፍቱን ካራቁለት በኋላ ግን እንደገና ልቡ በክፋት እንደፀና

ምዕራፍ 10-ሙሴ በትሩን ወደሰማይ በዘረጋ ጊዜ እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ አንበጣን እንዳመጣና አንበጣውም የምድሩን ገጽ ሁሉ እንደሸፈነው

-ፈርዖን መልሶ በድያለሁ ተጸጸትኩ መቅሠፍቱን አርቁልኝ ማለቱ

-ሙሴ መቅሠፍቱን ካራቀ በኋላ ፈርዖን መልሶ ልቡ በክፋት እንደፀና

-ሙሴ በትሩን ወደሰማይ በዘረጋ ጊዜ ለሦስት ቀን ጽኑ ጨለማና ጭጋግ በግብጽ ላይ መምጣቱ፣ ለእስራኤል ልጆች ግን ብርሃን እንደነበራቸው።

ምዕራፍ 11-እግዚአብሔር በግብጻውያን ፊት ለሕዝቡ ለእስራኤል ሞገስን እንደሰጠና እስራኤላውያን የተለያዩ ዕቃዎችንና ልብሶችን ከግብጻውያን እንደተዋሱ

-ሙሴ በግብጻውያንና በፈርዖን በሹሞቹም ፊት እጅግ የከበረ ሰው እንደነበረ

ምዕራፍ 12-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የሚያዝያ ወር የመጀመሪያ ወራቸው እንዲሆን መንገሩ

-ሚያዝያ 10 እያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ ጠቦት ወስደው ሚያዝያ 14 እንዲያርዱት፣ ከበጉ ደም በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን እንዲቀቡት እግዚአብሔር ማዘዙ

-የበጉን ሥጋ ሚያዝያ 14 ሌሊት እንዲበሉ፣ ሲበሉም ጥሬ ሥጋን እንዳይበሉ፣ በእሳት የተጠበሰውን እንዲበሉት፣ ከበጉ ሥጋ እስከ ጠዋት ምንም እንዳያስተርፉ መንገሩ

-የበጉን አጥንቱን እንዳይሰብሩ መንገሩ

-የበጉን ሥጋ ሲበሉም ወገባቸውን ታጥቀው፣ ጫማቸውን ተጫምተው፣ በትራቸውን በእጃቸው ይዘው እየቸኮሉ እንዲበሉት መንገሩ

-ሚያዝያ 14 የእግዚአብሔር ፋሲካ እንደሆነ መነገሩ፣ በዚሁ ቀን እግዚአብሔር የግብጻውያንን በኩር በኩራቸውን ከሰው እስከ እንስሳ እንዳጠፋ

-እግዚአብሔር የደሙን ምልክት አይቶ እስራኤላውያንን እንደማያጠፋ መናገሩ

-እግዚአብሔር የፋሲካ በዓል መታሰቢያ እንዲሆናቸውና ለልጅ ልጆቻቸው እስከ ዘለዓለም ሥርዓት እንዲሆናቸው መናገሩ

-እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሰባት ቀን (ከሚያዝያ 14 ቀጥሎ) የቂጣ በዓልን በቂጣ እንዲያከብሩ መንገሩ፣ በዚህ በዓለም በነፍስ ከሚሠራው ሥራ ሁሉ በቀር ማናቸውንም ሥራ እንዳይሠሩ መንገሩ፣ በዚህ በዓል እርሾ ያለበትን ማንኛውንም ነገር እንዳይቀምሱ መንገሩ

-ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዲወጡ ማዘዙ

-እስራኤላውያን ግብጻውያንን በዝብዘው እንደወጡ

-እስራኤላውያን ከ600,000 በላይ ሆነው እንደወጡ

-የፋሲካውን በግ የተገረዙት ብቻ እንዲበሉ መታዘዛቸው

ምዕራፍ 13-እግዚአብሔር ከእንስሳትም ከሰውም መጀመሪያ የተወለደውን በኩር ለእኔ ይለይልኝ ማለቱ

-ወንድ ሆኖ ማኅፀንን የከፈተው ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሠዋል። የሰው በኩር ደግሞ በገንዘብ ይዋጃል።

-የበኩር ልጅ ለእግዚአብሔር እንደሚሆን መነገሩ

-ሙሴ የዮሴፍን ዐጽም ይዞ ጉዞ ወደከነዓን መጀመሩ

-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ቀን በዐምደ ደመና፣ ሌሊትም በዐምደ እሳት ይመራቸው እንደነበረ

ምዕራፍ 14-ፈርዖን እስራኤላውያንን እንዲወጡ ካዘዙ በኋላ እንደገና መከተላቸው

-ሙሴ በበትሩ ባሕረ ኤርትራን መክፈሉ፣ ውሃው ግራና ቀኝ እንደግድግዳ መቆሙና እስራኤላውያን እንደተሻገሩ

-ፈርዖን ከነሠራዊቱ በኤርትራ ባሕር እንደሰጠመ

ምዕራፍ 15-የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዳቀረቡ

-የአሮን እኅት ነቢዪት ማርያም ከበሮ በእጇ ወስዳ፣ ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዝማሬ በኋላዋ መጥተው ለእግዚአብሔር እንደዘመሩ

-ሙሴ ወደእግዚአብሔር ጮኾ መራራውን ውሃ አጣፍቶ ለሕዝቡ መስጠቱ።

ምዕራፍ 16-እስራኤላውያን በምግብ ምክንያት በሙሴና በአሮን ላይ ማንጎራጎራቸው

-እግዚአብሔር ካዘዛቸው ውጭ ምግብ ያሳደሩ ሰዎች ምግቡ እንደተበላሸባቸው

-እስራኤል ከሰማይ የወረደላቸውን መና አርብ አርብ የቅዳሜውን ጨምረው እንዲሰበስቡና ቅዳሜ ግን ምንም እንዳይሰበስቡ መነገሩ

-በሰንበት ቅዳሜ መና ሊሰበስቡ የወጡ ሰዎች መና እንዳላገኙ

-መና መልኩ እንደ ድንብላል ነጭ ሲሆን ጣዕሙ ደግሞ እንደማር እንጆራ እንደሆነ

-ሙሴ የወርቅ መሶብ ወስዶ አንድ ጎሞር ሙሉ መና ለልጅ ልጆች ይጠበቅ ዘንድ ማስቀመጡ

-እስራኤላውያን ከነዓን እስኪገቡ ድረስ ለአርባ ዓመት መና እንደበሉ

ምዕራፍ 17-ሙሴ ከዓለት ላይ በተአምራት ውሃ አፍልቆ ሕዝቡን እንዳጠጣ

-ኢያሱ ከአማሌቃውያን ጋር እንደተዋጋ

-ከአማሌቃውያን ጋር በነበረው ጦርነት ሙሴ እጁን ሲያነሣ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ እንደነበረ፣ እጁን ሲያወርድ ግን አማሌቃውያን ድል ያደርጉ እንደነበረ

-እስራኤላውያን እንዲያሸንፉ የሙሴ እጅ ሲከብድባቸው ድንጋይ ወስደው በበታቹ አኑረው ግራና ቀኝ ሆነው አሮንና ሖር ይደግፉት እንደነበረ

ምዕራፍ 18

-አማቱ ዮቶር የሙሴን ሚስትና ልጆቹን ይዞ ወደሙሴ መጌዱ

-ዮቶር እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ተአምር ሰምቶ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን መሠዋቱ

-ሙሴ በሕዝቡ ላይ ይፈርድ እንደነበረ

-ዮቶር ሙሴን አማካሪዎችን እንዲሾምና በፍርድ እንዲያግዙት መምከሩ፣ ሙሴም የዮቶርን ምክር ሰምቶ ተግባራዊ ማድረጉ

ምዕራፍ 19-እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ሕዝቦች እንደሚሆኑ መነገሩ

-እስራኤላውያን ሁሉም ራሳቸውን አንጽተው ልብሳቸውን አጥበው በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር በሲና ተራራ እንደተገለጠላቸው

-እስራኤላውያንን ወደሲና ተራራ ከመቅረባቸው በፊት ሦስት ቀን ከሴቶቻቸው ጋር እንዳይገናኙ እግዚአብሔር ማዘዙ፣ እንዳይቀሠፉ ተራራውን ማንም እንዳይነካው ማዘዙ

-በሲና ተራራ ነጎድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና፣ የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅም እንደተሰማ በዚህም ምክንያት ሕዝቡ እንደደነገጠ

-ሙሴ ወደተራራው ራስ እንደሄደና ከእግዚአብሔር ጋር እንደተነጋገረ

ምዕራፍ 20-ከእግዚአብሔር ውጭ አምላክ እንደሌለ

-የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት እንደማይገባ

-ሰንበትን ማክበር እንደሚገባ

-ዕድሜያችን ይረዝም ዘንድ አባትና እናትን ማክበር እንደሚገባ

-መግደል፣ መስረቅ፣ ማመንዘር፣ በባልንጀራ ላይ በሐሰት መመስከርና የባልንጀራን ገንዘብ መመኘት እንደማይገባ

-ሕዝቡ ፈርተው ሙሴን አንተ ከእኛ ጋር ተናገር። ነገር ግን እንዳንሞት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር አይናገር እንዳሉ

-መሥዋዕትን ሲሠው እግዚአብሔር እንደሚባርክ

ምዕራፍ 21-ስለባርነት ሥርዓት መገለጹ

-ሰውን የገደለ ሰው በብሉይ ሕግ ይገደል እንደነበረ

-እናቱንና አባቱን የሚሳደብ በብሉይ ሕግ በሞት ይቀጣ እንደነበረ

-በተለያየ ዐመፅ ያሉ ሰዎች ስለሚቀጡበት ቅጣት መነገሩ

ምዕራፍ 22-አንድ ሰው በሬ በግ ቢሰርቅ በአንድ በሬ ፋንታ አምስት በሬዎችን፣ በአንድ በግም ፋንታ አራት በጎች እንዲከፍል መደረጉ

-ስለሌባ ቅጣት መነገሩ

-የሰውን አዝመራ ያስበሉ ሰዎች ቅጣት መነገሩ

-ያልታጨችን ድንግል አታሎ ከእርሷ ጋር የተኛ ሰው ሚስት አድርጎ እንዲይዛት

-ከመተተኛ ጋር አንድ መሆን እንደማይገባ

-ከእንስሳት ጋር ግንኙነት የፈጸመ ቅጣቱ ሞት እንደነበረ

ምዕራፍ 23-ሐሰተኛ ወሬን መቀበል እንደማይገባ

-ፍርድን ለማጣመም ከብዙ ሰው ጋር መጨመር እንደማይገባ

-የጠላትህን ገንዘብ ጠፍቶ ብታገኘው መመለስ እንደሚገባ

-በፍርድ ጊዜ ማዳላት እንደማይገባ

-ጉቦ የዓይናማዎችን ዓይን እንደሚያሣውር

-በስደተኞች ላይ ግፍን ማድረግ እንደማይገባ

-ስድስት ዓመት ምድርን ዘርቶ በሰባተኛው ዓመት ምድርን ከማረስ መከልከል እንደሚገባ በብሉይ ኪዳን መነገሩ

-በዓመት ሦስት ጊዜ ለእግዚአብሔር በዓል ማድረግ እንደሚገባ

-በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጅን መታየት እንደማይገባ

-በዓመት ሦስት ጊዜ ወንዱ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዲታይ መታዘዙ

-የምድርን ፍሬ በኩራት ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን ቢያመልኩት እንደሚባርክ

ምዕራፍ 24-እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያለንን እናደርጋለን ማለታቸው

-እግዚአብሔር ለሙሴ ጽላትን እንደሚሰጠው መንገሩ

ምዕራፍ 25-እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር መባ እንዲያቀርቡ መታዘዛቸው

-ጽላቱ የሚቀመጥበትን ታቦት ሙሴ እንዲሠራ መታዘዙ

-ሙሴ መቅረዝን እንዲሠራ መታዘዙ

ምዕራፍ 26-እግዚአብሔር ለሙሴ የደብተራ ኦሪትን አሠራር ማሳየቱ

ምዕራፍ 27-እግዚአብሔር ለሙሴ የመሠዊያውን አሠራር እንደነገረው

-የመብራት ዘይትን በደብተራ ኦሪት አሮንና ልጆቹ ከማታ እስከ ማለዳ ድረስ እንዲያበሩ መታዘዛቸው

ምዕራፍ 28-እግዚአብሔር ለሙሴ ስለልብሰ ተክህኖ አሠራር መንገሩ

ምዕራፍ 29-አሮንና ልጆቹ ክህነት እንደተሾሙ

-በደብተራ ኦሪት ስለሚቀርበው መሥዋዕት መነገሩ

ምዕራፍ 30-የመታጠቢያ ሰን እንዲሠራ እግዚአብሔር ለሙሴ መንገሩ

ምዕራፍ 31-ባስልኤልና ኤልያብ ደብተራ ኦሪትንና ሌሎችንም ንዋያተ ቅድሳት እንዲሠሩ በእግዚአብሔር መመረጣቸው

-እስራኤላውያን ሰንበትን እንዲያከብሩ እግዚአብሔር መናገሩ

-እግዚአብሔር ሁለቱን የምስክር ጽላት ለሙሴ እንደሰጠው

ምዕራፍ 32-ሙሴ በተራራው እንደቆየ ባዩ ጊዜ እስራኤላውያን አሮንን አማልክትን ሥራልን እንዳሉትና እንደሠራላቸው

-እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝብህ በደሉኝ እንዳለው

-ሙሴ ለእስራኤላውያን እንዳይጠፉ እግዚአብሔርን እንደማለደና እግዚአብሔርም የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ እስራኤልን ሳያጠፋቸው መቅረቱ

-ሙሴ እስራኤላውያን ያመለኩትን ጣዖት በእሳት እንዳቀለጠውና ፈጭቶ እንዳደቀቀው ከዚያም እስራኤላውያንን እንዳጠጣቸው

-ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤልን ይቅር እንዲል መለመኑና ይቅር ካላላቸው ግን ከሕይወት መጽሐፍ እንዲደመስሰው መጠየቁ

ምዕራፍ 33-ሙሴ እግዚአብሔርን ፊትህን አሳየኝ እንዳለውና እግዚአብሔር ግን ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም እንዳለው

-እግዚአብሔር ሙሴን ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም እንዳለው

ምዕራፍ 34-እግዚአብሔር ሙሴን ሁለት የድንጋይ ጽላት እንደፈተኞቹ አድርጎ እንዲቀርጽ መንገሩና በጽላቶቹ ትእዛዛቱን እንደጻፈባቸው

ምዕራፍ 35-እስራኤላውያን ለደብተራ ኦሪትና ለሌሎችም ንዋያት መሥሪያ በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር መስጠታቸው

ምዕራፍ 36-ደብተራ ኦሪት መሠራቷ

ምዕራፍ 37-የቃል ኪዳኑ ታቦትና መቅረዙ መሠራታቸው

ምዕራፍ 38-መሠዊያ መሠራቱ

ምዕራፍ 39-የልብስ ተክህኖ መሠራት

ምዕራፍ 40-ደብተራ ኦሪትና በውስጧ ያሉት ንዋያት ተሠርተው መፈጸማቸው

-ድንኳኗ የእግዚአብሔርን ክብር እንደተሞላች

ኦሪት ዘሌዋውያን

ምዕራፍ 1፡- -እስራኤል ለእግዚአብሔር መባ የሚያቀርብ ሰው ቢኖር መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች አቅርቡ መባላቸው

-የሚቀርበው የሚቃጠል መሥዋዕት ነውር የሌለበት ተባዕት እንዲሆንና ሲያቀርቡም በምስክሩ ድንኳን ፊት እንዲሆን መነገሩ

-መሥዋዕቱ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ እርሱም ያስተሰርይለት ዘንድ እጅን በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ መጫን እንደሚገባ

-መሥዋዕቱ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚታረድ

ምዕራፍ 2፡- -ማንኛውም ሰው ቍርባን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲሆን ቢያቀርብ ቁርባኑ ከመልካም ስንዴ ዱቄት እንዲሆን መነገሩ፣ በዱቄቱም ላይ ዘይትን ማፍሰስ ዕጣንን መጨመር እንደሚገባ

-ከመሥዋዕቱ የተረፈው ለአሮንና ለልጆቹ እንደሚሆኑ

-ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የእህል ቁርባን ሁሉ እርሾ እንዳይሆንበት መነገሩ

-የሚቀርበው መሥዋዕት ሁሉ በጨው እንደሚጣፈጥ

ምዕራፍ 3፡- -ስለ ደኅንነት መሥዋዕት አቀራረብ

ምዕራፍ 4፡- -ስለኃጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት አቀራረብ

-እስራኤላውያን ኃጢአት ከሠሩ ስለሠሩት ኃጢአት ነውር የሌለበትን ወይፈን ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርቡ

ምዕራፍ 5፡- -ሰው ዐውቆም ሳያውቅም ኃጢአትን ቢሠራና በሥራው ቢጸጸት እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር እንደሚልለት

ምዕራፍ 6፡- -ሰው ኃጢአትን ሠርቶ ከነበረ ንስሓ መግባትና የኃጢአት መሥዋዕት መሠዋት እንደሚገባው

-የሰረቀ ሰው ቢኖር ለባለቤቱ እንዲመልስ

-የመሠዊያውን አመድ ከሰፈሩ ወደውጭ ማውጣት እንደሚገባ

ምዕራፍ 7፡- -ስለበደል መሥዋዕት ሕግ፣ ስለደኅንነት መሥዋዕት ሕግ ይናገራል

-ስብንና ደምን መብላት እንደማይገባ

-ከመሥዋዕቱ ለካህናት ምግብ ስለሚሆነው ፋንታ

ምዕራፍ 8፡- -አሮንና ልጆቹ ክህነት እንደተሾሙ

ምዕራፍ 9፡- -አሮን ስለራሱ መሥዋዕት ማቅረቡና በኋላ ደግሞ የሕዝቡን መሥዋዕት ማቅረቡ

ምዕራፍ 10፡- -የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩዔ በእግዚአብሔር ፊት እግዚአብሔር ያላዘዛቸውን ሌላ እሳት እንዳቀረቡ

-አሮንና ልጆቹ ወደመሠዊያው ሲቀርቡ የወይን ጠጅና የሚያሰክር ነገር እንዳይጠጡ መታዘዙ

ምዕራፍ 11፡- -ስለሚበሉ እና ስለማይበሉ እንስሳት መነገሩ

-የተሰነጠቀ ሰኮና ያለውንና የሚያመሰኳውን እንስሳ አርዶ መብላት እንደሚገባ፣ የማያመሰኳውንና የተሰነጠቀ ሰኮና የሌለው ግን እንደማይበላ

-ውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ክንፍና ቅርፊት ያላቸው እንደሚበሉ፣ ቅንፍና ቅርፊት የሌላቸው ግን እንደማይበሉ

ምዕራፍ 12፡- -ሴት ወንድ ልጅ ስትወልድ በስምንተኛው ቀን መገረዝ እንደሚገባ፣ በአርባኛው ቀን ወደ ደብተራ ኦሪት መሥዋዕት ይዛ መምጣት እንደሚገባት፣ ሴት ስትወልድ ደግሞ ወደ ደብተራ ኦሪት በሰማንያኛው ቀን መምጣት እንደሚገባ

ምዕራፍ 13፡- -ለምጽ የወጣበት ሰው ርኩስ ይባል እንደነበረ

ምዕራፍ 14፡- -የለምጽ ደዌ ከለምጻሙ ላይ ቢጠፋ ካህኑ ስለሚነጻው ሰው መሥዋዕት ያቀርባል።

ምዕራፍ 15፡- -ከሰውነቱ ዘር የሚፈስሰው ሰው ቢኖር ርኩስ እንደሆነ፣ የሚተኛበት መኝታም ርኩስ እንደሆነ

-ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት እንዲሁም በማዳጂ (በወር አበባዋ) ሰባት ቀን እንደምትቀመጥ

ምዕራፍ 16፡- -አሮን ስለራሱ፣ ስለሕዝቡ መሥዋዕት መሠዋቱ

ምዕራፍ 17፡- -ደምን መብላት እንደማይገባ

-የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደም እንደሆነች

ምዕራፍ 18፡- -ከዘመድ ጋር መጋባት እንደማይገባ

-ሰው ከእንስሳት ጋር ሩካቤ መፈጸም እንደሌለበት

-የተመሳሳይ ጾታ ሩካቤ ፈጽሞ እንደማይፈቀድ

ምዕራፍ 19፡- -እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ማለቱ

-አጥርቶ ማጨድ እንደማይገባ

-መስረቅ፣ መዋሸት እንደማይገባ

-ባልንጀራን እንደራስ መውደድ እንደሚገባ

-ሥርዓትን መጠበቅ እንደሚገባ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እንደሚገባ

ምዕራፍ 20፡- -እናት አባትን መሳደብ እንደማይገባ

-ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ እንደሚገባ

-ከእንስሳት ጋር ሩካቤ የፈጸመም ተመሳሳይ ጾታ ጋር ሩካቤ የፈጸመም እንዲገደሉ መነገሩ

ምዕራፍ 21፡- -ስለሞተ ሰው ተብሎ ራስን መላጨት፣ ጺምን መላጨት፣ ሥጋን መንጨት እንደማይገባ

-ነውረ ሥጋ ያለበት ሰው መባ ያቀርብ ዘንድ መቅረብ እንደማይገባው

ምዕራፍ 22፡- -ከአሮን ዘር ለምጽ ወይም ፈሳሽ ነገር ያለበት ሁሉ ንጹሕ እስኪሆን ድረስ ከተቀደሰው እንዳይበላ መነገሩ

-የሞተውን፣ አውሬም የሰበረውን መብላት እንደማይገባ

-ነውረ ሥጋ የሌለበትን መሥዋዕት ማቅረብ ይገባል

ምዕራፍ 23፡- -ሰንበትን ማክበር እንደሚገባ

-በዓለ ፋሲካንና በዓለ ናዕትን ማክበር እንደሚገባ

-በኵራትን ለቤተ እግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ

-በዓለ ሠዊትን፣ በዓለ መጥቅዕን ማክበር እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ 24፡- -በመቅረዙ ላይ ያሉ መብራቶችን እስኪነጋ ማብራት እንደሚገባ መነገሩ

-የእግዚአብሔርን ስም መስደብ ቅጣቱ መገደል እንደሆነ

ምዕራፍ 25፡- -እስራኤል ስድስት ዓመት ሠርተው በሰባተኛው ዓመት እንዲያርፉ መነገሩ

-እስራኤል ሃምሳኛውን ዓመት ኢዮቤልዩ ብለው እንዲያከብሩት መነገሩ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዙን በረከትን እንደምናገኝ

-ርስትን መሸጥ እንደማይገባ

-በወለድ ማበደር ተገቢ እንዳልሆነ

ምዕራፍ 26፡- -ለጣዖት መስገድ እንደማይገባ

-በእግዚአብሔር ሥርዓትና በትእዛዙ መኖር እንደሚገባ

-ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ መሄድ ጥፋትን እንደሚያስከትል

ምዕራፍ 27፡- -ስለ ስእለት ተገልጿል።

-ዐሥራት ለእግዚአብሔር እንደሚገባ

ኦሪት ዘኍልቁ

ምዕራፍ 1፦ -እግዚአብሔር ሙሴን ሕዝቡን ይቆጥር ዘንድ ማዘዙ

-ሙሴ የሚቆጥራቸው ሰዎች ወንዶች ብቻና ከ20 ዓመት በላይ የሆናቸው እንዲሆኑ መነገሩ

-በሕዝብ ቆጠራው ሂደት ለቆጠራው እንዲረዱ ከየነገዱ አንዳንድ አለቆች መመረጣቸው

-ከላይ ባነሣነው መሥፈርት የተቆጠሩት ሰዎች 603,550 (ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ አምሳ) እንደሆኑ

-በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ሌዋውያን እንዳልተቆጠሩ

-ሌዋውያን ደብተራ ኦሪትን እንዲያገለግሉ መነገሩ

ምዕራፍ 2፦ -ሕዝበ እስራኤል በደብተራ ኦሪት ዙሪያ ይሰፍሩ እንደነበረ

-በምሥራቅ በኩል መጀመሪያ ነገደ ይሁዳ፣ ከነገደ ይሁዳ አጠገብ ነገደ ይሳኮርና ከዚያ የዛብሎን ነገድ ይሠፍሩ እና ይጓዙ እንደነበረ

-በአዜብ በኩል መጀመሪያ ነገደ ሮቤል፣ ከነገደ ሮቤል አጠገብ ነገደ ስምዖንና ከዚያ ነገደ ጋድ ይሠፍሩና ይጓዙ እንደነበረ

-በባሕር በኩል መጀመሪያ ነገደ ኤፍሬም፣ ከነገደ ኤፍሬም አጠገብ ነገደ ምናሴና ከዚያ ነገደ ብንያም ይሠፍሩ ነበረ።

-በመስዕ በኩል መጀመሪያ ነገደ ዳን፣ ከነገደ ዳን አጠገብ ነገደ አሴርና ከዚያ ነገደ ንፍታሌም ይሠፍሩና ይጓዙ ነበር

ምዕራፍ 3፦ -በክህነት ያገለግሉ ዘንድ የተቀቡ የአሮን ልጆች ናዳብ፣ አብዩድ፣ አልዓዛር፣ ኢታምር እንደሆኑ

-የሌዊ ነገድ እግዚአብሔርን በክህነት እንዲያገለግል መመረጡ

-ነገደ ሌዊ በእስራኤላውያን ልጆች በኵሮች ፋንታ ለእግዚአብሔር መሠጠቱ

-የሌዊ ልጆች ጌድሶን፣ ቀዓት፣ ሜራሪ እንደሆኑ

-የጌድሶን ልጆች ከድንኳን በኋላ በባሕር በኩል እንደሚሠፍሩ፣ በደብተራ ኦሪት የሚጠብቁት ማደሪያውንና ድንኳኑን፣ የደብተራ ኦሪትን ደጃፍ መጋረጃ፣ የአደባባዩን መጋረጃ እንደሆነ።

-የቀዓት ልጆች በአዜብ በኩል እንደሚሰፍሩና ታቦቱን፣ ገበታውን፣ መቅረዙን፣ መሠዊያዎችን፣ የመቅደሱን ዕቃ፣ መጋረጃውን፣ ማገልገያውንም እንደሚጠብቁ።

-የሜራሪ ልጆች በድንኳኑ አጠገብ በሰሜን በኩል እንደሚሰፍሩና የድንኳኑን ምሰሶዎች፣ ኩላቦችን፣ መወርወሪያዎችን፣ ተራዳዎችን፣ እግሮቹን፣ ካስማዎችን፣ አውታሮችን እንደሚጠብቁ

-በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሙሴና አሮን የቆጠሯቸው ከአንድ ወር በላይ ያሉ ሌዋውያን ሁሉ 22,000 (ኻያ ሁለት ሺህ) እንደሆነ

-የእስራኤል ልጆች በኵር ከአንድ ወር ጀምሮ ያሉት 22273 (ኻያ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሦስት) እንደሆኑና ለእነዚህ ቤዛ ሌዋውያን እንደሆኑ በተረፉት 273 ሰዎች ፋንታ በእያንዳንዳቸው አምስት ዲድርክም ገንዘብ እንዲቀበል መታዘዙ

ምዕራፍ 4፦ -ከ25 ዓመት ጀምሮ እስከ 50 ዓመት ያሉ የቀዓት ልጆች ለአገልግሎት መለየታቸውና አገልግሎታቸውም ምን ምን እንደሆነ በዝርዝር መገለጡ

-ከ25 ዓመት ጀምሮ እስከ 50 ዓመት ያሉ የጌድሶን ልጆች ለአገልግሎቱ መለየታቸውና አገልግሎታቸውም መገለጹ

-ከ25 ዓመት ጀምሮ እስከ 50 ዓመት ያሉ የቀዓት ልጆች ለአገልግሎት መለየታቸውና አገልግሎታቸውም መገለጹ

-ሌዋውያን ሁሉ ከ25 ዓመት እስከ 50 ዓመት ያሉት ሲቆጠሩ 8580 እንደሆኑ መገለጹ

ምዕራፍ 5፦ -ለምጻም ከሰፈሩ እንዲወጣ መታዘዙ

-የበደል ካሣ መኖር እንዲኖር ሥርዓት መሠራቱ

-ሚስቱን ከሌላ ወንድ ደርሳለች ብሎ የጠረጠረ ሰው ካለ የቅንዐት ቁርባን እንዲያቀርብ መታዘዙ፣ ሴቲቱ ንጹሕ ከሆነች እግዚአብሔር እንዲባርካት አድርጋው ከነገበረም እግዚአብሔር እንዲቀጣት አስታውቆ ካህኑ መራራ ውሃ እንደሚያጠጣት

ምዕራፍ 6፦ -በተወሰነ ጊዜ ለእግዚአብሔር ራሱን የተለየ አድርጎ የተሳለ ሰው ከሚያሰክር መጠጥ ራሱን መለየት እንዳለበት፣ ራሱን መላጨት እንደሌለበት፣ ወደሬሳ መቅረብ እንደሌለበት፣ የስለቱ ወራት ሲፈጸም ወደደብተራ ኦሪት መጥቶ መሥዋዕት ማቅረብ እንደሚገባው

-ካህናት ሕዝቡን ሲባርኩ "እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህም፣ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይራራልህም ፣ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ ሰላምንም ይስጥህ" እንዲሉ መታዘዛቸው

ምዕራፍ 7፦ -ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ አለቆች በእግዚአብሔር ፊት መሥዋዕትን እንዳቀረቡ

-ሙሴ ወደደብተራ ኦሪት እግዚአብሔርን ለመነጋገር በገባ ጊዜ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ካለው ከሥርየት መክደኛው በላይ ከኪሩቤልም መካከል የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማ እንደነበረና ከእርሱም ጋር ይናገር እንደነበረ።

ምዕራፍ 8፦ -እግዚአብሔርን ያገለግሉ ዘንድ ሌዋውያን መመረጣቸው፣ ከእስራኤል ልጆች በኩራት ፋንታ እንደሆኑ፣ ሌዋውያን ራሳቸውን ከኃጢአት እንዳነጹ።

ምዕራፍ 9፦ -የፋሲካ በዓል እንደተከበረ

-ደብተራ ኦሪትን ሁልጊዜም ቀን ደመና ሌሊት የእሳት አምሳል ይሸፍናት እንደነበረ ነበረ። ደመናው በቆመበት በዚያ በእግዚአብሔር ትእዛዝ የእስራኤል ልጆች ይጓዙና ይሰፍሩ እንደነበረ፣ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይጠብቁ እንደነበረ።

ምዕራፍ 10፦ -እግዚአብሔር ሙሴን ማኅበሩን ለመጥራት፣ ወደሰልፍ ሲወጡ፣ በደስታቸው ቀን፣ በበዓላት ዘመን፣ በወር መባቻ ለምልክት እንዲሆናቸው ሁለት የብር መለከቶችን እንዲሠራ ማዘዙ።

-ሙሴ ታቦቷ በተጓዘች ጊዜ አቤቱ ተነሣ፣ ጠላቶችህ ይበተኑ፣ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ ይል እንደነበረ።

ምዕራፍ 11፦ -ሕዝቡ በክፋት በእግዚአብሔር ላይ እንዳጉረመረሙና እግዚአብሔርም ተቆጥቶ በእሳት እንዳቃጠላቸው

-ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ጸልዮ መዓተ እግዚአብሔርን እንዳራቀ

-እስራኤላውያን መና ሰለቸን ማለታቸውና ግብጽ ሳሉ ይበሉት የነበረውን ምግብ እንደተመኙ

-ሙሴ ሰባ ሽማግሌዎችን እንደመረጠና በእነርሱ ላይም የእግዚአብሔር መንፈስ አርፎባቸው ትንቢት እንደተናገሩ፣ ከሰባው ሁለቱ ግን ከሰፈር ቀርተው እንደነበረና ቢሆንም ግን መንፈስ እንዳረፈባቸውና ትንቢት እንደተናገሩ

-እስራኤላውያን ሥጋን ተመኝተው በእግዚአብሔር ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ እግዚአብሔር የድርጭት ሥጋን በነፋስ እንዳመጣላቸው፣ ሥጋውን እየበሉ ሳለም መቅሠፍተ እግዚአብሔር ወርዶ እንዳጠፋቸው

ምዕራፍ 12፦ -ሙሴ ኢትዮጵያዊቱን ሴት በማግባቱ እህቱ ማርያምና ወንድሙ አሮን እንደአሙት፣ በዚህም ምክንያት ማርያም ለምጻም እንደሆነች፣ በኋላ ሙሴ ጸልዮ ፈውስን ከእግዚአብሔር እንዳሰጣት

-ሙሴ በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ የዋህ ሰው እንደነበረ

-ሙሴ የታመነ አገልጋይ መሆኑን እግዚአብሔር መግለጹ

ምዕራፍ 13፦ -ሙሴ የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ 12 ሰዎችን መላኩ፣ የተላኩት ሰዎችም ሰልለው መጥተው የወይን ዘለላ፣ ሮማን፣ በለስ ተሸክመው እንደመጡ

-ሙሴ ከነገደ ኤፍሬም የሚወለደውን አውሴን ኢያሱ ብሎ እንደጠራው

-ሰላዮቹ ስለከነዓን አጋንንው በመናገራቸው ሕዝቡ እንደፈራ፣ ካሌብ ግን ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ ማለቱ

ምዕራፍ 14፦ -የእስራኤል ልጆች በሙሴና በአሮን ላይ ማጉረምረማቸው፣ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁት ሰዎች እንደተቀሠፉ

-ኢያሱና ካሌብ ከነዓንን ማሸነፍ እንደሚችሉ መናገራቸው፣ በዚህም ምክንያት ሌሎች ሲጠፉ ካሌብና ኢያሱ መትረፋቸውና ምድረ ርስትን እንደሚወርሱ መነገሩ

-ሙሴ ለሕዝቡ እንደለመነና እግዚአብሔርም ሕዝቡን ይቅር እንዳለ

-ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ስላልሰሙ ምድረ ርስትን እንደማይወርሱ መነገሩ

-እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ስላልሆነ ጠላቶቻችሁን አትግጠሙ እየተባሉ አንሰማም ብለው የገጠሙት እንደተሸነፉ

ምዕራፍ 15፦ -እስራኤላውያን ወደምድረ ርስት ሲገቡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ መታዘዛቸው

-ላልታወቀ ኃጢአት መሥዋዕት እንዲሠዋ መታዘዙ

-ትዕቢትን የሚያደርግ ሰው እግዚአብሔርን ሰድቧልና ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ መባሉ

-በሰንበት ቀን እንጨት ሲለቅም የተገኘው ሰው እንዲገደል መፈረዱ

-እስራኤላውያን በልብሳቸው ዘርፍ ሰማያዊ ፈትል እንዲያደርጉ መታዘዙ

ምዕራፍ 16፦ -ቆሬ ከዳታን፣ ከአቤሮን፣ ከአውናንና ከእስራኤል ከተመረጡ 250 ሰዎች ጋር ሆኖ በሙሴና በአሮን ላይ መነሣቱ፣ በድፍረት ተነሥተውም ጥናዎችን ይዘው እናጥናለን ማለታቸው፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር መቅሠፍትን እንዳወረደባቸው ከብቶቻቸውን፣ ቤቶቻቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውን ሁሉ ምድር ተከፍታ እንደዋጠቻቸው

-ሙሴ በመጸለዩ መቅሠፍቱ እንደቆመ

ምዕራፍ 17፦ -ሙሴ ከዐሥራ ሁለቱ ነገድና ከነገደ ሌዊ አንድ አንድ በትር ወስዶ በደብተራ ኦሪት እንዲያስቀምጥ መታዘዙ

-የአሮን በትር ለምልማ፣ አብባ፣ የበሰለ ለውዝ አፍርታ መገኘቷ

ምዕራፍ 18፦ -በእስራኤል ልጆች ላይ መዓት እንዳይመጣባቸው የሌዊ ነገዶች የደብተራ ኦሪትን ሕግና ሥርዓት እንዲጠብቁ መታዘዛቸው

-በኵራት፣ ክፍለ መሥዋዕት፣ ቀዳምያት፣ ዐሥራት የሌዋውያን ፈንታ እንዲሆን መታዘዙ

-ሌዋውያን የዐሥራት ዐሥራት እንዲያወጡ መታዘዛቸው

ምዕራፍ 19፦ -ንጹሕ የሆነች ቀይ ጊደርን ካህኑ አልዓዛር ከሰፈር ውጭ ወስዶ በንጹሕ ስፍራ ላይ በፊቱ እንደሚያርዷት፣ አልዓዛር ከደሟ በጣቱ ወስዶ በምስክሩ ድንኳን ፊት ሰባት ጊዜ እንደሚረጨው፣ ጊደሪቱን በፊቱ እንደሚያቃጥሏት፣ ንጹሕ ሰው የጊደሯን አመድ ከንጹሕ ቦታ እንደሚያስቀምጠውና ይህም የእስራኤል መንጻ እንዲሆን መታዘዙ

-የሞተ ሰውን በድን የነካ ሰው ሰባት ቀን ርኩስ እንደሚሆን፣ ርኩሱን ሰው የሚነካ ሰው ደግሞ እስከ ሠርክ እንደሚረክስ

ምዕራፍ 20፦ -ማኅበረ እስራኤል በውሃ ጥም በተቸገሩ ጊዜ ሙሴ በበትሩ ከድንጋይ ውሃ አፍልቆ ሕዝቡን እንዳጠጣቸው

-አሮን እንደሞተና በእርሱ ምትክ ልጁ አልዓዛር እንደተሾመ

ምዕራፍ 21፦ -ሕዝበ እስራኤል እግዚአብሔርንና ሙሴን በማማታቸው በእባብ እንደተነደፉ፣ በኋላ በድለናል ብለው በደላቸውን አምነው ይቅርታ እንደጠየቁ፣ እግዚአብሔር ሙሴን የናስ እባብ እንዲሰቅል ማዘዙ፣ የናስ እባቡን አይቶ በእባብ የተነደፈው ሁሉ እንደዳነ

-እስራኤላውያን ንጉሥ ሴዎንንና ንጉሥ አግን ከነሠራዊታቸው ማሸነፋቸው

ምዕራፍ 22፦ -ባላቅ የእስራኤልን ሕዝብ አይቶ እንደፈራና እንዲረዳው በለዓም የተባለ ጠንቋይን መጥራቱ

-ባላቅ በለዓምን እስራኤልን እንዲረግምለት መጠየቁ

-በለዓም ወደ ባላቅ ሲሄድ ባላቅ የነበረባት አህያ መልአኩን የተመለከተ ሰይፍ ይዞ እንዳየችውና በለዓም ግን ባለማየቱ አህያይቱን ወደፊት እንድትሄድለት መምታቱ፣ በኋላ መልአኩን እርሱም እንዳየው

ምዕራፍ 23፦ -የእግዚአብሔር መንፈስ በበለዓም አድሮ እስራኤላውያንን እንደመረቀ

-በለዓም እስራኤልን የሚመርቁ የተመረቁ፣ እስራኤልን የሚረግሙ የተረገሙ ይሁኑ ብሎ እንደተናገረ

ምዕራፍ 24፦ -በለዓም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ብሎ ትንቢት እንደተናገረ

ምዕራፍ 25፦ -እስራኤላውያን ከሞዓባውያን ጋር እንዳመነዘሩ፣ እስራኤላውያን ለሞዓብ አማልክቶች እንደሰገዱ፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንደተቆጣ

-ፊንሐስ ለእግዚአብሔር ቀንቶ ዘንበሪንና ከስቢን በመግደሉ መዓተ እግዚአብሔርን መመለሱ

ምዕራፍ 26፦ -እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ዳግመኛ መቆጠራቸውና ከ20 ዓመት በላይ የሆኑት የ12ቱ ነገድ ወንዶች ልጆች ብዛት 601,730 (ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ እንደነበሩ።

-እስራኤላውያን ምድረ ርስትን በእጣ እንዲከፋፈሏት መነገሩ

-የሌዊ ነገዶች ከአንድ ወር ጀምሮ በላይ ያሉ ወንዶች ልጆች 23,000 (ኻያ ሦስት ሺ) እንደነበሩ

ምዕራፍ 27፦ -የሰለጰአድ ሴት ልጆች የሞተውን የአባታቸውን ርስት ይገባናል ብለው ጠይቀው እግዚአብሔር እንደፈቀደላቸው

-አባት ቢሞት ልጆች እንዲወርሱት፣ ልጆች ከሌሉት ወንድሞቹ እንዲወርሱት፣ ወንድሞች ከሌሉት ከወገኑ የቀረበ ዘመድ እንዲወርሰው መነገሩ

-ሙሴ በጺን ምድረ በዳ ባለው በቃዴስ በነበረው የክርክር ውሃ እግዚአብሔርን ስላላከበረው ምድረ ርስት እንደማይገባና በናባው አሻገር ባለው ተራራ ሆኖ ከርቀት አይቷት እንደሚሞት መነገሩ

-ኢያሱ ከሙሴ ቀጥሎ እንዲያስተዳድር መሾሙ

ምዕራፍ 28፦ -እስራኤላውያን በበዓላት ቀን ለእግዚአብሔር መባ፣ ቁርባን፣ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ መነገሩ

-በዘወትር፣ በሰንበት፣ በመባቻ፣ በፋሲካና በበዓለ ናዕት፣ በበዓለ ሠዊት ስለሚቀርቡ የመሥዋዕት አቀራረቦች መገለጡ

ምዕራፍ 29፦ -በበዓለ መጥቅዕ፣ በኃጢአት ማስተሥረያ ቀን፣ በዳስ በዓል ቀን ስለሚቀርቡ የመሥዋዕት አቀራረቦች መገለጡ

ምዕራፍ 30፦-ሰው ከተሳለና ለእግዚአብሔር ከማለ ቃሉን መፈጸም እንደሚገባው

-ስለ ስእለት ሥርዓት መነገሩ

ምዕራፍ 31፦ -እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ምድያማውያንን እንዲወጉ መታዘዛቸው፣ እነርሱ ግን ወንዶችን ሲወጉ ሴቶችን ማርከው በማምጣታቸው መቅሠፍት መሆኑ

ምዕራፍ 32፦ -የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች ከዮርዳኖስ ማዶ ያለውን ሀገር ወርሰው እንደኖሩ

ምዕራፍ 33፦ -ከግብፅ ጀምሮ ስለነበረው ጉዞ ጠቅለል ተደርጎ መገለጹ

ምዕራፍ 34፦ -ስለተስፋይቱ ምድር ወሰኖች መነገሩ

-ምድረ ርስትን እንደተከፋፈሏት

ምዕራፍ 35፦ -ለሌዋውያን ከተሞች መሰጠታቸው፣ ከተሰጡት ከተሞች ስድስቱ የመማፀኛ ከተሞች እንዲሆኑ መነገሩ፣ ከመማጸኛ ከተሞች በተጨማሪ 42 ከተሞች እንደተሰጡ

-ባለማወቅ ነፍስ የገደለ ሰው ቢኖር ወደመማጸኛ ከተሞች ገብቶ እንዲሸሸ መታዘዙ፣ ታላቁ ካህን እስኪሞት ድረስም ከዚያው እንዲቆይ መነገሩ፣ ታላቁ ካህን ከሞተ በኋላ ግን ወደርስቱ እንዲመለስ መነገሩ

-በአንድ ምስክር ማናቸውንም ሰው መግደል እንደማይገባ

-ምድርን የሚያረክሳት ደም ነውና የምትኖሩባትን ምድር በነፍስ ግድያ አታርክሷት መባሉ

ምዕራፍ 36፦ -እስራኤላውያን በየርስታቸው እንዲኖሩ መነገሩ

አሪት ዘዳግም

ምዕራፍ 1፦ -የወንድሞቻችንን ነገር መስማት እንደሚገባ፣ በጽድቅ መፍረድ እንደሚገባ

-ፍርድ የእግዚአብሔር ስለሆነ ማዳላት እንደማይገባ

-ሙሴ ከቀድሞ ጀምሮ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን መተረኩ

ምዕራፍ 2፦ -ሙሴ በአርባው ዓመት የእስራኤል ጉዞ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን መልካም ሥራ መግለጡ

ምዕራፍ 3፦ -ሙሴ ቀድሞ በጉሟቸው ጊዜ የተደረገውን ነገር ለሕዝቡ መተረኩ

ምዕራፍ 4፦ -ሕዝበ እስራኤል የተደረገላቸውን ነገር ለልጅ ልጆቻቸው እንዲነግሩ መነገራቸው

-እስራኤላውያን የተቀረጸን ምስል (ጣዖትን)፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን በጠቅላላው ፍጥረታትን እንዳያመልኩ መነገሩ

-እግዚአብሔር የሚበላ እሳት፣ ቀናተኛ አምላክ እንደሆነ መነገሩ

-እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ከበደሉና ጣዖት ካመለኩ የተለያዩ መከራዎች እንደሚደርሱባቸው መነገሩ

-እስራኤል ከእነርሱ በፊት ስለነበረው ስለቀደመው ታሪክ እንዲጠይቁ መነገራቸው

-ከእግዚአብሔር ሌላ አምላክ እንደሌለ መነገሩ

ምዕራፍ 5፦ -ዐሥሩን ትእዛዛት ሙሴ ለሕዝቡ መንገሩ

-በሕይወት እንድትኖሩ መልካምም እንዲሆንላችሁ በምትወርሱትም ምድር እድሜያችሁ እንዲረዝም እግዚአብሔር አምላካችሁ ባዘዛችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ መባላቸው

ምዕራፍ 6፦ -እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ ነው ተብሎ መነገሩ

-እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ ውደድ መባሉ

-እናት አባት የእግዚአብሔርን ቃል ለልጆቻቸው ማስተማር እንደሚገባቸው መነገሩ

-በማናቸውም ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እንደሚገባ መገለጹ

-እግዚአብሔርን መፍራት እርሱንም ብቻ ማምለክ እንደሚገባ መነገሩ

-እግዚአብሔርን መፈታተን እንደማይገባ

ምዕራፍ 7፦ -በዘመኑ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር የመረጠው ቅዱስ ሕዝብ መሆኑ

-የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ በረከትን እንደሚያስገኝ

ምዕራፍ 8፦ -ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንደማይኖር መገለጡ

-እስራኤላውያን እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ነገር ረስተው እንዳይበድሉ መነገሩ

-እግዚአብሔርን ማሰብ እንደሚገባ

ምዕራፍ 9፦ -ሙሴ እስራኤል በቀደመ ጉዟቸው የገጠማቸውንና የተደረገውን ነገር መተረኩ

ምዕራፍ 10፦ -እግዚአብሔርን መፍራት፣ እግዚአብሔርን መውደድ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር አምላክ አማልክት፣ የጌቶች ጌታ፣ ታላቅ አምላክ፣ ኃያል፣ በፍርድ የማያዳላ መሆኑ

ምዕራፍ 11፦ -የእግዚአብሔርን ሕጉን፣ ሥርዓቱን፣ ትእዛዙን በዘመን ሁሉ መጠበቅ እንደሚገባ

-እስራኤል እግዚአብሔር የሚጎበኛት ሀገር እንደሆነችና የእግዚአብሔር ዓይን ሁልጊዜ በእርሷ ላይ እንደሆነ መገለጡ

-እስራኤል ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ መታዘዛቸው

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መስማት በረከት፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አለመስማት መርገም እንደሆነ መገለጡ

ምዕራፍ 12፦ -የጣዖት አማልክቶችን ማቃጠል እንደሚገባ

-እስራኤላውያን በምድር ሲኖሩ ሌዋውያንን ቸል ማለት እንደማይገባቸው

-ደምን መብላት እንደማይገባ

ምዕራፍ 13፦ -ሕልም አላሚ ወይም ነቢይ ነኝ ባይ ሌሎች አማልክትን እንከተል ቢል መስማት እንደማይገባ፣ እግዚአብሔርን ለማስካድና ሌላ አማልክት እንዲያመልኩ ያደረገ ሰው ነቢይ ካለ እንዲገደል መነገሩ

ምዕራፍ 14፦ -ለሞተ ሰው ፊትን መንጨት፣ ራስን መላጨት እንደማይገባ

-ርኩስን ነገር መብላት እንደማይገባ መነገሩ፣ ንጹሕ የሆነን መብላት እንደሚገባ

-ዐሥራት መስጠት እንደሚገባ

ምዕራፍ 15፦ -ሰው ቢቸገር መርዳት፣ ማበደር እንደሚገባ

-ለሚለምን ሰው እጅን መዘርጋት እንደሚገባ

-በኵራትን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ

ምዕራፍ 16፦ -በዓለ ፋሲካን ማክበር እንደሚገባ መነገሩ

-ከፋሲካ በኋላ ሰባት ሳምንት ቆጥሮ፣ መከሩን ማጨድ ከጀመሩበት ቀን ሰባት ቀን ቆጥሮ የሰባት ሱባዔ በዓል ማድረግ እንደሚገባ (ይህ የመከር በዓል) ነው።

-ከአውድማና ከወይን ጭማቂ ፍሬ በተሰበሰበ ጊዜ ሰባት ቀን የዳስ በዓል ማድረግ እንደሚገባ

-በዓመት ሦስት ጊዜ (በቂጣ በዓል፣ በሰባቱ ሱባዔ በዓል፣ በዳስ በዓል) ወንድ ሁሉ እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ እንዲታይ መነገሩ

-ለሕዝቡ ቅን ፍርድን መፍረድ እንደሚገባ፣ ጉቦ መቀበል እንደማይገባ፣ እውነተኛውን ፍርድ መከተል እንደሚገባ

-እግዚአብሔር የሚጠላውን (የጣዖት) ሐውልት አትትከል መባሉ።

ምዕራፍ 17፦ -ነውር ያለበትን በሬ ለእግዚአብሔር አትሠዋ መባሉ

-በሀገራቸው ጣዖት የሚያመልክ ቢገኝ እንዲገድሉት እስራኤላውያን መታዘዛቸው

-ሞት የሚገባቸው ሰዎች በሁለት ወይም በሦስት ምስክር መገደል ይገባቸዋል እንጂ በአንድ ምስክር መግደል ተገቢ እንዳልሆነ

-እስራኤላውያን ክፉውን ከመካከላችሁ አስወግዱ መባላቸው

-ማናቸውም ሰው ቢኮራ ወይም ዳኛውን ባይሰማ ሞት እንደሚገባው መነገሩ

-እስራኤላውያን ከራሳቸው መካከል ማንገሥ እንጂ ከሌላ ንጉሥን ማንገሥ እንደማይገባቸው መነገሩ

-በእስራኤል የነገሠ ንጉሥ ኦሪት ዘዳግምን ወስዶ በዕድሜ ዘመኑ ሁሉ እንዲያነበው መነገሩ፣ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሚገባው መነገሩ

ምዕራፍ 18፦ -ለሌዋውያን ርስታቸው እግዚአብሔር ነውና ሌላ ርስት እንዳይኖራቸው መነገሩ

-ሟርተኛ፣ ሞራ ገላጭ፣ አስማተኛ፣ መተተኛ፣ ጠንቋይ፣ መናፍስትን ጠሪ በመካከላቸው እንዳይገኝ እግዚአብሔር ለእስራኤል መንገሩ

-እንደሙሴ ያለ ነቢይ እንደሚነሣ መነገሩ

-ከእግዚአብሔር ሳይላክ ተልኬያለሁ የሚል ነቢይ እንዲገደል መነገሩ

ምዕራፍ 19፦ -ሰው ባልንጀራውን ጠልቶ፣ ሸምቆ፣ በእርሱ ላይ ተነሥቶ ቢገድለውና በመማጸኛ ከተማዎች ቢማጸን የከተማው ሽማግሌዎች ይዘው በባለደሙ እጅ አሳልፈው ይሰጡትና እንዲሞት ይደረጋል መባሉ

-ድንበር ማፍረስ እንደማይገባ መነገሩ

-ነፍስ በነፍስ፣ ዐይን በዐይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር መመለስ እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ 20፦ -በጦርነት ጊዜ የጠላትን ብዛት አይቶ መፍራት እንደማይገባ መነገሩ

-ጦርነት መሄድ ስለሌለባቸው አካላት መነገሩ

-ከጦርነት በፊት የሰላም አማራጮችን መጠቀም እንደሚገባና ስለጦርነት ሕግ መነገሩ

ምዕራፍ 21፦ -ሰው ተገድሎ በሜዳ ቢገኝና ገዳዩ ባይታወቅ መደረግ ስላለበት ሥርዓት መነገሩ

-በሌዋውያን ቃል ክርክር ሁሉ ጉዳትም ሁሉ እንደሚቆም መነገሩ

-ስለተማረኩ ሴቶች፣ ስለበኩር ልጅ መነገሩ

-ለአባቱና ለእናቱ የማይታዘዝ ልጅ እንዲገደል መነገሩ

ምዕራፍ 22፦ -የጠፋ በግ ወይም በሬ ቢኖር ለባለቤቱ መመለስ እንደሚገባ መነገሩ

-ሴት የወንድን ልብስ ወንድም የሴትን ልብስ መልበስ እንደማይገባው መነገሩ

-ድንግልናን መጠበቅ እንደሚገባ መነገሩ

- ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ተኝቶ የተገኘ እንዲገደል መታዘዙ

ምዕራፍ 23፦ -በብሉይ ሕግ ፍሬ ዘሩ የተቀጠቀጠ፣ አባለዘሩ የተቆረጠና ዲቃላ ወደቤተ እግዚአብሔር እንዳይገቡ መነገሩ

-አሞናዊና ሞዓባዊ ወደእግዚአብሔር ቤት እንዳይገቡ መነገሩ

-ጠላቶችህን ልትወጋ በወጣህ ጊዜ ከክፉ ነገር ሁሉ ሰውነትህን ጠብቅ መባሉ

-ከእስራኤል ሰዎች አመንዝራ እንዳይገኝ መነገሩ

-ወለድ መውሰድ ተገቢ እንዳልሆነ መነገሩ

ምዕራፍ 24፦ -ስለጋብቻ ፍቺ መነገሩ

-አዲስ ሚስት ያገባ ሰው ወደጦርነት መሄድ እንደማይገባው መነገሩ

-ሰው የሰረቀ ሰው እንዲገደል መታዘዙ

-የሠራተኛን ደመወዝ መከልከል እንደማይገባ

-አባቶች ስለልጆቻቸው ፋንታ፣ ልጆችም ስለአባቶቻቸው ፋንታ መገደል እንደማይገባቸው

ምዕራፍ 25፦ -ለጻድቁ እንዲፈረድለት ለበደለኛ እንዲፈረድበት መነገሩ

-በደለኛን ከአርባ በላይ መግረፍ እንደማይገባ

-እህልን ስታበራይ በሬውን አፉን አትሰረው መባሉ

-በብሉይ ኪዳን ሕግ ወንድም ልጅ ሳይወልድ ቢሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ እንዲወልድለትና የተወለደው ልጅ በሞተው ወንድሙ አባት ተብሎ እንዲጠራ መነገሩ

ምዕራፍ 26፦ -ምድር ከምትሰጠው ፍሬ ሁሉ ቀዳምያትን ወደቤተ እግዚአብሔር መውሰድ እንደሚገባ

-ዐሥራትን ለሌዋዊ፣ ለመጻተኛ፣ ለድኻ፣ ለመበለት መስጠት እንደሚገባ

ምዕራፍ 27፦ -እስራኤላውያን ድንጋይ ወስደው በዚያ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጽፈው በጌባል ተራራ እንዲያስቀምጡትና በዚያም መሠዊያ እንዲሠሩ መታዘዛቸው

-ሕዝቡን ይባርኩ ዘንድ በገሪዛን ተራራ ላይ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዮሴፍና ብንያም እንዲቆሙ መነገሩ። ይረግሙ ዘንድ ደግሞ በጌባል ተራራ ሮቤል፣ ጋድ፣ አሴር፣ ዛብሎን፣ ዳንና ንፍታሌም እንዲቆሙ መነገሩ

-ዐሥራ ሁለት ርግማኖች መነገራቸው

ምዕራፍ 28፦ -የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ከሁሉ በላይ ከፍ እንደሚያደርግ፥ በረከትን እንደሚያስገኝና ረድኤትን እንደሚያሰጥ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አለመጠበቅ መርገምን፣ ረኃብን፣ በሽታን፣ ጭንቀትን፣ ቸነፈርንና የተለያዩ መከራዎችን እንደሚያመጣ

ምዕራፍ 29፦ -እስራኤላውያን በአርባው ዓመት ጉዟቸው የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንዲሁም እንጀራ እንዳልበሉ

ምዕራፍ 30፦ -ወደ እግዚአብሔር መመለስ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር እንደሚል

-እግዚአብሔር ያዘዘው ትእዛዝ ከባድ እንዳልሆነ

-እግዚአብሔርን መውደድ ቃሉን መስማት እንደሚገባ

ምዕራፍ 31፦ -ኢያሱ በሙሴ ምትክ ሕዝቡን መርቶ ወደምድረ ርስት እንዲያስገባቸው መነገሩ

ምዕራፍ 32፦ -እግዚአብሔር በሥራው እውነተኛ፣ መንገዱ የቀና፣ የታመነ፣ ጻድቅና ቸር፣ ለዘለዓለም ሕያው እንደሆነ

-አባትን ሽማግሌን ስላለፈው ነገር መጠየቅ እንደሚገባ

ምዕራፍ 33፦ -ሙሴ እስራኤላውያንን መባረኩ

-ሙሴ በሞዓብ ምድር እንደሞተ

መጽሐፈ ኢያሱ

ምዕራፍ 1፦ -ኢያሱ እስራኤላውያንን ዮርዳኖስን አሻግሮ ምድረ ርስት ማግባቱ

-እግዚአብሔር ኢያሱን ከሙሴ ጋር እንደነበርኩ እንዲሁ ከአንተ ጋር እኖራለሁ እንዳለው

ምዕራፍ 2፦ -ኢያሱ ሁለት ሰላዮችን በስውር ወደኢያሪኮ መላኩ

-ሰላዮቹ ረዓብ ወደምትባለዋ ዘማ ቤት መግባታቸው፣ የኢያሪኮ ሰዎች ሲፈልጓቸው ረዓብ እንደደበቀቻቸው

-ሰላዮች ቸርነት እንዲያደርጉላት ረዓብ መጠየቋ

-ሰላዮቹ ረዓብን ስንመጣ ቀዩን ፈትል በመስኮት እሰሪው እንዳሏት

ምዕራፍ 3፦ -እስራኤላውያን ሌዋውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ ተነሥታችሁ ተከተሉት መባላቸው፣ በእናንተና በታቦቱ መካከል ሁለት ሺህ ክንድ ይሁን መባላቸው።

ምዕራፍ 4፦ -ሕዝበ እስራኤል ዮርዳኖስን ፈጽመው በተሻገሩ ጊዜ በዮርዳኖስ መካከል የካህናት እግር ከቆመበት ስፍራ ለመታሰቢያ 12 ቀላል ድንጋዮችን እንዲያነሱና እንዲወስዷቸው መታዘዛቸው።

-የካህናት እግር ወደዮርዳኖስ ወንዝ ሲገባ የዮርዳኖስ ውሃ ደረቀና ሕዝቡ መሻገሩ፣ ሕዝቡ ተሻግሮ ከጨረሰ በኋላ ዮርዳኖስ መልሶ መመላቱ

ምዕራፍ 5፦ -ኢያሱ የእስራኤልን ልጆች እንዲገርዝ መታዘዙ፣ በምድረ በዳ የተወለዱት ሁሉ አልተገረዙም ነበረና።

-መልአክ ለኢያሱ እንደተገለጸለትና ኢያሱም እንደሰገደለት (የጸጋ ስግደት)

-መልአክ ኢያሱን የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ ማለቱ

ምዕራፍ 6፦ -እስራኤላውያን የኢያሪኮን ግንብ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሰባት ቀን መዞራቸው፣ በሰባተኛው ቀን ሰባት ጊዜ መዞራቸው፣ ካህናት ቀንደ መለከቱን እንዲነፉና ሕዝቡም እንዲጮሁ መታዘዛቸው

-የኢያሪኮ ከተማ ቅጥር መፍረሱ

-እስራኤላውያን እርም የሆነውን ከኢያሪኮ እንዳይወስዱ መታዘዛቸው

-ረዓብ ዘማ ከነዘመዶቿ ከኢያሪኮ መትረፏ

ምዕራፍ 7፦ -አካን ወልደ ከርሚ እርም በሆነው ነገር መበደሉና በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ መቆጣቱ፣ በዚህም ምክንያት በጋይ ሰዎች መሸነፋቸው፣ እስራኤል አካን ወልደ ከርሚንን በድንጋይ ወግረው መግደላቸውና በእሳት ማቃጠላቸው

-ኢያሱ እስራኤላውያንን በመካከላችሁ እርም የሆነውን ነገር ካላጠፋችሁ ትሸነፋላችሁ ማለቱ

ምዕራፍ 8፦ -እስራኤላውያን የጋይን ከተማ መደምሰሳቸው

-ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መሠዊያን እንደሠራና የእግዚአብሔርን ሕጉን ለእስራኤላውያን እንዳነበበ

ምዕራፍ 9፦ -የገባዖን ሰዎች ያረጀ ልብስ ለብሰው፣ የደረቀና የሻገተ ምግብ ይዘው ዋሽተው ኢያሱን እንዳታለሉት፣ ኢያሱም በኋላ እውነታውን ሲያውቅ እንደረገማቸውና በኋላ ለእግዚአብሔር መሠዊያ እንጨት ቀራጮችና ውሃ ቀጂዎች እንዳደረጋቸው

ምዕራፍ 10፦ -አሞራውያን የአቅራቢያ ነገሥታቶችን ይዘው እስራኤልን እንደገጠሙና በእስራኤል እንደተሸነፉ

-እግዚአብሔር ኢያሱ ጠላቶቹን እስኪያጠፋ ፀሐይን ማቆሙ

-ኢያሱ ሌሎች ከተሞችንም አሸንፎ መያዙ

ምዕራፍ 11፦ -ኢያሱ በጦርነት ምድረ ርስትን ሁሉ እንደያዘና ምድሪቱንም ለእስራኤላውያን በየነገዳቸው ርስት አድርጎ እንደሰጣቸው

ምዕራፍ 12፦ -ሙሴና ኢያሱ ድል ስላደረጓቸው ነገሥት ይናገራል

ምዕራፍ 13፦ -ኢያሱ እንደሸመገለ መነገሩ

-የርስት አከፋፈል በየነገዳቸው

ምዕራፍ 14፦-ለሌዋውያን ምድራዊ ርስት እንዳልተሰጠ

-ኢያሴ ለካሌብ ኬብሮንን ርስት አድርጎ እንደሰጠው

ምዕራፍ 15፦ -ለይሁዳ ነገድ ስለተሰጠ ርስት

ምዕራፍ 16፦ -ስለ ኤፍሬም ነገድ ርስት ይናገራል

ምዕራፍ 17፦ -ስለምናሴ ነገድ እኩሌታ ርስት ይናገራል

ምዕራፍ 18፦ -ስለብንያም ነገድ ርስት ይናገራል

ምዕራፍ 19፦ -ስለስምዖን ነገድ ርስት፣ ስለዛብሎን ነገድ ርስት፣ ስለይሳኮር ነገድ ርስት፣ ስለአሴር ነገድ ርስት፣ ስለንፍታሌም ነገድ ርስት፣ ስለዳን ነገድ ርስት ይናገራል

-እስራኤላውያን ርስት ተካፍለው እንደጨረሱ

ምዕራፍ 20፦ -ስለመማፀኛ ከተሞች መነገሩ

ምዕራፍ 21፦ -ለሌዋውያን ስለተሰጡ ከተሞች

ምዕራፍ 22፦ -የሮቤል፣ የጋድ፣ የመ*ን-/ፈ*ቀ ምናሴ ነገዶች በዮርዳኖስ አጠገብ መሠዊያ መሥራታቸው

ምዕራፍ 23፦ -ኢያሱ ሕዝቡን በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን እንዲጠብቁ መንገሩ

ምዕራፍ 24፦ -ኢያሱ ከቀድሞ ጀምሮ የተደረገውን እንደተረከ

-ኢያሱ እግዚአብሔርን ፍሩት ብሎ ለሕዝቡ መናገሩና እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን ማለቱ

-እስራኤላውያን የአሕዛብን አማልክት እንዳመለኩ

መጽሐፈ መሳፍንት

ምዕራፍ 1፦-ኢየሩሳሌም በይሁዳ ነገድ እንደተያዘች

-የካሌብ ወንድም ጎቶንያል ዳቤርን መያዙ

-እግዚአብሔር ከይሁዳ ጋር በረድኤት እንደነበረ

ምዕራፍ 2፦ -ከትውልድ በኋላ እግዚአብሔርንና ለእስራኤልም ያደረገውን ሥራ ያላወቀ ሌላ ትውልድ እንደተነሣ።

-እስራኤላውያን አምልኮተ እግዚአብሔርን እንደተዉ፣ በዓሊምን፣ በአልንና አስታሮትን እንዳመለኩ፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ እንደሰጣቸው፣ በኋላ መሳፍንትን እንዳስነሣላቸውና እንዳዳናቸው

-እግዚአብሔር መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከመስፍኑ ጋር እንደነበረ

ምዕራፍ 3፦-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመፈተን አሕዛብን እንደተዋቸው፣ ይህም ጦርነት እንዲያስተምሯቸው እንደሆነ

-የእስራኤል ልጆች ክፉ ሥራን እንደሠሩ፣ በዚህም ምክንያት እስራኤል በጦርነት እንደተመታች

-የእስራኤል ልጆች ወደ እግዚአብሔር እንደጮሁና እግዚአብሔርም ናያድን እንዳስነሣላቸው

ምዕራፍ 4፦-እስራኤላውያን በበደላቸው ምክንያት እግዚአብሔር ለአሦር ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ለሲሣራ አሳልፎ እንደሰጣቸው

-እስራኤላውያን ወደእግዚአብሔር እንደጮሁና በዲቦራና በባርቅ አማካኝነት እንዳዳናቸው

-ሲሣራን የሔቤር ሚስት ኢያዔል በካስማ መትታ እንደገደለችው

ምዕራፍ 5፦ -ዲቦራና ባርቅ እንደዘመሩ

ምዕራፍ 6፦ -የእስራኤል ልጆች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ መሥራታቸውና በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በምድያም እጅ አሳልፎ እንደሰጣቸው

-የእስራኤል ልጆች መከራ ስለደረሰባቸው ወደእግዚአብሔር መጮኻቸው፣ እግዚአብሔርም በጌዴዎን አማካኝነት እስራኤልን መርዳቱ

-ጌዴዎን መሥዋዕትን መሠዋቱ፣ የሠዋበትን ቦታም የእግዚአብሔር ሰላም እንዳለው፣ የጣዖታትን መሠዊያዎች እንዳፈረሰ

-ጌዴዎን በአውድማ ላይ የተባዘተ የበግ ጸጉር እንዳኖረ፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ በተባዘተው ጸጉር ብቻ ጠል ማውረዱ፣ ቀጥሎ በሌላው ጠል አውርዶ በተባዘተው የበግ ጸጉር ጠል አለማውረዱ

ምዕራፍ 7፦ -ጌዴዎን የፈራ ይመለስ ብሎ አዋጅ መንገሩ

-ጌዴዎን ውሻ እንደሚጠጣ ውሃ በምላሱ የሚጠጣውንና በጉልበቱ ተንበርክኮ የሚጠጣውን ወደጦር ሜዳ እንዳልወሰደው

-ጌዴዎን 300 ሰዎችን ይዞ ምድያማውያንን ድል እንዳደረገ

- ጌዴዎን ኃይል የእግዚአብሔር ሰይፍ የጌዴዎን በሉ እንዳለ

ምዕራፍ 8፦ -የኤፍሬም ሰዎች ለጦርነት ለምን አልጠራህንም ብለው ጌዴዎንን መጠየቃቸው

-እስራኤላውያን ጌዴዎንን ከምድያም እጅ አድነህናልና አንተ ልጅህም የልጅ ልጅህም ደግሞ ግዙን ማለታቸው። ጌዴዎን ግን እኔ አልገዛችሁም እግዚአብሔር ይገዛችኋል እንጂ እንዳላቸው።

-በጌዴዎን ዘመን ምድሪቱ (እስራኤል) አርባ ዓመት እንዳረፈች

-ጌዴዎን ሸምግሎ እንዳረፈ

-ጌዴዎን ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ጣዖት ማምለካቸው

ምዕራፍ 9፦ -የጌዴዎን ልጅ አቤሜሌክ ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ እንደገደላቸው

-የጌዴዎን ትንሹ ልጁ ኢዮአታም በገሪዛን ተራራ ላይ ቆሞ እንዳለቀሰ፥ ዛፎች ተሰብስበው ወይራን ንገሽልን አሏት ከሚለው ጀምሮ ዛፎች ዶግን ንገሽልን አሏት እስከሚለው ድረስ ያለውን መስሎ እንደተናገረ

-የሰቂማ ሰዎች አቤሜሌክን እንደከዱት

-አቤሜሌክን አንዲት ሴት በወፍጮ መጅ አናቱን እንደመታችው፣ ሴት ገደለችው እንዳይባልም ጋሻ ጐግሬውን በሰይፍ ግደለኝ ብሎት በሰይፍ እንደሞተ

ምዕራፍ 10፦ -ከአቤሜሌክ ሞት በኋላ ቶላ እስራኤልን ለማዳን እንደተነሣ፣ ከእርሱ በኋላ ኢያዕር እንደተነሣ

-የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ስለበደሉ እግዚአብሔር ለፍልስጤማውያን አሳልፎ እንደሰጣቸው

ምዕራፍ 11፦ -ዮፍታሔ ጽኑዕ ኃያል ሰው እንደነበረ

-ሕዝቡ ዮፍታሔን መስፍን እንዳደረጉት

-የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ እንደመጣ

-ዮፍታሔ ከጦርነት ከተመለስኩ ከቤቴ ደጅ ወጥቶ የሚቀበለኝን መሥዋዕት አደርገዋለሁ ብሎ እንደተሳለ፣ ጦርነቱን አሸንፎ ሲመለስ ልጁ ልትቀበለው እንደወጣች፣ በቃሉ መሠረት ልጁን እያዘነ ለእግዚአብሔር እንደሠዋት፣ እርሷም ለእግዚአብሔር በአፍህ እንደተናገርክ አድርግ ማለቷ፣ ለድንግልናዋ ሁለት ወር እንድታለቅስ ማስፈቀዷ

ምዕራፍ 12፦ -ዮፍታሔ ከኤፍሬም ሰዎች ጋር ጦርነት እንደገጠመ

-ከዮፍታሔ ሞት በኋላ ሐሴቦን፣ ኤሎን፣ ለቦን በተከታታይ እስራኤልን እንደገዙ

ምዕራፍ 13፦ -የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደገና ክፉ ሥራ እንደሠሩ፣ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ለፍልስጥኤማውያን አሳልፎ እንደሰጣቸው

-መልአክ የማኑሄን ሚስት ልጅ ትወልጃለሽ እንዳላትና ከፀነሰች በኋላ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ እንዳትጠጣ መታዘዟ፣ ከእርሷ የሚወለደው ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን መነገሯና በራሱ ላይ ምላጭ እንዳይደርስበት መነገሩ

-ማኑሄ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር እንደሠዋና መልአኩ በመሠዊያው ነበልባል አድርጎ ወደሰማይ እንዳረገ

-የማኑሄ ሚስት ሶምሶንን እንደወለደች

ምዕራፍ 14፦ -ሶምሶን የአንበሳውን ደቦል እንደገደለውና ይህንን ግን ለእናት ለአባቱ እንዳልተናገረ፣ ከጥቂት ቀናት በኋላ ከሞተው አንበሳ አፍ ማር አግኝቶ እንደበላ

-ሶምሶን ሚስት እንዳገባ፣ ከበላተኛ መብል ወጣ ከብርቱም ጣፋጭ ወጣ ብሎ እንቆቅልሽ መጠየቁ፣ እንቆቅልሹን የተጠየቁት አካላት መፍታት እንዳልቻሉ፣ መፍታት ሲያቅታቸው ሚስቱን ማስፈራራታቸው፣ ሶምሶን ለሚስቱ እንቆቅልሹን መንገሩ፣ እንቆቅልሹን የተጠየቁት አካላት ከሚስቱ ተረድተው መመለሳቸው፣ በዚህ ሶምሶን ተናዶ ወደሀገሩ መመለሱ፣

ምዕራፍ 15፦ -የሶምሶን ሚስቱ ከስር ሚዜው ጋር መጋባቷ፣ በዚህ ተናዶ ሶምሶን 300 ቀበሮዎችን ሰብስቦ በጅራቶቻቸው መካከል አንድ ችቦ አድርጎ ቢለቃቸው የፍልስጥኤማውያንን እህል ማቃጠሉ፣ ሶምሶን በወደቀ የአህያ መንጋጋ አንድ ሺ ሰው መግደሉ፣ በኋላ ተጠምቶ ሳለ ከአህያው መንጋጋ ውሃ አግኝቶ መጠጣቱና ከጥሙ እንዳረፈ

ምዕራፍ 16፦ -ሶምሶን ደሊላን እንዳገባ

-ፍልስጥኤማውያን ሶምሶን በምን እንደሚሸነፍ ጠይቃ እንድትነግራቸው ደሊላን ገንዘብ እንሰጥሻለን ብለው መጠየቃቸው

-ሶምሶን ለደሊላ ስለኃይሉ ሦስት ጊዜ ዋሽቶ እንደነገራት፣ በአራተኛው ግን የኃይሉን ምንጭ በትክክል እንደነገራትና ጸጉሬ ከተላጨ ኃይሌን አጣለሁ እንዳላት፣ አስተኝታም ጸጉሩን እንዳስላጨችውና የእርሱም ኃይሉ እንደደከመ

-ፍልስጥኤማውያን ሶምሶንን ይዘው ዓይኑን እንዳወጡትና በእግር ብረት እንዳሠሩት፣ በግዞት ሆኖም እህል ይፈጭ እንደነበረ

-ፍልስጥኤማውያን ለጣዖታቸው መሥዋዕት ሊሠዉ መሄዳቸው፣ ሶምሶንን ጠርተው እንደተዘባበቱበት፣ የሶምሶን ጸጉሩ እንደገና አድጎ ስለነበረ የሚመራውን ሰው እንድደገፋቸው ምሰሶዎች ጋር ውሰደኝ ማለቱ

-ሶምሶን ጸልዮ ምሰሶዎቹን በሙሉ ኃይሉ ቢገፋቸው ቤቱ በቤቱ ውስጥ ባሉ ሰዎች ሁሉ መውደቁና ሁሉም መሞታቸው ሶምሶንም መሞቱ

-ሶምሶን በሕይወቱ ከገደላቸው በሞቱ የገደላቸው መብዛታቸው

ምዕራፍ 17፦ -በኤፍሬም ሀገር ሚካ የተባለ ሰው ጣዖት እንዳስቀረጸና አንዱን ሌዋዊም የጣዖቱ ካህን እንዳደረገው

ምዕራፍ 18፦ -የዳን ነገድ የተቀረጸውን የሚካን ጣዖት ለራሳቸው እንዳቆሙ

ምዕራፍ 19፦-በተራራማው በኤፍሬም ሀገር ማዶ የተቀመጠ አንድ ሌዋዊ እንደነበረና ከይሁዳ ቤተልሐም ሚስት እንዳገባ

-ይህ ሌዋዊ ከሚስቱ ጋር እንግዳ ሆኖ ከአንድ ሽማግሌ ቤት እንዳደረ፣ የኢያቡሴዎን ሰዎች ሽማግሌውን ሰው ወደቤትህ የገባውን ሰው እንድረስበት አውጣልን እንዳሉት፣ ሌዋዊውም ዕቅብቱን እንዳወጣላቸውና እንዳዋረዷት፣ ሌሊቱን ሙሉ እስኪነጋ ድረስ እንዳመነዘሩባት፣ ጠዋት ሞታ መገኘቷ፣ ሌዋዊውም በሕይወት ያለች መስሎት "ተነሺ እንሂድ" ማለቱ፣ መሞቷን ሲያውቅ ሰውነቷን ለአሥራ ሁለት ቆራርጦ ፍረዱኝ ብሎ ለእያንዳንዱ ነገድ መላኩ

ምዕራፍ 20፦ -የእስራኤል ልጆች ሁሉ ከነገደ ብንያም ጋር መግጠማቸው፣ ለመጀመሪያ ጊዜና ደግመውም ለሁለተኛ ጊዜ ነገደ ብንያም ከእስራኤላውያን ብዙ እንደገደሉ፣ በሦስተኛው ነገደ ብንያም እንደተሸነፈ

ምዕራፍ 21፦ -በእስራኤል ንጉሥ እንዳልነበረና ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ እንደነበረ

መጽሐፈ ሩት

ምዕራፍ 1፦ -መሳፍንት ይገዙ በነበረ ጊዜ በሀገሩ ላይ ረኃብ መሆኑ፣ አቤሜሌክም ከሚስቱና ከሁለት ልጆቹ ጋር ከይሁዳ ቤተልሔም ተነሥቶ ወደሞዓብ ምድር መሄዱ፣ የሚስቱ ስም ኑኃሚን እንደሆነ

-አቤሜሌክ በተሰደደበት ሀገር መሞቱ፣ ልጆቹ ከሞዓብ ሴቶችን አግብተው እንደኖሩና ትንሽ ቆይተው እንደሞቱ

-ኑኃሚን ከሁለት ምራቶቿ ጋር ብቻዋን መቅረቷ፣ በሞዓብ ምድር ሳለች እግዚአብሔር ሕዝቧን እንደጎበኘ መስማቷና ወደሀገሯ ለመመለስ መወሰኗ፣ ምራቶቿን ግን መርቃ ወደወገኖቻችሁ ተመለሱ ማለቷ፣ የአንዱ ልጇ ሚስት ዖርፋ ወደወገኖቿ መመለሷ

-ሩት ኑኃሚንን ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል በምትሞችበትም እሞታለሁ ብላ ተከትላት መሄዷ

ምዕራፍ 2፦ -ሩት ከቦዔዝ እርሻ አጫጆች ኋላ ኋላ እየሄደች በእርሻ ውስጥ መቃረሟ፣ ቦዔዝም ቃርሚያ ለመቃረም ወደሌላ እርሻ አትሂጂ ከዚሁ ቃርሚ እንዳላት፣ ለኑኃሚን ያደረገችላትን

መልካም ነገር ሰምቶ እንደመረቃት፣ የተጠበሰ እሸት እንደሰጣት፣ የቃረመችውን ወቅታ ወደኑኃሚን እንደወሰደችው

ምዕራፍ 3፦ -ኑኃሚን ሩትን ታጥበሽ፣ ተቀብተሽ ወደ ቦዔዝ አውድማ ውረጂ እንዳለቻት፣ ሩት አማቷ ያዘዘቻትን ሁሉ እንዳደረገች፣ ቦዔዝ ስድስት መሥፈሪያ ገብስ ሠፈሮ ለሩት እንደሰጣት

ምዕራፍ 4፦ -ቦዔዝ ሩትን እንዳገባት፣ ሩትም ከእርሱ ወንድ ልጅን እንደወለደችና ስሙንም ኢዮቤድ እንዳለችው፣ ኢዮቤድ የዳዊትን አባት እሴይን እንደወለደ

አንደኛ ሳሙኤል

ምዕራፍ 1፦ -ሕልቃና ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ይሠዋ ዘንድ ከከተማው ከአርማቴም በየዓመቱ ይወጣ እንደነበረ

-ሐና ልጅ ስላልነበራት ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየችና ልጅ ከወለደች ለእግዚአብሔር እንደምትሰጠው መሳሏ

-ዔሊ ሐናን በሰላም ሂጂ የእስራኤል አምላክ ከአንቺ ጋር ይሁን ብሎ እንደመረቃት

-ሐና ወንድ ልጅ እንደወለደችና ስሙንም ሳሙኤል እንዳለችው

ምዕራፍ 2፦- ሐና በጸሎቷ የእግዚአብሔርን ቅዱስነት፣ ጻድቅነት፣ ዐዋቂነት፣ ጸሎትን የሚሰማ መሆኑን፣ የጻድቃንን ዘመን እንደሚባርክ መግለጿ

-ሐና ኃይለኛ በኃይሉ፣ ሀብታም በሀብቱ፣ ጥበበኛ በጥበቡ መመካት እንደሌለበት በጸሎቷ መግለጿ

-የካህኑ የኤሊ ልጆች ክፉዎች እንደነበሩ መገለጹ

-ካህኑ ኤሊ ልጆቹ መበደላቸውን ሰምቶ አለመገሠጹ

ምዕራፍ 3፦ -ሳሙኤል እግዚአብሔርን ያገለግል እንደነበር

-እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንደጠራው

-ኤሊ ልጆቹን ባለመገሠጹ በእርሱና በልጆቹ መቅሠፍት እንደሚመጣ እግዚአብሔር ለሳሙኤል መግለጡ

ምዕራፍ 4፦ -ፍልስጥኤማውያን እስራኤላውያንን መግጠማቸውና ማሸነፋቸው

-ፍልስጥኤማውያን ታቦተ ጽዮንን መማረካቸው፣ አፍኒንና ፊንሐስን መግደላቸው

-ኤሊ የታቦተ ጽዮንን መማረክ ሲሰማ ከወንበሩ ወድቆ እንደሞተ

ምዕራፍ 5፦ -ፍልስጥኤማውያን ታቦተ ጽዮንን ማርከው ወደዳጎን ቤት ማስገባታቸውና በዳጎን አጠገብ ማስቀመጣቸው

-ዳጎንን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በምድር ላይ በግንባሩ ወድቆ ማግኘታቸው፣ የዳጎን ራስ ሁለቱ እጆቹም ተቆርጠው እየራሳቸው ወድቀው እንደነበር

-በታቦተ ጽዮን ምክንያት የማረኳት ሀገር ሰዎች መታመማቸው

ምዕራፍ 6፦ -የእግዚአብሔር ታቦት በፍልስጥኤማውያን ሀገር ሰባት ወር እንደተቀመጠችና በዚህ ምክንያት በሀገሩ አይጦች መብዛታቸው

-ለታቦተ ጽዮን የበደል ካሣ ሰጥተው በሠረገላ አድርገው ወደሌላ ሀገር መላካቸው

-ታቦተ ጽዮን በሠረገላ በሁለት ላሞች እየተሳበች ስትመጣ በአጨዳ የነበሩት የቤትሳሚስ ልጆች ደስ ብሏቸው እንደተቀበሏት፥ የኢያኮንዩ ልጆች ግን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት ተመልክተው ከቤትሳሚስ ሰዎች ጋር አለመቀበላቸው

ምዕራፍ 7፦ -ሳሙኤል እስራኤላውያንን ከጣዖት አምልኮ እንዲርቁ መናገሩ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲያመልኩ መንገሩ

-እስራኤላውያን ሳሙኤልን ወደእግዚአብሔር ጸልይልን ማለታቸው፣ ሳሙኤልም መሥዋዕትን መሠዋቱ

-ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤል ጋር ገጥመው መሸነፋቸው

ምዕራፍ 8፦ -የሳሙኤል ልጆች ፍርድ ማድላታቸው፣ መማለጃ መብላታቸው

-እስራኤላውያን ሳሙኤልን ንጉሥ አንግሥልን ማለታቸው

ምዕራፍ 9፦ -ሳኦል የአባቱ አህዮች ጠፍተው ሊፈልግ መሄዱ

-ሳኦል አህዮች ያሉበትን ይጠቁመው ዘንድ ወደሳሙኤል መሄዱ

-እግዚአብሔር ለሳሙኤል ሳያልን እንዲያገሠው መንገሩ

ምዕራፍ 10፦ -ሳሙኤል ሳኦልን ቀብቶ እንዳነገሠው

ምዕራፍ 11፦ -አሞናዊው ናያስ እስራኤላውያንን ቀኝ ዓይናችሁን ገብሩልኝና ቃል ኪዳን እናድርግ ብሎ መሳደቡ

-ሳኦል ሕዝቡን በሦስት ወገን አሰልፎ አሞናውያንን እንደመታ

ምዕራፍ 12፦ -ሳሙኤል ለሕዝቡ የመሰናበቻ ንግግር ማድረጉ እግዚአብሔርን ፍሩ ማለቱ፣ እግዚአብሔርን ባትፈሩ ትጠፋላችሁ ማለቱ

ምዕራፍ 13፦ -ሳኦል ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጪ ቢሄድ ሳሙኤል እንደገሠጸው

ምዕራፍ 14፦ -ዮናታን ወደ ፍልስጥኤማውያን ሰፈር ገብቶ እንደበታተናቸው

ምዕራፍ 15፦ -ሳኦል አማሌቃውያንን ፈጽሞ እንዲያጠፋ መታዘዙ፣ ሳኦል ግን አጥፋ የተባለውን ባለማጥፋቱ ንግሥናው እንደተናቀ

-ሳሙኤል ሳኦልን መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል እንዳለው

ምዕራፍ 16፦ -ሳሙኤል ቀጣዩን ንጉሥ መርጦ ይቀባ ዘንድ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወደእሴይ ቤት መሄዱ

-እግዚአብሔር ሳሙኤልን ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል ብሎ እንደነገረው

-ሳሙኤል ዳዊትን በወንድሞቹ መካከል ቀብቶ ማንገሡ

-የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል እንደራቀና ሳኦልን ክፉ መንፈስ እንዳስጨነቀው

-ዳዊት በገና ይዞ በእጁ ሲመታ ሳኦልን ደስ ያሰኘውና ያሳርፈው እንደነበረ፣ ክፉ መንፈስም ከሳኦል ይርቅ እንደነበር

ምዕራፍ 17፦ -ጎልያድ ግዙፍ ሰው እንደነበር

-ዳዊት ለወንድሞቹ ስንቅ ይዞ ወደጦር ሜዳ መሄዱ

-ዳዊት ከወንዝ አምስት ድብልብል ድንጋዮች ወስዶ ጎልያድን በወንጭፍ እንደገደለው

ምዕራፍ 18፦ -ዮናታን ዳዊትን እንደነፍሱ ይወደው እንደነበር

-እስራኤላውያን ዳዊት እልፍ ገዳይ ሳኦል ሺ ገዳይ እያሉ ሲዘፍኑ ሳኦል በዳዊት ላይ መቅናቱ

-ሳኦል ዳዊትን በያዘው ጦር ሊገድለው እንደሞከረ

-ዳዊት የሳኦልን ልጅ ሜልኮልን እንዳገባ

ምዕራፍ 19፦ -ሳኦል ለልጁ ለዮናታንና ለብላቴኖቹ ሁሉ ዳዊትን ይገድሉ ዘንድ እንደነገራቸው

-ዮናታን ዳዊትን አባቱ ሳኦል ሊገድለው እንደሚፈልግ መንገሩ፣ ዳዊትም ከሳኦል ሸሽቶ እንዳመለጠ

-በነቢያት ጉባኤ መካከል የተገኙ የሳኦል መልእክተኞች ትንቢት መናገራቸው

ምዕራፍ 20፦ -ዮናታን ዳዊችን እንዲሸሽ እንደረዳው፣ ዳዊትና ዮናታንም በእግዚአብሔር ስም መማማላቸው

ምዕራፍ 21፦ -ዳዊት ወደካህኑ ወደአቤሜሌክ ሄዶ የተቀደሰ እንጀራ እንደበላ

-አቤሜሌክ የጎልያድን ሰይፍ ለዳዊት እንደሰጠው

-ዳዊት በጌት ንጉሥ በአንኩስ ፊት እብድ መስሎ ከመገደል እንደተረፈ

ምዕራፍ 22፦ -ሳኦል ዳዊትን ስለረዱ ካህኑን አቤሜሌክንና ሌሎችንም ካህናት በዶይቅ እንዳስገደላቸው

ምዕራፍ 23፦ -ዳዊትና ሰዎቹ ቂአላን ከፍልስጥኤማውያን እጅ እንዳዳኑ

ምዕራፍ 24፦ -ሳኦል በዋሻ ውስጥ በዳዊትና በዳዊት ሰዎች እጅ ወድቆ እንደነበረና ዳዊት ግን ልብሱን ብቻ በቀስታ ቆርጦ እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን አላነሣም ብሎ ሳኦልን አለመግደሉ፣ ሳኦልም በኋላ ሲያውቅ ዳዊትን እኔ ክፉ በመለስኩልህ ፋንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ እንዳለውና እግዚአብሔር መልካሙን ይመልስልህ ብሎ እንደመረቀው

ምዕራፍ 25፦ -ሳሙኤል እንደሞተ

-የዳዊት ሰዎች የዳዊትን መልእክት ለናባል እንዳደረሱ፣ ናባል ግን ዳዊትን እንደተሳደበና እንደናቀ፣ ዳዊትም ሰይፉን ታጥቆ ወደናባል እንደሄደ፣ ወደናባል ሳይደርስ የናባል ሚስት ቀድማ ደርሳ ምሕረትን ለናባል እንደለመነችለት፣ ዳዊት በአቤግያ ልመና ምክንያት ናባልን አለመግደሉ፣ ናባል ዳዊት መጣ ሲሉት ደንግጦ እንደሞተ፣ ዳዊት አቢግያን ሚስቱ እንዳደረጋት

ምዕራፍ 26፦ -አቢሳ ሳኦልን አግኝቶት በጦር ከምድር ላጣብቀው ባለ ጊዜ ዳዊት እግዚአብሔር በቀባው እጅን ማንሣት አይገባም ብሎ አቢሳን እንደከለከለውና የሳኦልን ጦርና የውሃ መንቀል ብቻ እንደወሰደበት

ምዕራፍ 27፦ -ዳዊት ሸሽቶ ወደጌት ንጉሥ ወደአንኩስ እንደሄደ፣ ንጉሥ አንኩስም ዳዊት ይቀመጥባት ዘንድ ሴቂላቅ የምትባል ስፍራ እንደሰጠው

ምዕራፍ 28፦ -ሳኦል ወደመናፍስት ጠሪ ሴት ሄዶ ሳሙኤልን እንድታስነሣለት መጠየቁ

ምዕራፍ 29፦ -ፍልስጥኤማውያን ንጉሥ አንኩስን ዳዊት ጠላት እንዳይሆንብን አብሮን አይዝመት ማለታቸው

ምዕራፍ 30፦ -ሴቂላቅን አማሌቁውያን ማጥፋታቸውና የዳዊትን ሚስቶች አቤግያንና አኪናሆምን መማረካቸው

-ዳዊት አማሌቃውያንን ተዋግቶ ድል ማድረጉ

ምዕራፍ 31፦ -ፍልስጤማውያን እስራኤልን እንደወጉና ሳኦልን አቁስለው ልጁ ዮናታንን እንደገደሉ

ሁለተኛ ሳሙኤል

ምዕራፍ 1፡- ዳዊት የሳኦልንና የዮናታንን መሞት ሰምቶ ማዘኑ

-ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን የገዘን ቅኔ መቀኘቱ

ምዕራፍ 2፡- የይሁዳ ሰዎች ዳዊትን ቀብተው እንዳነገሡት

-ዳዊት ዮናታንንና ከወደቀበት አንሥተው የቀበሩትን የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎችን እግዚአብሔር ምሕረትንና ጽድቅን ያድርግላችሁ ብሎ መመረቁ

-የሳኦል ጭፍራ አለቃ የኔር ልጅ አበኔር የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን ማንገሡ

-የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ ዳዊትን ከተከተሉት ከይሁዳ ወገኖች ብቻ በቀር ሁለት ዓመት መንገሡ

-ኢያቡስቴና ዳዊት ገጥመው የዳዊት ጦር ማሸነፉ

-አሣሄል አበኔርን ለመግደል ፈጥኖ መሄዱ፣ አበኔር ከምድር እንዳላጣብቅህ አታሳደኝ ብሎ አሣሄልን መለመኑ፣ አሣሄል እምቢ ብሎ አበኔርን ሲያሳድድ አበኔር አሣሄልን እንደገደለው

ምዕራፍ 3፡- በሳኦል ቤትና በዳዊት ቤት መካከል ለብዙ ጊዜ ጦርነት እንደነበረ

-ዳዊት ልጆችን እንደወለደ

-አበኔርን ለወንድሙ ለአሣሄል ደም ተበቅሎ ኢዮአብ እንደገደለው

ምዕራፍ 4፡- የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ እንደተገደለ

ምዕራፍ 5፡- ዳዊት በይሁዳና በሌላውም እስራኤል ላይ ሁሉ እንደነገሠ

-ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደነበረ

ምዕራፍ 6፡- ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት በኮረብታው ላይ ከነበረው ከአሚናዳብ ቤት እንዳስመጣት

-ያላ ታቦተ እግዚአብሔርን ለመያዝ እጁን በዘረጋ ጊዜ እንደተቀሠፈ

-ዳዊት ታቦተ እግዚአብሔርን በአቢዳራ ቤት እንዳስቀመጣትና በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ እንደባረከ

-ዳዊት ታቦተ እግዚአብሔርን ከአቢዳራ ቤት ወደከተማ በደስታ እንዳመጣት

-ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት በገና ይደረድር እንደነበር

-የዳዊት ሚስት ሜልኮል ዳዊት ሲዘምር ብታየው እንደናቀችው

-ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት እንደዘመረ

ምዕራፍ 7፡- ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት እንዳሰበ

-እግዚአብሔር ዳዊትን ልጅህ እንጂ አንተ ቤቴን አትሠራልኝም እንዳለው

ምዕራፍ 8፡- የሶርህያ ልጅ ኢዮአብ የዳዊት የጦር አለቃ እንደነበር

ምዕራፍ 9፡- ዳዊት የዮናታንን ልጅ ሜምፌቡስቴን እንዳከበረው

ምዕራፍ 10፡- ዳዊት የአሞን ልጆች ንጉሥ ቢሞት ለማጽናናት ወደተተካው ወደአሞን ንጉሥ ወደ ሐኖን ብላቴኖችን እንደላከ፣ የአሞን ንጉሥ ግን ዳዊት የላካቸውን መልእክተኞች ልብሳቸውን ቀድዶ ግማሽ ጺማቸውን ላጭቶ አዋርዶ እንደላካቸው፣ ዳዊት ይህንን ሰምቶ ጦር እንዳዘመተና አሞናውያንን እንዳሸነፋቸው።

ምዕራፍ 11፡- ዳዊት ከኦርዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋር እንደተኛ

-ዳዊት ቤርሳቤህ ከእርሱ መጽነሷን ሲረዳ ጽንስ ለማሳሳት ባሏን ኦርዮን ከጦር ሜዳ አስመጥቶ ከእርሷ ጋር እንዲተኛ መፈለጉ፣ ኦርዮ ግን ታቦተ እግዚአብሔርና ወገኖቹ ጦር ሜዳ ሳሉ እኔ ከእርሷ ጋር አልተኛም ማለቱ

-ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ልኮ ኦርዮ በጦር ሜዳ እንዲሞት በጽኑ ሰልፍ መካከል ትተውት እንዲሸሹ መላኩ፣ ኦርዮም በዚህ ደብዳቤ መሠረት መሞቱ

-ቤርሳቤህ በባሏ በኦርዮ መሞት እንዳለቀሰች፣ ኦርዮ ከሞተ በኋላ ዳዊት ቤርሳቤህን እንዳገባት

ምዕራፍ 12፡- ነቢዩ ናታን ዳዊት በኦርዮ ላይ ያደረገውን ግፍ አንዲት በግ ባለችው ድኻ መስሎ መናገሩ፣ ዳዊትም የሠራውን በደል ማመኑና በበደሉም ማዘኑ፣ ዳዊት ከቤርሳቤህ ሰሎሞንን መውለዱ

ምዕራፍ 13፡- አምኖን በአሚናዳብ ምክር እኅቱን ትእማርን እንዳዋረዳት

-የትእማር ወንድም አቤሴሎም አምኖንን እንደገደለውና ከአባቱ ከዳዊት እንደሸሸ

ምዕራፍ 14፡- ዳዊት ከልጁ ከአቤሴሎም ጋር እንዲታረቅ ኢዮአብ በዘዴ መጠየቁ

ምዕራፍ 15፡- አቤሴሎም ወደ አባቱ ወደዳዊት እንደተመለሰ

-አቤሴሎም የእስራኤላውያንን ልብ እንደማረከ

-አቤሴሎም በሕገ ወጥ መልኩ ብዙዎቹን አስከትሎ ነገሥኩ ማለቱ

-ዳዊት ከልጁ ከአቤሴሎም ሸሽቶ እንዳመለጠ

-አኪጦፌል ከአቤሴሎም ጋር በሴራ አንድ ሆኖ ዳዊትን ሊያስገድል ይጥር እንደነበር

-ኩሲ ከአቤሴሎም ጋር ሆኖ ነገር ግን ለዳዊት የሚጠቅም ምክር ይመክር እንደነበር

ምዕራፍ 16፡- ሳሚ የሚባል የጌራ ልጅ ዳዊትን እንደረገመውና ዳዊትም ተውት ይርገመኝ እንዳለ

ምዕራፍ 17፡- ከአኪጦፌል ምክር ይልቅ የኩሲ ምክር ለአቤሴሎም ደስ እንዳሰኘው

-አኪጦፌል ምክሩ ተቀባይነትን እንዳጣ ሲያውቅ ታንቆ እንደሞተ

ምዕራፍ 18፡- አቤሴሎም ዛፍ ጸጉሩን ይዞት ተንጠልጥሎ ሳለ ኢዮአብ እንደገደለው

-ልጁ አቤሴሎም በመሞቱ ዳዊት ማልቀሱ

ምዕራፍ 19፡- ኢዮአብ ዳዊትን እንደወቀሰው

ምዕራፍ 20፡- ብንያማዊው የቢኮሪ ልጅ ሳቡሄ በዳዊት ላይ እንዳመፀ

ምዕራፍ 21፡- በዳዊት ዘመን በተከታታይ ለሦስት ዓመታት ረኃብ እንደሆነ

-ዳዊት የሳኦልን ልጆች ይገድሏቸው ዘንድ ለገባዖን ሰዎች አሳልፎ መስጠቱ

-በፍልስጥኤማውያንና በእስራኤል መካከል ጦርነት መነሣቱ

-ከራፋይም ወገን የሆነ ኤስቢ ዳዊትን ሊገድለው ሲመጣ አቢሳ እንደገደለው፣ ከዚህ በኋላ ዳዊትን ወደሰልፍ አትውጣ እንዳሉት

ምዕራፍ 22፡- ዳዊት ከጠላቶቹ በዳነ ጊዜ የዘመረውን መዝሙር ይገልጻል

ምዕራፍ 23፡- ዳዊት ከቤተልሔም ምንጭ ውሃ ማን ባጠጣኝ ባለ ጊዜ ሦስቱ ኃያላን የፍልስጥኤምን ጦር ሰንጥቀው ሄደው እንዳመጡለት፣ ዳዊት ግን ሕይወታቸውን ለእርሱ ሲሉ ሊሰጡ መሆኑን አይቶ ያመጡለትን ውሃ ሳይጠጣው ማፍሰሱ

ምዕራፍ 24፡- ዳዊት እስራኤላውያንን ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲቆጠሩ ማዘዙ፣ በዚህም ምክንያት ዳዊት ከሦስት መቅሠፍቶች አንዱን እንዲመርጥ መታዘዙ፣ ዳዊት ከሦስቱ መቅሠፍቶች ቸነፈርን መምረጡ፣ በቸነፈሩም 70 ሺ ሰው እንደሞተ፣ ዳዊት እኔ ባጠፋሁ ሕዝቡ ለምን ይሞታል ማለቱ፣ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ መሠዊያ ሠርቶም መቅሠፍቱን እንዳራቀው

አንደኛ ነገሥት

ምዕራፍ 1፡- ንጉሥ ዳዊት እንዳረጀና የምታሞቀው ድንግል ሴት እንደፈለጉለት

-የአጊት ልጅ አዶንያስ ኢዮአብንና አብያታርን ይዞ ለመንገሥ እንደሞከረ

-ንጉሥ ዳዊት በበቅሎው ላይ አስቀምጦ ሰሎሞንን እንዳነገሠው

ምዕራፍ 2፡- ዳዊት ልጁ ሰሎሞንን በርታ ሰውም ሁን ብሎ እንደመከረው

-ሰሎሞን አዶንያስን፣ ኢዮአብን፣ ሳሚ ወልደ ጌራን በተለያዩ ምክንያቶች እንደገደለ

ምዕራፍ 3፡- ሰሎሞን እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡናን እንዲሰጠው መለመኑ

-ሰሎሞን በልጅ ምክንያት ለተጣሉት ሴቶች መልካም ፍርድን መፍረዱ

ምዕራፍ 4፡- የሰሎሞን ሹማምንት እነማን እንደነበሩ መገለጹ

-ሰሎሞን ሦስት ሺ ምሳሌዎችን እንደተናገረ፣ መሓልይውም ሺህ አምስት እንደነበረ

-ሰሎሞን ስለዛፎች፣ስለአራዊት፣ስለእንስሳት፣ስለዓሣዎች፣ስለወፎች ሁሉ ይናገር እንደነበረ

ምዕራፍ 5፡- ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ስላደረገው ዝግጅት

-ኪራም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሥሪያ የሚያገለግል ዝግባና ጥድ እንዲሁም የሚሻውን ሁሉ ለሰሎሞን እንደሰጠው

-በኪራምና በሰሎሞን መካከል ሰላም እንደነበረና በመካከላቸውም ቃል ኪዳን እንዳደረጉ

ምዕራፍ 6፡- ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ እንደሠራ

ምዕራፍ 7፡- ሰሎሞን ቤተ መንግሥቱን በ13 ዓመት ሠርቶ እንዳጠናቀቀ

ምዕራፍ 8፡- የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን መጥታ ወደ ቤተ መቅደስ መግባቷ

-ንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላውያንን እንደመረቃቸው

-ሰሎሞን ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየ

ምዕራፍ 9፡- እግዚአብሔር ሰሎሞን የሠራውን ቤተ መቅደስ እንደባረከ

-እስራኤላውያን ኃጢአትን ከሠሩ ቤተ መቅደስን እንደሚያጠፋው እግዚአብሔር መናገሩ

ምዕራፍ 10፡- ንግሥተ ሳባ ጥበብን ልትጠይቅ ወደሰሎሞን መሄዷ

-ንጉሥ ሰሎሞን በእጁ ከሰጣት ሌላ ለንግሥት ሳባ የጠየቀችውን ሁሉ እንደሰጣት

ምዕራፍ 11፡- ሰሎሞን ሴቶችን ይወድ እንደነበረና ሰባት መቶ ሚስቶችና ሦስት መቶ ዕቁባቶች እንደነበሩት

-ሰሎሞን ከባዕድ ያገባቸው ሚስቶች ወደጣዖት አምልኮ እንደሳቡትና ጣዕትን እንዳመለከ

-ሰሎሞን ለሞሎክ በኢየሩሳሌም አንጻር ባለው ተራራ ላይ መስገጃን እንደሠራ

-ሰሎሞን ለጣዖት መሥዋዕትን እንደሠዋ በዚህም ምክንያት መንግሥቱ ለሁለት እንደሚከፈል መነገሩ

-በሰሎሞን ላይ ጠላት እንደተነሣበት

-አዶር ንጉሠ ኤዶምያስ እስራኤልን እንዳስጨነቃት

-የኤፍሬማዊው የናባጥና ሳሩሃ ልጅ ኢዮርብዓም የሰሎሞን አገልጋይ እንደነበር

-ነቢዩ አኪያ ኢዮርብዓም በአሥሩ ነገደ እስራኤል ላይ እንደሚነግሥ ትንቢት መናገሩ

-ሰሎሞን ኢዮርብዓምን ሊገድለው እንደፈለገ

-ኢዮርብዓም ወደግብፅ ንጉሥ ወደ ሱስቀም ኮብልሎ እንደሄደና ሰሎሞን እስኪሞት ድረስም በዚያ እንደተቀመጠ

-ሰሎሞን እንደሞተና በእርሱ ፈንታ ልጁ ሮብዓም እንደነገሠ

ምዕራፍ 12፡- ሮብዓም አገዛዝ እንዲያቀልላቸው እስራኤላውያን መጠየቃቸው

-ሮብዓም የሽማግሌዎችን ምክር ትቶ በወጣቶቹ ምክር መታለሉ

-የእስራኤል መንግሥት ለሁለት እንደተከፈለች

-ኢዮርብዓም ወልደ ናባጥ ጣዖት ሠርቶ አሥሩን ነገድ ጣዖት እንዳስመለካቸው

-ኢዮርብዓም በኮረብታዎች ላይ የጣዖት መስገጃዎችን እንደሠራና የጣኦት ካህናትን ከሌዋውያን ሳይሆን ከማንኛውም ሕዝብ እንደሾመ

ምዕራፍ 13፡- ኢዮርብዓም በመሠዊያ ለጣዖቱ ሲሠዋ ያየው አንድ ነቢይ መሠዊያ ሆይ መሠዊያ ሆይ ኢዮስያስ የተባለ ንጉሥ ያፈርስሀል፣ ካህናተ ጣዖቱንም ይሠዋብሀል ብሎ እንደተናገረ፣ ኢዮርብዓምም ነቢዩ እንደዚህ ሲናገር ቢሰማው ያዙት ብሎ እጁን ከመሠዊያው ላይ ቢያነሣ በነቢዩ ላይ የዘረጋት የኢዮርብዓም እጁ እንደደረቀች፣ በኋላ ነቢዩ ጸልዮ እጁን እንዳዳነለት፡፡

-ይህ ኢዮርብዓምን የፈወሰ ነቢይ በኋላ በቤቴሉ ሽመግሌ ሐሰተኛ ነቢይ መታለሉና በዚህም ምክንያት መንገድ ላይ አንበሳ አግኝቶ እንደገደለው፣ ያንን ነቢይ ሽማግሌው ሐሰተኛ ነቢይ በእርሱ መቃብር ላይ መቅበሩና እኔንም ስሞት ከዚህ ቅበሩኝ ብሎ ለልጆቹ መናገሩ

ምዕራፍ 14፡- የኢዮርብዓም ልጅ አብያ በታመመ ጊዜ የኢዮርብዓም ሚስት ሐኖን ወደነቢዩ አኪያ መሄዷና ስለልጇ ደህንነት መጠየቋ፣ ነቢዩ አኪያ ግን ኢዮርብዓም ስለበደለ እርሱም ዘሩም እንደሚጠፉ እንደ ነገራት፣ ልጅሽም አንቺ ተመልሰሽ ከቤት ልትደርሺ ስትይ ይሞታል እንዳላትና ነቢዩ እንዳለው እንደሆነ

-ኢዮርብዓም እንደሞተና በእርሱ ምትክ ልጁ ናባጥ እንደነገሠ

-ሮብዓም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንደሠራ

-ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት የግብፅ ንጉሥ ሱስቀም በኢየሩሳሌም ላይ መዝመቱና የንጉሡን ቤተ መዛግብትና የእግዚአብሔርን ቤት ቤተ መዛግብት እንደወሰደ

-ሮብዓም እንደሞተና በፋንታው ልጁ አብያ እንደነገሠና የእርሱም አካሄዱ ክፉ እንደነበረ

ምዕራፍ 15፡- -አብያ ሞቶ ልጁ አሳ በይሁዳ ላይ እንደነገሠና አሳ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

-አሳ የጣዖት ማምለኪያ አፀድ ስለሠራች እናቱን ከእቴጌነት መሻሩና አፀዱንም መቁረጡ

-የአሳ ልቡ በዘመኑ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም እንደነበረ

-አሳ እንደሞተና በፋንታው ኢዮሳፍጥ እንደነገሠ

ምዕራፍ 16፡- ባኦስ እንደሞተና ልጁ ኤላ በምትኩ እንደነገሠ

-ኤላ ሞቶ በፋንታው ዘምሪ እንደነገሠ

-ዘንበሪና ታምኒ በንግሥና እንደተጣሉና ታምኒን ገድሎ ዘንበሪ እንደነገሠ

-ኢዮሳፍጥ በአባቱ በአሳ መንገድ እንደሄደና የእግዚአብሔርን ሕግ እንደጠበቀ

-ኢዮሳፍጥ ሞቶ ልጁ ኢዮራም እንደነገሠ

ምዕራፍ 17፡- ነቢዩ ኤልያስ ዝናብ እንዳይዘንብ ስለመከልከሉ

-ለኤልያስ ቁራዎች በየጠዋቱና በየማታው እንጀራና ሥጋ ያመጡለት እንደነበር

-ከፈፋው ይጠጣ እንደነበር፣ በኋላ ግን ዝናብ ስለቀረ ፈፋው እንደደረቀ

-ኤልያስ ወደሰራፕታዋ መበለት ሄዶ ምግብ እንደበላ

-ነቢዩ ኤልያስ እንደተናገረው እንደእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ የሰራፕታዋ ሴት ዱቄትና ዘይት አለመጉደሉ

-ኤልያስ ሞቶ የነበረውን የሰራፕታዋን ልጅ ጸልዮ እንዳዳነው።

ምዕራፍ 18፡- -አብድዩ ነቢያትን በዋሻ ደብቆ ይመግባቸው እንደነበር

-አክዓብ ኤልያስን ባየው ጊዜ እስራኤልን የምትገለባብጥ አንተ ነህን እንዳለው፣ ኤልያስ ግን እኔ ሳልሆን ጣዖትን እያመለካችሁ እናንተ ናችሁ ማለቱ

-ኤልያስ እስራኤላውያንን እስከመቼ በሁለት ሐሳብ ታነክሳላችሁ እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፣ በዓልም አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ ማለቱ

-የጣዖቱ የበአል ነቢያት በአል ሆይ ስማን እያሉ የሠሩትን መሠዊያ እያነከሱ ቢዞሩም ምንም ድምፅ ሳያገኙ መቅረታቸው፣ እንደልማዳቸው ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ገላቸውን በጦርና በሰይፍ ቢቧጭሩም ምንም ድምፅ አለማግኘታቸው

-ኤልያስ መሥዋዕት ባቀረበ ጊዜ ከሰማይ እሳት ወርዶ መሥዋዕቱን መብላቱ፣ ሕዝቡም ይህንን ተአምር አይተው እግዚአብሔር በእውነት እርሱ አምላክ ነው ማለታቸው፣ ነቢያተ ሐሰትንም ከበው መግደላቸው

ምዕራፍ 19፡- -ነቢያተ ሐሰትን ኤልያስ እንዳስገደላቸው ሰምታ የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤል ኤልያስን ልትገድለው እንደፈለገች፣ ኤልያስም እንደሸሸና እግዚአብሔርን እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ማለቱ፣ በደደሆ ዛፍ በታች ተኝቶ ሳለ መልአክ ዳሰሰውና ተነሥተህ ብላ ብሎ የተጋገረ እንጎቻና በማሰሮ ውሃ መስጠቱ፣ በልቶ ሁለተኛ ሲተኛም መልአኩ ቀስቅሶ የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነሥተህ ብላ ማለቱ፣ ኤልያስ ያንን በልቶ ኃይል ሆኖት እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደሄደ

-ኤልሳዕ በሬዎቹን ትቶ ኤልያስን እንደተከተለው

ምዕራፍ 20፡- ኤልዛቤል ናቡቴን በግፍ እንዳስገደለችው

-ኤልያስ አክዓብ ናቡቴን ገድሎ በመውረሱ የናቡቴን ደም ውሾችችና ጅቦች በላሱበት ቦታ አክዓብም እንደሚሞት መንገሩ፣ አክዓብም መጸጸቱ

ምዕራፍ 21፡- የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዶር ሰማርያን እንደከበባትና እንደወጋት ነገር ግን እንደተሸነፈና ወልደ አዶርም በፈረስ እንዳመለጠ

ምዕራፍ 22፡- ነቢዩ ሚክያስ አክዓብ እንደሚሸነፍ ትንቢት መናገሩ፣ አክዓብ ግን በእኔ ክፉ ነገርን የሚናገር ነቢይ ስለሆነ ጦርነቱ እስኪያልቅ ብሎ ነቢዩ ሚክያስን አስሮ እንዳቆየውና ከጦርነቱ ሲመለስ ሊገድለው እንዳሰበ፣ አክዓብ ግን ነቢዩ ሚክያስ እንደተናገረው በጦርነቱ እንደሞተ

-ሰይጣን በነቢያተ ሐሰት እያደረ ሰዎችን እንደሚያሳስት መገለጹ

ሁለተኛ ነገሥት

ምዕራፍ 1፡- አካዝያስ በሰማርያ በሰገነቱ ላይ ሳለ በዐይነ ርግቡ ወድቆ እንደታመመና እድን እንደሆነ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ጠይቁ ብሎ መልእክተኞችን እንደላከ

-ነቢዩ ኤልያስ መልእክተኞችን በመንገድ አግኝቷቸው ትሞታለህ በሉት ብሏቸው እንደተመለሱ

-ኤልያስ ከአካዝያስ የተላኩ መልእክተኞችን ከእሳት ሰማይ እያወረደ እንደገደላቸው

-ኤልያስ በእግዚአብሔር ቃል እንደተናገረው አካዝያስ እንደሞተ

ምዕራፍ 2፡- ኤልያስ መጠምጠሚያውን ጠቅልሎ የዮርዳኖስን ውሃ ቢመታው የዮርዳኖስ ውሃ ወዲያና ወዲህ እንደተከፈለ

-ኤልያስ በእሳት ሠረገላና በእሳት ፈረስ ወደሰማይ እንዳረገ

-ኤልያስ ኤልሳዕን ከአንተ ሳልወሰድ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ለምን እንዳለው

-ኤልሳዕ ኤልያስን መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ እንዳለው

-ኤልሳዕ አዲስ ማሰሮ ጨውም ጨምራችሁ አምጡልኝ ብሎ በዚያ ውሃውን እንደፈወሰው

-ኤልሳዕን አንተ ራሰ በራ ብለው የሰደቡት ልጆች በድብ እንደተበሉ

ምዕራፍ 3፡- የአክአብ ልጅ ኢዮራም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-ኤልሳዕ ባለበገና አምጡልኝ እንዳለ፣ ባለበገናውም በደረደረ ጊዜ የእግዚአብሔር እጅ ወደ ኤልሳዕ ይመጣ እንደነበር

ምዕራፍ 4፡- ኤልሳዕ የአንዲትን ድኻ ሴት ገንዘብ እንዳበረከተላት

-ኤልሳዕ በጸሎቱ የሞተውን ሰው እንዳስነሣ

ምዕራፍ 5፡- የሶርያ ንጉሥ የሠራዊት አለቃ ንዕማን በዮርዳኖስ ውሃ ተጠምቆ ከለምጹ እንደዳነ

-ግያዝ ከኤልሳዕ ተደብቆ ሄዶ ከንዕማን ገንዘብ እንደተቀበለ

ምዕራፍ 6፡- ኤልሳዕ ወደውሃው የገባውን ብረት ቅርፊት ወደውሃው ጥሎ ቅርፊቱን አጥልቆ ብረቱን እንዳወጣው

-የሶርያ ንጉሥ በድብቅ የመከረውን ምክር ኤልሳዕ በሀብተ ትንቢቱ ያውቅ እንደነበር

-ኤልሳዕ ጸልዮ ለግያዝ ዙሪያቸውን ያሉትን የእሳት ፈረሶችና ሠረገሎች እንደገለጸለት

-ኤልሳዕ ግያዝን እኛ ጋር ያሉት እነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉና አትፍራ እንዳለው

-በሰማርያ ታላቅ ረኃብ ደርሶ እንደነበር

ምዕራፍ 7፡- እግዚአብሔር ሶርያውያንን የፈረስ ድምፅና የብዙ ጭፍራ ድምፅ አሰምቷቸው ሸሽተው እንደሄዱ

ምዕራፍ 8፡- አካዝያስ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

ምዕራፍ 9፡- ኢዩ በእስራኤል ላይ እንደነገሠ

ምዕራፍ 10፡- ኢዩ የጣዖት ካህናትንና አገልጋዮችን ሁሉ እንደገደለ

ምዕራፍ 11፡- ጎቶልያ የንጉሡን ዘሮች እንዳጠፋች

ምዕራፍ 12፡- ካህኑ ዮዳሄ ያስተምረው በነበረ ዘመን ሁሉ ኢዮአስ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር እንዳደረገ

ምዕራፍ 13፡- የሰማርያ ንጉሥ ኢዩአካዝ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን እንዳደረገ

-ከኢዮአካዝ ቀጥሎ የነገሠው ዮአስም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-ነቢዩ ኤልሳዕ እንደሞተ

ምዕራፍ 14፡- አሜስያስ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

-የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ ለአሜስያስ የሊባኖስ ኩርንችት ልጅህን ለልጄ ሚስት አድርገህ ስጠው ብሎ ወደሊባኖስ ዝግባ ላከ፡፡ የሊባኖስም አውሬ አልፎ ኩርንችቱን ረገጠ" ብሎ በምሳሌ እንደላከለት

-የዮአስ ልጅ ኢዮርብዓም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን እንዳደረገ

ምዕራፍ 15፡- የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያስ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-በእስራኤል ንጉሥ በፋቁሔ ዘመን የአሶር ንጉሥ ቴልጌልቴልፌልሶር እንደመጣና ከእስራኤላውያን ብዘሆችን ወደ አሶር እንዳፈለሳቸው

ምዕራፍ 16፡- አካዝ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን አለማድረጉ

ምዕራፍ 17፡- ሆሴዕ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን እንዳደረጉ

-የአሦር ንጉሥ በእስራኤል ሀገር ሌላ ሰዎችን እንዳሰፈረና እነዚያን ሰዎች አንበሳ እንዳስቸገራቸው እንዲሁም የአሦር ንጉሥ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲያስተምሯቸው ካህናትን መላኩ

ምዕራፍ 18፡- ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

-ሙሴ የሠራውን የነሐስ እባብ እስራኤላውያን ስላመለኩት ሕዝቅያስ ማጥፋቱ

ምዕራፍ 19፡- ንጉሡ ሕዝቅያስ ከሰናክሬም ይድን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብቶ እንደጸለየ

-የእግዚአብሔር መልአክ አሦራውያንን ማጥፋቱ

ምዕራፍ 20፡- ሕዝቅያስ ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል እንደተባለ

-ሕዝቅያስ ንስሓ በመግባቱ 15 ዓመት እንደተጨመረው

-ነቢዩ ኢሳይያስ ጸልዮ ጥላውን ዐሥር ደረጃ ወደኋላ እንደመለሰው

-ሕዝቅያስ ለባቢሎኑ ንጉሥ ለመሮዳህ በቤተ መዛግብቱ ያለውን ንብረት ሁሉ እንዳሳየው

ምዕራፍ 21፡- ምናሴ ጣዖትን እንዳመለከና አባቱ ሕዝቅያስ ያፈረሳቸውን የመስገጃ ኮረብታዎች መልሶ እንደሠራ፣ ልጁን በእሳት እንደሠዋ

ምዕራፍ 22፡- ኢዮስያስ በስምንት ዓመቱ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

ምዕራፍ 23፡- ኢዮስያስ ጣዖታትን እንዳስወገደ

ምዕራፍ 24፡- ኢዮአቄም ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነፆር እንደተገዛ

-ናቡከደነፆር ይሁዳን እንደማረከ

ምዕራፍ 25፡- ሴዴቅያስ ተማርኮ ወደ ባቢሎን እንደሄደ

-የናቡከደነፆር የአበዛዎች አለቃ የቀሩትን እስራኤላውያን ከጥቂት ድኻዎች በስተቀር ማርኮ ወደ ባቢሎን መውሰዱ

-ናቡከደነፆር በቀረው ሕዝብ ላይ ጎዶልያን መሾሙ

አንደኛ ዜና መዋዕል

ምዕራፍ 1፡- ከአዳም እስከ አብርሃም ያለው የዘር ሐረግ መገለጹ

-የይስማኤል የዘር ሐረግ መገለጹ፣ የኤሳው የዘር ሐረግ መገለጹ

ምዕራፍ 2፡- የእስራኤል (ያዕቆብ) ልጆች ስምና የልጅ ልጆቹ መገለጻቸው

ምዕራፍ 3፡- የዳዊት ልጆችና የልጅ ልጆች መገለጻቸው

ምዕራፍ 4፡- የይሁዳ እንዲሁም የስምዖን ልጆችና የልጅ ልጆች መገለጻቸው

ምዕራፍ 5፡- የሮቤል ትውልድ፣ የጋድ ትውልድ፣ የምናሴ ነገድ እኩሌታ ትውልድ መገለጹ

ምዕራፍ 6፡- የሌዊ ትውልድ መገለጹ

ምዕራፍ 7፡- የይሳኮር ትውልድ፣ የብንያም ትውልድ፣ የምናሴ ትውልድ፣ የኤፍሬም ትውልድ፣ የአሴር ትውልድ መነገሩ

ምዕራፍ 8፡- የብንያም ትውልድ፣ የንጉሥ ሳኦል ትውልድ መነገሩ

ምዕራፍ 9፡- እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ወደባቢሎን መማረካቸው፣ ስለሌሎች የእስራኤላውያን ትውልዶች መነገሩ

ምዕራፍ 10፡- ፍልስጥኤማውያን ከእስራኤላውያን ጋር እንደተዋጉ

ምዕራፍ 11፡- ንጉሥ ዳዊት በእስራኤላውያን ላይ እንደነገሠ

ምዕራፍ 12፡- ከተለያዩ የእስራኤል ነገዶች ዳዊትን የተከተሉት ሰዎች ዝርዝር መገለጹ

-የዳዊት ሠራዊት ብዛት መገለጹ

ምዕራፍ 13፡- ዳዊት ታቦተ እግዚአብሔርን ወደኢየሩሳሌም ማምጣቱ

ምዕራፍ 14፡- ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን በኃያላኖን ሽለቆ ድል እንዳደረጋቸው

ምዕራፍ 15፡- ዳዊት በከተማው ለራሱ ቤትን እንደሠራ

ምዕራፍ 16፡- ታቦተ እግዚአብሔርን ዳዊት በተከለላት ድንኳን እንዳኖሯትና መሥዋዕትም በእግዚአብሔር ፊት እንዳቀረቡ፣ እስራኤላውያን በታቦተ እግዚአብሔር ፊት ስለዘመሩት መዝሙር

ምዕራፍ 17፡- ዳዊት ቤተ መቅደስን ለመሥራት ቢያስብም እርሱ ሳይሆን ልጁ እንደሚሠራው መነገሩ

ምዕራፍ 18፡- ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን እንዳሸነፈ፣ እግዚአብሔር ዳዊትን በሄደበት ሁሉ ያድነው እንደነበር

ምዕራፍ 19፡- ዳዊት አሞናውያንንና ሶርያውያንን እንዳሸነፈ

ምዕራፍ 20፡- ዳዊት አራቦትን እንደያዘ፣ ከፍልስጥኤማውያን ጋር እንደገና እንደገጠመ

ምዕራፍ 21፡- ዳዊት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ እስራኤላውያንን እንደቆጠረ

-ዳዊት ከኦርና አውድማን እንደገዛ

ምዕራፍ 22፡- ቤተ መቅደስን ለመሥራት የሚያገለግሉ ዝግጅቶችንና ሌሎችንም ዳዊት ማዘጋጀቱ፣ ሲዶናውያንና የጢሮስ ሰዎች ለዳዊት ብዙ ዝግባ ያመጡ እንደነበር

-ዳዊት ብዙ ደምን በማፍሰሱ ቤተ መቅደስን እንዳይሠራ መደረጉ

ምዕራፍ 23፡- ዳዊት በእርሱ ፋንታ ልጁን ሰሎሞንን እንዳነገሠው

ምዕራፍ 24፡- ስለ ካህናት የትውልድ ሐረግና የአገልግሎት ድርሻ

ምዕራፍ 25፡- በቤተ መቅደስ በመዘምራንነት ስለሚያገለግሉ ሰዎች

ምዕራፍ 26፡- የእግዚአብሔርን ቤት የሚጠብቁ በረኞች መሾማቸው

ምዕራፍ 27፡- የእስራኤላውያን የጦር ሠራዊት አቆጣጠር በየነገዱና በየአለቃው መገለጹ

ምዕራፍ 28፡- ዳዊት ልጁን ሰሎሞንን ጠንክር ሰው ሁን እንዳለው፡፡

ምዕራፍ 29፡- ዳዊት እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ

ሁለተኛ ዜና መዋዕል

ምዕራፍ 1፡- ሰሎሞን በመንግሥቱ እንደበረታና እግዚአብሔር እንዳከበረው

ምዕራፍ 2፡- ሰሎሞን ቤተ መቅደስንና ቤተ መንግሥቱን ለመሥራት እንደተዘጋጀ

ምዕራፍ 3፡- ሰሎሞን ቤተ መቅደስን እንደሠራና በመቅደሱም ኪሩቤልን እንደሠራ

ምዕራፍ 4፡- ሰሎሞን የቤተ መቅደስን ንዋያት እንደሠራ

ምዕራፍ 5፡- ሰሎሞን ከአባቱ ዳዊት ለቤተ እግዚአብሔር የተቀበለውን ዕቃ ወደ ግምጃ ቤት ማስገባቱ

ምዕራፍ 6፡- ሰሎሞን እስራኤላውያንን ሁሉ እንደመረቀ

-ሰሎሞን ወደ እግዚአብሔር ጸሎትን እንዳቀረበ

ምዕራፍ 7፡- ሰሎሞን ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን ቍርባንና መሥዋዕት ሁሉ እንደበላ

ምዕራፍ 8፡- የንጉሥ ሰሎሞን ዓይነተኞች አለቆች 250 እንደነበሩ

ምዕራፍ 9፡- የሳባ ንግሥት የሰሎሞንን ዝና ሰምታ ሰሎሞንን በእንቆቅልሽ ልትፈትነው መሄዷ

-የሰሎሞን ሀብት ብዛት መገለጹ

ምዕራፍ 10፡- ዐሥሩ ነገደ እስራኤል ዐምፀው ኢዮርብዓምን እንዳነገሡት

ምዕራፍ 11፡- ሰማያ ዐሥሩ ነገድና ሁለቱ ነገድ ጦርነት እንዳይገጥሙ መናገሩ

ምዕራፍ 12፡- ሮብዓም የእግዚአብሔርን ሕግ እንደረሳ

ምዕራፍ 13፡- በሰማርያና በይሁዳ መካከል ጦርነት እንደነበረ

ምዕራፍ 14፡- አሳ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን ነገርን እንዳደረገ

ምዕራፍ 15፡- አዛርያስ “እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ብትሆኑ እርሱ ከእናንተ ጋር ይሆናል፡፡ ብትተዉት ግን ይተዋችኋል” ብሎ ለይሁዳና ለብንያም ነገድ መንገሩ

ምዕራፍ 16፡- ይሁዳና ሰማርያ ጦርነት እንደገጠሙ

ምዕራፍ 17፡- ኢዮሳፍጥ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳደረገ

ምዕራፍ 18፡- ነቢዩ ሚክያስ በአክዓብ ላይ ትንቢት እንደተናገረ

ምዕራፍ 19፡- ነቢዩ ኢዩ የይሁዳን ንጉሥ ኢዮሳፍጥን እንደገሠፀው

ምዕራፍ 20፡- ኢዮሳፍጥ እንደጸለየ

ምዕራፍ 21፡- የኢዮሳፍጥ ልጅ ኢዮራም ከነገሠ በኋላ ከእርሱ የሚሻሉ ወንድሞቹንና ሌሎችንም የእስራኤል መሳፍንት እንደገደለ፣ በዚህም ምክንያት ነቢዩ ኤልያስ ልጆችህም፣ ሚስትህም፣ ያለህ ንብረት ሁሉ በታላቅ መቅሠፍት ይቀሠፋል እንዳለው፣ ኢዮራም መድኃኒት በማይገኝለት ደዌ አንጀቱን እንደተቀሠፈ

ምዕራፍ 22፡- ኢዮራም ሞቶ ልጁ አካዝያስ እንደነገሠና እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ፣ አካዝያስ ከሞተ በኋላ እናቱ ጎቶልያ እንደነገሠች

ምዕራፍ 23፡- ጎቶልያ እንደተገደለች

ምዕራፍ 24፡- ኢዮአስ እንደነገሠ፣ ኢዮአስ በእግዚአብሔር ፊት ቅን እንዳደረገ

-ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ጣዖታትን እንዳመለኩና በዚህ ምክንያት ቁጣ መውረዱ

-እግዚአብሔር ለሕዝቡ ነቢያትን ይሰድላቸው እንደነበረና ነገር ግን ሕዝቡ እንዳልተመለሰ

ምዕራፍ 25፡- አሜስያስ እንደነገሠና በእግዚአብሔርም ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

-አሜስያስ በኋላ ጣዖት እንዳመለከ

ምዕራፍ 26፡- ዖዝያን እንደነገሠ፣ በዘመኑ እግዚአብሔርን እንደፈለገና እግዚአብሔርም ነገሩን እንዳከናወነለት

ምዕራፍ 27፡- ኢዮአታም እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊትም ቅን ነገርን እንዳደረገ

ምዕራፍ 28፡- አካዝ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳላደረገ

ምዕራፍ 29፡- ሕዝቅያስ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊትም ቅን ነገርን እንዳደረገ

-ሌዋውያን በእግዚአብሔር መቅደስ ያገኙትን ርኩስ ነገር ወደቂድሮን ወንዝ እንደጣሉት

ምዕራፍ 30፡- በዓለ ፋሲካ እንደተከበረ

ምዕራፍ 31፡- ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ቤት እንዲያገለግሉ ሌዋውያንን መመደቡ

ምዕራፍ 32፡- የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን ለመውረር መምጣቱ

ምዕራፍ 33፡- ምናሴ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገርን እንዳደረገ፣ ምናሴን የአሦር ንጉሥ ሠራዊት አለቆች በዛንጅር በያዙት ጊዜ እንደተጨነቀና አምላኩን እግዚአብሔርን እንደፈለገ

-ምናሴ ወደ እግዚአብሔር ጸሎትን ማቅረቡ

-አሞፅ እንደነገሠ

ምዕራፍ 34፡- ኢዮስያስ በስምንት ዓመቱ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን እንዳደረገ

-ኢዮስያስ ጣዖታትን እንዳጠፋ

-ካህኑ ኬልቅያስ የሕጉን መጽሐፍ እንዳነበበ

ምዕራፍ 35፡- ንጉሡ ኢዮስያስ የፋሲካን በዓል እንዳከበረ

ምዕራፍ 36፡- የኢዮስያስ ልጅ ኢዮአክስ እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራን እንደሠራ

-ኢዮአክስ በኢየሩሳሌም እንዳይነግሥ ፈርዖን ኒካዑ ወደግብፅ ማርኮ እንደወሰደው

-የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ በኢዮአክስ ፋንታ የኢዮስያስን ልጅ ኤልያቄምን እንዳነገሠውና ስሙንም ኢዮአቄም ብሎ እንደለወጠው

-ኢዮአቄም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢዮአቄምን ማርኮ ወደ ባቢሎን እንደወሰደው

-ኢዮአቄም ከሞተ በኋላ ኢኮንያን እንደነገሠና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ እንዲሁም እርሱንም ናቡከደነፆር ወደባቢሎን እንደወሰደው

-ሴዴቅያስ እንደነገሠና በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ እንዳደረገ

-እስራኤላውያን በእግዚአብሔር መልእክተኞች በነቢያት ይማለቁ እንደነበረ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል ያቃልሉ እንደነበረ፣ በነቢያቱ ላይ ያፌዙ እንደነበረ

-ሕዝቡ ሁሉ ወደባቢሎን ተማርከው እንደሄዱ

መጽሐፈ ኩፋሌ

ምዕራፍ 1፦ -እግዚአብሔር ለሙሴ በደብረ ሲና እንደተገለጠለትና ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደተቀመጠ

-እግዚአብሔር ለሙሴ ሕጉን እንደሰጠው

-ሙሴ ለሕዝቡ እንደጸለየ

ምዕራፍ 2፦ -እግዚአብሔር በዕለተ እሑድ ሰባት፣ በዕለተ ሠሉስ አራት ፍጥረታትን እንደፈጠረ

-እግዚአብሔር እስከ ኃጢአ ስለፈጠራቸው ፍጥረታት

ምዕራፍ 3፦ -ሰው እንደተፈጠረ

-በዕለተ ቅዳሜ ማረፍ እንደሚገባንና ስንበትን ማክበር እንደሚገባ

-በበዓላት ቀን ሥጋዊ ሥራን መሥራት እንደሚያስቀጣ

ምዕራፍ 4፦ -አዳም በሁለተኛው ሱባኤ ለፍጥረታት ስም እንዳወጣ

-ሔዋን በሳምንቱ ዓርብ ከአዳም ጎን እንደተገኘች

-አዳም በተፈጠረባት ምድር አርባ ቀን ቆይቶ ወደገነት እንዳረገ ሔዋን ሰማንያ ቀን ቆይታ እንዳረገች

-አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን እንደበሉና እንደተረገሙ

ምዕራፍ 5፦ -አዳም ከገነት ሲወጣ መሥዋዕትን እንዳቀረበ

-አዳም እስከሚስት ድረስ የፍጥረታት ሁሉ ቋንቋ አንድ እንደነበረ፣ በኋላ ግን ሰው ሲበድል ሌሎች ፍጥረታት ከመናገር እንደተከለከሉ

-ለአዳም ጎፍረቱን ይሸፍን ዘንድ እግዚአብሔር ልብስ እንደሰጠው

-እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት እንደተቀበለ

-እስከ ላሜሕ ያለው የዘር ሐረግ መገለጡ

ምዕራፍ 6፦ -ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ባለሟልነትን ማግኘቱ

-በምድር መገዳደል በርክቶ እንደነበረ

-ኖኅ መርከብን እንደሠራ

ምዕራፍ 7፦ -ኖኅ ከማየ አይኅ በኋላ ከመርከብ እንደወጣ

-ኖኅ መሥዋዕትን እንደሠዋ፣ እግዚአብሔር ለኖኅ ቃል ኪዳን እንደሰጠው

-ሰው ደምን፣ ብርዶን እንዳይበላ መታዘዙ

ምዕራፍ 8፦ -ኖኅ ወይን እንደተከለ

-ኖኅ ሴምንና ያፌትን እንደመረቃቸው

-ኖኅ ልጆቹን በመልካም ሥራ ይጸኑ ዘንድ እንደመከራቸው

ምዕራፍ 9፦ -ምድር ለካም፣ ለሴም እና ለያፌት ለሦስት ተከፍላ እንደተሰጠቻቸው

ምዕራፍ 10፦ -ለኖኅ የመድኃኒት ዓይነቶች እንደተገለጡለት

-ኖኅ እንደሞተና ሉባር በሚባል ተራራ እንደተቀበረ

-የሰው ቋንቋ እንደተደበላለቀ

-አብርሃም እርሻን በማረሻ ማረስ እንደጀመረ

ምዕራፍ 11፦ -አብርሃም ሌሊት ተነሥቶ የጣዖቱን ቤት እንዳቃጠለ፣

-የአብርሃም ወንድም አራን ጣዖታቱን ለማዳን ወደእሳቱ እንደገባና በዚያው እንደተቃጠለ

-አብርሃምን እግዚአብሔር ከወገኖችህ ተለይተህ ውጣ እንዳለውና እንደሚባርከው መንገሩ

-አባቱ ታራ አብርሃምን እንደመረቀው

-አብርሃም ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን እንዳቀረበ

ምዕራፍ 12፦ -እግዚአብሔር በሕልም አብርሃምን እንዳናገረው

-አብርሃም በሣራ ፈቃድ ከአጋር ይስማኤልን መውለዱ

-እግዚአብሔር ለአብርሃም "ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ" እንዳለው

-እግዚአብሔር ለአብርሃም መገረዝን የቃል ኪዳን ምልክት አድርጎ እንደሰጠው

ምዕራፍ 13፦ -ሣራ ይስሐቅን እንደወለደች

-የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን እንደረዳት

ምዕራፍ 14፦ -እግዚአብሔር አብርሃምን እንደሚወደው ከሰማይ ቃሎች መሰማታቸው

-አብርሃም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ይስሐቅን ሊሠዋ ሄዶ እንደነበረና በይስሐቅ ምትክ ግን በግ እንደወረደለት

-አብርሃም ያዕቆብን እንደመረቀው

ምዕራፍ 15፦ -አብርሃም ይስሐቅን እንደመከረው

-አብርሃም ለይስሐቅ መሥዋዕት የሚሠዋባቸው እንጨቶችን ለይቶ መንገሩ

ምዕራፍ 16፦ አብርሃም ይስሐቅን እና ያዕቆብን እንደመከራቸውና እንደመረቃቸው

-አብርሃም ያዕቆብን በፍጹም ልቡናው እንደመረቀው

ምዕራፍ 17፡- አብርሃም ባረፈ ጊዜ ያዕቆብ በአጠገቡ ተኝቶ እንደነበር

-አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር በሥራው ፍጹም እንደነበረና በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን በእውነት ደስ እንዳሰኘው መገለጹ

-በኋላ ዘመን የሚነሡ ሰዎች በጣም ክፉዎች እንደሚሆኑ መገለጹ

-ሰዎች በሚሠሩት ኃጢአት ምክንያት ብዙ መከራዎች እንደሚመጡ

ምዕራፍ 18፡- ኤሳው ብኵርናውን በዳቦና በምስር ወጥ ለያዕቆብ እንደሸጠለት

ምዕራፍ 19፡- ርብቃ ልጇን ያዕቆብን ከከነዓን ሴቶች እንዳያገባ መምከሯ

-ርበቃ ያዕቆብን እንደመረቀችው

-ይስሐቅ ያዕቆብን እንደባረከው

ምዕራፍ 20፡- ያዕቆብ በሎዛ መሰላል ከምድር እስከሰማይ ደርሳ ራእይን እንዳየ

-ያዕቆብ ስለራሔል ኻያ አንድ ዓመት እንደተገዛ

-ያዕቆብ ከልያ፣ ከራሔል፣ ከባላ፣ ከዘለፋ ልጆችን እንደወለደ

ምዕራፍ 21፡- ሴኬም የያዕቆብን ልጅ ዲናን እንዳስነወራትና በዚህም ምክንያት የዲና ወንድሞች ሌዊና ስምዖን ለዲና መበቀላቸውና ይህም ጽድቅ ሆኖ እንቀተቆጠረላቸው

-ሴሰኛና አመንዝራ እንዲቀጡ መነገሩ

-ሰውነቱን በኃጢአት የሚያሳድፍ እንዳይኖር መነገሩ

ምዕራፍ 22፡- ርብቃ ይሁዳንና ሌዊን እንደመረቀቻቸው፣ ይስሐቅም ሌዊን በቀኝ እጁ ይሁዳን በግራ እጁ ይዞ መርቋቸዋል።

ምዕራፍ 23፡- ያዕቆብ መሥዋዕትን እንዳቀረበ፣ እግዚአብሔርም ለያዕቆብ ተገልጦለት ብዙ ነገርን እንደነገረው

-ሮቤል ከአባቱ ዕቅብት ከባላ እንደደረሰና በዚህ ምክንያት ያዕቆብ እንደተቆጣ

ምዕራፍ 24፡- ዮሴፍን ወንድሞቹ ለነጋዴ እንደሸጡት፣ ያዕቆብን ዮሴፍ ሞተ ባሉት ጊዜ ማልቀሱ

-ዮሴፍ እንደሞተ ሰምታ ባላ ስለእርሱ ስታለቅስ መሞቷ

-የያዕቆብ የልጆቹ ሚስቶች መገለጻቸው

ምዕራፍ 25፡- ርብቃ ልጇን ያዕቆብን መምከሯ

-በወንድሙ ላይ ክፉ ነገርን የሚያደርግ ቅጣት እንደሚያገኘው መነገሩ

ምዕራፍ 26፡- ይስሐቅ በ180 ዓመቱ እንዳረፈ

-ልያ ያዕቆብን ታከብረው እንደነበረ፣ ከአፏም ክፉ ነገር ተሰምቶ እንደማያውቅ መነገሩ

-ልያ እንደሞተች መነገሩ

-ኤሳውና ልጆቹ ከያዕቆብና ከልጆቹ ጋር ገጥመው መሸነፋቸው

ምዕራፍ 27፡- ዮሴፍ በፋጢፋራን ቤት መሾሙ፣ የፋጢፋራን ሚስት ዮሴፍን ለዝሙት ብትፈልገውም እርሱ እግዚአብሔርን ፈርቶ እንቢ እንዳላት

-ዮሴፍ በሐሰት ክሥ እስር ቤት እንደታሰረና የእስረኞችን ሕልም እንደተረጎመ

ምዕራፍ 28፡- ፈርዖን ሕልም እንዳየና ሕልም ፈቺዎች መተርጎም እንዳልቻሉ

-ዮሴፍ የፈርዖንን ሕልም እንደተረጎመለትና ፈርዖን ዮሴፍን እንደሾመው

ምዕራፍ 29፡- ይሁዳ ከምራቱ ከትእማር ጋር ባለማወቅ ስለተኛ ራሱን እንዳዋረደ፣ በእግዚአብሔር ፊት ያዝንና ይለምን እንደነበረ

-የዮሴፍ ወንድሞች እህል ለመሸመት ወደ ግብጽ መውረዳቸው

ምዕራፍ 30፡- ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ እንዳሳወቀ

ምዕራፍ 31፡- ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር ወደ ግብፅ እንደሄደ

-ያዕቆብ ዮሴፍን በማግኘቱ በጣም እንደተደሰተ

ምዕራፍ 32፡- ያዕቆብ ከልጆቹ ጋር በግብፅ ምድር እንደኖረ

-ግብጻውያን እስራኤላውያንን መጥላታቸው

ምዕራፍ 33፡- የፈርዖን ልጅ ሙሴን ከባሕር አግኝታ ወስዳ እንዳሳደገችው

-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በተአምራት ከግብጽ እንዳወጣቸው

-ሥጋን አብስሎ ወይም ጠብሶ መብላት ይገባል እንጂ ብርንዶውን መብላት እንደማይገባ

ምዕራፍ 34፡- እስራኤላውያን በዓመት አንድ ጊዜ ፋሲካን እንዲያከብሩ መታዘዛቸው

-ሰንበትን ማክበር እንደሚገባ መነገሩ

መጽሐፈ ሄኖክ

ምዕራፍ 1፡- ለሄኖክ እግዚአብሔር በኋላ ዘመን በደብረ ሲና እንደሚገለጥ መላእክት ራእይ እንዳሳዩት

-እግዚአብሔር ለጻድቃን ሰላምን እንደሚያደርግላቸውና የተመረጡትንም እንደሚጠብቃቸው

-ለተመረጡ ሰዎች ብርሃን፣ ፍቅር፣ ደስታና ሰላም እንደሚሆን

ምዕራፍ 2፡- ደቂቀ ሴት ወደ ደቂቀ ቃኤል ለመሄድ እንደተማማሉና ስሞቻቸው መገለጡ

-ከደቂቀ ሴትና ከደቂቀ ቃየል ረኃጅሞች ረዓይት እንደተወለዱ

-ከመሳርጋቸው የወረዱት የሴት ልጆች ለሰው ልጆች የተለያዩ ሰይጣናዊ ሥራዎችን ማስተማራቸው

ምዕራፍ 3፡- እግዚአብሔር ምድር እንደምትጠፋ ለኖኅ መንገሩ፣ ሩፋኤል መልአክ አዛዝኤልን እንዲቀጣው መታዘዙ፣

-ምድር በአዛዝኤል ትምህርት እንደጠፋች

-ጻድቃን ከመከራ እንደሚያመልጡ፣ የሰው ልጆች ጻድቃን እንዲሆኑ መነገሩ

ምዕራፍ 4፡- ሄኖክ እንደተሰወረና የተሰወረበትን ቦታ ማንም እንደማያውቅ መነገሩ

-ሄኖክ እግዚአብሔርን ያመሰግን እንደነበር፣ ሄኖክ ራእይ እንዳየ

-ሄኖክ መንበረ ስብሐትን በራእይ እንዳየ

ምዕራፍ 5፡- ረዓይት እንደሚጠፉ መነገሩ

-ሄኖክ ነፋሳትንና መካነ ነፋሳትን እንዳየ

ምዕራፍ 6፡- ዑርኤል በመብረቅና በነጎድጓድ ላይ የተሾመ መልአክ እንደሆነ

-ሄኖክ የጻድቃንንና የኃጥኣንን መካነ ነፍሳትን እንዳየ

ምዕራፍ 7፡- ሄኖክ በራእይ ያየው ዛፍ ለጻድቃንና ለትሩታን እንደሚሰጥ መነገሩ

ምዕራፍ 8፡- ሄኖክ በገነት ዕፀ በለስን እንዳየ

-በመስዕ በኩል ነፋስ በነፈሰ ጊዜ ቀቅና በረዶ፣ ውርጭና አመዳይ፣ ጤዛና ዝናም እንደሚፈስ መነገሩ

ምዕራፍ 9፡- ሄኖክ የቅዱሳን መላእክትንና የጻድቃንን መኖሪያ እንደተመለከተ

ምዕራፍ 10፡- ሩፋኤል በበሽታና በሰው ቍስል ላይ የተሾመ መልአክ እንደሆነ

ምዕራፍ 11፡- ሄኖክ የሰማያትን ምሥጢሮች እንዳየ፣ የፀሐይን የጨረቃን ጎዳና እንደተመለከተ

ምዕራፍ 12፡- ሄኖክ የሰማይ ከዋክብትን እንዳየ፣ ሄኖክ እግዚአብሔርን በራእይ እንዳየው

-ክርስቶስ እንደሚወለድ ሄኖክ ትንቢት መናገሩ

ምዕራፍ 13፡- እግዚአብሔር ጻድቃንን በስሙ እንደሚያድናቸው

ምዕራፍ 14፡- ኃጥኣን ወደ ገሃነም እንደሚጣሉ ሄኖክ በራእይ ማየቱ

ምዕራፍ 15፡- ሰዎች ከሰዎች ጋር እንደሚጣሉና ጦርነትን እንደሚያነሡ መነገሩ

-ጻድቃን በዘለዓለማዊ የሕይወት ብርሃን እንደሚኖሩ

ምዕራፍ 16፡- ሌዋታን በባሕር፣ ብሔሞት በየብስ እንደሚኖር መገለጡ

ምዕራፍ 17፡- በሰማይ ያሉ ሠራዊት ከእግዚአብሔር ትእዛዝን እንደሚቀበሉ

ምዕራፍ 18፡- ኖኅ በማየ አይኅ እንደማይጠፋ ሄኖክ ለኖኅ መንገሩ

ምዕራፍ 19፡- የሳቱ እና ያሳቱ የደቂቀ ሴት ስም ዝርዝር መጻፉ

ምዕራፍ 20፡- ለውሃዎች ሕይወታቸው ነፋስ እንደሆነ መነገሩ

ምዕራፍ 21፡- ለፀሐይ በምሥራቅ ስድስት በምዕራብ ስድስት መውጫና መግቢያ እንዳለው

ምዕራፍ 22፡- ጨረቃ ከፀሐይ ብርሃንን እየተቀበለ እንደሚያበራ መነገሩ

ምዕራፍ 23፡- በሄኖክ አቆጣጠር አንድ ዓመት በፀሐይ 364 በጨረቃ ደግሞ 354 ቀናት እንደሆኑ መነገሩ

ምዕራፍ 24፡- ፀሐይ ከከዋክብት ይልቅ እንደሚያበራና ከዋክብትን እንደሚበልጣቸው

ምዕራፍ 25፡- በምድር ዳርቻ ለነፋሳት የተከፈቱ 12 መስኮቶች እንዳሉ

ምዕራፍ 26፡- ፀሐይ በተጨማሪም ኦርያሬስ፣ ቶማስስ ተብሎ እንደሚጠራ

-ጨረቃ ደግሞ አሶንያ፣ ዕብላ፣ ብናሴ፣ ኤራዕ ተብሎ እንደሚጠራ

ምዕራፍ 27፡- በኃጥኣን ወራት ክረምቶች እንደሚያጥሩ፣ ዝናም እንደሚከለከል መነገሩ

ምዕራፍ 28፡- ጻድቃን ብዑዓን እንደሆኑ መነገሩ

-ስለዕለት መጋቢ ከዋክብት፣ ስለወር መጋቢ ከዋክብት፣ ስለአራቱ ወቅቶች መጋቢ ከዋክብት መነገሩ

ምዕራፍ 29፡- ሄኖክ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነና እንደጸለየ

ምዕራፍ 30፡- ሄኖክ ሌላ ሕልምን እንዳየ ለልጁ ለማቱሳላ መንገሩ

ምዕራፍ 31፡- ሄኖክ ስለማየ አይኅ ራእይን ማየቱ

ምዕራፍ 32፡- ሄኖክ ሌላ ራእይን እንዳየ

ምዕራፍ 33፡- ሄኖክ ሌላ ራእይን እንዳየ

ምዕራፍ 34፡- ምድር በማየ አይኅ እንደምትጠፋ ሄኖክ መናገሩ

ምዕራፍ 35፡- ሄኖክ ልጆቹ በጽድቅ መንገድ እንዲሄዱ መምከሩ

ምዕራፍ 36፡- ሄኖክ ልጆቹን ጽድቅን ውደዷት በእርሷም ሂዱ እንዳላቸው

ምዕራፍ 37፡- ኃጥኣን እንደሚፈረድባቸው፣ ክፉ ሥራን የሚሠሩ ሰዎች ወዮታ እንዳለባቸው

-ሐሰት ነገርንና የዝንጉዎች ነገርን መጻፍ እንደማይገባ

ምዕራፍ 38፡- ለኃጥኣን ወዮታ እንዳለባቸው

ምዕራፍ 39፡- የሰማይ ልጆች ሁሉ ሰማይን እንዲረዱ፣ የልዑልን ሥራ እንዲረዱ መነገራቸው

-ኃጥኣን ልዑልን እንደማይፈሩትና በዚህም ምክንያት መከራ እንደሚመጣባቸው

ምዕራፍ 40፡- ለጻድቃን በጎው ነገር ሁሉ፣ ደስታውና ክብሩ እንደተዘጋጀላቸው

ምዕራፍ 41፡- ኖኅ እንደተወለደ እግዚአብሔርን ማመስገኑ

ምዕራፍ 42፡- ጻድቃን እያበሩ እንደሚኖሩ

መጽሐፈ ዕዝራ

ምዕራፍ 1፦ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ቤተ እግዚአብሔርን ለመሥራት እንዳሰበ

-ናቡከደነፆር ማርኳቸው የነበሩ የቤተ መቅደስ ንዋያትን ንጉሥ ቂሮስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደመለሳቸው

ምዕራፍ 2፦ ወደ ሀገራቸው የተመለሱ የአይሁድ ስም ዝርዝር መጻፉ

ምዕራፍ 3፦ የኢዮሴዴቅ ልጅ ኢያሱና የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል እና ወንድሞቻቸው መሠዊያን እንደሠሩ

ምዕራፍ 4፦ የእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንደተቋረጠ

ምዕራፍ 5፦ የቤተ እግዚአብሔር ሥራ እንደገና መሠራት እንደተጀመረ

ምዕራፍ 6፦ ዳርዮስ በባቢሎን ቤተ መዛግብት ያሉ መጻሕፍት እንዲመረመሩ ማዘዙ

-ቤተ መቅደስ ተሠርቶ መጠናቀቁ

ምዕራፍ 7፦ ዕዝራ ለእስራኤል ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ እንደነበር

-ንጉሥ አርተሰስታ (አርጤክስስ) የእግዚአብሔርን ቤት በሚሠሩ አገልጋዮች ግብርና ቀረጥ እንዳይጣልባቸው ማዘዙ

ምዕራፍ 8፦ ከባቢሎን ስለወጡት አይሁድ መነገሩ

-እስራኤል ጾምን እንዳወጁ፣ እግዚአብሔርን እንደለመኑና እርሱም እንደሰማቸው

ምዕራፍ 9፦ ዕዝራ እስራኤላውያን ከአሕዛብ ጋር ተጋብተው ባየ ጊዜ እንዳዘነና እንደጸለየ

ምዕራፍ 10፦ እስራኤላውያን ከአሕዛብ ሚስቶቻቸው (ባሎቻቸው) እንደተለዩ

መጽሐፈ ነህምያ

ምዕራፍ 1፦ ነህምያ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረሱን ሰምቶ እንዳዘነና እንደጸለየ

ምዕራፍ 2፦ ንጉሡ አርተሰስታ የነህምያን ማዘን አይቶ ለምን እንዳዘነ መጠየቁ

-ንጉሥ አርተሰስታ ለነህምያ የኢየሩሳሌምን ከተማ እንዲሠራ መፍቀዱ

-ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት እንዳስተባበረ

ምዕራፍ 3፦ እስራኤላውያን የኢየሩሳሌም ከተማን ቅጥሮቿንና ቤቶቿን መሥራት እንደጀመሩ

ምዕራፍ 4፦ ነህምያ ጠላቶቹን እንደተቋቋመ፣

-እስራኤላውያን ጠላት ቢነሣባቸውም ሰይፍ በወገባቸው ታጥቀው ይሠሩ እንደነበረ

ምዕራፍ 5፦ ረኃብ በእስራኤል መከሠቱ

ምዕራፍ 6፦ ጠላቶች በነህምያ ላይ ሴራ ማሴራቸው

-የኢየሩሳሌም ቅጥር ተሠርቶ መጠናቀቁና የእስራኤል ጠላቶች ሁሉ ይህንን ሰምተው መደናገጣቸው

ምዕራፍ 7፦ ከስደት የተመለሱ የአይሁድ ስም ዝርዝር መገለጡ

ምዕራፍ 8፦ ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ ለሕዝቡ እንዳነበበ

-እስራኤላውያን የዳስ በዓልን እንዳከበሩ

ምዕራፍ 9፦ እስራኤላውያን ስለኃጢአታቸው ማዘናቸውና ኃጢአታቸውን መናዘዛቸው

-ዕዝራ የባለፈውን ዘመን እያስታወሰ እንደጸለየ

ምዕራፍ 10፦ እስራኤላውያን ቃል ኪዳን እንዳደረጉ

ምዕራፍ 11፦ እስራኤላውያን በየርስታቸውና በየከተማቸው እንደተቀመጡ

ምዕራፍ 12፦ የሌዋውያን ስም ዝርዝር መጻፉ

ምዕራፍ 13፦ እስራኤላውያን በሙሴ መጽሐፍ መሠረት ከአሕዛብ መለየታቸው

-እስራኤላውያን ሰንበትን በሚገባ እንዲያከብሩ መነገሩ

መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

ምዕራፍ 1፦ ዕዝራ ሌላ ስሙ ሱቱኤል እንደሆነ

-ዕዝራ የሚያስደነግጥ ራእይ እንዳየ

ምዕራፍ 2፦ የሰው እእምሮ ውሱንነት መነገሩ

-ስለዛፎችና ስለባሕር ምሳሌ

-ዓለም የጻድቃንን ተስፋ ማስቀረት እንደማይችል መነገሩ

ምዕራፍ 3፦ ስለ ዓለም ፍጻሜ መነገሩ

-ብዙዎች ያልጠረጠሩት እንደሚነግሥ መነገሩ

-በብዙ ሀገሮች ሽብር እንደሚሆን መነገሩ

ምዕራፍ 4፦ በምጽአት ክፋት እንደምትደመሰስ፣ ተንኮልም እንደምትጠፋ፣ ሞት ድል እንደሚነሡ መነገሩ

-ዕዝራ ዳግመኛ ሰባት ቀን ቢጾምና ቢጸልይ የበለጠ ሞሥጢር እንደሚያይ መነገሩ

ምዕራፍ 5፦ ጻድቃን ሰፊውን ዓለም ተስፋ አድርገው ጠባቡን እንደሚታገሡት፣ ኃጥኣን ግን ጠባቡን ታምነው ሰፊውን እንደማያገኙት መነገሩ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የጠበቁ ብፁዓን እንደሆኑ መነገሩ

ምዕራፍ 6፦ እግዚአብሔር እገሌ ይሙት ባለ ጊዜ ነፍሱ ከሥጋው እንደምትለይ

-የፍርድ ቀን ለአንድ ጊዜ እንደሆነች መነገሩ

ምዕራፍ 7፦ ዕዝራ ራእይ እንዳየና እንደጸለየ

ምዕራፍ 8፦ ዛሬ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቸል ያሉ ያንጊዜ መከራን እንደሚቀበሉ

-ሄኖክ ዳግመኛ ሰባት ቀን ቢጾምና ቢጸልይ፣ ግንብ ወዳልተሠራባት ምድረ በዳ ቢሄድና ከእንጨት ፍሬ ብቻ ቢበላ፣ ሥጋ ባይበላ ወይን ባይጠጣ ወደ ልዑል ሁልጊዜ ቢጸልይ ምሥጢር እንደሚገለጥለት መነገሩ

-ዕዝራ ጽዮንን በምታለቅስ ሴት አምሳል በራእይ ማየቱ

ምዕራፍ 9፦ ዕዝራ የደረሰባቸውን መከራ መዘርዘሩ

ምዕራፍ 10፦ ዕዝራ በንስር አምሳል ራእይ እንዳየ

ምዕራፍ 11፦ ዕዝራ ከዱር በወጣ አንበሳ አምሳል ራእይን እንዳየ

ምዕራፍ 12፦ ዕዝራ ሌላ ራእይን እንዳየ

ምዕራፍ 13፦ ዕዝራ ሌላ ራእይን እንዳየ፣

-በኋላ ዘመን እውነት እንደምትጠፋ፣ ሐሰት እንደምትጸና መነገሩ

-ዕዝራ በአርባ ቀናት ኻያ አራት መጻሕፍትን እንዳስጻፈ

መጽሐፈ ዕዝራ ካልእ

ምዕራፍ 1፦ ኢዮስያስ የፋሲካውን በግ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳመጣና እስራኤላውያን እንደ ሥርዓቱ የፋሲካን በዓል እንዳከበሩ

-ኢዮስያስን በሥራው በፈጣሪው ፊት የቀና እንደነበር

-እስራኤላውያን እንደተማረኩ

ምዕራፍ 2፦ የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ቤተ እግዚአብሔርን ለመሥራት እንደተነሳሳ

ምዕራፍ 3፦ ሦስቱ የንጉሡ ጠባቂዎች በንጉሥ ዳርዮስ ፊት የሚወደድ ቃል ለመናገር እንደተወዳደሩ

ምዕራፍ 4፦ ስለንጉሥ አሸናፊነት፣ ስለሴት አሸናፊነት፣ ስለእውነት አሸናፊት በየተራ አቅራቢዎቹ እንደገለጹ

-እውነት ሁልጊዜ እንደምታሸንፍ መነገሩ

-የኢየሩሳሌምና የቤተመቅደስ ሥራ እንዲከናወን ዳርዮስ እንደፈቀደና ለሠሪዎች ምግብ እንዲሠፈርላቸው ማድረጉ

ምዕራፍ 5፦ ከምርኮ ስለተመለሱት ሰዎች የስም ዝርዝር

ምዕራፍ 6፦ ተቋርጦ የነበረው የቤተ መቅደሱ ሥራ በዳርዮስ ዘመነ መንግሥት እንደገና መሠራት እንደተጀመረ

ምዕራፍ 7፦ ቤተ መቅደሱ ተሠርቶ እንዳለቀና እንደተመረቀ

ምዕራፍ 8፦ ዕዝራ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ኦሪት ሁሉ ያውቅ እንደነበረ፣ ብዙ ትምህርትን የሚያውቅ እንደነበረና ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ከእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ የሚጎድለው እንዳልነበረ

ምዕራፍ 9፦ ዕዝራ ስለሕዝቡ ኃጢአት እንዳለቀሰ

መጽሐፈ ጦቢት

ምዕራፍ ፩፦ ጦቢት ነገዱ ከንፍታሌም እንደሆነ

-ጦቢት በጽድቅና በቅንነት መንገድ እንደሄደ

-ምጽዋትን ያደርግ እንደነበር

-ጦቢት ጦብያን እንደወለደ

ምዕራፍ ፪፦ ጦቢት የአሕዛቡ ንጉሥ ይገድላቸው የነበሩትን ሰዎች ሳይፈራ ይቀብራቸው እንደነበር

-በጦቢት ዓይን ላይ ወፍ ኩስ ቢጥልበት ዓይኑ እንደበለዘ

ምዕራፍ ፫፦ ጦቢት እንደጸለየ

-የራጉኤል ልጅ ሣራ ስታገባ ባሎቿን አስማንድዮስ የሚባል ሰይጣን ይገድልባት እንደነበረ መገለጹ

-ሣራ እንደጸለየች

ምዕራፍ ፬፦ ጦቢት ልጁን ጦቢያን ከዝሙት እንዲጠበቅ፣ ከትዕቢት እንዲጠበቅ፣ ምጽዋት እንዲሰጥ፣ እንደመከረው

-ስለምጽዋትና ስለምጽዋት ጥቅሞች መገለጹ

ምዕራፍ ፭፦ ጦቢት ጦብያን ከመልአኩ ሩፋኤል ጋር እንደላከው

ምዕራፍ ፮፦ መልአኩ ሩፋኤል ጦብያን የዓሣውን ጉበትና ሐሞት እንዲይዝ መንገሩ

ምዕራፍ ፮፥ መልአኩ ሩፋኤልንና ጦብያን ሣራ ወለተ ራጉኤል ተቀብላ ደስ እንዳሰኘቻቸው

ምዕራፍ ፯፥ አስማንድዮስ የተባለው ጋኔን ከሣራ ወጥቶ እንደሄደ

-ጦብያና ሣራ እንደጸለዩ

-የሣራ አባት ራጉኤል ጦብያና ሣራ ደህና መሆናቸውን ሲያውቅ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ

-ራጉኤል አስቆፍሮት የነበረውን መቃብር እንዳስደፈነው

ምዕራፍ ፰፥ ሩፋኤል የአደራውን ገንዘብ እንደተቀበለ

ምዕራፍ ፱፥ ጦብያ ከሄደበት ሀገር በቀጠሮው መሠረት ስላልመጣ እናቱና አባቱ ጦብያ እንዳዘኑ መገለጡ

ምዕራፍ ፲፩፥ የጦቢት ዓይን በዓሣ ጉበት ምክንያት እንደዳነና ጦቢትም እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ

ምዕራፍ ፲፪፥ እነ ጦቢት አዛርያ መልአኩ ሩፋኤል እንደሆነ መረዳታቸው

-መልአኩ እነጦቢትን እንደመከራቸው

-መልአኩ ሩፋኤል ጦቢት መልካም ባደረገ ጊዜ ሁሉ በረድኤት ከእርሱ ጋር እንደነበረ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፫፥ ጦቢት እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ

ምዕራፍ ፲፬፥ ጦቢት ፈሪሀ እግዚአብሔርን እንደጨመረ መገለጹ

-ነነዌ እንደምትጠፋ ዮናስ የተናገረው ትክክል ስለሆነ ወደ ሜዶን ሂድ ብሎ ጦቢት ጦብያን እንደመከረው

መጽሐፈ ዮዲት

ምዕራፍ ፩፥ ናቡከደነፆርና ንጉሠ ሜዶን አርፋክስድ ጦርነት እንደገጠሙ

-ንጉሥ አርፋክስድ እንደተሸነፈ

ምዕራፍ ፪፥ ናቡከደነፆር ትእዛዙን ያልተቀበሉትን በጦርነት ማጥፋቱ

ምዕራፍ ፫፥ አንዳንድ ሀገሮች ለአንተ እንገዛለን ብለው የሰላም መልእክተኞችን ወደ ናቡከደነፆር መላካቸው

-ሆሎፎርኒስ አሕዛብን ሁሉ እንዳጠፋ

ምዕራፍ ፬፡ እስራኤላውያን ሆሎፎርኒስ በአሕዛብ ላይ ያደረገውን ሰምተው እንደፈሩ መገለጹ

-የእስራኤል ልጆች ሊቀ ካህናቱና የሕዝብ አለቆች ያዘዟቸውን እንዳደረጉ

ምዕራፍ ፭፡ እስራኤል በጽድቅ መንገድ ካሉ ሆሎፎርኒስ በጦርነት እንደማያሸንፋቸው የአሞን ልጆች ሹም እንደነገረው

ምዕራፍ ፮፡ ሆሎፎርኒስ አክዮርን ለእስራኤላውያን ተላልፎ እንዲሰጥ ማድረጉ

ምዕራፍ ፯፡ ሆሎፎርኒስ የእስራኤላውያንን የውሃ ምንጭ እንደያዘ

-እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር እንደጮሁ

ምዕራፍ ፰፡ ዮዲት ደግ ሴት እንደነበረች

ምዕራፍ ፱፡ ዮዲት እንደጸለየች

ምዕራፍ ፲፡ ዮዲት አጊጣ፣ ጥሩ ልብስ ለብሳ ወደ ሆሎፎርኒስ እንደሄደች

ምዕራፍ ፲፩፡ ዮዲት እስራኤላውያን ፈጣሪያቸውን ካልበደሉ ሰይፍ ሊያጠፋቸው እንደማይችል መናገሯ

-የዮዲት ቃል ሆሎፎርኒስን ደስ እንዳሰኘውና ከሠራዊቱ ጋር በጥበቧ እንደተደነቀ

ምዕራፍ ፲፪፡ ዮዲት በሆሎፎርኒስ ግብዣ ራሷ ካመጣችው ምግብ እንደተመገበች

-ዮዲት መንገዷን ያቃናላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ እንደነበር

ምዕራፍ ፲፫፡ ዮዲት የሆሎፎርኒስን አንገት እንደቆረጠች

ምዕራፍ ፲፬፡ እስራኤላውያን የሆሎፎርኒስን ቸብቸቦ ይዘው ጠላቶቻቸውን እንደገጠሙ

ምዕራፍ ፲፭፡ አሦራውያን ደንግጠው እንደሸሹ

-እስራኤላውያን ዮዲትን እንደመረቋት

ምዕራፍ ፲፮፡ የዮዲት የምስጋና መዝሙር መገለጹ

-ዮዲት በእስራኤል ዘንድ ስለሚጨነቁት ሰዎች ስትል የመበለትነት ልብሷን እንደተወች፣ ሸቱ እንደተቀባች

መጽሐፈ አስቴር

ምዕራፍ ፩፡ መርዶክዮስ በንጉሡ በአርጤክስስ አደባባይ ያገለግል እንደነበረ

-መርዶክዮስ ሕልም እንዳየ

-መርዶክዮስ የንጉሡን ሕይወት እንዳዳነ

-ሐማ የንጉሡ የአርጤክስስ ባለሟል እንደነበረ

-ንጉሡ አርጤክስስ ግብጣ እንዳደረገና ንግሥት አስጢን በግብጣው እንዲልተገኘች በዚህም ምክንያት እንደተገደለች

ምዕራፍ ፪፡ አስቴር ከብዙዎች ሴቶች ተመርጣ ንግሥት እንደሆነች

-አስቴር የመርዶክዮስ የአጎቱ ልጅ እንደነበረች

ምዕራፍ ፫፡ መርዶክዮስ ለሐማ አይሰግድ እንደነበረ

-ሐማ አይሁድን ለማጥፋት እንዳስፈቀደ

-ሐማ መርዶክዮስ ስላልሰገደለት መቆጣቱ

ምዕራፍ ፬፡ መርዶክዮስ የአይሁድን የጥፋት አዋጅ ሰምቶ እንዳዘነ

-መርዶክዮስ አስቴርን ንጉሡን ለምነሽ አድኚን እንዳላትና እንደጸለየ

ምዕራፍ ፭፡ አስቴር ንጉሥ አርጤክስስን እና ሐማን ግብጣ እንደጠራች

ምዕራፍ ፮፡ ንጉሥ አርጤክስስ የዘመኑን የታሪክ መጽሐፍ ሲያነብ የመርዶክዮስን ውለታ ማስታወሱ

-አርጤክስስ መርዶክዮስን እንዳከበረው

ምዕራፍ ፯፡ ሐማ ራሱ ባዘጋጀው መስቀል እንደተሰቀለ

ምዕራፍ ፰፡ ንጉሡ አርጤክስስ የሐማን ንብረት ሁሉ ለአስቴር እንደሰጣት

-አይሁድ እንዲጠፉ የታወጀው አዋጅ በአዋጅ መቅረቱ

-አይሁድ ጠላቶቻቸውን እንደተበቀሉ

ምዕራፍ ፱፡ የአይሁድ ጠላቶች እንደጠፉ

-አስቴር የሐማን ልጆች በግንድ እንዳሰቀለቻቸው

ምዕራፍ ፲፡ አርጤክስስ በመንግሥቱ በምድርና በባሕር ላይ ግብር እንደጣለ

ምዕራፍ ፲፩፡ የፋሪምን መልእክት ጸጠሎሜዎስና ዞሲጢዮስ እንዳመጡ

መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

ምዕራፍ ፩፡- ጲሩጳይዳን ክፋትን የሚወድ፣ በፈረሶቹ ብዛትና ከሥልጣኑ በታች ባሉ በጭፍራዎች ይመካ እንደነበረና የሚያመልካቸው ብዙ ጣዖታት እንደነበሩት

-ጲሩጳይዳን በልቡናው ድንቁርና ጣዖታት ኃይልንና ብርታትን የሚሰጡት ይመስለው እንደነበር መገለጹ

-ጣዖታቱን የሚያገለግሉ ካህናት መሥዋዕቱን እነርሱ እየበሉ ጣዖቶቹ የሚበሉ አስመስለው ይነግሩት እንደነበር መገለጹ

-ጲሩጳይዳን ጣዖታቱ የፈጠሩት፣ ጣዖታቱም የሚመግቡትና የሚያነግሡት ይመስለው እንደ ነበር መገለጹ

-ጣዖታትን ሙታን ሊሏቸው እንደሚገባ መገለጹ

-ጲሩጳይዳን ትዕቢተኛ እንደነበር፣ በወንዶች አምሳል የተሠሩ ሃምሳ እና በሴቶች አምሳል የተሠሩ ሃያ ጣዖቶች እንደነበሩት መገለጹ

-ጲሩጳይዳን ጣዖታቱን የማያመልኩ ሰዎች እንዲቀጡ አዋጅ ማወጁ

ምዕራፍ ፪፡- መቃቢስ ከነገደ ብንያም የተወለደ እንደሆነና መልከ መልካም ልጆች እንደነበሩት መገለጹ

-የመቃቢስ ልጆች እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ስለነበሩ ለጲሩጳይዳን ጣዖታት አንሰግድም ማለታቸው

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር የመቃቢስን ልጆች ሰማዕትነትን እንዲቀበሉ መንገሩ

-ከመቃቢስ ልጆች ሦስቱ አብያ፣ ሲላ፣ ፈንቶስ እንደሚባሉ መነገሩ

-የመቃቢስ ልጆች ጣዖታትን አናመልክም በማለታቸው በጲሩጳይዳን የተለያዩ መከራዎች እንደደረሱባቸው

-የመቃቢስ ልጆች መከራችን ሲበዛ ዋጋችን ይበዛል ማለታቸው

ምዕራፍ ፬፡- ጲሩጳይዳን የመቃቢስን ልጆች በድን እንዲቃጠል ማዘዙ

-እሳት የመቃቢስን ልጆች በድን ማቃጠል እንዳልቻለ ባሕርም ማስጠም እንዳልቻለ

-በጲሩጳይዳን ግዛት የሚኖሩ ሰዎች ወንዶች ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ይሠዉ እንደነበር መገለጹ

ምዕራፍ ፭፡- ጲሩጳይዳን በወባ ትንኝ አማካኝነት እንደሞተ

-እግዚአብሔር በተለያዩ ዘመናት ያደረጋቸው መልካም ነገሮች በጥቂቱ መጠቀሳቸው

ምዕረፍ ፮፡- እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያደርጉ ነገሥታቱን እንደሚያነግሥ

-የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ነገሥታት በመንግሥተ ሰማያት እንደሚኖሩ

-ደጋግ ነገሥታት በዚህ ዓለም ሳሉ በጎ ሥራን እንደሚሠሩ መገለጹ

-ክፉ ነገሥታት የድኾችን ጩኸት ቸል እንደሚሉና የተገፋውን ሰው እንደማያድኑ

ምዕራፍ ፯፡- ንጉሥ እግዚአብሔር እንደሾመው በሚገባና በእውነት መፍረድ እንደሚገባው

-ንጉሥ የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና ትእዛዙንም ማድረግ እንደሚገባው

-ምድራዊ መንግሥት ኃላፊ እንደሆነ መገለጡ

ምዕራፍ ፰፡- ትንግሌ ሙታን በተክልና በአዝርዕት ፍሬ፣ በሰው መተኛትና መንቃት፣ በፀሐይ መግባትና መውጣት መመሰሉ

-በትንግሌ ለሁሉም እንደሥራው እንደሚከፈለው ማሰብ እንደሚገባና መስነፍ እንደማይገባ

-የእግዚአብሔር የሕይወት ጠል ካልወረደ ሙታን እንደማይነሡ መገለጹ

ምዕራፍ ፱፡- በዕለተ ትንግሌ ተራሮችና ኮረብቶች፣ ወንዞችና ጥልቆች እንደ ጥርጊያ ጎዳና እንደሚሆኑና ሥጋ ለባሽም ሁሉ ትንግሌን እንደሚነግ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፡- እግዚአብሔር ሰውን ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣው ሁሉ የሞተውን ሰውም እንደገና እንደሚያስነሣው መገለጡ

ምዕራፍ ፲፩፡- ክፉዎች በክፋታቸው እንደሚፈረድባቸውና እንደሚያለቅሱ መገለጡ

ምዕራፍ ፲፪፡- እስራኤል እግዚአብሔርን እንዳሳዘነች መገለጧ

ምዕራፍ ፲፫፡- ለኃጢአተኞች ወዮታ እንዳለባቸው መገለጹ

-ዲያብሎስ በትዕቢቱ እንደተዋረደ መገለጹ

-ቅዱሳን መላእክት በልብ ትሕትና እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት መገለጹ

-ቅዱሳን መላእክት ከእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዳይወጡና እንዳይተላለፉ ሕሊናቸውን እንደሚጠብቁ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፬፡- እግዚአብሔር ምድርን በማየ አይኅ ከቃየን ልጆች ኃጢአት ሁሉ እንዳነጻት መገለጹ

-ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ፣ ሌሎች አማልክትን አለማምለክ፣ የባልንጀራን ገንዘብ አለመመኘት፣ እግዚአብሔርን ፈጽሞ መውደድ እንደሚገባ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፮፡- መቃቢስ፣ መብክዩስ እና ይሁዳ እስራኤላውያንን ከንጉሠ ምድያም ከአክራንድዮስ እንዳዳኗቸው

ምዕራፍ ፲፯፡- ከእስራኤላውያን ውጭ ከነበሩ ሕዝቦችም እግዚአብሔርን የሚያውቁ እንደነበሩ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፰፡- የኤዶምያስና የአማሌቅ ሠራዊት እግዚአብሔርን የማያመልኩ እንደነበሩ መገለጹ

-ሰብልያኖስ ለሰው ልጅ ክፋትን እንደሚያስተምር መነገሩ

ምዕራፍ ፲፱፡- ወደ እግዚአብሔር እንደምንሄድ ማስብ እንደሚገባን

ምዕራፍ ፲፱፡- የቃየን ልጆች ለብዙ ጊዜ ጨዋታንና ዘፈንን እንዳደረጉ

-ቃየን አቤልን ከገደለ በኋላ ለአቤል የተወሰነችለትን ሚስት እንዳገባ

ምዕራፍ ፳፡- እግዚአብሔር የጻድቃንን ፍሬ እንደሚያበዛ መነገሩ

ምዕራፍ ፳፩፡- ዳዊት በእግዚአብሔር በመታመኑ ከሳኦልና ከሌሎችም ጠላቶቹ እጅ እንደዳነ መነገሩ

-ድል መንሣት ከእግዚአብሔር እንደሆነ መገለጡ

-እግዚአብሔር ሕጉን በማይጠብቅ ሰው ላይ መከራን እንደሚያመጣበት መገለጡ

ምዕራፍ ፳፪፡- በእውነት መፍረድ፣ ቸር፣ የዋህና ቅን መሆን እንደሚገባ መገለጹ

ምዕራፍ ፳፫፡- በቃየል መንገድ መሄድ እንደማይገባ

ምዕራፍ ፳፬፡- ጌዴዎን እግዚአብሔርን በመታመኑ በጥቂት ሠራዊት ብዙ የአሕዛብን ሠራዊት ድል እንደነሣ

ምዕራፍ ፳፭፡- ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ የሚገዛና የሚያስተዳድር እግዚአብሔር እንደሆነ

-ደም ግባት፣ ገንዘብ ኃላፊ እንደሆነ መገለጹ

ምዕራፍ ፳፮፡- የሰው ራሱ የጽድቅ ፍሬ እንደሆነ እና ፍሬ የሌለው በጎ ሥራ እንደሌለ መገለጹ

ምዕራፍ ፳፯፡- እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ፣ ምድርን በውሃ ላይ እንዳጸናት

ምዕራፍ ፳፰፡- ከአዳም ደጋግ ልጆች ነቢያት ነገሥታትና ክፉዎች ልጆች እንደተወለዱ

ምዕራፍ ፳፱፡- እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ቸል እንደሚላቸው መገለጹ

ምዕራፍ ፴፡- እግዚአብሔር እንደ ሕጉ የማይሄዱ ነገሥታትን ልጆች ከመንግሥትነት እንደሚከለክላቸው መናገሩ

-እግዚአብሔር ያላከበሩኝን፣ ሕጌንም ያልጠበቁትን ከሰጠኋቸው ስጦታ እለያቸዋለሁ ማለቱ

ምዕራፍ ፴፩፡- ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ነገሥታት እንደማይነግሡ መነገሩ

ምዕራፍ ፴፪፡- እግዚአብሔር ነገሥታትን ቃሌን ጠብቁ ማለቱ

ምዕራፍ ፴፫፡- እስራኤላውያን አምልኮቱን ቢተዉ መከራ እንደደረሰባቸው

ምዕራፍ ፴፬፡- ወንድም በወንድሙ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ እንደሚነሣ መነገሩ

ምዕራፍ ፴፭፡- የሚሰክሩ፣ ፍርድን የሚያዳሉና በመዳራት የሚኖሩ ሰዎች ወዮታ እንዳለባቸው

ምዕራፍ ፴፮፡- ትምክህት እንደሚያስቀጣ መነገሩ፣ መልካም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ክፉ የሠሩ ወደ ዘለዓለም ቅጣት እንደሚሄዱ መነገሩ

መጽሐፈ መቃብያን ካልእ

ምዕራፍ ፩፡- ሞዓባዊው መቃቢስ እስራኤልን ከሌሎች አሕዛብ ጋር ሆኖ እንዳጠፋቸው

-እስራኤላውያን ቢበድሉ መቃቢስ ዘሞዓብን እንዳስነሳባቸው

-መቃቢስ ዘሞዓብ እግዚአብሔር የማይወደውን የክፋት ሥራ ሁሉ እንዳደረገ

ምዕራፍ ፪፡- ንስሓ ካልገባ በመቃቢስ ዘሞዓብ የልብ በሽታና የተለያዩ መከራዎች እንደሚደርሱበት ነቢይ መናገሩ

-መቃቢስ ስለኃጢአቱ ማቅ ለብሶ በእግዚአብሔር ፊት እንዳለቀሰ

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር የመቃቢስን ንስሓ ተቀብሎ ይቅር እንዳለው

-ንስሓ የሚገቡ ሰዎች ብዙዓን እንደሆኑ መገለጹ

ምዕራፍ ፬፡- እግዚአብሔር በተለያዩ ሰዎች እያደረ እስራኤላውያንን ይረዳቸው እንደነበረ

-መቃቢስ በጎ ሥራን መሥራት እንደጀመረና መንገዱን ያቀና እንደነበር

ምዕራፍ ፭፡- መቃቢስ እንደሞተና ልጆቹ በሥርዓት እንዳደጉ፣ ገንዘባቸውን ለድሆች ይመጸውቱ እንደነበር

ምዕራፍ ፮፡- የእግዚአብሔር ጠላት ጺሩጻይዳን የሐሰት ካህናትንና የጣዖታቱን አገልጋዮች እንደሾመ፣ እነዚህም ለጣዖታት መሥዋዕትን ይሠዉ እንደነበር

-የመቃቢስ ልጆች ለጣዖታት አንሰግድም በማለታቸው እንደታሰሩና እንደተሰደቡ

-የመቃቢስ ልጆች በሰማዕትነት በእሳት ተቃጥለው እንደሞቱ

ምዕራፍ ፮፡- ሰማዕት ከሆኑ በኋላ የመቃቢስ ልጆች ለጺሩጻይዳን በራእይ ተገልጠው እንዳስፈራሩት

ምዕራፍ ፯፡- ጺሩጻይዳን በኩራትና በልብ ተንኮል እንደሄደ

ምዕራፍ ፰፡- ሰው ነገ መሬትና አመድ የሚሆን እንደመሆኑ መኩራት እንደማይገባው መነገሩ

-ኃጥኣን በጻድቃን ምክር ይኖሩ ዘንድ እንደማይወዱ መገለጹ

-ጻድቃን እግዚአብሔር ከማይወደው መንገድ ሁሉ እንደሚርቁ መነገሩ

ምዕራፍ ፱፡- ነገሥታትና መኳንንት በሰይጣን ጎዳና መሄድ እንደማይገባቸው መገለጹ

-ነገሥታትና መኳንንት እግዚአብሔርን መፍራት እንደሚገባቸው መገለጹ

ምዕራፍ ፲፩፡- ሙሴ ሕዝቡን ሲመራ እንዳልተበሳጨ መገለጡ

-የእግዚአብሔርን ቃል ካልተላለፍን ፈቃዳችንን እንደሚያደርግልን መገለጡ

ምዕራፍ ፲፪፡- የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማያደርጉ ሰዎች ወዮታ እንዳለባቸው

-ክፋትን የሚሠሩትን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው

-ጺሩጻይዳን እንደሞተ

ምዕራፍ ፲፫፡- ይህ ዓለም እንደሚያረጅና እንደሚያልፍ ተድላውም ለዘለዓለም እንደማይኖር ዐውቀው ያመኑ የመቃቢስ ልጆች ለጣዖት የተሠዋውን መሥዋዕት አንበላም በማለታቸው በሰማዕትነት ሰውነታቸው ለሞት እንደሰጡ

-ከንጉሥ ቁጣ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚከፋ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፬፡- ስለ ፈሪሳውያን፣ ስለ ሳምራውያን እና ስለሰዱቃውያን አስተምህሮ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፭፡- ጻድቃን በዳግም ምጽአት ጊዜ በደስታ እንደሚኖሩ መገለጹ

-በዕለተ ምጽአት ሁሉ እንደ ሥራው እንደሚከፈለው

-ኃጥኣን በዕለተ ምጽአት ቀድሞ በሠሩት ክፉ ሥራ እንደሚጸጸቱና እንደሚያለቅሱ

ምዕራፍ ፲፮፡- ምሥጢረ ትንሣኤን በጸጉር፣ በጥፍር መረዳት እንደሚቻል

-በጎ ሥራን የሠሩ ሰዎች የሕይወት ትንሣኤን እንደሚነሡ

-ክፉ ሥራን የሠሩ ሰዎች የደይን ትንሣኤን እንደሚነሡ

ምዕራፍ ፲፯፡- ትንሣኤ በስንዴ ቅንጣት ተመስሎ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፰፡- የሙታንን መነሣት የማያምኑ ሰዎች በዕለተ ትንሣኤ ጊዜ እንደሚጸጸቱ

ምዕራፍ ፲፱፡- ምድር መኳንንትን፣ ታላላቆችን፣ ክቡራንን፣ የተዋቡ ሴቶችንና መልካማ ቆነጃጅትን ሳይቀር፣ ደም ግባት ያላቸውን፣ ምሁራንን፣ ቃላቸው የሚያምረውን፣ ዜማቸው ደስ የሚያሰኙትን፣ ጽኑዓንን፣ ኃያላንን ሁሉ በሞት እንደሰበሰበቻቸው መገለጹ

-ምግባችንን ከመሬት እንደምናገኝና ስንሞት ደግሞ ሥጋችንን፣ ደም ግባታችንን መሬት እንደምትበላው መገለጹ

-የጻድቃንን ነፍሳት ይቀበሉ ዘንድ ወደ ሕይወት ብርሃን ቦታም ይወስዱ ዘንድ ወደ ደጋጉ የሚላኩ ረቂቃን መላእክተ ብርሃን እንደሆኑ

ምዕራፍ ፳፡- በዕለተ ትንሣኤ በምድር የሠራነው ሥራችን ሁሉ እንደማይሰወርና እንደሚገለጥ

ምዕራፍ ፳፩፡- በሞት እንደምናልፍ ገንዘባችንም እንደሚያልፍ መረዳት እንደሚገባ

መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ

ምዕራፍ ፩፡- ዲያብሎስ ግፈኛና አሳች የፈጣሪውንም መንገድ የሚጻረር እንደሆነ

-ዲያብሎስ በገንዘብና በመልከ መልካም ሴቶች ምክንያት ብዙ ሰዎችን እንደሚያሳስት

-ዲያብሎስ በሚርተኞች እያደረ ብዙዎችን እንደሚያሳስት

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማይጠብቁ ሰዎች ከዲያብሎስ ጋር ለዘለዓለም በገሃነም እንደሚኖሩ

ምዕራፍ ፪፡- ሰይጣን ማሳት ያልቻላቸው ሰዎች መንግሥተ ሰማያትን ወርሰው እንደሚኖሩ

-ዲያብሎስ በብዙ መልኩ ሰውን እንደሚያሳስት

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር ያመሰግነው ዘንድ ለዲያብሎስ አንድ ጎሊና ሰጥቶት እንደነበረና ዲያብሎስ ግን እንደሳተ መነገሩ

-እግዚአብሔር ለአዳም አሥር አሳቦች እንደሰጠው መገለጡ

-አዳምና ሔዋን በዲያብሎስ ምክር ከገነት እንደወጡ መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- ጌታ አዳምን እንደሚቤገሮው መነገሩ

-እግዚአብሔር አዳምን በመልኩና በምሳሌው እንደፈጠረው

-አዳም በንስሓ ወደ እግዘአብሔር እንደተመለሰ

ምዕራፍ ፭፡- የፈጠረንን ልዑል እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚገባ

-በእጅ ሥራ መመገብ እንጂ ቅሚያ ተገቢ እንዳልሆነ

-ከብዙ የኃጢአተኞች ገንዘብ በእውነት ያለ ጥቂት ገንዘብ እንደሚሻል

ምዕራፍ ፮፡- የምንሞትበትን ቀን ማሰብ እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎችን አጋንንት እንደሚፈሯቸው

-ኃጥኣን ዘመናቸው ሳያልፍ ንስሓ መግባት እንደሚገባቸው

-ያለ ልክ የጠገበች ሰውነት እግዚአብሔርን እንደማታስብ

-ያለ ልክ መብላትና መጠጣት ማመንዘርም እንደ እሪያ መሆን እንደሆነ

-በልክ የሚበላ ሰው በእግዚአብሔር መሠረት እንደ አድማስ የጸና እንደሚሆን

-እግዚአብሔርን የማይወዱ ሰዎች ቃሉን እንደማይጠብቁና ልቡናቸውም የቀና እንዳልሆነ

ምዕራፍ ፯፡- በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ፍርሃት እና ድንጋጤ እንደሌለባቸው

ምዕራፍ ፰፡- ኢዮብ በደረሰበት መከራ ልቡን እንዳላሳዘነ መገለጹ

-ወደእኛ ከሚላኩ ጠላቶች ብንታገሥ ብዑዓን እንደሆንን መነገሩ

ምዕራፍ ፱፡- ፍጥረታት ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆኑና እርሱም እንደሚመግባቸው መነገሩ

-ነፍሳችን ከሥጋችን ሳትለይ የፈጣሪያችንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንፈጽም

ምዕራፍ ፲፡- ስለትንሣኤ ሙታን መነገሩ

-ለሰው ጌጡ ንጽሕና፣ ጥበብና ዕውቀት፣ ያለ መቅናትና ያለ ምቀኝነትና መዋደድ እንደሆነ

-ክፉ ላደረገብህ ሰው ክፉ ነገር አለማድግ እና መታገሥ እንደሚገባ

መጽሐፈ ኢዮብ

ምዕራፍ ፩፡- ኢዮብ አውስጢድ በሚባል ሀገር ይኖር እንደነበር

-ኢዮብ ቅን፣ ንጹሕና ጻድቅ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ ከክፉ ሥራ ሁሉ የራቀ ነበር

-ኢዮብ ሰባት ወንዶች ልጆችና ሦስት ሴቶች ልጆች እንዲሁም ብዙ ሀብት እንደነበረው

-ኢዮብ ስለ ልጆቹ በቁጥራቸው የኃጢአት መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ያቀርብ እንደነበር

-ሰይጣን የኢዮብን ልጆች እንደገደላቸውና ንብረቱንም ሁሉ እንዳጠፋበት

ምዕራፍ ፪፡- ሰይጣን በኢዮብ ላይ ደዌን እንዳመጣበት

-የኢዮብ ሚስት ኢዮብን እግዚአብሔርን ስደበውና ሙት እንዳለችው

-ኢዮብ መከራ በደረሰበት ጊዜ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በከንፈሩ እንዳልበደለ

-የኢዮብ ወዳጆች ኢዮብን ሊጎበኙት እንደመጡ

ምዕራፍ ፫፡- ኢዮብ የተወለደባትን ቀን እንደረገመ

-ሞት ለሰው ዕረፍቱ እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡- ቴማናዊው ኤልፋዝ ኢዮብን በመከራ ሳለህ ነገር አታብዛ እንዳለው

-ቴማናዊው ኤልፋዝ ኢዮብን አንዳች እውነት አድርገህ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ባልደረሰብህም ነበር እንዳለው

ምዕራፍ ፭፡- እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-የአምላክን ተግሣጽ መናቅ እንደማይገባ

ምዕራፍ ፮፡- ኢዮብ እግዚአብሔር አልጎበኘኝም አልተመለከተኝም እንዳለ

-ኢዮብ ሦስቱን ወዳጆቹን አስተምሩኝ እኔም አዳምጣችኋለሁ የተሳሳትኩትም ካለ አስረዱኝ እንዳላቸው

ምዕራፍ ፯፡- የሰው ሕይወት በምድር ላይ እንደ ጥላ እንደሆነ

ምዕራፍ ፰፡- አውኬናዊው በልዳዶስ ኢዮብን ወደ እግዚአብሔር ገሥግሥ ሁሉንም ወደሚችለው አምላክ ጸልይ እንዳለው

-የዝንጉ ሰው ተስፋ እንደምትጠፋ

-እግዚአብሔር የዋሁን ሰው እንደማይጥለው

ምዕራፍ ፱፡- እግዚአብሔር ታላቅ፣ ጠቢብ፣ ኃይለኛ እንደሆነ

-የኃጥኣን ሞታቸው ክፉ እንደሆነ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፡- ኢዮብ እግዚአብሔርን እጆችህ ፈጠሩኝ ሠሩኝም እንዳለ

ምዕራፍ ፲፩፡- አሜናዊው ሶፋር ኢዮብን ንግግር አታብዛ፣ በሥራዬ ንጹሕ ነኝ በፊቱም ጻድቅ ነኝ አትበል እንዳለው

ምዕራፍ ፲፪፡- የሕያዋን ሁሉ ነፍስ በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ መነገሩ

-በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኃይል ምክርና ማስተዋል እንዳለ

ምዕራፍ ፲፫፡- ኢዮብ ሦስቱን ወዳጆቹን ጥበብ ከእናንተ ጠፍታለች፣ ሽንገላን ትናገራላችሁ እንዳላቸው

ምዕራፍ ፲፬፡- የሰው ልጅ በዚህ ምድር የሚኖረው የሕይወት ዘመኑ ጥቂት እንደሆነ መገለጡ

-ሰው ከሞተ በኋላ እንደሚተላ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፭፡- ቴማናዊው ኤልፋዝ ኢዮብን ጥቂት ብትበድል ተገረፍክ እንዳለው

-የኃጥእ ሰው ዕድሜው በጭንቅ እንደሚያልፍ

ምዕራፍ ፲፮፡- ኢዮብ እኔ ብናገር ቁስሌ አይድንም ዝም ብልም ሕመሜ ይብስብኛል እንዳለ

-ኢዮብ ጸሎቱ ወደ እግዚአብሔር ትድረስ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፯፡- ኢዮብ ደስታዬን ተማምኛት ነበር ነገር ግን ጠፋችብኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፰፡- አውሔናዊው በልዳዶስ ኢዮብን መከራው ይገባሃል እንዳለው

ምዕራፍ ፲፱፡- ኢዮብ ዘመዶች አልተረዱኝም የሚያውቁኝም ረሱኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፳፡- አሜናዊው ሶፋር ኢዮብን በዕውቀትም ከእኔ አትሻልም እንዳለው

ምዕራፍ ፳፩፡- የኃጥኣን መብራት እንደምትጠፋና መቅሠፍትም እንደምትመጣባቸው

ምዕራፍ ፳፪፡- ማስተዋልንና ዕውቀትን የሚያስተምር እግዚአብሔር እንደሆነ

ምዕራፍ ፳፫፡- ኢዮብ በተገሠጽኩ ጊዜ እግዚአብሔርን አሰብኩት እንዳለ

ምዕራፍ ፳፬፡- የአመንዝራ ዓይን ድንግዝግዝታን እንደሚጠብቅ

ምዕራፍ ፳፭፡- ሰው ፈራሽ በስባሽ እንደሆነ መገለጹ

ምዕራፍ ፳፮፡- ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት መናገሩ

ምዕራፍ ፳፯፡- ኢዮብ አንደበቱ ዐመፅን አይናገርም እንዳለ

-በእግዚአብሔር የማያምን እንደማይድን

ምዕራፍ ፳፰፡- ብር የሚወጣበት ቦታ እንዳለ መነገሩ

-ብረት ከመሬት ውስጥ እንደሚወጣ መነገሩ

ምዕራፍ ፳፱፡- ኢዮብ ያደረገውን መልካም ሥራ መዘርዘሩ

ምዕራፍ ፴፡- ኢዮብ መከራውን እያሰበ መናገሩ

ምዕራፍ ፴፩፡- ኢዮብ እግዚአብሔር ቅንነቴን ያውቃል ማለቱ

ምዕራፍ ፴፪፡- ኢዮብ በሦስቱ ወዳጆቹ ፊት ራሱን ጻድቅ አድርጎ ነበርና ሦስቱ ወዳጆቹ ከመናገር ዝም እንዳሉ

-ከአውስጢድ ሀገር የቡዛዊው የባርክኤል ልጅ ኤሊዩስ ኢዮብንም ሦስቱን የኢዮብ ወዳጆችንም እንደተቆጣ

ምዕራፍ ፴፫፡- ኤሊዩስ የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ያስተምረኛል እንዳለ

ምዕራፍ ፴፬፡- ጆሮ ቃልን ጉረሮ ምግብን እንደሚለይ መገለጹ

-በመከከላችን ምን እንደሚሻል እንወቅ መባሉ

-እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያይ መነገሩ

ምዕራፍ ፴፭፡- ኢዮብ ራሱን በማጽደቁ ኤልዩስ እንደተቃወመው

ምዕራፍ ፴፮፡- በጥበብ ብርቱና ኃያል የሆነ እግዚአብሔር እንደሆነ

-እግዚአብሔር ፍርድን ለጻድቃን እንደማያዘገይ

-የእግዚአብሔር የዘመኑ ቁጥር እንደማይመረመር

ምዕራፍ ፴፯፡- እግዚአብሔር ለፍጥረታት በየጊዜው ምግባቸውን እንደሚያዘጋጅ

ምዕራፍ ፴፰፡- እግዚአብሔር በደመናና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ኢዮብን እንዳናገረው

ምዕራፍ ፴፱፡- እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን እየጠቀሰ ኢዮብን እንደገሠጸው

ምዕራፍ ፵፡- ኢዮብ ከአንተ ጋር መናገር አይቻለኝም ብሎ ዝም ብሎ እግዚአብሔርን ይሰማ እንደነበር

ምዕራፍ ፵፩፡- እግዚአብሔርን ተከራክሮ በሕይወት የሚኖር እንደሌለ

ምዕራፍ ፵፪፡- ኢዮብ እኔ አፈርና አመድ እንደሆንኩ አውቃለሁ ማለቱ

-እግዚአብሔር ሦስቱን የኢዮብ ወዳጆች ሰባት ወይፈኖችንና ሰባት በጎችን ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱ እርሱ የሚቃጠል መሥዋዕትን ያሳርግላችሁ ኢዮብም ስለ እናንተ ይጸልይ እኔም ፊቱን እቀበላለሁ ስለ እርሱ ባይሆን ባጠፋኋችሁ ነበር እንዳላቸው

-ኢዮብ እንደዳነና እግዚአብሔርም ከፊተኛው ይልቅ የኋላውን እንደባረከለት

መዝሙረ ዳዊት

መዝሙር ፩፡- በዝንጉዎች መንገድ ያልሄደ፣ በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመና በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ሕግ ብቻ ፈቃዱ የሆነና ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ ሰው በውሃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለችና ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠሏም እንደማይረግፍ ዛፍ እንደሆነ መገለጹ

-ኃጥኣን ነፋስ ከገጸ ምድር ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው መባሉ

መዝሙር ፪፡- በእግዚአብሔርና በመሢሁ ላይ አለቆችና የምድር ነገሥታት እንደተነሡ

-ለእግዚአብሔር በፍርሀት መገዛት እንደሚገባ

-በእግዚአብሔር የታመነ ብፁዕ እንደሆነ

መዝሙር ፫፡- ማዳን የእግዚአብሔር እንደሆነ መገለጡ

መዝሙር ፬፡- እግዚአብሔርን ስንጠራው ጸሎታችንን እንደሚሰማን

-ተቆጡ ነገር ግን አትበድሉ እንደተባለ

-በእግዚአብሔር መታመንና የጽድቅን መሥዋዕት መሠዋት እንደሚገባ

መዝሙር ፭፡- እግዚአብሔር ሐሰትን የሚናገሩ ሰዎችን ሁሉ እንደሚጥላቸው

-እግዚአብሔር ደም አፍሳሹንና ሸንጋዩን ሰው እንደሚጸየፍ

-በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሰዎች ለዘለዓለሙ ደስ እንደሚሰኙ

መዝሙር ፮፡- እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን መለመን እንደሚገባ

መዝሙር ፯፡- እግዚአብሔር በእውነት እንደሚረዳና ልበ ቅኖችን እንደሚያድናቸው

-እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ እንደሆነና ኃይለኛም ታጋሽም እንደሆነ

-ለልዑል እግዚአብሔር ስም መዘመር እንደሚገባ

መዝሙር ፰፡- እግዚአብሔር ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን እንዳዘጋጀ

መዝሙር ፱፡- ዳዊት አቤቱ በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ ተአምራትህንም እናገራለሁ፣ በአንተ ደስ ይለኛል ሐሴትንም አደርጋለሁ እንዳለ

-እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ እንደሚዳኝና ለዘለዓለም ኗሪ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ለድኾች መጠጊያ እንደሚሆናቸው

-እግዚአብሔርን የሚወዱ ሁሉ በእርሱ እንደሚታመኑ እና እርሱንም የሚሹትን እንደማይተዋቸው፣ የድኾችን ጩኸት እንደማይረሳ መገለጡ

መዝሙር ፲፫:- እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱ ነው መባሉና ዙፋኑ በሰማይ ነው መባሉ

-የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወደ ድኻ እንደሚመለከቱ

-እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነና ጽድቅንም እንደሚወድ መገለጹ

መዝሙር ፲፩:- ደግ ሰው እንዳለቀ፣ ከሰው ልጆች መተማመን እንደጎደለ መገለጹ

-ሰዎች እርስ በእርሳቸው በሸንገላ ነገር ከንቱ ነገርን እንደሚናገሩ

-እግዚአብሔር የሸንገላ ከንፈሮችን እንደሚያጠፋቸው

-የእግዚአብሔር ቃል ንጹሕ ነው መባሉ

መዝሙር ፲፪:- የረዳንን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

መዝሙር ፲፫:- ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም እንደሚል

-እግዚአብሔር ለድኾች ተስፋቸው እንደሆነ

መዝሙር ፲፬:- በቅንነት የሚሄድ፣ ጽድቅንም የሚያደርግ፣ በልቡም እውነትን የሚናር፣ በአንደበቱ የማይሸነግል፣ በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ ሰው በተቀደሰው ተራራ እንደሚኖር

መዝሙር ፲፭:- የእግዚአብሔር ፈቃዱ በምድር ባሉት ቅዱሳን እንደተገለጠ

መዝሙር ፲፮:- ዳዊት እገዚአብሔርን ክብርህን በማየት እጠግባለሁ እንዳለው

መዝሙር ፲፯:- እግዚአብሔር ኃይላችን፣ አምባችን፣ መድኃኒታችን፣ ረዳታችን እንደሆነ

-ዳዊት እግዚአብሔርን በጠራሁት ጊዜ ከጠላቶቼ እድናለሁ እንዳለ

-ሰው ከጻድቅ ሰው ጋር ጻድቅ፣ ከቅን ሰው ጋር ቅን፣ ከጠማማ ጋር ጠማማ እንደሚሆን

-የእግዚአብሔር መንገዱ ንጹሕ እንደሆነ መገለጡ

-እግዚአብሔር ሕያውና ቡሩክ እንደሆነ

መዝሙር ፲፱:- ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር እንደሚናገሩ

-የእግዚአብሔር ሕግ ንጹሕ እንደሆነና ነፍስንም እንደሚመልስ

-የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ እንደሆነና ዐይኖችንም እንደሚያበራ

-የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት እንደሆነ

መዝሙር ፲፱፡- በእግዚአብሔር በአምላካችን ስም ከፍ ከፍ እንደምንል

መዝሙር ፳፡- እግዚአብሔር በኃይሉ ከፍ ከፍ ያለ እንደሆነ

መዝሙር ፳፩፡- እግዚአብሔር በቅዱሳን እንደሚኖር

-እግዚአብሔር ያመኑበትን እንደሚያድን

-እግዚአብሔር የምትፈሩት አመስግኑት እንደተባለ

-እግዚአብሔርን የሚሹት እንደሚያመሰግኑት

መዝሙር ፳፪፡- እግዚአብሔር በጽድቅ መንገድ እንደሚመራ

-እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ካለ ምንም እንደማያስፈራን

መዝሙር ፳፫፡- ምድር በመላዋና ዓለምም በእርሷ የሚኖረውም ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ

-እግዚአብሔር የክብር ንጉሥ፣ የኃያላን አምላክ እንደሆነ

መዝሙር ፳፬፡- የእግዚአብሔር ምሕረት ለዘለዓለም እንደሆነ

-እግዚአብሔር ቸር፣ ጻድቅም እንደሆነና ለየዋሃን ፍርድን እንደሚያስተምራቸው

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነፍሱ በመልካም እንደምታድር

መዝሙር ፳፭፡- ዳዊት እንዳልደክም በእግዚአብሔር አመንኩ ማለቱ

መዝሙር ፳፮፡- ዳዊት እግዚአብሔር የሕይወቱ መታመኛዋ ነው እንዳለ

-እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ እንደሚገባ

መዝሙር ፳፯፡- እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይላቸው እንደሆነ

መዝሙር ፳፰፡- የእግዚአብሔር ቃል ኃያል እንደሆነ

መዝሙር ፳፱፡- ለእግዚአብሔር መዘመር እንደሚገባ

መዝሙር ፴፡- በትዕቢትና በመናቅ በጻድቅ ላይ ዐመፃን የሚናገሩ የሸንገላ ከንፈሮች ወዮታ እንዳለባቸው

-እግዚአብሔር ጽድቅን እንደሚሻ

-በእግዚአብሔር የምናምን ሰዎች ሁሉ ልባችንን ማዕናትና መታገሥ እንደሚገባን

መዝሙር ፴፩፡- በልባቸው ሽንገላ የሌለባቸው ሰዎች ብፁዓን እንደሆኑ

-የኃጥኣን መቅሠፍታቸው ብዙ እንደሆነ

-በእግዚአብሔር የሚታመኑትን ይቅርታ እንደሚከባቸው

መዝሙር ፴፪፡- ለቅኖች ክብር እንደሚገባቸው መገለጹ

-እግዚአብሔርን በመሰንቆና በበገና ማመስገን እንደሚገባ

-የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ

-እግዚአብሔር ጽድቅንና ምጽዋትን እንደሚወድ

-እግዚአብሔር አምላክ የሚሆንለት ሕዝብ ብፁዕ እንደሆነ

-ንጉሥ በሠራዊት ብዛት እንደማይድን

መዝሙር ፴፫፡- ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ያበራላችኋል እንደተባለ

-የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ እንደሚሰፍርና እንደሚያድናቸው

-በእግዚአብሔር የሚታመን ብፁዕ እንደሆነ

-አንደበትን ከክፉ መከልከል እንደሚገባ

-ሰላምን መሻትና መከተል እንደሚገባ

-የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃኑ ጆሮዎቹም ወደ ልመናቸው ናቸው መባሉ

መዝሙር ፴፬፡- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ታላቅ እንደሆነ

መዝሙር ፴፮፡- ኃጢአተኛ ራሱን የሚያስትበትን ነገር እንደሚናገር

መዝሙር ፴፯፡- በክፉዎች ላይ ዐመፃንም በሚያደርጉ ላይ መቅናት እንደማይገባ

-በእግዚአብሔር መታመንና መልካምንም ማድረግ እንደሚገባ

-ለእግዚአብሔር መገዛትና እርሱን ማገልገል እንደሚገባ

-መዓትን መተው ቁጣን መጣል እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ጻድቃንን እንደሚደግፋቸውና ርስታቸውም ዘለዓለማዊ እንደሆነ

-ከክፉ መሸሽ መልካምንም ማድረግ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ለንጹሓን እንደሚበቀልላቸውና የኃጥኣንን ዘር ግን እንደሚያጠፋ

-የጻድቅ አፍ ጥበብን ይማራል አንደበቱም ጽድቅን ይናገራል መባሉ

-ቅንነትን መጠበቅ ጽድቅን ማየት እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ጻድቃንን እንደሚረዳና እንደሚያድናቸው

መዝሙር ፴፯፡- ዳዊት አቤቱ በመዓትህ አትቅሠፈኝ እንዳለ

መዝሙር ፴፰፡- ዳዊት በአንደበቱ እንዳልስት አፌን እጠብቃለሁ እንዳለ

-የሰው ልጅ ከንቱ እንደሆነ እና በጥላ እንደሚመሰል

-ተስፋችን እግዚአብሔር እንደሆነ

መዝሙር ፴፱፡- መታመኛው የእግዚአብሔር ስም የሆነ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

መዝሙር ፵፡- ለድኻና ለምስኪን የሚያስብ ብፁዕ ነው እንደተባለ

መዝሙር ፵፩፡- እግዚአብሔር ይቅር ባይ እንደሆነ

መዝሙር ፵፪፡- ዳዊት ከዐመፀኛና ከሸንጋይ ሰው አድነኝ እንዳለ

መዝሙር ፵፫፡- ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር እንደምንከብር

መዝሙር ፵፬፡- የአምላክ ዙፋን ለዘለዓለም እንደሆነና በትረ መንግሥቱም በትረ ጽድቅ እንደሆነ

መዝሙር ፵፮፡- አምላካችን መጠጊያችን ኃይላችን ረዳታችን እንደሆነ

መዝሙር ፵፯፡- ለእግዚአብሔር በደስታ ቃል እልል ማለትና በእጅ ማጨብጨብ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ እንደሆነ

መዝሙር ፵፰፡- እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ

መዝሙር ፵፰፡- ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ እንዳላወቀና እንስሳትን እንደመሰለ

መዝሙር ፵፱፡- እግዚአብሔር በግልጥ እንደሚመጣና ዝም እንደማይል

-ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕትን መሠዋት እንደሚገባ

መዝሙር ፶፡- ዳዊት ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ እንዳለ

-የእግዚአብሔር መሥዋዕት የዋህ መንፈስ እንደሆነ

መዝሙር ፶፩፡- ሰው በክፋቱ መኩራትና ሁል ጊዜ መበደል እንደማይገባው

መዝሙር ፶፪፡- ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም እንደሚል

መዝሙር ፶፫፡- መልካም ነውና እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

መዝሙር ፶፬፡- እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠርም እንደነበረ

መዝሙር ፶፭፡- ዳዊት በእግዚአብሔር ቃሌን አከብራለሁ የተናገርኩትም በእግዚአብሔር ዘንድ ይከብራል እንዳለ

መዝሙር ፶፮፡- ወደሚረዳን ወደ እግዚአብሔር መጮህ እንደሚገባ

መዝሙር ፶፯፡- ኃጥኣን ከማጎፀን ጀምረው እንደተለዩ

መዝሙር ፶፰፡- ዳዊት በምሕረትህም በማለዳ ደስ ይለኛል እንዳለ

መዝሙር ፶፱፡- እግዚአብሔር ለሚፈሩት ምልክትን እንደሰጣቸው

መዝሙር ፷፡- እግዚአብሔር ለሚፈሩት ርስትን እንደሰጣቸው

መዝሙር ፷፩፡- እግዚአብሔር አምላካችን ረዳታችንም መድኃኒታችንም እንደሆነ

-ዳዊት ክብሬ በእግዚአብሔር ነው እንዳለ

-ይቅርታ የእግዚአብሔር እንደሆነ

-እግዚአብሔር ለሁሉ እንደ ሥራው እንደሚከፍለው

መዝሙር ፷፪፡- ንጉሥ በእግዚአብሔር ደስ እንደሚለው

መዝሙር ፷፫፡- ጻድቅ በእግዚአብሔር ደስ እንደሚለው ልባቸውም የቀና እንደሚከብሩ

መዝሙር ፷፬፡- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ እንደሆነ

መዝሙር ፷፭፡- እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

-ለእግዚአብሔር ነውር የሌለበትን ንጹሕ መሥዋዕትን መሠዋት እንደሚገባ

መዝሙር ፷፮፡- እግዚአብሔር በቅን እንደሚፈርድ

መዝሙር ፷፯፡- የእግዚአብሔር ተራራ የለመለመ ተራራ ነው መባሉና እግዚአብሔር ያድርበት ዘንድ የወደደው ተራራ ይህ ነው መባሉ

-እግዚአብሔር አምላክ ቡሩክ እንደሆነና የማዳን አምላክ እንደሆነ

-ኢትዮጵያ እጆቿን እንደምትዘረጋ መነገሩ

መዝሙር ፷፰፡- ሰውነትን በጾም ማድከም እንደሚገባ

-የእግዚአብሔር ይቅርታው በጊዜው እንደሚሆን

መዝሙር ፶፱፡- ዳዊት እኔን ለማዳን ተመልከት ብሎ እንደጸለየ

መዝሙር ፷፡- እግዚአብሔርን የታመነ እንደማያፍር

-የእግዚአብሔርን ጽድቅና ማዳኑን መናገር እንደሚገባ

መዝሙር ፷፩፡- ልዑል እግዚአብሔር ብቻውን ተአምራትን እንደሚያደርግ

መዝሙር ፷፪፡- እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ

-እግዚአብሔርን መከተል እንደሚሻል

መዝሙር ፷፫፡- እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ እንደሆነና በምድርም መካከል መድኃኒትን እንዳደረገ

-በጋንና ክረምትን የሚያፈራርቅ እግዚአብሔር እንደሆነ

መዝሙር ፷፬፡- በእግዚአብሔር ላይ ዐመፃን መናገር እንደማይገባ

መዝሙር ፷፭፡- እግዚአብሔር ግሩም እንደሆነ

መዝሙር ፷፮፡- ዳዊት እግዚአብሔርን አሰብኩት ደስ አለኝም እንዳለ

-የእግዚአብሔር ፍለጋው እንደማይታወቅ

መዝሙር ፷፯፡- የእግዚአብሔርን ምስጋና፣ ኃይሉንና ያደረገውን ተአምራት መናገር እንደሚገባ

-እግዚአብሔር መሓሪ እንደሆነ

መዝሙር ፷፰፡- ዳዊት ስለስምህ ክብር አቤቱ ታደገን፣ ስለስምህም ኃጢአታችንን አስተሥርይልን እንዳለ

መዝሙር ፷፱፡- እግዚአብሔር ፊቱን ካበራልን እንደምንድን

መዝሙር ፸፡- ከእግዚአብሔር ውጭ ሌላ አምላክ ማምለክ እንደማይገባ

መዝሙር ፸፭፡- እግዚአብሔር በአማልክት መካከል እንደቆመና በአማልክትም መካከል እንደሚፈርድ

መዝሙር ፸፪፡- ዳዊት እግዚአብሔርን አንተ ብቻ ልዑል እንደሆንክ አሕዛብ ይረዱ ዘንድ በመቅሠፍት ምታቸው እንዳለ

መዝሙር ፸፫፡- በእግዚአብሔር ቤት የሚኖሩ ሰዎች ብፁዓን እንደሆኑ

-የአማልክት አምላክ በጽዮን እንደሚታይ

-እግዚአብሔር ምጽዋትንና እውነትን እንደሚወድ

መዝሙር ፹፬፡- እግዚአብሔር ምሕረቱን እንደሚሰጥ

መዝሙር ፹፭፡- እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ እንደሆነ

-እግዚአብሔር መዓቱ የራቀ ምሕረቱ የበዛ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ

መዝሙር ፹፮፡- እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች እንደሚወድ

-እግዚአብሔር ለሕዝቡ በመጽሐፍ እንደሚነግራቸው

መዝሙር ፹፯፡- ዳዊት የድኅነቱ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ ጸሎቱን ስማ ብሎ እንደጸለየ

መዝሙር ፹፰፡- እግዚአብሔር ከመረጣቸው ጋር ቃል ኪዳንን እንዳደረገ

-እግዚአብሔር በቅዱሳን ምክር ክቡር እንደሆነ

-ሰማያትም ምድርም የእግዚአብሔር እንደሆነች

-የእግዚአብሔር የዙፋኑ መሠረት ፍትሕና ርትዕ እንደሆኑ

-እልልታን የሚያውቅ ሕዝብ ብፁዕ እንደሆነ

መዝሙር ፹፱፡- እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት እንደነበረ

-የሰው ልጅ እድሜ ሰባ ቢበዛም ሰማንያ እንደሆነ

መዝሙር ፺፡- እግዚአብሔር ከሚያስደነግጥ ነገር ሁሉ እንደሚያድን

መዝሙር ፺፩፡- በእግዚአብሔር መታመን እንደሚሻል

-የእግዚአብሔር ሥራው እጅግ ትልቅ እንደሆነ

-ጻድቅ እንደ ዘንባባ እንደሚያፈራና እንደ ሊባኖስ ዝግባ እንደሚበዛ መገለጹ

መዝሙር ፺፪፡- የእግዚአብሔር ዙፋን ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ እንደሆነ

መዝሙር ፺፫፡- እግዚአብሔር በግልጥ ተበቃይ እንደሆነና ለንጹሕ ደም እንደሚፈርድ

መዝሙር ፺፬፡- ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን እንደተባለ

-አምላካችን እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ

መዝሙር ፺፭፡- ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን ማቅረብ እንደሚገባ

-ለእግዚአብሔር በቅድስናው ስፍራ መስገድ እንደሚገባ

መዝሙር ፺፮፡- በእግዚአብሔር ምድር ሐሴትን እንደምታደርግ ብዙ ደሴቶችም ደስ እንደሚላቸው

-እግዚአብሔር የጻድቃኑን ነፍሶች እንደሚጠብቅና ከኃጥኣንም እጅ እንደሚጠብቃቸው

-ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ እንደሚላቸውና ለቅድስናውም መታሰቢያ እንደሚያመሰግኑ

መዝሙር ፺፯፡- እግዚአብሔር ማዳኑን እንዳሳየ

መዝሙር ፺፰፡- እግዚአብሔር ግሩምና ቅዱስ እንደሆነ

-ክቡር ንጉሥ ፍርድን እንደሚወድ

መዝሙር ፺፱፡- በደስታ ለእግዚአብሔር መገዛት እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ቸር ምሕረቱም ለዘለዓለም እንደሆነ

መዝሙር ፻፡- ትዕቢትን የሚያደርግ በእግዚአብሔር ቤት እንደማይኖር

-በንጹሕ መንገድ የሚሄድ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል

መዝሙር ፻፩፡- እግዚአብሔር ለዘለዓለም እንደሚኖር መታሰቢያውም ለልጅ ልጅ እንደሆነ

-እግዚአብሔር እንደማይለወጥ

መዝሙር ፻፪፡- እግዚአብሔር ይቅርታ አድራጊ እንደሆነና ለተበደሉ ሁሉ እንደሚፈርድ

-እግዚአብሔር ለሚፈሩት እንደሚራራ

-ሰው በዘመኑ እንደ ሣር፣ እንደ ዱር አበባ እንደሆነ

መዝሙር ፻፫፡- ወይን የሰውን ልብ ደስ እንደሚያሰኝ

-እግዚአብሔር በሥራው ደስ የሚለው እንደሆነ

መዝሙር ፻፬፡- እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ እንደሚለው

-የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኑ ዘለዓለማዊ እንደሆነ

-እግዚአብሔር በነቢያቱ ላይ ክፉ አታድርጉ እንዳለ

መዝሙር ፻፭፡- ጽድቅን ሁልጊዜ የሚያደርጉ ብፁዓን እንደሆኑ

መዝሙር ፻፮፡- በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የጮኹትን ከመከራቸው እንዳዳናቸው

-የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሰው ልጆችም ያደረገውን ድንቁን ነገር መናገር እንደሚገባ

መዝሙር ፻፯፡- በሰው መታመን ከንቱ እንደሆነና በእግዚአብሔር ኃይልን እንደምናደርግ

መዝሙር ፻፰፡- እግዚአብሔርን በብዙዎች መካከል ማመስገንና ማክበር እንደሚገባ

መዝሙር ፻፱፡- አብ ወልድን ቅድመ ዓለም እንደወለደው

መዝሙር ፻፲፡- የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ እንደሆነች

-የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ

መዝሙር ፻፲፩፡- እግዚአብሔርን የሚፈራ ትእዛዙንም እጅግ የሚወድ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ጻድቅ፣ ርኅሩኅ፣ ይቅር ባይና ቸር እንደሆነ

-የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም እንደሚኖር

መዝሙር ፻፲፪፡- የእግዚአብሔር ክብሩ ከሰማያትም በላይ እንደሆነ

መዝሙር ፻፲፫፡- የአሕዛብ ጣዖቶች የሰው የእጅ ሥራ እንደሆኑ

-እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ እንደሚያደርግ

መዝሙር ፻፲፬፡- እግዚአብሔር መሓሪና ጻድቅ እንዲሁም ይቅር ባይ እንደሆነ

መዝሙር ፻፲፭፡- የጻድቅ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ እንደሆነ

መዝሙር ፻፲፮፡- የእግዚአብሔር እውነት ለዘለዓለም እንደምትኖር

መዝሙር ፻፲፯፡- በሰው ከመታመን በእግዚአብሔር መታመን እንደሚበልጥ

-በአለቆች ተስፋ ከማድረግ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ እንደሚሻል

-በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ እንደሆነ

መዝሙር ፻፲፰፡- በመንገዳቸው ንጹሓን የሆኑና በእግዚአብሔር ሕግ የሚሄዱ ብፁዓን እንደሆኑ

-ጎልማሳ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቅ መንገዱን እንደሚያቀና

-ከእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚርቁ ርጉማን እንደሆኑ

-የእግዚአብሔር ትእዛዛት ሁሉ እውነት እንደሆኑ

-ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ እንዳለው

መዝሙር ፻፲፱፡- ወደ እግዚአብሔር ስንጮኽ እንደሚሰማን

መዝሙር ፻፳፡- ረድኤት ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር እንደሆነ

መዝሙር ፻፳፩፡- ወደ እግዚአብሔር ቤት መሄድ ደስ እንደሚያሰኝ

መዝሙር ፻፳፪፡- ዳዊት ዐይኖቹን ወደ እግዚአብሔር አንሥቶ እንደጸለየ

መዝሙር ፻፳፫፡- ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር ስም እንደሆነ

መዝሙር ፻፳፬፡- በኢየሩሳሌም የሚኖር (እግዚአብሔር፣ ጻድቅ) ለዘለዓለም እንደማይታወክ

መዝሙር ፻፳፭፡- በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ እንደሚሰበስቡ

መዝሙር ፻፳፮፡- እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ቤትን የሚሠሩ በከንቱ እንደሚደክሙ

-እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ የሚጠብቁ በከንቱ እንደሚተጉ

መዝሙር ፻፳፯፡- እግዚአብሔርን የሚፈሩት ሁሉና በመንገዶቹም የሚሄዱ ብፁዓን እንደሆኑ

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንደሚባረክ

መዝሙር ፻፳፰፡- እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነ

መዝሙር ፻፳፱፡- ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታና ብዙ ማዳን እንዳለ

መዝሙር ፻፴፡- መታበይ እንደማይገባና ራስን ማዋረድ እንደሚገባ

መዝሙር ፻፴፩፡- የጌታችን እግሮች በሚቆሙበት ቦታ መስገድ እንደሚገባ

-ጻድቃን ደስ እንደሚላቸው

መዝሙር ፻፴፪፡- ወንድሞች በጎብረት ቢቀመጡ መልካም እንደሆነ

መዝሙር ፻፴፫፡- እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

መዝሙር ፻፴፬፡- እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ፣ ከምድር ዳር ደመናትን እንደሚያወጣ

-እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ እንደሚያደርግ

መዝሙር ፻፴፭፡- እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

መዝሙር ፻፴፮፡- የእግዚአብሔርን ዝማሬ በባዕድ ምድር መዘመር እንደማይገባ

መዝሙር ፻፴፯፡- የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ እንደሆነ

መዝሙር ፻፴፰፡- እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ያለ እንደሆነ

መዝሙር ፻፴፱፡- ዐመፀኛ ሰውን ክፋት ለጥፋት እንደምታድነው

መዝሙር ፻፵፡- ዳዊት እግዚአብሔርን በጽድቅ ገሥጸኝ በምሕረትም ዝለፈኝ እንዳለ

መዝሙር ፻፵፩፡- ዳዊት እግዚአብሔርን በርትተውብኛልና ከከበቡኝ አድነኝ እንዳለ

መዝሙር ፻፵፪፡- ዳዊት አቤቱ አምላኬ ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ እንዳለ

መዝሙር ፻፵፫፡- የሰው ዘመኑ እንደ ጥላ እንደሚያልፍ መነገሩ

-እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ ብፁዕ እንደሆነ

መዝሙር ፻፵፬፡- እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነና ምስጋናውም ብዙ እንደሆነ ለታላቅነቱም ዳርቻ እንደሌለው

-እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር እንደሆነ

-የእግዚአብሔር መንግሥት የዘለዓለም መንግሥት እንደሆነች

-እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉ የታመነ እንደሆነ

-እግዚአብሔር የወደቁትን እንደሚያነሣና የሰው ሁሉ ዓይን እርሱን ተስፋ እንደሚያደርግ

-እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ እንደሆነ

መዝሙር ፻፵፭፡- ማዳን በማይችሉ በአለቆችና በሰው ልጆች መታመን እንደማይገባ

-መታመኛው በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ጻድቃንን እንደሚወድና የኃጥኣንን መንገድ ደግሞ እንደሚያጠፋ

መዝሙር ፻፵፮፡- የእግዚአብሔር ኃይሉ ታላቅ እንደሆነና ለጥበቡም ቁጥር እንደሌለው

-እግዚአብሔር የዋሃንን እንደሚያነሣቸው

-እግዚአብሔር በሚፈሩትና በምሕረቱም በሚታመኑ ደስ እንደሚለው

መዝሙር ፻፵፯፡- ኢየሩሳሌም እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባት

መዝሙር ፻፵፰፡- እግዚአብሔርን መላእክቱና ሌሎችም ፍጥረታቱ እንደሚያመሰግኑት

-ፍጥረታት እግዚአብሔር ባላቸውና በወሰነላቸው ጸንተው እንደሚኖሩ

መዝሙር ፻፵፱፡- ጻድቃን እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ

መዝሙር ፻፶፡- እግዚአብሔርን በተቀደሱ ቦታዎች ማመስገን እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን በመለከት ድምፅ፣ በበገናና በመሰንቆ፣ በጸናጽልና በእልልታ ማመስገን እንደሚገባ

ከቁጥር የወጣ፡- ዳዊት በገና ይደረድር፣ መሰንቆ ይመታ እንደነበር

-ዳዊት ከወንዝ ሦስት ወንጭፍ አንሥቶ የጎልያድን ግንባር በወንጭፍ እንደመታው

መጽሐፈ ምሳሌ

ምዕራፍ ፩፡- አስተዋይ ሰው ምክርን ገንዘብ እንደሚያደርግ

-የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ

-እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ እንደሆነ

-ሰነፎች ጥበብንና ተግሣጽን እንደሚንቁ

-የአባትን ምክር መስማት፣ የእናትንም ትእዛዝ ቸል አለማለት እንደሚገባ

-ከክፉ ሰዎች ጋር መተባበር እንደማይገባ

-የኃጢአተኞች ሰዎች አወዳደቃቸው ክፉ እንደሆነ

-ሰነፎች ስድብን የሚወዱ እንደሆኑ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር ጥበብን እንደሚሰጥ

-መልካም ምክር እንደምትጠብቅ

-ክፉን በመሥራት ደስ ለሚላቸው ሰዎች፣ ክፋትንም በመመለስ ሐሴትን ለሚያደርጉ ወዮታ እንዳለባቸው

-የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ከብዙ ክፉ ነገሮች እንደሚያድን

ምዕራፍ ፫፡- የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መጠበቅ እንደሚገባ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እድሜንና ሰላምን እንደሚጨምር

-በእግዚአብሔርና በሰው ፊት መልካምን ማሰብ እንደሚገባ

-በፍጹም ልብ እግዚአብሔርን አምነን መኖር እንደሚገባን

-በራስ ጥበብ መደገፍ እንደማይገባ

-እግዚአብሔርን መፍራትና ከክፉ ሁሉ መራቅ እንደሚገባ

-ቀዳምያትን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ

-አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚገሥጽ እግዚአብሔር የሚወደውን እንደሚገሥጽ

-ለተቸገረ ሰው በጎ ነገር ማድረግን ቸል ማለት እንደማይገባ

-ኃጢአተኛ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወማቸውና ለትሑታን ግን ክብርን እንደሚሰጥ

-ጠቢባን ክብርን እንደሚወርሱ

ምዕራፍ ፬፡- የአባትን ተግሣጽ መስማት እንደሚገባ

-የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ መልካም ስጦታን እንደሚያስገኝ

-ጥበብን ማክበር እንደሚገባ

-በክፉዎች መንገድ መሄድ እንደማይገባ

-የኃጥኣን መንገድ ጨለማ፣ የጻድቃን መንገድ ደግሞ ብርሃን እንደሆነ

-ልብን አጥብቆ መጠበቅ የሕይወት መገኛ እንደሆነ

ምዕራፍ ፭፡- ወደ አመንዝራ ሴት መመልከት እንደማይገባ

ምዕራፍ ፮፡- ሰነፍ መሆን እንደማይገባ

-ሰው እንደ ንብ ትጉህ መሆን እንደሚገባው

-ዐመፃኛና ሰነፍ የሆነ ሰው ቀና ያልሆኑ መንገዶችን እንደሚሄድ

-እግዚአብሔር ትዕቢትን፣ ሐሰትን፣ ግድያን፣ ክፉ ሐሳብን እንደሚጠላ

ምዕራፍ ፯፡- ከእርሱ በቀር የሚገድልም የሚያድንም ስለሌለ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላውን መፍራት እንደማይገባ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ በሕይወት እንደሚያኖር

-አመንዝራ ሴት በብዙ መንገድ እንደምትሸነግል መገለጹ

ምዕራፍ ፰፡- ጥበብን ማስተዋል እንደሚገባና ዕውቀትን ገንዘብ ማድረግ እንደሚገባ

-ዋጋው ብዙ ከሆነ ዕንቁ ጥበብ እንደምትበልጥ

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ዐመፃን እንደሚጠላ

-ነገሥታት በእግዚአብሔር እንደሚነግሡ መነገሩ

-ከወርቅና ከከበረ ዕንቁ ይልቅ እግዚአብሔርን መምረጥ እንደሚሻል

-የእግዚአብሔር መንገዶች የሕይወት መንገዶች እንደሆኑ

ምዕራፍ ፱፡- ለጠቢብ ሰው ትምህርትን መስጠት እንደሚገባ

-ሕግን ማወቅ ለልብ ደግ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፡- ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ እንደሚያሰኝ

-ሰነፍ ልጅ እናቱን እንደሚያሳዝን

-የተማረ ልጅ ብልህ እንደሚሆን

-የእግዚአብሔር በረከት በጻድቃን ራስ ላይ እንደሆነ

-የጻድቃን መታሰቢያ ከምስጋና ጋር እንደሆነ

-በከንፈሩ የማይታገሥ በመሰናክል እንደሚወድቅ

-የሕይወት ምንጭ በጻድቃን አፍ እንደሆነ

-ልዝብ ከንፈሮች ጥልን እንደሚሸፍኑ፣ ከንፈሩን የሚገታ አስተዋይ እንደሆነ

-የጻድቅ ምኞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደች እንደሆነች

-እግዚአብሔርን መፍራት ዘመንን እንደሚያረዝም

-የጻድቃን አፍ ጥበብን እንደሚናገር

ምዕራፍ ፲፩፡- አባይ ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ እንደሆነና እውነተኛ ሚዛን ግን በእርሱ ዘንድ የተመረጠ እንደሆነ

-ትዕቢት ባለበት ውርደት እንዳለ

-ጽድቅ ከሞት እንደምታድን

-የፍጹም ሰው ጽድቁ መንገዱን እንደሚያቀናለት

-ቅኖች ሰዎችን ጽድቃቸው እንደሚታደጋቸው

-የክፉዎች ትምክሕት እንደምትጠፋ

-የጻድቃን ዕውቀት መልካም ጎዳና እንደሆነች

-ጥበብ የጎደለው ሰው የሀገሩን ሰው እንደሚንቅ

-መምህር የሌላቸው እንደ ቅጠል እንደሚወድቁ

-ደግ ሴት ለባሏ ክብርን እንደምታስገኝ

-ጠማማ መንገድ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ እንደሆነ

-መልካምን የሚያስብ መልካም ክብርን እንደሚወድ

-በባለጠግነቱ የሚተማመን ሰው እንደሚወድቅ

-ከጻድቅ ፍሬ የሕይወት ዛፍ እንደሚወጣ

ምዕራፍ ፲፪፡- ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን እንደሚወድ፣ ተግሣጽን የሚጠላ ግን ሰነፍ እንደሆነ

-ልባም ሴት ለባሏ ዘውድ እንደሆነች

-የጻድቃን ሐሳብ ቅን እንደሆነ

-የብልህ ሰው አንደበት በሰው ሁሉ ዘንድ እንደሚመሰገን

-ሰው የከንፈሩን ዋጋ እንደሚቀበል

-ጻድቅ ሰው የተገለጠ እውነትን እንደሚያስተምር

-በጽድቅ መንገድ ሕይወት እንዳለ

ምዕራፍ ፲፫፡- አዋቂ ልጅ የአባቱን ተግሣጽ እንደሚሰማ፣ የማይሰማ ልጅ ግን እንደሚጠፋ

-ደግ ሰው ከጽድቅ ፍሬ መልካምን እንደሚበላ

-አፉን የሚጠብቅ ነፍሱን እንደሚጠብቅ

-የደጋጎች እጅ እንደሚተጋ

-ጻድቅ የሐሰትን ቃል እንደሚጠላ፣ ጻድቃን እንደሚራሩና እንደሚመጸውቱ

-ራሳቸውን የሚያውቁ ብልሆች እንደሆኑ

-መልካም ምኞት የሕይወት ዛፍ እንደሆነች

-መልካም ዕውቀት ሞገስና ጥበብን እንደሚሰጥ

-ትምህርት ድህነትንና ጉስቁልናን እንደሚያስወግድ

ምዕራፍ ፲፬፡- ብልሆች ሴቶች ቤቶችን እንደሚሠሩ

-በቅንነት የሚሄድ ሰው እግዚአብሔርን እንደሚፈራ

-ከሰነፎች አፍ የስድብ በትር እንደሚወጣ

-ብልህ ሰው ፈርቶ ከክፉ እንደሚሸሽ

-ለድሃ የሚራራ ብፁዕ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ትእዛዝ የሕይወት ምንጭ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፮፡- የለዘበ ቃል ቁጣን እንደሚመልስ

-የእግዚአብሔር ዓይኖች በሁሉ ቦታ እንደሆኑ

-አላዋቂ ልጅ የአባቱን ተግሣጽ እንደሚያቃልል

-የቅኖች ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንደሆነ የክፉዎች መሥዋዕት ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ እንደሆነ

-አላዋቂ ሰው የሚዘልፈውን እንደማይወድ

-ደጋግ ሰዎች ሁልጊዜም ዝም እንደሚሉ

-ትዕግሥተኛ ሰው ክርክርን እንደሚያጠፋ

-ማኅበርን የሚያከብሩ ማስተዋልን ገንዘብ እንደሚያደርጉ

-በምጽዋትና በእምነት ኃጢአት እንደሚሠረይ

-የደግ ሰው ልብ እውነትን እንደሚያስብ

ምዕራፍ ፲፯፡- እግዚአብሔርን መፍራት በጎ ዕውቀትና ጥበብ እንደሆነ

-የዋሃንን ክብር እንደምትከተላቸው

-የትሑት ሰው ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንደሆነ

-በልቡ የታበየ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ እንደሆነ

-የደግ ነገር መጀመሪያ እውነት መሥራት እንደሆነ

-ቅንነትን የሚሹ ሰላምን እንደሚያገኙ

-የእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ ከእውነት ጋር እንደሆነ

-የሕይወት መንገዶች ከክፉ እንደሚያርቁ

-በእግዚአብሔር የታመነ ብፁዕ እንደሆነ

-ያማረ ቃል የማር ወለላ እንደሆነ

-መልካም ሽምግልና የክብር አክሊል እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፮፡- ጻድቅ የሐሰት ከንፈሮችን እንደማይመለከት

-የልጆች ክብር አባቶቻቸው እንደሆኑ

-የጽድቅ መጀመሪያ በነገር መሠልጠንን እንደሚሰጥ

-ኃጥኡን ጻድቅ ጻድቁን ኃጥእ ብሎ መፍረድ በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ እንደሆነ

-ጠማማ ልብ ያለው መልካም ነገርን እንደማያገኝ

-ሻካራ ቃልን ከመናገር የሚከለከል ዐዋቂ እንደሆነ

-ትዕግሥተኛ ሰው ብልህ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፯፡- በፍርድ ጊዜ እውነትን ማራቅ መልካም እንዳይደለ

-የእግዚአብሔር ስም ታላቅ እንደሆነና ጻድቃን እርሱን በመከተል ከፍ ከፍ እንደሚሉ

-የብልህ ልብ ዕውቀትን ገንዘብ እንደሚያደርግ

-ደግ ሚስትን ያገኘ ሞገስን እንዳገኘና ደግ ሴትን የፈታ ደስታን እንዳጣ

ምዕራፍ ፲፱፡- ነፍስ ዕውቀት የሌለባት ትሆን ዘንድ መልካም እንዳይደለ

-ማስተዋልን የሚጠብቅ መልካም ነገርን እንደሚያገኝ

-ሐሰተኛ ምስክር ከቅጣት እንደማይድን

-ይቅር ባይ ሰው ታጋሽ እንደሆነ

-እግዚአብሔርን መፍራት ሕይወት እንደሆነ

-አስተዋይን ሰው ብትገሥጻው ዕውቀትን እንደሚያገኝ

ምዕራፍ ፳፡- ለተሳዳቢና ለሰካራም ወይን ክፉ እንደሆነ

-የሰው ክብሩ ከስድብ መከልከል እንደሆነ

-ይቅር ባይ ሰው ታላቅና ክቡር እንደሆነ

-ቸርነትና እውነት ንጉሥን እንደሚጠብቁት

ምዕራፍ ፳፩፡- ሰው ሁሉ ለራሱ ጻድቅ መስሎ እንደሚታይ

-ክፉ ሰው ሲዋረድ የዋህ ሰው አዋቂ እንደሚሆን

-ከነዝናዛና ከነገረኛ ሴት ጋር ከመቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ እንደሚሻል

-አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ነፍሱን ከመከራ እንደሚጠብቅ

-የኃጥኣን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ እንደሆነ

-ረድኤት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ

ምዕራፍ ፳፪፡- ከብዙ ባለጠግነት መልካም ስም እንደሚሻል

-ሐሰትን የሚዘራ መከራን እንደሚያጭድ

-እግዚአብሔር ደስ ብሎ የሚሰጥ ሰውን እንደሚወድ

-እግዚአብሔር የልብን የዋሃት እንደሚወድ

-ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ መሆን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፳፫፡- ድሃ ስትሆን ከባለጠጋ ጋር መወዳደር እንደማይገባ

-ከስስታም ሰው ጋር መመገብ እንደማይገባ

-የነገርህን ጥበብ እንዳይንቅብህ በሰነፍ ጆሮ አንዳች ነገር መናገር እንደማይገባ

-አባቶች ያኖሩትን የድንበር ምልክት ማፍለስ እንደማይገባ

-ሕፃናትን ከመቅጣት ቸል ማለት እንደማይገባ

-ሰካራምና አመንዝራ እንደሚደኸይ

-የወለደንን አባት መስማት እንደሚገባና እናትም ባረጀች ጊዜ መናቅ እንደማይገባ

-ጻድቅ አባት በመልካም እንደሚያሳድግ

ምዕራፍ ፳፬፡- በክፉ ሰዎች መቅናት እንደማይገባና ከእነርሱ ጋር መኖርን አለመውደድ እንደሚገባ

-ከታላቅ ርስት ይልቅ ዕውቀት ያለው ሰው እንደሚበልጥ

-ብልሆች ከእግዚአብሔር ቃል እንደማይርቁ

-እግዚአብሔር የሁሉን ልብ እንደሚያውቅ

-ጻድቅ ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ሰባት ጊዜ እንደሚነሣ

-ጠላትህ ቢወድቅ ደስ አይበልህ እንደተባለ

-እግዚአብሔርንና ንጉሥን መፍራት እንደሚገባ

-ክፉ ልጅ አባቱን እንደሚረግምና እናቱንም እንደማያመሰግን

-ነገርን መጎተት ጭቅጭቅንና ቅጣትን እንደሚያመጣ

-አፍን በእግዚአብሔር ቃል መክፈት እንደሚገባ

መጽሐፈ ተግሣጽ

ምዕራፍ ፩፡- የእግዚአብሔር ክብር ነገርን እንደሚሰውር

-በእግዚአብሔር ፊት መመጻደቅ እንደማይገባ

-ጸጋና ወንድማማችነት ነጻ እንደሚያደርግ

-የብልህ ነገር በሚሰማ ሰው ጆሮ ያማረ እንደሆነ

-የሕይወት ውበት በትዕግሥት እንደምትነግሥ

-እንዳይጠላንና እንዳይሰለቸን እግራችንን ወደባልንጀራችን ቤት አለማዘውተር እንደሚገባ

-የክፉ መንገድና የኀጢአተኛ እግር በክፉ ቀን እንደሚጠፉ

-ጠላታችን ቢራብ ማብላት ቢጠማ ማጠጣት እንደሚገባና ይህንን ያደረግን እንደሆነ እግዚአብሔር መልካም ዋጋን እንደሚመልስልን

-የራስን ክብር መፈለግ እንደማያስከብር

ምዕራፍ ፪፡- ከንቱ ርግማን በማንም ላይ እንደማይደርስ

-ኃጢአትን የምታመጣ ኀፍረት እንዳለች ክብርንና ጸጋን የሚያመጣ ኀፍረትም እንዳለ

-በእንጨት መታጣት እሳት እንደሚጠፋ በእንጨት ብዛትም እሳት እንደሚነድ

-ቁጡ በሌለበት ጸብ ጸጥ እንደሚል

-ጠላትነቱን የሚሸሽግ ተንኮልን እንደሚሰበስብ

-ጉድጓድን ለባልንጀራው የሚምስ ራሱ ይወድቅበታል

-ሐሰተኛ ምላስ እውነትን እንደምትጠላ ዝም የማይል አፍ ክርክርን እንደሚያመጣ

ምዕራፍ ፫፡- ለቁጡና ቁጣን ለሚያፋጥን ምሕረት እንደሌለው

-ከጠላት መልካም አሳሳም የወዳጅ ንክሻ እንደሚሻል

-የቀረበ ወዳጅ ከራቀ ወንድም እንደሚሻል

-የሽሙጥን ቃል ማራቅ እንደሚገባ

-ብረት ብረትን እንደሚስለው ሰውም ባልንጀራውን እንደሚስል

-በዐይኑ የሚገላምጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡- ኃጥእ ማንም ሳያሳድደው እንደሚሸሽ

-ጻድቅ ግን እንደ አንበሳ ተማምኖ እንደሚኖር

-በክፉዎች በደል መቅሠፍት እንደሚነሣ

-ከሐሰተኛ ባለጠጋ በእውነት የሚሄድ ድሃ እንደሚሻል

-በጻድቃን ረድኤት ብዙ ክብር እንዳለ

-ግፍን የሚጠላ ብዙ ዘመን እንደሚኖር

ምዕራፍ ፭፡- በጻድቃን መመስገን ሕዝቦች ደስ እንደሚላቸው

-ጥበብን በሚወድ ልጅ አባቱ ደስ እንደሚለው

-እውነተኛ ንጉሥ ሀገሩን እንደሚያጸና ዐመፀኛ ሰው ግን እንደሚያፈርስ

-ጻድቅ በደስታና በሐሴት እንደሚኖር

-ጠቢባን ቁጣን እንደሚመልሱ

-ለድሆች በእውነት የሚፈርድ ንጉሥ ዙፋኑ ለዘለዓለም እንደሚጸና

-ትዕቢት ሰውን እንደሚያዋርደው

ምዕራፍ ፮፡- ልባም ሴት ዋጋው ብዙ ከሆነ ከከበረ ዕንቁ እጅግ የከበረች እንደሆነች

-ልባም ሴት እድሜዋን ሁሉ በበጎ ላይ በጎ እየሠራች ባሏን እንደምትረዳው

-ብልህ ሴት እንደምትባረክ

መጽሐፈ ጥበብ

ምዕራፍ ፩፡- ጽድቅን መውደድ እንደሚገባ

-ጠማማ ሐሳብ ከእግዚአብሔር እንደሚያርቅ

-በተተነኮለች ሰውነት ጥበብ እንደማትገባ ለኃጢአት በተገዛች ሰውነትም እንደማታድር

-ጥበብን የሚገልጽ መንፈስ ሰው ወዳጅ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ሞትን እንዳልፈጠረ

ምዕራፍ ፪፡- ከሞትን በኋላ ሥጋችን ትቢያ እንደሚሆን፣ ስማችን እንደሚዘነጋ

-ሕይወታችን እንደጥላ የሚያልፍ እንደሆነ

-በዲያብሎስ ቅንዐት ሞት እንደመጣና ወደዚህ ዓለምም እንደገባ

ምዕራፍ ፫፡- የጻድቃን ነፍስ በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነችና መከራ እንደማያገኛት

-ጻድቃን ጥቂት መከራ ተቀብለው ብዙ ክብርን እንደሚያገኙ

-ወርቅ በከውር እንደሚፈተን ጻድቃንም በመከራ እንደሚፈተኑ

-ምእመናን በእግዚአብሔር ፍቅር ጸንተው እንደሚኖሩ

-ጥበብንና ተግሣጽን የሚንቁ ሰዎች ጎስቋሎች እንደሆኑ

-የደግ ሰው የድካሙ ፍሬ ክብርና ጌጥ እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡- ጻድቅ ሰው ለመሞት በደረሰ ጊዜ በዕረፍት እንደሚኖር

-የሽምግልና አክሊሏ ያለ ነውር መኖር እንደሆነ

-ጻድቅ ሰው ከሞተ በኋላ በሕይወት ባሉ ክፉዎች ላይ እንደሚፈርድ

ምዕራፍ ፭፡- ክፉ ሰዎች በምጽአት ጊዜ እንደሚጸጸቱ

-የጻድቃን ዋጋቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የጸና እንደሆነ

ምዕራፍ ፮፡- የነገሥታትና የመኳንንት ሹመት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ

-ጥበብ ፈጽማ የጎላች እንደሆነና ውበቷም እንደማይጠወልግ

-የጥበብ መጀመሪያ ተግሣጽን መውደድ እንደሆነ

-የጠቢባን ብዛት የዓለም መድኃኒት እንደሆነ

ምዕራፍ ፯፡- የሰው ሁሉ ወደዚህ ዓለም አመጣጡ አንዲት አወጣጡም አንዲት እንደሆነች

-እግዚአብሔር ከጥበብ ጋር የሚኖርን ሰው እንደሚወድ

ምዕራፍ ፰፡- ጥበብ ባለችበት ብልጽግና እንዳለ

ምዕራፍ ፱፡- ጥበብ ቅድመ ዓለም እንደነበረች

ምዕራፍ ፲፡- ጥበብ የሚያገለግሏትን ሰዎች ከድካምና ከመከራ እንደምታድን

ምዕራፍ ፲፩፡- እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል ነውና ሁሉን ይቅር እንደሚል

-እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ እንደሚራራ

ምዕራፍ ፲፪፡- እግዚአብሔር ሁሉን መፍጠሩና መግዛቱ ይቅር እንዲል እንደሚያደርገው

ምዕራፍ ፲፫፡- ውበትን የፈጠረ እግዚአብሔር እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፬፡- የዝሙት መጀመሪያዋ ጣዖትን የመሥራት አሳብ እንደሆነ

-ጣዖቶችን ማምለክ የክፋት ሁሉ መጀመሪያ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፭፡- እግዚአብሔርን ማወቅ ፍጽምት ጽድቅ እንደሆነች

ምዕራፍ ፲፮፡- የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን እንደሚያድን

-እግዚአብሔር በሕይወትና በሞት ላይ ሥልጣን እንዳለው

ምዕራፍ ፲፯፡- የእግዚአብሔር ፍርድ ታላቅ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፰፡- በጻድቃን ዘንድ ታላቅ ብርሃን እንደነበር

ምዕራፍ ፲፱፡- እግዚአብሔረ በታላላቅ ተአምራት እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣ

መጽሐፈ መክብብ

ምዕራፍ ፩፡- ሰሎሞን ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው እንዳለ

-ከፀሐይ በታች ከተደረገው ሁሉ አዲስ ነገር እንደሌለ መነገሩ

ምዕራፍ ፪፡- የጠቢብ ዓይኖች በራሱ ላይ እንደሆኑ

-አላዋቂ በከንቱ መናገርን እንደሚያበዛ

ምዕራፍ ፫፡- ለሁሉ ዘመን እንዳለው መነገሩ

-እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ሁሉ በጊዜው መልካም እንደሆነ

-ለሰው ልጆች ሞት እንዳለባቸው መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን እንደሚሻል

ምዕራፍ ፭፡- የጠቢባንን ትምህርት ለመስማት መቅረብ እንደሚገባ

-የተሳሉትን ስእለት መስጠት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፮፡- እግዚአብሔር ለሰው ሀብትንና ጥሪትን ክብርንም እንደሰጠው

ምዕራፍ ፯፡- ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ከመወለድ ቀንም የሞት ቀን እንደሚሻል

ምዕራፍ ፷፡- ለኃጥእ ድኅነት እንደሌለው

ምዕራፍ ፷፩፡- ከሕያዋን ጋር አንድነት ያለው ማንም ሰው ተስፋ እንዳለው

-ከኃይል ይልቅ ጥበብ እንደምትበልጥ

ምዕራፍ ፷፪፡- የሞቱ ዝንቦች የተቀመመውን የዘይት ሽቱ እንደሚያገሙት

-ትዕግሥት ኃጢአትን እንደሚያስተሠርይ

-ለባልንጀራው ጉድጓድን የሚምስ ራሱ እንደሚወድቅበት

-የጠቢብ ሰው የአፉ ቃል ሞገስ እንደሆነች

ምዕራፍ ፷፫፡- ከልብ ቁጣን ማራቅ ከሰውነትም ክፉ ነገርን ማስወገድ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፷፬፡- የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝና ወራት ፈጣሪን ማሰብ እንደሚገባ

መሓልየ መሓልይ ዘሰሎሞን

ምዕራፍ ፩፡- መሓልየ መሓልይ ላይ ቤተ እስራኤል በሙሽሪት እግዚአብሔር በሙሽራ ተመስሎ ተነግሯል፡፡

ምዕራፍ ፪፡- ቤተ እስራኤል ጌታን “ልጅ ወንድሜ” እንዳለችው

ምዕራፍ ፫፡- ቤተ እስራኤል ጌታን “ነፍሴ የወደደችው” እንዳለችው

ምዕራፍ ፬፡- ቤተ ክርስቲያን አንድም ድንግል ማርያም ሁለንተናሽ ውብ ነው እንደተባለች

ምዕራፍ ፭፡- በሙሽራ የተመሰለ እግዚአብሔር ጉሮሮው ጣፋጭ ነው እንደተባለ

ምዕራፍ ፮፡- ልጅ ወንድሜ የተባለ ጌታ በሱፍ አበባ መካከል መንጋውን እንደሚያሰማራ

ምዕራፍ ፯፡- ሱላማጢስ የተባለች ምእመን መመለስ እንደሚገባት መነገሩ

ምዕራፍ ፰፡- ፍቅር እንደሞት የበረታች እንደሆነች

-ብዙ ውሃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ እንደማይችል

መጽሐፈ ሲራክ

ምዕራፍ ፩፡- የጥበብ ሁሉ መገኛዋ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነና ለዘለዓለምም ከእርሱ ጋር እንደሆነች

-ጥበብ ከሁሉ አስቀድሞ እንደተፈጠረች

-ጥበበኛ አንድ እንደሆነና ይህም እጅግ የሚያስፈራና በዙፋኑ ላይ ጸንቶ የሚኖር እንደሆነ

-እግዚአብሔር ለሚወዱት ሁሉ ጥበብን እንደሰጣቸው

-እግዚአብሔርን መፍራት ክብር፣ ደስታ እንደሆነ

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ፍጻሜው እንደሚያምር

-ጥበብን መጥገብ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ

-የጥበብ መጀመሪያና የጥበብ ዘውድ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ

-ቁጡና አመፀኛ ሰው መጽደቅ እንደማይችል

-ጊዜዋ እስክታልፍ ድረስ ቁጣን መታገሥ እንደሚገባ

-ጊዜውን እስክናገኝ ድረስ ነገራችንን መሰወር እንደሚገባ

-ጥበብን መውደድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እንደሆነ

-ጥበብም ዕውቀትም እግዚአብሔርን መፍራት እንደሆነ

-እየተጠራጠሩ እግዚአብሔርን በሁለት ልብ ማገልገል እንደማይገባ

ምዕራፍ ፪፡- ለእግዚአብሔር ለመገዛት ሰውነትን ለመከራ ማዘጋጀት እንደሚገባ

-ልብን ማቅናትና መታገሥ እንደሚገባ

-በችግር ወራት መታገሥ እንደሚገባ

-ወርቅን በእሳት እንደሚፈትኑት ጻድቅንም ሰው በመከራ እንደሚፈትኑት

-በዘመን የቀደሙ ሰዎችን መመልከትና ማወቅ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ እንደሆነ

ምዕራፍ ፫፡- አባቱን የሚያከብር ልጅ ኃጢአቱ እንደሚሠረይለት፣ ጸሎቱ እንደሚሰማለት፣ ዕድሜው እንደሚረዝምለት

-በረከቱ ይደርሰን ዘንድ በቃላችንም በሥራችንም አባታችንን ማክበር እንደሚገባን

-የአባት በረከት የልጅን ቤት እንደሚያጸና

-የእናት ርግማን መሠረትን እንደሚነቅል

-ሰው በአባቱ ክብር እንደሚከብር

-እናቱን የሚያሳዝን በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ እንደሆነ

-አላስፈላጊ ሥራዎችን መመራመር እንደማይገባ

-የብልህ ሰው ልቡና ምሳሌን እንደሚተረጉም

-የዐዋቂ ሰው ጆሮ ጥበብ መስማትን እንደምትወድ

-ምጽዋት ኃጢአትን እንደምታስተሠርይ

ምዕራፍ ፬፡- የተራበች ሰውነትን እና ያዘነ ሰውን ማሳዘንና ማበሳጨት እንደማይገባ

-ከድሃ ፊትን መመለስ እንደማይገባ

-ይረግመን ዘንድ ለሰው ምክንያት መስጠት እንደማይገባ

-ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ እንደማይገባ

-የተበደለውን ሰው ከሚበድለው እጅ ማዳን እንደሚገባ

-አባቱ ለሞተበት ልጅ እንደ አባት መሆን እንደሚገባ

-የሰው ፊት አይቶ ማዳላት እንደማይገባ

-ጽድቅን መቃወም እንደማይገባ

ምዕራፍ ፭፡- ገንዘብን በከንቱ መበተን እንደማይገባ

-የሰውነትን ፈቃድ መከተል እንደማይገባ

-ስለኃጢአታችን ንስሓ መግባትን መፍራት እንደሌለብን

-የእግዚአብሔር ምሕረቱ ብዙ ነው ኃጢአቴንም ይቅር ይለኛል እያልን በኃጢአት ላይ ኃጢአትን መጨመር እንደማይገባን

-ሞት ድንገት ትመጣለችና ለእግዚአብሔር መገዛትን ቸል ማለት እንደማይገባ

-ለሰው ሁሉ ምሥጢርን ማውጣት እንደማይገባ

-የወደድነውን ሁሉ መከተል እንደማይገባ

-ለመስማት ፈጣን፣ ቃልን ለመመለስ ግን የዘገየን መሆን እንደሚገባን

-ሐሜተኛ መሆን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፮፡- ከልቡናችን ባነቃነው ምክር ራሳችንን ከፍ ከፍ ማድረግ እንደማይገባ

-ልዝብ አንደበት ወንድማማችነትን ወዳጅን እንደሚያበዛ

-ወዳጅ ብናበጅ በችግራችን ወራት ማበጀት እንደሚገባና ፈጥነን ግን እምነታችንን በእርሱ ላይ መጣል እንደማይገባን

-የታመነ ወዳጅ የሕይወት መድኃኒት እንደሆነ

-የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማሰብ መጻሕፍቱንም ሁልጊዜ ማንበብ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፮፡- ክፋትን አለመሥራትና ከበደል መራቅ እንደሚገባ

-በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ነኝ ማለት እንደማይገባ

-የሀገርን ሰው መበደል እንደማይገባ

-በምንጸልይበት ጊዜ መቸኮል እንደማይገባ

-በምንም ቢሆን ሐሰትን መውደድ እንደማይገባ

-በፍጹም ሰውነት እግዚአብሔርን መፍራት እንደሚገባ

-ካህናትን ማክበር እንደሚገባ

-ስለሞተ ሰው ምጽዋትን መስጠት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፯፡- ከኃጢአቱ የተመለሰውን ሰው መንቀፍ እንደማይገባ

-በእርጅናው ምክንያት ሰውን ማቃለል እንደማይገባ

-ከቁጡ ሰው ጋር መከራከር እንደማይገባ

ምዕራፍ ፰፡- ርስታችንን እንዳናጣ ለአመንዝራ ሴት ልቡናችንን መስጠት እንደማይገባ

-የተቻለንን ያህል ለባልንጀራችን መልካም ማድረግ እንደሚገባን

-ከጠቢባን ጋር መማከር እንደሚገባ

ምዕራፍ ፱፡- ጠቢብ ንጉሥ ሕዝቡን እንደሚመክር

-አላዋቂ ንጉሥ ሕዝቡን እንደሚያጠፋ

-ሀገር በሽማግሌዎች ጥበብ እንደምትጸና

-የምድር ግዛት በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነና በጊዜውም የሚጠቅመውን ሰው በእርሷ ላይ እንደሚያስነሣ

-የሰው በረከቱ በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ

-ባልንጀራችን በሳተበት ሁሉ መንቀፍ እንደማይገባ

-ትዕቢት በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ የተጠላ እንደሆነ

-ሰውነቱ የሚተላ ሰው መታበይ እንደማይገባው

-ሰው ከሞተ በኋላ የትል እድል ፋንታ እንደሆነ

-ትዕቢት የኃጢአት መጀመሪያ እንደሆነች

-እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ዘር የከበረ ዘር እንደሆነ

-ድሃን ስለድህነቱ መናቅ ኃጢአተኛን ስለባለጠግነቱ ማክበር እንደማይገባ

ምዕራፍ ፲፩፡- ስለመልከ መልካምነቱ ለሰው ማዳላት እንደማይገባ፣ ስለ መልከ ጥፉነቱም ሰውን መናቅ እንደማይገባ

-በልብስ ጌጥ መታበይ እንደማይገባ

-በከበርንበት ወራት ራሳችንን ማኩራት እንደማይገባን

-ሳንመረምር መንቀፍ እንደማይገባና አስቀድመን መረዳት እንደሚገባን

-ሳንሰማ መመለስ እንደማይገባንና በሌላው ነገር ውስጥ መግባት እንደማይገባ

-ግዳጃችን ባልሆነ ነገር መጨነቅ እንደማይገባን

-ከኃጢአተኞች ጋር በፍርድ መቀመጥ እንደማይገባ

-ሕይወትና ሞት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆኑ

-የእግዚአብሔር ጸጋው ጻድቃንን እንደምትጠብቅ

-የእግዚአብሔር በረከት ለጻድቃን ዋጋቸው እንደሆነ

-ፍጻሜውን ሳናይ ሰውን ብፁዕ ማለት እንደማይገባን

ምዕራፍ ፲፪፡- ለጻድቅ በጎ ነገርን ማድረግ ዋጋን እንደሚያስገኝ

-ኀጢአትን በሚሠራና ምጽዋትን በማይመጸውት ዘንድ በጎ ሥራ እንደሌለ

-ለድሃ መልካም ማድረግ እንደሚገባ እና ለክፉ ግን መስጠት እንደማይገባ

-እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ሰዎችን እንደሚጠላና ክፉ ሰዎችንም እንደሚበቀል

ምዕራፍ ፲፫፡- ትዕቢተኛ ሰውን ወዳጅ ያደረገ ትዕቢተኛ እንደሚሆን

-በደስታ መካከል ኀዘንን ማስገባት እንደማይገባ

-የባልንጀራውን ምሥጢር ለሚያወጣ ሰው ይቅርታ እንደሌለው

-ትዕቢተኛ ሰው ራሱን የሚያዋርደውን ሰው እንደሚጸየፈው

-ኃጢአት ሳይሠሩ ባለጸግነት መልካም እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፬፡- በአፉ ያልተሰነካከለ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-ሰውነቱን የማያሳዝን ተስፋውንም የማይቆርጥ ሰው ብፁዕ እንደሆነ

-ነገርን ለማያውቅና ለንፉግ ሰው ብልጽግና እንደማይገባው

-ሞት እንደማይቀር ማሰብ እንደሚገባ

-ሳትሞት ለባልንጀራህ በጎ አድርግ መባሉ

ምዕራፍ ፲፭፡- የእግዚአብሔርን ሕጉን የሚጠብቅ ጥበብን እንደሚያገኛት

-የኀጢአተኛ ሰው የቃሉ ነገር ያማረ እንዳልሆነ

-የእግዚአብሔር ጥበቡ ታላቅ እንደሆነና ኃይሉም የጸና እንደሆነ

-እግዚአብሔር ኃጢአትን ይሠራ ዘንድ ያዘዘው ማንም እንደሌለ

ምዕራፍ ፲፮፡- ጥቅም የሌላቸው ብዙ ልጆችን መመኘት እንደማይገባ

-ከሺህ አንድ ደግ እንደሚሻል

-ክፉን ከመውለድ ሳይወልዱ መሞት እንደሚሻል

-በአንድ አዋቂ ሀገር እንደምትጸናና በኃጢአተኞች ብዛት ግን እንደምትጠፋ

-እግዚአብሔር ለሰው እንደ ሥራው እንደሚከፍለው

-ጻድቅ ሰው የትዕግሥቱን ዋጋ እንደማያጣ

-ምጽዋት ሁሉ ይቅርታን እንደሚያመጣ

ምዕራፍ ፲፯፡- እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ የፍጥረታት ገዢ እንዳደረገው

-እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሁሉ ነገሥታትን እንዳነገሠላቸው

-የሰው ዋጋው እንደ ዓይን ብሌን እንደምትጠበቅለት

-ለበደላችን ንስሓ መግባት እንደሚገባ

-ኃጢአትን መጥላትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ እንደሚገባ

-በሕይወታችን ደስ እያለን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን

-የእግዚአብሔር ቸርነቱ ታላቅ እንደሆነና የሚገዙለትን ሰዎች ይቅር እንደሚል

ምዕራፍ ፲፮፡- እውነተኛ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ታጋሽ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ይቅር እንደሚል

-ክፉ ነገርን መናገር እንደማይገባ

-ሳይፈረድብን ራሳችንን መመርመር እንደሚገባን

-ሳንሞት ጽድቅን መሥራት እንደሚገባን

-የሞትን ቀን ማሰብ እንደሚገባ

-ከክፉ ፍትወት መራቅ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፲፱፡- ሰካራም ሠራተኛ እንደማይበለጽግ

-ፈጥኖ የሚያምን ልቡናው ቀሊል እንደሆነ

-ብዙ መናገርን የሚጠላ ኃጢአቱን እንደሚያሳንስ

-የሰማነውን ቃል ማውጣት እንደማይገባ

-አላዋቂ ሰው የሰማውን ነገር እስከሚያወጣ ድረስ እንደሚቅበዘበዝ

-የነገሩንን ነገር ሁሉ ማመን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፳፡- ከመንቀፍ መገሠጽ እንደሚሻል

-ስሕተቱን የሚያምን ከጥፋት እንደሚድን

-ብልህ ሰው ጊዜውን እስከሚያገኝ ድረስ ዝም እንደሚል

-በአንደበትህ አድጦህ ከምትወድቅ በምድር ላይ አድጦህ ብትወድቅ እንደሚሻልህ

-እንዳገኘ የሚናገር ሰው ራሱን እንደሚያስነውርና ለቃሉም መወደድ እንደሌለው

-እጅ መንሻና መማለጃ የጠቢበንን ዐይን እንደሚያሳውር

ምዕራፍ ፳፩፡- የበደልነው በደል ቢኖር ንስሓ መግባት እንደሚገባ

-ሰው ክፉ አውሬ እንደሚሸሽ እንዲሁ ከኃጢአት መሸሽ እንደሚገባው

-ድኻ በሚለምንበት ጊዜ አፉን እስከ ጆሮው እንደሚከፍትና ጩኸቱም ፈጥኖ ወደ እግዚአብሔር እንደሚደርስ

-ለብልህ ሰው የተሳተው ኃጢአቱ እንደሚታወቀው

-የኃጢአተኞች አንድነታቸው እንደ ገለባ ክምር እንደሆነ

-ልቡናውን ያጸና ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ እንደሚጠብቅ

-የብልህ ሰው ነገሩ ወደ ልብ እንደሚገባ

-አላዋቂ ሰው በሳቀ ጊዜ ቃሉን ከፍ እንደሚያደርግና ብልህ ሰው ግን በጭንቅ ከንፈሩን ፍግግ እንደሚያደርግ

-የለፍላፊ ከንፈር የማይመለከተውን እንደሚናገር

-ኃጢአተኛ ሰው ሰይጣንን ቢረግመው ራሱን መርገሙ ነው መባሉ

-ሐሜተኛ ሰው ሰውነቱን እንደሚያረክስ

ምዕራፍ ፳፪፡- ሰነፍ ሰው በተቀመጠበት ቦታ እንደ ዋሻ ድንጋይ እንደሆነ

-ያልተቀጣ ልጅ ለአባቱ ኀፍረት እንደሆነ

-ባገኘበት ቦታ ነገሩን የሚናገር ሰው በልቅሶ ቤት መሰንቆ እንደሚመታ ሰው እንደሆነ

-ግርፋትና ተግሣጽ ሁልጊዜ ብልህ እንደሚያደርጉ

-ለሞተ ሰው ማልቀስ እንደሚገባ

-ከሰነፍ ሰው ጋር ነገርን ማብዛት እንደማይገባ

-በወዳጁ የሚዘብት ሰው ወዳጅነትን እንደሚያጠፋ

ምዕራፍ ፳፫፡- አንደበቱን የጠበቀ እንደማይወድቅ

-መሐላን የሚያበዛ ሰው ሐሰቱ ብዙ እንደሆነና ከቤቱም መቅሠፍት እንደማይርቅ

-ከአንደበታችን የመዘባበት ነገር እንዳይወጣ መጠንቀቅ እንደሚገባን

-በሰው ላይ መሳለቅ እንደማይገባ

-እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከመፍጠሩ በፊት ሁሉ ነገራቸውን ያውቅ እንደነበር

ምዕራፍ ፳፬፡- በእግዚአብሔር የሚጸና እንደማይደክም

-ሁሉን የሚችል ጌታ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነና ከእርሱ በቀርም ሌላ አዳኝ እንደሌለ

ምዕራፍ ፷፩፡- በአንድ ልብ የሚተባበሩ ወንድማማቾች፣ የባልንጀሮች ፍቅርና የባልና የሚስት ስምምነት በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ እንደሆነ

-የትምህርት ብዛት የሽማግሌች ዘውዳቸው እንደሆነ

-በአንደበቱ ያልሳተ ብፁዕ እንደሆነ

ምዕራፍ ፷፪፡- ደግ ሴትን ባሏ እንደሚያመሰግናት እርሷም ባሏን ደስ እንደምታሰኘው

-ባሏን የምታስቀና ሴት የልብ ቁስል የሰውነት ጎዘን እንደሆነች

-ሰካራም ሴት ታላቅ ጥፋት እንደሆነችና ኀፍረቷንም እንደማትሸፍን

-የዋህ ሴት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነች

-የምታፍር ሴት በበረከት ላይ በረከት እንደሆነች

ምዕራፍ ፷፫፡- የሰው ነገሩ የልቡናውን ፈቃድ እንደሚገልጥበት

-ሰውን ሳይረዱ ማድነቅ እንደማይገባ

-ኃጢአት የሚሠሯትን እንደምታድ*ናቸው

-ጻድቅ ሰው ሁልጊዜ ጥበብን እንደሚያስተምር

-የባልንጀራውን ምሥጢር የሚያወጣ ሰው መታመኑን እንደሚያጠፋ

-በጻድቅ ሰው መውደቅ ደስ የሚላቸው ሰዎች በወጥመድ እንደሚያዙ

ምዕራፍ ፷፬፡- እግዚአብሔር ለሚታገሥ ሰው እንደሚበቀልለት

-ባልንጀራችን የበደለንን በደል ይቅር ማለት እንደሚገባን

ምዕራፍ ፷፭፡- ምጽዋትን የሚመጸውት ሰው ለእግዚአብሔር እንደሚያበድር

-ቃልን መጠበቅ እንደሚገባ

-ኃጢአተኛ ሰው ውለታን እንደሚዘነጋ

ምዕራፍ ፷፮፡- ያልተቀጣ ልጅ አውታታ እንደሚሆን

ምዕራፍ ፷፯፡- ሕልም ሰነፍ ሰውን እንደሚያስደነግጥ

-ሕልምን የሚያምን ሰው ጥላን እንደሚጨብጥ ነፋስንም እንደሚከተል እንደሆነ

-ሕልም፣ ጥንቆላና ሟርት ሁሉም ከንቱ እንደሆኑ

-የተማረ ሰው ብዙ ምክርን እንደሚያውቅ

-ብዙ መከራን የተቀበለ ሰው ብዙ ትምህርትን እንደሚማር

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰውን የሚያስፈራው እንደሌለ

-የእግዚአብሔር ዐይኖቹ ወደ ወዳጆቹ እንደሆኑ

-ባልን ከሚስቱ የሚያፋታ ሰው ባልንጀራውን እንደሚገድል ሰው እንደሆነ

ምዕራፍ ፴፪፡- የእግዚአብሔር ፈቃዱ ክፉ እንዳንሠራ እንደሆነና ፈቃዱም ከበደል እንርቅ ዘንድ እንደሆነ

-ወደ እግዚአብሔር ፊት ባዶን መግባት እንደማይገባ

-የጻድቅ ሰው መሥዋዕት ቅዱስ እንደሆነ

-በደስታ ዐይን እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

-ለእግዚአብሔር ዐሥራትን፣ መባን ማስገባት እንደሚገባ

-እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ እንደሆነና ፊትን አይቶ እንደማያዳላ

-የትሑት ጸሎት ከደመና እንደምታልፍ

ምዕራፍ ፴፫፡- ያለ እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሌለ

ምዕራፍ ፴፬፡- ገንዘብን የሚወድ ሰው እንደማይጸድቅ

-መጥኖ መብላት እንደሚገባና መጥኖ የሚበላ ሰው እንቅልፉ ጤና እንደሆነ

-ወይንን መጥኖ ለሚጠጣው ሰው ደስታ እንደሆነ

ምዕራፍ ፴፮፡- አለቃ አድርገው ቢሾሙህ ራስህን አታኩራ መባሉ

-ለበጎ ነገር ቸል ማለት እንደማይገባ

-ለመረመረን ሰው ሁሉ ቃላችንን መናገር እንደማይገባ

-አንድ ጊዜ ተናግሮ ወዲያውኑ ነገርን መጨረስ እንደሚገባ

-እያወቅንም ቢሆን ዝም ማለት እንደሚገባ

-ሌላ ሰው ሲናገር መነገር እንደማይገባ

-የሚያፍር ሰው መከበሩ በፊቱ እንደሆነ

-እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ለሕጉ እንደሚገዛ

-በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው የሚያጣው ነገር እንደሌለ

ምዕራፍ ፴፮፡- እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰውን መከራ እንደማያገኘውና ከመከራይቱም እንደሚድን

-ብልህ ሰው መጽሐፍ መስማትን እንደሚወድ

-ብልህ ሰው አምኖ በእግዚአብሔር ሕግ እንደሚገዛና እግዚአብሔርም ወዳጁ እንደሚሆን

ምዕራፍ ፴፯፡- በተመቸን ጊዜ ወዳጃችንን መርሳት እንደማይገባ

-ከሚመክርህ ሰው ልቡናህን ጠብቅ አስቀድመህ ፍላጎቱን ዕወቅበት መባሉ

-ብልህ ሰው በበረከት እንደሚጠግብ

ምዕራፍ ፴፰፡- ማዳን ከእግዚአብሔር እንደሚገኝ

-እግዚአብሔር መድኃኒትን ከምድር እንደፈጠረ

-ኀዘንን ወደ ልቡና ማግባት እንደማይገባ

ምዕራፍ ፴፱፡- በሥራው ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

-የእግዚአብሔር ሥራው ገናና እና ያማረ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር እስከ ዘለዓለም ድረስ ሁሉን እንዳወቀ

-የጻድቅ መንገዱ የቀና እንደሆነ

-የኃጥእ መንገድ እንቅፋት እንደሆነ

-ለእግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለስሙ ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፵፡- ሃይማኖት ለዘለዓለም እንደምትጸና

-የዐመፃ ገንዘብ እንደ ፈሳሽ ውሃ እንደሚደርቅ

-ወይንና ማሕሌት ልብን ደስ እንደሚያሰኙ

ምዕራፍ ፵፩፡- ሞት ሲመጣ እንደሚያስፈራ

-የእግዚአብሔርን ፈቃድ መንቀፍ እንደማይገባ

-ከሺ ታላላቅ መዛግብት ስምን ማስጠራት እንደሚበልጥ

-ወዳጅን መሳደብና ምሥጢርን መግለጥ ኀፍረት እንደሆነ

ምዕራፍ ፵፪፡- የሰውን ፊት አይቶ ማዳላት እንደማይገባ

-ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ

-እግዚአብሔር የልቡናን ሐሳብ እንደሚያውቅ

ምዕራፍ ፵፫፡- ጨረቃ የዘመን መለኪያ እንደሆነች

-የተቻለንን ያህል እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ

ምዕራፍ ፵፬፡- የከበሩ ሰዎችንና አባቶቻችንን በዘመናቸው ማመስገን እንደሚገባ

ምዕራፍ ፵፭፡- ስለ ሙሴ፣ ስለ አሮን፣ ስለ ፊንሐስ መገለጹ

ምዕራፍ ፵፮፡- ኢያሱ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ከመከራ እንዳዳናቸው

-ሳሙኤል በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንደነበር

ምዕራፍ ፵፯፡- ናታን በዳዊት ዘመን ትንቢትን እንደተናገረ

ምዕራፍ ፵፰፡- እግዚአብሔርን የሚያውቁና በፍቅሩ ያጌጡ ሰዎች ብዙዓን እንደሆኑ

ምዕራፍ ፵፱፡- ስለ ንጉሥ ኢዮስያስ፣ ስለ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ስለ ነቢዩ ሕዝቅኤል መነገሩ

ምዕራፍ ፶፡- ስለኦንያ ልጅ ስምዖን መነገሩ

ምዕራፍ ፶፩፡- የሲራክ ልጅ የኢያሱ ልጅ ጸሎት መገለጹ

ትንቢተ ኢሳይያስ

ምዕራፍ ፩፡- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮ አለማወቃቸው

-የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን እንዳስቀረልን

-የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጥ እንደሚገባ

-በበደል ላይ ሆነን ለእግዚአብሔር ምንም ብናቀርብ እንደማይቀበለን

-እግዚአብሔር እሺ ብትሉና ብትሰሙኝ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንዳለ

ምዕራፍ ፪፡- የእግዚአብሔር ቤት በተራሮች ላይ እንደሚታይ ትንቢት መነገሩ

-ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት መውጣትና በጎዳናውም መሄድ እንደሚገባ

-ኑ በእግዚአብሔር ብርሃን እንመላለስ መባሉ

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር ከእስራኤል ኃይልን እንደሚያስወግድ ትንቢት መነገሩ

-እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ሊፈርድ እንደሚነሣ

ምዕራፍ ፬፡- ሰባት ሴቶች አንዱን ወንድ አግባን እንደሚሉት

ምዕራፍ ፭፡- እግዚአብሔር ለወይኑ ስላደረገለት ነገር መነገሩ

-በጥዋት ወደ መሸታ ቤት ለሚገሠግሡና በመጠጥ ቤት ለሚውሉ ወዮላቸው መባሉ

-የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በፍርድ ከፍ ከፍ እንደሚል

-በደልን እንደ ረዥም ገመድ የሚስቡ ኃጢአትንም እንደ በሬ ቀንበር ለሚያሥሩ ወዮላቸው

-ክፉውን መልካም መልካሙንም ክፉ ለሚሉ ወዮላቸው መባሉ

-ለክፋት ጥበበኞች ለሆኑ ወዮላቸው መባሉ

ምዕራፍ ፮፡- ንጉሡ ያዝያን በሞተበት ዓመት ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ እንዳየው

-ነቢዩ ኢሳይያስ ከሱራፌል በአንዱ አማካኝነት እንደዳነ

ምዕራፍ ፯፡- የአራም ንጉሥ ረአሶንና የእስራኤል ንጉሥ የሮሜልዩ ልጅ ፋቁሔ ኢየሩሳሌምን ሊወጉ እንደመጡ

-ድንግል ፀንሳ ወንድ ልጅን እንደምትወልድና ስሙንም አማኑኤል እንደምትለው

ምዕራፍ ፰፡- የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን መቀደስ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፱፡- በጨለማ የሄደ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን እንዳየ

-ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፣ አለቅነትም በጫንቃው ላይ እንደሚሆን መነገሩ

-በእግዚአብሔር ቁጣ ምድር ሁሉ እንደምትቃጠል

ምዕራፍ ፲፡- ክፉን ጽሕፈት ለሚጽፉ ወዮላቸው መባሉ

ምዕራፍ ፲፩፡- ከእሴይ ሥር በትር እንደምትወጣና አበባም ከግንዱ እንደሚወጣ መገለጹ

-በዚህ ግንድም ሰባቱ የእግዚአብሔር ሀብታት እንደሚያድሩበት መገለጹ

ምዕራፍ ፲፪፡- ጌታ እግዚአብሔር ክብራችንና መድኃኒታችን እንደሆነ

-እግዚአብሔርን ማመስገንና ስሙንም መጥራት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፲፫፡- በመዓት ተመልቶ የእግዚአብሔር ቀን እንደሚመጣ

ምዕራፍ ፲፬፡- እግዚአብሔር ያዕቆብን እንደሚምረው

-የእግዚአብሔርን ምክር የሚመልስ እንደሌለ

ምዕራፍ ፲፭፡- ሞዓብ እንደምትጠፋ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፮፡- ዙፋን በምሕረት እንደሚጸና

ምዕራፍ ፲፯፡- ደማስቆ እንደምትጠፋና እንደምትፈርስ

ምዕራፍ ፲፰፡- በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች ሀገር ወዮላት መባሉ

ምዕራፍ ፲፱፡- እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተጭኖ ወደ ግብጽ እንደሚመጣ መነገሩ

-ግብጻውያን ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን እንደሚያቀርቡለት

ምዕራፍ ፳፡- በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ምልክትና ተአምራት እንደሚደረግ

ምዕራፍ ፳፩፡- ስለባቢሎንና ስለኤዶምያስ ትንቢት መነገሩ

ምዕራፍ ፳፪፡- ስለኢየሩሳሌም ትንቢት መነገሩ

ምዕራፍ ፳፫፡- ስለጢሮስ ትንቢት መነገሩ

ምዕራፍ ፳፬፡- እግዚአብሔር ዓለምን እንደሚያጠፋት መነገሩና ጥቂት ሰዎች ብቻ እንደሚቀሩ መገለጹ

ምዕራፍ ፳፭፡- እግዚአብሔርን ማክበርና ማመስገን እንደሚገባ

-እግዚአብሔር በችግር የተጨነቁትን እንደሚያድን

ምዕራፍ ፳፮፡- ጌታ እግዚአብሔር የዘለዓለም አንባ ነውና በእርሱ መታመን እንደሚገባ

-የጻድቃን መንገድ የቀናች እንደምትሆን

-የእግዚአብሔር መንገድ የቀና እንደሆነ

-የእግዚአብሔርን ክብር እንዳያይ ኃጢአተኛን እንደሚያስወግዱት

-ሙታን እንደሚነሡ በመቃብር ያሉም እንደሚድኑ መነገሩ

ምዕራፍ ፳፯፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደሚያድን

ምዕራፍ ፷፮፡- እግዚአብሔር ለመልካሞች የተጎነጎነ ዘውድና የተስፋ አክሊል እንደሚሆን

-የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፷፱፡- የኃጥኣን ብልጽግና እንደደቀቀ ትቢያ እንደሆነ

-ነዳያን ደስታቸውን በእግዚአብሔር እንደሚያበዙ

ምዕራፍ ፸፡- በግብጽ መታመን ከንቱ እንደሆነ

-አምላካችን እግዚአብሔር ፈራጅ እንደሆነ

-እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ብፁዓን እንደሆኑ

ምዕራፍ ፸፩፡- እግዚአብሔር ጠቢብ እንደሆነ

-የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንደሚጋርዳት እንደሚታደጋት

ምዕራፍ ፸፪፡- ጻድቅ ንጉሥ እንደሚነግሥ

-ጻድቃን ጥበብን እንደሚመክሩና ምክራቸውም እንደምትጸና

ምዕራፍ ፸፫፡- ወንጀለኞች ብል እንደበላው ልብስ እንደሚያልቁ

-ጥበብና ምክር ጽድቅም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆኑ

-አምላካችን እግዚአብሔር ቸል እንደማይለን

-እግዚአብሔር አምላካችን፣ ፈራጃችንና ንጉሣችን እንደሆነ

ምዕራፍ ፸፬፡- በአሕዛብ ላይ መከራ እንደሚደርስ መነገሩ

ምዕራፍ ፸፭፡- የዳኑ ሰዎች ሐሴትና ደስታን እንደሚያደርጉ

ምዕራፍ ፸፮፡- ሰናክሬም ኢየሩሳሌምን ለመውረር እንደዛተና

ምዕራፍ ፸፯፡- ንጉሡ ሕዝቅያስ ማቅ ለብሶ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደገባ

-ሕዝቅያስ ነቢዩ ኢሳይያስን ምክር እንደጠየቀው

-የእግዚአብሔር መልአክ ከአሦራውያን 185000 ሰዎችን እንደገደለ

-ሰናክሬምን ልጆቹ እንደገደሉት

ምዕራፍ ፸፰፡- ሕዝቅያስ እንደታመመ

-ነቢዩ ኢሳይያስ ሕዝቅያስን ትሞታለህና ቤትህን አስተካክል እንዳለው

ምዕራፍ ፴፱፡- የባቢሎን ንጉሥ ሕዝቅያስ ታሞ እንደተፈወሰ በሰማ ጊዜ ደብዳቤና እጅ መንሻን ለሕዝቅያስ እንደላከለትና ሕዝቅያስም ደስ ብሎት ለመልእክተኞቹ በቤተ መዛግብቱ ያለውን እንዳሳያቸው

ምዕራፍ ፵፡- እግዚአብሔር ሕዝቤን አጽናኑ እንዳለ

-የሰው ክብሩ እንደ ሣር አበባ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ቃል ለዘለዓለም ጸንቶ እንደሚኖር

-እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉና የሚታገሡ ኃይላቸውን እንደሚያድሱ

ምዕራፍ ፵፩፡- እግዚአብሔር ፈተኛና ኃለኛ እንደሆነ

ምዕራፍ ፵፪፡- ስለ እስራኤል ባሏ ማልነት መገለጹ

-ለእግዚአብሔር አዲስ መዝሙር ዘምሩ መባሉ

ምዕራፍ ፵፫፡- ልዑል እግዚአብሔር ከእኔ በፊት አምላክ አልነበረም ከእኔም በኋላ አይኖርም ከእኔ ሌላ የሚያድን አምላክ የለም ብሎ መናገሩ

ምዕራፍ ፵፬፡- ከእግዚአብሔር ውጭ አምላክ እንደሌለ

ምዕራፍ ፵፭፡- ልዑል እግዚአብሔር ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም ማለቱ

-እግዚአብሔር እስራኤልን በዘለዓለማዊ መድኃኒት እንደሚያድነው መገለጹ

-ከእግዚአብሔር የሚርቁ ሁሉ እንደሚያፍሩ

ምዕራፍ ፵፮፡- ቤልና ዳጎን እንደተሰባበሩ

-እግዚአብሔር ይቅር እንደሚልና እንደሚታገሥ

ምዕራፍ ፵፯፡- ባቢሎን እንደምትወድቅ መነገሩ

ምዕራፍ ፵፰፡- እግዚአብሔር ዘለዓለማዊ እንደሆነ መናገሩ

-ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል መባሉ

ምዕራፍ ፵፱፡- እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ መገለጹ

ምዕራፍ ፶፡- ጆርባዬን ለግርፋት ጉንጩንም ለጽፋት ሰጠሁ ፊቴንም ከምራቅ ኀፍረት አልመለስኩም መባሉ

ምዕራፍ ፶፩፡- እስራኤላውያን ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃምና ወደ እናታችሁ ወደ ሣራ ተመልከቱ መባሉ

-ኢየሩሳሌም ሆይ ተነሺ ተነሺ መባሏ

ምዕራፍ ፶፪፡- እግዚአብሔር እስራኤልን እቤዣሻለሁ እንዳላት

ምዕራፍ ፶፫፡- እርሱ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፣ ሕማማችንንም ተሸከመ፣ ስለእኛም ታመመ፣ ስለኃጢአታችን ቆሰለ፣ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን እንደተባለ

ምዕራፍ ፶፬፡- እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚወዳት መገለጹ

ምዕራፍ ፶፭፡- እግዚአብሔር መሓሪ እንደሆነ

ምዕራፍ ፶፮፡- ሰንበታትን የሚጠብቅና እጁንም ክፋት ከማድረግ የሚጠብቅ ብፁዕ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ሕጉን ለሚጠብቁት ጃንደረቦቹ በቤቱ መታሰቢያ እንደሚያደርግላቸው

ምዕራፍ ፶፯፡- እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ እንደሚኖር፣ ለተዋረዱት ትዕግሥትን እንደሚሰጥ

-ለኃጥኣን ደስታ እንደሌላቸው

ምዕራፍ ፶፰፡- በጾም ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን መገለጹ

ምዕራፍ ፶፱፡- መቅሠፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ

-ከጽዮን ታዳጊ እንደሚመጣና ከያዕቆብም ኃጢአትን እንደሚያርቅ

ምዕራፍ ፷፡- ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር እንደምትከብርና በእርሱ ብርሃን እንደምታበራ

ምዕራፍ ፷፩፡- እስራኤላውያን እንደሚድኑ መገለጹ

-ጌታ እግዚአብሔር ጽድቅንና ደስታን በአሕዛብ ሁሉ ፊት እንደሚያበቅል

ምዕራፍ ፷፪፡- ስለጽዮን ዝም ማለት እንደማይገባ

ምዕራፍ ፷፫፡- ልዑል እግዚአብሔር ስለጽድቅ የምከራከር ስለማዳንም የምፈርድ እኔ ነኝ ማለቱ

ምዕራፍ ፷፬፡- እግዚአብሔርን በቸርነቱ የሚታገሡ መንገዱንም የሚያስቡ እንደሚገናኙት

ምዕራፍ ፷፭፡- አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚታይ

ምዕራፍ ፷፮፡- እግዚአብሔር ሰማይ ዙፋኔ ነው ምድር የእግሬ መረገጫ ናት እንዳለ

-አሕዛብ እንደሚጠፉ መነገሩ

ትንቢተ ኤርምያስ

ምዕራፍ ፩፡- ልዑል እግዚአብሔር ኤርምያስን በእናትህ ሆድ ሳልሠራህ አውቄሀለሁ ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሀለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሀለሁ እንዳለው

-እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ የኤርምያስን አፍ እንደዳሰሰና ቃሉን በአፉ እንዳደረገ

-እግዚአብሔር ኤርምያስን ወገብህን ታጠቅ ያዘዝሁህንም ሁሉ ንገራቸው እንዳለው

ምዕራፍ ፪፡- እስራኤል ለእግዚአብሔር ቅዱስ እንደነበረ

-እስራኤል ክብራቸውን ለማይረባ ነገር እንደለወጡ

-እግዚአብሔርን መተው ክፉና መራራ እንደሆነ

-እስራኤላውያን ጣዖትን እንዳመለኩና ለጣዖት እንደሠዉ

ምዕራፍ ፫፡- ጌታ እግዚአብሔር እስራኤልን በአመንዝራ ሴት መስሎ እንደተናገራት

-እግዚአብሔር እስራኤልን መሓሪና ዘለዓለም የማልቆጣ ነኝና ተመለሺ እንዳላት

-እግዚአብሔር እኔ እገዛችኋለሁና ተመለሱ እንዳለ

-እግዚአብሔር ቁስላችሁን እፈውሳለሁና ተመለሱ እንዳለ

-የእስራኤል መዳን በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው መባሉ

ምዕራፍ ፬፡- የልባችሁን ሸለፈት አስወግዱ መባሉ፣ ወደ ጽዮን ሽሹ መባሉ

-ኢየሩሳሌም ሆይ ትድኚ ዘንድ ልብሽን ከክፉ ነገር እጠቢ መባሏ

ምዕራፍ ፭፡- እስራኤላውያን ተግሣጽን እንቢ እንዳሉ

ምዕራፍ ፮፡- ኢየሩሳሌም በጠላት እንደተከበበች

-እስራኤላውያን ከሐሳዊ ነቢይ ጀምሮ እስከ ካህኑ ድረስ ሁሉም ሐሰትን እንዳደረጉ

-ሐሳውያን ነቢያት ሰላም ሳይሆን ሰላም ሰላም ይሉ እንደነበር

-በመንገድ ላይ ቁሙ መልካም የሆነችውን መንገድ ጠይቁና በእርሷ ሂዱ መባሉ

ምዕራፍ ፯፡- እግዚአብሔር መንገዳችሁንና ሥራችሁን አቅኑ ማለቱና በሐሰት ቃል በራሳችሁ አትታመኑ ማለቱ

-እስራኤላውያን ክፉ ቢሠሩ ክፉ ነገር እንደሚያገኛቸው መነገሩ

-እግዚአብሔር ኤርምያስን ለዚህ ሕዝብ አትጸልይ እንዳለው

ምዕራፍ ፮፡- እስራኤላውያን በክፋታቸው ምክንያት ለጨካኞች ተላልፈው እንደሚሰጡ

ምዕራፍ ፱፡- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ እንቢ ማለታቸው

-ጠቢብ በጥበቡ፣ ኃያል በኃይሉ፣ ባለጠጋ በባለጠጋነቱ መመካት እንደማይገባው

ምዕራፍ ፲፡- እግዚአብሔር የአሕዛብን መንገድ አትማሩ ከሰማይ ምልክት የተነሣም አትፍሩ ማለቱ

-እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፩፡- የእስራኤል ቤትና የይሁዳ ቤት ከአባቶቻቸው ጋር እግዚአብሔር ያደረገውን ቃል ኪዳን እንዳፈረሱ

-እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ መቅሠፍትን እንደሚያመጣ

ምዕራፍ ፲፪፡- እግዚአብሔር በእስራኤልና በይሁዳ ላይ መከራን እንደሚያመጣ

ምዕራፍ ፲፫፡- ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ እንደማይችል መነገሩ

ምዕራፍ ፲፬፡- እግዚአብሔር ስለእስራኤላውያን ቢጾሙም ቢጸልዩም ጾማቸውን ጸሎታቸውን አልሰማም አልቀበልም እንዳለ

-ሐሰተኛ ነቢያት እስራኤላውያንን በሐሰት ትንቢታቸው ማታለላቸው

-እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነቢያትን በሰይፍና በረኃብ እንደሚያጠፋቸው

ምዕራፍ ፲፭፡- እስራኤል እግዚአብሔርን ስለከዳችው እንደሚያጠፋት መናገሩ

-የእግዚአብሔር ቃል ሐሴትና የልብ ደስታ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፮፡- እስራኤላውያን ስለበደሉ እግዚአብሔር ሰላሜን ቸርነቴንና ምሕረቴን ከዚህ ሕዝብ አስወግጃለሁ ማለቱ

ምዕራፍ ፲፯፡- የይሁዳ ኃጢአት በብረት ብርዕ በደንጊያ ሰሌዳ እንደተጻፈ

-በእግዚአብሔር የሚታመን ተስፋውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ እንደሆነ

-እግዚአብሔር ልብንና ኩላሊትን እንደሚመረምር

-የመቅደሳችን ስፍራ ከጥንት ጀምሮ ከፍ ያለ የክብር ዙፋን እንደሆነ

-እግዚአብሔር ራሳችሁን ጠብቁ፣ በሰንበትም ቀን ምንም ሸክም አትሸከሙ ማለቱ

ምዕራፍ ፲፰፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ እንዳላቸው

-እስራኤላውያን በኤርምያስ ላይ ሴራ እንዳሴሩ

ምዕራፍ ፲፱፡- ኤርምያስ እስራኤላውያንን በተሰበረ ገንቦ መስሎ እንደተናገራቸው

ምዕራፍ ፳፡- ጳስኮር ኤርምያስን ትንቢት በመናገሩ እንደገረፈውና በአዘቅት ውስጥ እንደጣለው

-ኤርምያስ ጎዘኑን እንደገለጸ

ምዕራፍ ፳፩፡- ኢየሩሳሌም በባቢሎን ንጉሥ እንደምትያዝ መነገሩ

-ወደ ከለዳውያን የሚገባ በሕይወት እንደሚኖርና ሰውነቱም ምርኮ እንደምትሆን

ምዕራፍ ፳፪፡- ኤርምያስ ለይሁዳ ንጉሥና መኳንንት መልእክትን እንደተናገረ

-እግዚአብሔር ፍርድንና ጽድቅን አድርጉ ማለቱ

-ቤትን በዐመፅ መሥራት ባልንጀራንም በከንቱ ማሠራት እንደማይገባ

-እግዚአብሔር በኢዮአቄም ላይ እንደፈረደበት

ምዕራፍ ፳፫፡- እግዚአብሔር የማሰማርያቸን በጎች ለሚያጠፉና ለሚበትኑ እረኞች ወዮላቸው እንዳለ

-ክፉ እረኞችን በክፋትታቸው ምክንያት በክፉ እንደሚጎበኛቸው እግዚአብሔር መናገሩ

-ኤርምያስ በሐሰተኛ ነቢያት ላይ ትንቢት እንደተናገረ

-ልዑል እግዚአብሔር ቅርብ አምላክ እንጂ ሩቅ አምላክ አይደለሁም ማለቱ

ምዕራፍ ፳፬፡- እግዚአብሔር ለኤርምያስ የእስራኤልን ሚጠት በበለስ መስሎ እንዳሳየው

ምዕራፍ ፳፭፡- እስራኤል የነቢያትን ትንቢት ባለመስማታ እንደተማረከች

ምዕራፍ ፳፮፡- ሐሰተኛ ነቢያት፣ ካህናትና ሕዝቡ ኤርምያስን ለመግደል እንደያዙት

-ኤርምያስ ከእግዚአብሔር ተልኬ ነው የመጣሁ ባለ ጊዜ ሕዝቡ ሞት አይገባውም ማለታቸው

ምዕራፍ ፳፯፡- እስራኤላውያን ለባቢሎን እንደሚገዙ ኤርምያስ በቀንበር እንዳስረዳቸው

ምዕራፍ ፳፰፡- ሐሰተኛ ነቢያት የሐሰት ትንቢት ተናግረው ሕዝቡን እንዳታለሉ

-ነቢዩ ኤርምያስ ስለሰላም ትንቢት የተናገረ ነቢይ ትንቢቱ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር በእውነት የላከው ነቢይ እንደሆነ ይታወቃል ማለቱ

-ሐሰተኛው ነቢይ ሐናንያ እንደሞተ

ምዕራፍ ፳፱፡- ኤርምያስ በባቢሎን ለሚኖሩ እስራኤላውያን ደብዳቤ እንደላከ

-ወደ እርሷ ላስማረካችሁ ሀገር ሰላምን ፈልጉ ስለ እርሷም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ መባሉ

-የሐሰት ነቢያት፣ ሟርተኞች፣ ሕልም አላሚዎች አያታሏችሁ መባሉ

-ልዑል እግዚአብሔር ሰባው ዓመት በተፈጸመ ጊዜ እጎበኛችኋለሁ ማለቱ

ምዕራፍ ፴፡- ልዑል እግዚአብሔር እስራኤልን ከምርኮ እንደሚያድናቸው ተስፋን መስጠቱ

ምዕራፍ ፴፩፡- ልዑል እግዚአብሔር ለእስራኤል ወገኖች ሁሉ አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል እንዳለ

-ልዑል እግዚአብሔር ኤርምያስን በዘለዓለም ፍቅር ወድጄሃለሁ እንዳለው

-እግዚአብሔር ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ማለቱ

ምዕራፍ ፴፪፡- ኤርምያስ እንደጸለየ

ምዕራፍ ፴፫፡- እግዚአብሔር ኤርምያስን ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሀለሁ እንዳለው

ምዕራፍ ፴፬፡- ኤርምያስ በሴዴቅያስ ላይ ትንቢት እንደተናገረ

ምዕራፍ ፴፭፡- እግዚአብሔር እያንዳንዳችሁ ከክፉ መንገድ ተመለሱ እንዳለ

ምዕራፍ ፴፮፡- የኔርዩ ልጅ ባሮክ ነቢዩ ኤርምያስ ያዘዘውን ሁሉ እንዳደረገና በእግዚአብሔርም ቤት የእግዚአብሔርን ቃል በመጽሐፍ እንዳነበበ

-በእግዚአብሔር ፊት ለመጾም አዋጅ እንደተነገረ

-የይሁዳ ንጉሥ የኤርምያስን ቃል የያዘውን ደብዳቤ እንዳቃጠለው

ምዕራፍ ፴፯፡- የኢዮስያስ ልጅ ሴዴቅያስ በኢዮአቄም ልጅ በኢኮንያን ፋንታ እንደነገሠ

ምዕራፍ ፴፰፡- ኤርምያስ ወደ ከለዳውያን የሚወጡ በሕይወት እንደሚኖሩ ትንቢት መናገሩ

-ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርምያስን ከተጣለበት ጉድጓድ እንዳወጣው

-ኤርምያስ ንጉሥ ሴዴቅያስን እኔ የምነግርህን የእግዚአብሔርን ቃል ስማ ለአንተም ይሻልሀል። ነፍስህም በሕይወት ትኖራለች እንዳለው

ምዕራፍ ፴፱፡- ናቡከደነፆርና ሠራዊቱ ሁሉ ኢየሩሳሌምን ከበው እንደያዟት

-ናቡከደነፆር የንጉሡን የሴዴቅያስን ልጆች በፊቱ እንደገደላቸው፣ የሴዴቅያስንም ዓይን እንዳወጣና በሰንሰለትም አስሮ ወደ ባቢሎን እንደወሰደው

-ከለዳውያን የእስራኤላውያንን ቤቶቻቸውን እንዳቃጠሉ

-ናቡከደነፆር ነቢዩ ኤርምያስን በመልካም እንዲመለከቱት ለሠራዊቱ መንገሩ

ምዕራፍ ፵፡- የከለዳውያን የአዛዦች አለቃ ለኤርምያስ ስንቅና ስጦታ ሰጥቶ እንዳሰናበተው

ምዕራፍ ፵፩፡- እስማኤል ከጎዶልያስ ጋር በመሴፋ የነበሩትን አይሁድና ከለዳውያን እንደገደላቸው

ምዕራፍ ፵፪፡- ሕዝቡ ኤርምያስን ስለእኛ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን እንዳሉት

ምዕራፍ ፵፫፡- ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ እንደተናገረ

-እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ስላልሰሙ ወደ ግብፅ ምድር እንደገቡ

ምዕራፍ ፵፬፡- እስራኤላውያን የኤርምያስን ቃል አንሰማም ማለታቸውና ለሰማይ ንግሥት እናጥናለን ማለታቸው

ምዕራፍ ፵፭፡- እግዚአብሔር ለባሮክ ስለ እስራኤላውያን መንገሩ

ምዕራፍ ፵፮፡- የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ግብፅን እንደሚመታት ትንቢት መነገሩ

ምዕራፍ ፵፯፡- እግዚአብሔር በናቡከደነፆር አማካኝነት ፍልስጥኤማውያንን እንደሚያጠፋ

ምዕራፍ ፵፰፡- ሞዓብ እንደምትጠፋ ትንቢት መነገሩ

-የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን መባሉ

ምዕራፍ ፵፱፡- አሞን በመከራ እንደምትፈተን

ምዕራፍ ፶፡- ባቢሎን እንደምትወድቅ ትንቢት መነገሩ

ምዕራፍ ፶፩፡- እግዚአብሔር በባቢሎናውያንና በከለዳውያን ላይ የሚያቃጥል ነፋስን አስነሣለሁ እንዳለ፣ እንዲሁም ተሳዳቢ ሰዎችን ሰድጄ አሰድባታለሁ ማለቱ

-ከባቢሎን መካከል ሽሹ እያንዳንዳችሁም ነፍሳችሁን አድኑ መባሉ

-ኑ በጽዮን የአምላካችን የእግዚአብሔርን ሥራ እንናገር መባሉ

-ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፣ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ፣ ሰማያትን በማስተዋሉ የዘረጋ፣ ከምድር ዳር ደመናትን የሚያመጣ፣ ለዝናብም ጊዜ መብረቅን የሚያደርግ፣ ነፋስን ከቤተ መዛግብቱ የሚያወጣ እግዚአብሔር እንደሆነ

ምዕራፍ ፶፪፡- ኢየሩሳሌም እንደምትወድቅ ትንቢት መነገሩ

መጽሐፈ ባሮክ

ምዕራፍ ፩፡- ባሮክ በባቢሎን በሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ ጆሮ መጽሐፍ ባነበበላቸው ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንዳለቀሱ፣ እንደጾሙና እንደጸለዩ

-ሕዝቡ አምላካችንን በድለናልና መዓቱ እንዲርቅልን ጸልዩልን ማለታቸው

ምዕራፍ ፪፡- እስራኤላውያን ቀድሞ በሠሩት ክፉ ሥራ እንደተጸጸቱና በደላቸውን እንዳመኑ

-ሕዝቡ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ባዘዘው ሥራው ሁሉ ጻድቅ ነው ማለታቸው

ምዕራፍ ፫፡- እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር እንደጸለዩ

-በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ለዘለዓለም በሰላም እንደሚያኖር

ምዕራፍ ፬፡- ክብርን ለባዕድ መስጠት እንደማይገባ

-እስራኤላውያን መጽናናት እንደሚገባቸው

ምዕራፍ ፭፡- ኢየሩሳሌም የኀዘንና የመከራሽን ልብስ ከአንቺ አውልቂው መባሏ

-ኢየሩሳሌም የክብር ጌጥሽንና የክብር ዘውድሽን በራስሽ ተቀዳጂ መባሏ

ሰቆቃወ ኤርምያስ

ምዕራፍ ፩፡- እስራኤልን ማርከው ኢየሩሳሌምን ካጠፏት በኋላ ኤርምያስ ተቀምጦ ስለ ኢየሩሳሌም ያለቅስ እንደነበር

-እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነ መነገሩ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ላይ ስላመጣው ቅጣት መነገሩ

ምዕራፍ ፫፡- ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ምሕረት ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው መባሉ

-እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር እንደሆነ

-እግዚአብሔር ዝም ብላ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ለምታደርግ ነፍስ መልካም እንደሆነ

-መንገዳችንን እንመርምርና እንፈትን ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ መባሉ

ምዕራፍ ፬፡- እስራኤላውያን በመከራ እንደተሰቃዩ

ምዕራፍ ፭፡- ምሕረትን ለማግኘት ኤርምያስ እንደጸለየ

ተረፈ ኤርምያስ

-እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ይነግሯቸው ዘንድ የባቢሎን ንጉሥ ማርኮ ወደ ባቢሎን ወደ ወሰዳቸው ሰዎች ኤርምያስ የላከው መጽሐፍ ግልባጭ ይህ ተረፈ ኤርምያስ እንደሆነ

-እስራኤላውያን እግዚአብሔርን "ስግደት ለአንተ ይገባል" ሊሉት እንደሚገባ

-ጣዖታትን መፍራት እንደማይገባ መነገሩ፣ ጣዖታት ምንም ማድረግ የማይችሉ ደካሞች እንደሆኑ

-ለጣዖታት ምግብ ማቅረብ ለሞተ ሰው ምግብ እንደማቅረብ እንደሆነ

ተረፈ ባሮክ

ምዕራፍ ፩፡- ኤርምያስ ጳስኮርን በዘመናችሁ ሁሉ ጽድቅን ትቃረኢታላችሁ እንዳለው

-አይሁድ የተናቀች ኃጢአትን እንደሠሩ፣ ዋጋ የማይገኝለትን እንደሚሸጡ፣ ሕማማትን የሚያስወግደውን እንዲታመም እንደሚያደርጉት

-ሕዝቡ በሳቱ ጊዜ ኤርምያስ ያዝን እንደነበር፣ በራሱም ላይ ትቢያን ይነሰንስ እንደነበር

ምዕራፍ ፪፡- ጌታ ከወዳጁ ከኤርምያስ ጋራ እስክነጋገር ድረስ ከተማዪቱን አታጥፉ ብሎ ለመላእክት እንደነገራቸው

-ኤርምያስ ስለ አቤሜሌክ ከእግዚአብሔር ዘንድ መለመኑ

ምዕራፍ ፫፡- ኤርምያስ በለስ ያለባትን ሙዳይ ተንተርሶ ስድሳ ስድስት ዓመት እንደተኛ

-አቤሜሌክ ከእንቅልፉ ሲነቃ ሀገሪቱ ተለውጣበት እንደደነገጠ

-ሸማግሌው አቤሜሌክን አምላክ ወደ ሰማያዊት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ይምራህ ብሎ እንደመረቀው

ምዕራፍ ፬፡- አቤሜሌክ ከከተማ ወደ ውጭ ከወጣ በኋላ ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየ

-ንስር ባሮክን ሃይማኖትን የምታስተምር ባሮክ ሆይ ቸር አለህን እንዳለው

-ባሮክ በንስሩ አንገት አድርጎ ደብዳቤና አቤሜሌክ ያመጣውን በለስ ወደ ኤርምያስ እንደላከ

ምዕራፍ ፭፡- ንስሩ ደብዳቤውን ለኤርምያስ እንደሰጠው፣ ንስሩ ሬሳውን ቢረግጠው ሬሳው እንደተነሣ

-ኤርምያስ ለባሮክ ልጄ ወደ ጎዳናችን ይመራን ዘንድ ለአምላካችን እየተገዛህ ስለእኛ መጸለይን ቸል አትበል ብሎ በንስሩ ደብዳቤ እንደላከለት

-ኤርምያስ ሕዝቡ የባቢሎንን አሕዛብ ርኩሰት እንዳይሠሩ እያስተማራቸው እንደተቀመጠ

-ከባቢሎን ሴት ያገባ ወይም ባል ያገባች ወደ ኢየሩሳሌም አይገባም ብለው ኤርምያስ፣ ባሮክና አቤሜሌክ መናገራቸው

-ያገቡ ሰዎች በኢየሩሳሌም አውራጃ ከተማ አቅንተው ሰማርያ እንዳሏት

-የጽድቅ ሊቀ መላእክት ሚካኤል በእውነት አመስጋኝ ነው መባሉ

-በአንድ ቃል አመስግኑት፣ ሁላችሁም የአምላክን ልጅ መሢሑን አመስግኑት፣ የዓለሙ ሁሉ ብርሃን የአምላክ ልጅ ኢየሱስ ይፈርድባችኋል መባሉ

-ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ለመምጣት ሦስት መቶ ሠላሳ ሦስት የቀን ሱባኤ ይሆናል መባሉ

-እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ መነገሩ

-ኤርምያስ የአምላክን ልጅ አምላክን አየሁት ማለቱ

-ባሮክና አቤሜሌክ ለኤርምያስ ድንጋይ እንዳመጡለት፣ ጸልዮም ያ ድንጋይ ራሱን ኤርምያስን እንዲመስል እንዳደረገው፣ አይሁድም ድንጋዩ ኤርምያስን መስሏቸው ድንጋዩን በድንጋይ ሲደበድቡ እንደዋሉ

-ኤርምያስ ለባሮክና ለአቤሜሌክ የሚነግራቸውን ምሥጢር ከጨረሰ በኋላ በሕዝቡ መካከል እንደተገኘ እና በድንጋይ ወግረው እንደገደሉት

-አቤሜሌክና ባሮክ ኤርምያስን ቀድሞ ኤርምያስን እንዲመስል በተደረገው ድንጋይ እንደቀበሩትና በውስጡም የኤርምያስ ረዳቱ እነሆ ይህ ድንጋይ ነው ብለው እንደጻፉበት

ትንቢተ ሕዝቅኤል

ምዕራፍ ፩፡- ሕዝቅኤል በኮቦር ወንዝ የእግዚአብሔርን ራእይ እንዳየ

-ሕዝቅኤል በራእይ ኪሩቤልን እንደተመለከተ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአበሔር ለሕዝቅኤል እስራኤላውያንን አትፍራቸው እንዳለው

-እንደ እስራኤላውያን ዐመፀኛ መሆን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፫፡- ሕዝቅኤል ይህን መጽሐፍ ብላ መባሉ

-እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ለእስራኤላውያን ጉበኛ አድርጌሀለሁ እንዳለው

-ሕዝቅኤል እስራኤላውያንን እንዲገሥጽ መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- ኢየሩሳሌም በጠላት እንደምትከበብ ለሕዝቅኤል በራእይ መገለጡ

ምዕራፍ ፭፡- በኢየሩሳሌም ስለሚደርሰው መከራ መነገሩ

ምዕራፍ ፮፡- እግዚአብሔር ጣዖታትን፣ የጣዖታት መስገጃዎችንና መሠዊያዎችን እንደሚያጠፋ

ምዕራፍ ፯፡- በእስራኤል ላይ መከራ እንደሚደርስ

ምዕራፍ ፰፡- እስራኤላውያን ለጣዖት ይሰግዱ እንደነበር

ምዕራፍ ፱፡- እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ መዓትን እንደሚያመጣ ለሕዝቅኤል መንገሩ

ምዕራፍ ፲፡- ስለኪሩቤል ሕዝቅኤል ራእይ ማየቱ

-የእግዚአብሔር ክብር በኪሩቤል ላይ እንደተቀመጠ

ምዕራፍ ፲፩፡- እስራኤላውያን በአሕዛብ ሕግ እንጂ በእግዚአብሔር ሕግ ስላልኖሩ መከራ እንደሚደርስባቸው መነገሩ

ምዕራፍ ፲፪፡- ሕዝቅኤል ስደተኛ መስሎ ለሕዝቡ እንዲታይ መነገሩና ሕዝቅኤልም "እኔ ምልክታችሁ ነኝ እኔ እንዳደረግሁ እንዲሁ ይደረግባቸዋል። እነርሱንም ማርከው ይወስዷቸዋል" እንዳለ።

-ጌታ እግዚአብሔር የምናገረው ቃል ይፈጸማል እንጂ ከቃሌ ሁሉ የሚዘገይ የለም እንዳለ

ምዕራፍ ፲፫፡- ፈጽሞ ሳያዩ ከገዛ ልባቸው አንቅተው ትንቢት ለሚናገሩ ወዮላቸው መባሉ

-እግዚአብሔር ሳይልካቸው እግዚአብሔር ይላል የሚሉ ሰዎች ሐሰትን እንደሚያዩ፣ ከንቱን እንደሚያሟርቱ

-እግዚአብሔር እጁ ሐሰተኛ ራእይን በሚያዩ፣ ሕዝቤንም ለማታለል በከንቱ በሚያሟርቱ ነቢያት ላይ ትሆናለች እንዳለ

-ሐሰተኛ ነቢያት ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ ሕዝቡን በማታለላቸው እንደሚወድቅ

ምዕራፍ ፲፬፡- ልዑል እግዚአብሔር "ከእስራኤል ቤት ጣዖቶቹን በልቡ የሚያኖር፣ የበደሉንም መቅሠፍት በፊቱ የሚያቆም ሰው ሁሉ ወደ ነቢዩ ቢመጣ እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖቱ ብዛት እመልስለታለሁ" እንዳለ

-ጌታ እግዚአብሔር ንስሓ ግቡ፣ ከበደላችሁም ተመለሱ፣ ፊታችሁንም ከኃጢአታችሁ መልሱ ማለቱ

ምዕራፍ ፲፭፡- የእስራኤላውያን መከራ በሚቃጠል የወይን ግንድ ተመስሎ እንደተነገረ

ምዕራፍ ፲፮፡- ሕዝቅኤል ለኢየሩሳሌም ኃጢአቷን አስታውቃት መባሉ

-እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም ስላደረገላት ነገር በዝርዝር መናገሩ

-ኢየሩሳሌም ግን በተሰጣት ጸጋና በስሟ እንዳመነዘረች፣ እግዚአብሔር ያለበሳትን ልብስ ለጣዖታት ማልበሷ፣ እግዚአብሔር ከሰጣት ወርቅ ጣዖት መሥራቷ

-እግዚአብሔር ኢየሩሳሌም ላይ ስለሚያመጣው መከራ መናገሩ

-የሰዶም ኃጢአት ትዕቢት፣ እንጀራን መጥገብ፣ መዘለልና ሥራን መፍታት እንደነበረ

ምዕራፍ ፲፮:- ጌታ እግዚአብሔር እኔ ሕያው ነኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፯:- እግዚአብሔር እነሆ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው ማለቱ

-ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እንደምትሞት መነገሩ

-እግዚአብሔር ሰው እንደ ትእዛዜ ቢሄድ እርሱ ጻድቅ ነው ፈጽሞ በሕይወትም ይኖራል ማለቱ

-ልጅ የአባቱን ኃጢአት አባትም የልጁን ኃጢአት እንደማይሸከም

-ኃጢአተኛ ካደረጋት ኃጢአት ቢመለስና ትእዛዘ እግዚአብሔርን ቢጠብቅ ፈጽሞ በሕይወት እንደሚኖርና እንደማይሞት መነገሩ፣ የበደለው በደልም እንደማይታሰብበት

-እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ እንጂ ይሞት ዘንድ እንደማይፈቅድ

-ጻድቅ ከጽድቁ ቢመለስና ኃጢአትንም ቢሠራ ቀድሞ የሠራው ጽድቅ ሁሉ እንደማይታሰብለትና በሠራው ኃጢአት እንደሚሞት መነገሩ

-አዲስ ልብና አዲስ መንፈስን ለእናንተ አድርጉ መባሉ

ምዕራፍ ፲፱:- እስራኤልንና ኢየሩሳሌምን በአንበሳ፣ በጽጌረዳ መስሎ እንደተናገረ

ምዕራፍ ፳:- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በቀልን እንደሚበቀላቸው መናገሩ

ምዕራፍ ፳፩:- እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስለሚያመጣው መከራ መነገሩ

-ሕዝቅኤል ስለእስራኤል ወገብህን በማጕበጥ አልቅስ፣ በፊታቸውም ምርር ብለህ አልቅስ መባሉ

ምዕራፍ ፳፪:- ሕዝቅኤል የእስራኤልን ርኵሰቷን አስታውቃት መባሉ

-እስራኤላውያን የበደሉት በደል በዝርዝር መገለጹ

ምዕራፍ ፳፫:- ሁለቱ ነገድና አሥሩ ነገድ በአመንዝራ ሴት ተመስለው መነገራቸው

ምዕራፍ ፳፬:- እስራኤል በዛገች ድስት እንደተመሰለች

ምዕራፍ ፳፭:- በአሞን ላይ፣ በሞዓብ ላይ፣ በኤዶም ላይ፣ በፍልስጥኤም ላይ ትንቢት እንደተነገረ

ምዕራፍ ፳፮፡- በጢሮስ ላይ ትንቢት እንደተነገረ

ምዕራፍ ፳፯፡- ስለጢሮስ ዝርዝር ነገር መነገሩ

ምዕራፍ ፳፰፡- በጢሮስ ንጉሥ ላይ ስለተነገረ ትንቢት

ምዕራፍ ፳፱፡- ስለ ግብፅ ትንቢት መነገሩ

-ናቡከደነፆር ግብፅን ድል እንዳደረገ

ምዕራፍ ፴፡- ጌታ ግብፅን እንደሚቀጣ መናገሩ

ምዕራፍ ፴፩፡- አሦርም ግብጽም በዝግባ እንደተመሰሉ

ምዕራፍ ፴፪፡- ሕዝቅኤል ስለ ግብጽ ንጉሥ ስለፈርዖን ሙሾ አሙሽ መባሉ

-በፈርዖን የባቢሎን ንጉሥ እንደሚመጣበት መነገሩ

ምዕራፍ ፴፫፡- ጉበኛ በምድር ላይ የመጣውን ጦር ባየ ጊዜ መለከትን ቢነፋ፣ ሕዝቡንም ቢያስጠነቅቅ፣ የመለከቱን ድምፅ የሚሰማ ሰው ባይጠነቀቅና ጦር መጥቶ ቢወስደው ደሙ በራሱ በሕዝቡ ላይ እንደሚሆን

-ጉበኛ ጦር ሲመጣ ቢያይና መለከቱን ባይነፋ በዚህም ምክንያት ጦር መጥቶ ሰው ቢያጠፋ እግዚአብሔር ደሙን ከጉበኛው እጅ እንደሚፈልግ መነገሩ

-እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የእስራኤል ጉበኛ አድርጌሀለሁ እንዳለው

-ጉበኛ ሕዝቡን አስጠንቅቆት ሳለ ሕዝቡ ሳይሰማው ቢቀር እርሱ ነፍሱን እንዳዳነ፣ ሕዝቡ ደግሞ ጉበኛ የነገረውን ሰምቶ ባይጠነቀቅ በኃጢአቱ እንደሚሞት መነገሩ

-በበደለበት ቀን የጻድቅ ጽድቁ እንደማያድነው

-ኃጢአተኛ ከኃጢአቱ በተመለሰበት ቀን በኃጢአቱ እንደማይሰናከል

-ጻድቅ ከጽድቁ ተመልሶ ኃጢአት ቢሠራ እንደሚሞትበት

-ኃጥእ ከኃጢአቱ ተመልሶ ፍርድንና ጽድቅን ቢያደርግ በሕይወት እንደሚኖርበት

-ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ እንደወደቀች

ምዕራፍ ፴፬፡- ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው መባሉ

-ወተታቸውን እየጠጡ፣ ጸጕራቸውን እየለበሱ በጎችን ለማያሰማሩ እረኞች ወዮታ እንዳለባቸው

-እግዚአብሔር በጎቹ እረኛ በማጣት ተበተኑ ለዱርም አራዊት ሆኑ እንዳለ

-እግዚአብሔር እኔ ራሴ በጎቼን እሻለሁ እጎበኛቸዋለሁም እንዳለ

-እግዚአብሔር በጊዜው ዝናብን እንደሚያወርድ መናገሩ

ምዕራፍ ፴፫፡- በኤዶምያስ ላይ ትንቢት እንደተነገረ

ምዕራፍ ፴፬፡- እስራኤላውያን የጌታ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እንደተባሉ

-እግዚአብሔር እስራኤልን እንደሚባርክ መናገሩ

-እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን አዲስ ልብን እሰጣችኋለሁ እንዳላቸው

ምዕራፍ ፴፯፡- ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር እጅ በላዩ ነበረ በመንፈሱም አወጣኝ ማለቱ

-የደረቁ አጥንቶች ሥጋን ለብሰው ነፍሳቸው ተመልሳ እንደሚነሡ መናገሩ

-ይሁዳና እስራኤል አንድ ሀገር እንደሚሆኑ መናገሩ

ምዕራፍ ፴፰፡- ስለ ጎግ ሠራዊት መናገሩ

ምዕራፍ ፴፱፡- ጎግና ሠራዊቱ እንደሚወድቁ መናገሩ

-እስራኤላውያን እንደገና እንደሚቋቋሙ

ምዕራፍ ፵፡- ለሕዝቅኤል አዲስ ስለሚሠራው ቤተ መቅደስ በራእይ እንደተገለጸለት

ምዕራፍ ፵፩፡- ሕዝቅኤል ስለቤተ መቅደሱ ቅድስተ ቅዱሳንና ሌሎችም ክፍሎች ራእይ እንዳየ

ምዕራፍ ፵፪፡- ሕዝቅኤል ስለ ቤተ መቅደስ ተጨማሪ ራእይ እንዳየ

ምዕራፍ ፵፫፡- የእግዚአብሔር የክብሩ ብርሃን ለሕዝቅኤል እንደተገለጸ

-ስለ ቤተ መቅደሱ የመሠዊያ አሠራር መገለጹ

ምዕራፍ ፵፬፡- በምሥራቅ በኩል የነበረው ደጅ ተዘግቶ እንደነበርና ተዘግቶ እንደሚኖርም መገለጹ

-በቤተ መቅደስ ስለሚያገለግሉ ካህናት መነገሩ

ምዕራፍ ፵፭፡- ስለ ምድረ እስራኤል ርስት አከፋፈል መነገሩ

-ስለ መሥዋዕት አቀራረብ መነገሩ

ምዕራፍ ፵፮፡- ስለበዓላትና ስለአከባበራቸው መነገሩ

-ስለ ርስት መነገሩ

ምዕራፍ ፵፯፡- ከቤተ መቅደሱ በሚፈስ ምንጭ አምሳል ሕዝቅኤል ራእይ እንዳየ መነገሩ

-ስለምድረ እስራኤል ወሰን መነገሩ

ምዕራፍ ፵፰፡- ስለ ምድረ እስራኤል አከፋፈል መነገሩ

-ስለ ኢየሩሳሌም የቅጽር በሮች መነገሩ

ትንቢተ ዳንኤል

ምዕራፍ ፩፡- የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተኛው ዓመት የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ እንደከበባት

-የይሁዳው ንጉሥ ኢዮአቄም እንደተማረከ

-ንጉሥ ናቡከደነፆር እነ ዳንኤልንም ማርኮ ወስዶ ከሦስቱ ደቂቅ ጋር እንዲማር እንዳደረገ

-ዳንኤልና ሦስቱ ደቂቅ የንጉሡን የናቡከደነፆርን መዓድ አንበላም ማለታቸው

-እግዚአብሔር እነዳንኤልን በትምህርትና በጥበብ በዕውቀትና በማስተዋል ከፍ እንዳደረገ

ምዕራፍ ፪፡- ናቡከደነፆር ሕልም አልሞ ሕልሙን እንደዘነጋው

-ሕልም ተርጓሚዎች የናቡከደነፆርን ሕልም ማወቅ እንደተሳናቸውና በዚህም ምክንያት እንዲገደሉ ትእዛዝ መተላለፉ

-የናቡከደነፆር ሕልም ከነትርጉሙ ለዳንኤል እንደተገለጸለትና ዳንኤልም እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ

-ዳንኤል የናቡከደነፆርን ሕልም ከነትርጉሙ ለናቡከደነፆር እንደነገረው

-ናቡከደነፆር ያየው ሕልም ምስሉን ከረጅም ተራራ ድንጋይ መጥቶ ሲፈጨው እንደሆነ

-ሕልሙን ስለተረጎመለት ናቡከደነፆር ለዳንኤል እንደሰገደና ፈጽሞ እንዳከበረው

ምዕራፍ ፫፡- ናቡከደነፆር ቁመቱ ስድሳ ክንድ ወርዱ ስድስት ክንድ የሆነ የወርቅ ምስል እንዳሠራ

-ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል ሕዝቡ እንዲሰግድ መነገሩ

-ሠለስቱ ደቂቅና ዳንኤል ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል አንሰግድም ማለታቸው

-እነ ዳንኤል ወደ እሳት እንደተጣሉና እግዚአብሔር ከእሳቱ እንዳዳናቸው

-በእሳቱ መካከል ሆነው እነ ዳንኤል እግዚአብሔርን ማመስገናቸው

-ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ መገለጹ

-ናቡከደነፆር እነ ዳንኤል ከእሳት መዳናቸውን አይቶ በእነርሱ አምላክ ማመኑ

ምዕራፍ ፩፡- ናቡከደነፆር እግዚአብሔር መንግሥቱ ዘለዓለም ግዛቱም ለልጅ ልጅ እንደሆነ መናገሩ

-ናቡከደነፆር ሌላ ሕልም እንዳየና ዳንኤልም እንደተረጎመለት

-ናቡከደነፆር የእግዚአብሔርን ንጉሥነት እስኪረዳ አውሬ ሆኖ እንደቆየ

ምዕራፍ ፪፡- ብልጣሶር በንዋየ ቅድሳት ስለበላባቸው እንደተቀሠፈ

-ዳንኤል ማኔ ቴቄል ፋሬስ የሚለውን በሰው እጅ የተጻፈ ቃል ለብልጣሶር መተርጎሙ

ምዕራፍ ፫፡- ንጉሥ ዳርዮስ ዳንኤልን በመንግሥቱ ላይ ሁሉ እንደሾመው

-ሌሎች መሳፍንት በዳንኤል ላይ ሴራ እንዳሴሩበት

-ዳንኤል በሦስት ሰዓት ተንበረክኮ በአምላኩ ፊት ይጸልይ እንደነበር

-ዳንኤል ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንደተጣለ

-እግዚአብሔር የአንበሶችን አፍ እንደዘጋና አንበሶች ዳንኤልን እንዳልጎዱት

-ዳንኤል ከአንበሶች ጉድጓድ እንደወጣና ዳንኤልን ወደጉድጓድ ያስጣሉ ሰዎች ደግሞ ወደ ጉድጓድ ተጥለው በአንበሶች እንደተበሉ

-ዳርዮስ ሕዝቡ በዳንኤል አምላክ እንዲያምን ትእዛዝ ማስተላለፉ

ምዕራፍ ፯፡- ዳንኤል በአራዊት አምሳል ልዩ ልዩ ራእዮችን እንዳየ

-ዳንኤል በራእዩ የሰው ልጅ መጥቶ መንግሥት እንደተሰጠውና መንግሥቱም የማይጠፋ እንደሆነ ማየቱ

ምዕራፍ ፰፡- ዳንኤል በአውራ በግና በፍየል አምሳል ራእይ እንዳየ

-ቅዱስ ገብርኤል ለዳንኤል ራእዩን እንደገለጸለት

ምዕራፍ ፱፡- ዳንኤል እንደጸለየ

-አምላካችን እግዚአብሔር በሚሠራው ሥራ ሁሉ ጻድቅ እንደሆነ

-መልአኩ ገብርኤል ዳንኤልን እንዳስተማው

-ከሰባ ሁለት ሱባኤ በኋላ መሢሕ እንደሚገደል መነገሩ

ምዕራፍ ፲፡- ዳንኤል በጤግሮስ ወንዝ አጠገብ ራእይ እንዳየ

-ዳንኤል ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳው እንደመጣ መናገሩ

ምዕራፍ ፲፩፡- የተለያዩ ነገሥታት እንደሚነግሡ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፪፡- ስለ ዓለም ፍጻሜ እና ስለዳግም ትንሣኤ መነገሩ

-ብዙ ሰዎች እንደሚመረምሩና ዕውቀትም እንደሚበዛ መነገሩ

-ክፉዎች እንደማያስተውሉና ጥበበኞች ግን እንደሚያስተውሉ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፫፡- ሶስና እጅግ መልከ መልካምና እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት እንደነበረች

-በሶስና ላይ ሁለት ረበናት በሐሰት እንደመሰከሩባት

-ሶስና ረበናትን በእግዚአብሔር ፊት ከምበድል ኃጢአት ሳልሠራ በእጃችሁ መውደቅ ይሻለኛል እንዳለቻቸው

-የረበናት ነገራቸው እንደተለያየና በዚህም ምክንያት እንደተገደሉ

ምዕራፍ ፲፬፡- የባቢሎን ሰዎች የሚያመልኩት ቤል የሚባል ጣዖት እንደነበረ

-ዳንኤል ለፈጣሪው ይሰግድ እንደነበር

-ቂሮስ ቤል ይበላል ብለው ያታለሉትን የቤልን ካህናት እንደገደላቸው

-ዳንኤል ቤል የተባለውን ጣዖት እንደሰባበረውና ቤቱንም እንዳፈረሰው

-የባቢሎን ሰዎች የሚያመልኩት ታላቅ ዘንዶ እንደነበረና በኋላ ዳንኤል እንደገደለው

-ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ ሳለ ነቢዩ ዕንባቆም በመልአኩ አሳሳቢነት ምግብ ይዞለት እንደሄደ

ትንቢተ ሆሴዕ

ምዕራፍ ፩፡- ሆሴዕ ትንቢቱን በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያንና በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስም ዘመን በእስራኤል ንጉሥ በኢዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን መናገሩ

-እግዚአብሔር ነቢዩ ሆሴዕን ዘማዊቱንና የዘማዊቱን ልጅ ለአንተ ውሰድ እንዳለው

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ መከራን እንደሚያመጣ መናገሩ

-እግዚአብሔር ለእስራኤል በኋላ ይቅርታን እንዳደረገላት

ምዕራፍ ፫፡- እስራኤላውያን ከመከራ በኋላ እግዚአብሔርንና ቸርነቱን እንደሚያስቡ መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ መባላቸው

-እስራኤላውያን በክፋታቸው ውርደትን እንደመረጡ

ምዕራፍ ፭፡- እስራኤላውያን ጣዖት እንዳመለኩ

ምዕራፍ ፮፡- እስራኤላውያን በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንደሚገሠግሡ መነገሩ

-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደሚያድን መነገሩ

-እግዚአብሔር ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅን እንደሚወድ መናገሩ

ምዕራፍ ፯፡- ነገሥታቱ በክፋታቸው አለቀቹም በሐሰታቸው ደስ እንደተሰኙ

-እስራኤላውያን በክፋት እንደጸኑና እግዚአብሔርም እንደገሠጻቸው

ምዕራፍ ፰፡- እስራኤላውያን ደግነትን ስለጣሉ ጠላት እንዳሳደዳቸው

-እግዚአብሔር በኃጢአታቸው ምክንያት እስራኤላውያንን እንደሚበቀላቸው መነገሩ

ምዕራፍ ፱፡- እስራኤላውያን ክፋትን አብዝተው እንደሠሩ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፡- እስራኤላውያን የሐሰትን ቃል እንደሚናገሩ

ምዕራፍ ፲፩፡- እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚወድ መነገሩ

-እግዚአብሔር እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁም እንዳለ

ምዕራፍ ፲፪፡- ኤፍሬም ክብርንና ከንቱ ነገርን የሚያሳድድ ክፉ ጋኔን ነው መባሉ

-ዘወትር ወደ አምላክ መቅረብ እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፫፡- እግዚአብሔር ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ማለቱ

-እግዚአብሔር እስራኤልን እንደተቆጣ

ምዕራፍ ፲፬፡- እስራኤል ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ መጠራታቸው

-የእግዚአብሔር መንገዶች ቀናዎች እንደሆኑና ጻድቃን እንደሚሄዱባቸው ኃጥኣን ግን እንደሚወድቁባቸው መነገሩ

ትንቢተ አሞጽ

ምዕራፍ ፩፡- እግዚአብሔር ከጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንደሚናገር፣ ከኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን እንደሚሰጥ መነገሩ

-የተለያዩ ሀገሮች ኃጢአትን በመሥራታቸው እግዚአብሔር መቅሠፍትን እንደሚያመጣባቸው መናገሩ

ምዕራፍ ፪፡- የእግዚአብሔርን ሕግ ስላፈረሱ እግዚአብሔር በይሁዳ መከራን እንደሚያመጣ መናገሩ

ምዕራፍ ፫፡- ጌታ እግዚአብሔር ለባርያዎቹ ለነቢያት ያልነገረውን ምንም እንደማያደርግ መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- እስራኤላውያን ጣዖት በማምለክ እግዚአብሔርን እንዳሳዘኑ

ምዕራፍ ፭፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እኔን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ እንዳላቸው

-ክፉዉን ጥሉ መልካሙንም ውደዱ መባሉ

ምዕራፍ ፮፡- ጽዮንን ለሚንቁ በሰማርያም ተራራ ለሚታመኑ ሰዎች ወዮላቸው መባሉ

ምዕራፍ ፯፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በበደላቸው ምክንያት እንደሚቀጣቸው መነገሩ

ምዕራፍ ፰፡- እግዚአብሔር ለአሞጽ የእስራኤላውያንን መከራ ፍሬ በሞላበት ዕንቅብ መስሎ እንዳሳየው

ምዕራፍ ፱፡- እግዚአብሔር ሁሉን የሚገዛ እንደሆነ መገለጹ

-እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ሰዎች ናችሁ እንዳላቸው

ትንቢተ ሚክያስ

ምዕራፍ ፩፡- ሚክያስ በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታምና በአካዝ እንዲሁም በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት ትንቢትን እንደተናገረ

-በእስራኤላውያን ኃጢአት ምክንያት መከራ እንደሚመጣ መነገሩ

ምዕራፍ ፪፡- በመኝታቸው ላይ በደልን ለሚያስቡ ክፋትንም ለሚያደርጉ ወዮላቸው መባሉ

ምዕራፍ ፫፡- የእስራኤል አለቆች መልካሙን ጠልተው ክፉን መፈለጋቸው

ምዕራፍ ፬፡- ከጽዮን ሕግ ከኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚወጣ መነገሩ

-እስራኤላውያን ከስደት እንደሚመለሱ መነገሩ

ምዕራፍ ፭፡- መሢሕ ከቤተልሔም እንደሚወጣ መነገሩ

-መሢሑ በእግዚአብሔር ኃይል መንጋውን እንደሚጠብቅ መነገሩ

ምዕራፍ ፮፡- እግዚአብሔር እስራኤልን እንደወቀሰ

ምዕራፍ ፯፡- ስለእስራኤላውያን ውድቀት መነገሩ

-እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደሚራራ መነገሩ

ትንቢተ ኢዩኤል

ምዕራፍ ፩፡- ለመስከር ወይንን ለምትጠጡ ወዮላችሁ መባሉ

-ጾምን ቀድሱ ምሕላንም አውጁ መባሉ

ምዕራፍ ፪፡- በእስራኤል ላይ ስለሚደርሰው መከራ በዝርዝር መነገሩ

-እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በልቅሶና በዋይታ ወደእኔ ተመለሱ እንዳለ

-እግዚአብሔር የሕዝቡንና የካህናቱን ጸሎት ሰምቶ እንደ ራራ

-እግዚአብሔር መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ እንዳለ

-የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ እንደሚድን

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ እንደሚፈርድ መነገሩ

ትንቢተ አብድዩ

-በኤዶምያስ ላይ መከራ እንደሚደርስ መነገሩ

-በጽዮን ተራራ ላይ መድኃኒት እንደሚሆን

ትንቢተ ዮናስ

ምዕራፍ ፩፡- ዮናስ የነነዌ ሰዎችን እንዲሰብክ መነገሩ

-ዮናስ ወደ ተርሴስ ለመሸሽ በመርከብ እንደተሳፈረ

-ዮናስ በመርከቢቱ ውስጥ ስለነበረ ማዕበል መነሣቱ

-በማዕበሉ ሰዓት ዮናስ መርከቢቱ ውስጥ ተኝቶ ነበር

-መርከበኞቹ ዮናስን ወደ ባሕር ሲጥሉት ባሕሩ ከመናወጥ ጸጥ እንዳለ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር ዮናስን ይውጠው ዘንድ ታላቅ ዓሣ አንበሪን እንዳዘዘ

-ዮናስ ሦስት ቀንና ሦስት መዓልት በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ እንደነበረ

-ዮናስ በዓሣ አንበሪው ሆድ ውስጥ ሆኖ እንደጸለየ

-እግዚአብሔር ዮናስ በዓሣ አንበሪ ውስጥ ሆኖ የጸለየውን ጸሎት እንደሰማው

-ዓሣ አንበሪው ዮናስን በየብስ ላይ እንደተፋው

ምዕራፍ ፫፡- የነነዌ ሰዎች እንደጸሙ፣ ንስሓ እንደገቡና እግዚአብሔርም እንደማራቸው

ምዕራፍ ፬፡- ዮናስ የነነዌ ሰዎች ባለመጥፋታቸው እንዳዘነና እንደተከዘ

ትንቢተ ናሆም

ምዕራፍ ፩፡- እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፣ ኃይሉም ታላቅ እንደሆነ መነገሩ

-እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ እንዳለው

-በመከራቸው ቀን ለሚታገሡ እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል እንደሆነ መነገሩ

ምዕራፍ ፫፡- ሐሰትን ለተመላች ዓመፅንም ለጠገበች ለደም ከተማ ወዮላት መባሉ

-ነነዌ እንደምትጠፋ መነገሩ

ትንቢተ ዕንባቆም

ምዕራፍ ፩፡- ዕንባቆም ሕግ እንደተጣሰ መናገሩ

ምዕራፍ ፪፡- ጻድቅ በእምነቱ እንደሚኖር መነገሩ

-ከተማን በደም ለሚሠራ ከተማንም በኃጢአት ለሚያዘጋጃት ወዮለት መባሉ

-እንጨቱን ተነሥ፣ ንቃ፤ ድንጋዩንም ከፍ ከፍ በል ለሚል ወዮለት መባሉ

ምዕራፍ ፫፡- ነቢዩ ዕንባቆም እንደጸለየ

-ነቢዩ ዕንባቆም በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል በአምላኬ በመድኃኒቴም ሐሤትን አደርጋለሁ እንዳለ

ትንቢተ ሶፎንያስ

ምዕራፍ ፩፡- በእስራኤላውያን ላይ ስለ እግዚአብሔር የፍርድ ቀን መነገሩ

-የእግዚአብሔር የመዓት ቀን ድምፀ መራራና ክፉም እንደሆነች መነገሩ

ምዕራፍ ፪፡- የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ሳይደርስባችሁ እግዚአብሔርን ለምኑ መባሉ

-በእስራኤል ዙሪያ በሚኖሩ አሕዛብ መከራ እንደሚደርስባቸው

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነ

-በእስራኤል ላይ ስድብን ላነሣ ሰው ወዮለት መባሉ

ትንቢተ ሐጌ

ምዕራፍ ፩፡- እግዚአብሔር ወደተራራው ውጡ፣ እንጨትንም ቁረጡ፣ ቤቱንም ሥሩ። እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል እመሰገናለሁም እንዳለ

-ሕዝቡና የሕዝቡ መሪዎች የነቢዩ ሐጌን ቃል እንደሰሙ

ምዕራፍ ፪፡- እግዚአብሔር ዘሩባቤልንና ሕዝቡን በርቱ እንዳላቸው

-ለካህናት ምክር እንደተሰጠ

ትንቢተ ዘካርያስ

ምዕራፍ ፩፡- የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ ሥራችሁ ወደእኔ ተመለሱ ማለቱ

-እግዚአብሔር በተለያዩ ፈረሶች አምሳል ለዘካርያስ ራእይ እንዳሳየውና እንደተረጎመለት

-የእግዚአብሔር መልአክ ስለእስራኤል መመለስ እግዚአብሔርን መጠየቁ

ምዕራፍ ፪፡- ዘካርያስ በእጁ መለኪያ ገመድ የያዘ ሰውን በራእይ እንዳየ

ምዕራፍ ፫፡- መልአክ እግዚአብሔር ሰይጣንን እግዚአብሔር ይገሥጽህ እንዳለው

ምዕራፍ ፬፡- ዘካርያስ በራእዩ ሁለንተናዋ ወርቅ የሆነች መቅረዝን እንዳየ

ምዕራፍ ፭፡- ዘካርያስ በራእዩ ማጭድ ሲበርር እንዳየ

ምዕራፍ ፮፡- ዘካርያስ አራት ሠረገላዎችን በራእይ እንዳየ

-የኢዮሴዔቅ ልጅ ኢያሱ ሀገሪቱን ይገዛ ዘንድ እንደተሾመ

ምዕራፍ ፯፡- ልዑል እግዚአብሔር እውነተኛውን ፍርድ ፍረዱ፣ ምጽዋትንና ምሕረትን ለወንድሞቻችሁ አድርጉ እንዳለ

ምዕራፍ ፰፡- እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም መካከል እኖራለሁ እንዳለ

-እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ መባሉ

-ሁላችሁ በባልንጀራችሁ ላይ ክፉ ነገርን በልባችሁ አታስቡ መባሉ

ምዕራፍ ፱፡- ኢየሩሳሌም ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፣ ትሑትም ሆኖ በአህያ ተቀምጦ ወዳንቺ ይመጣል መባሏ

ምዕራፍ ፲፡- የበልጉንና የመከሩን ዝናም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለምኑ መባሉ

-እግዚአብሔር የበልግ ዝናምን ለእያንዳንዱም በሜዳ ውስጥ ሣርን እንደሚያበቅል

ምዕራፍ ፲፭፡- እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚቀጣ መናገሩ

ምዕራፍ ፲፮፡- እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በሚኖሩት ላይ የደስታንና የሐሴትን መንፈስ አፈስሳለሁ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፫፡- እግዚአብሔር ሐሰተኛ ነቢያትንና ርኩስ መንፈስን ከምድር ላይ አስወግዳለሁ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፬፡- እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ጋር እንደሚመጣ መነገሩ

-እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል መባሉ

ትንቢተ ሚልክያስ

ምዕራፍ ፩፡- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንደወደዳቸው መናገሩ

-ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ተገዙ እርሱንም ለምኑት መባሉ

ምዕራፍ ፪፡- ካህን ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል መባሉ

-የልጅነት ሚስትህን አትፍታ መባሉ

ምዕራፍ ፫፡- እግዚአብሔር እንደማይለወጥ መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- እግዚአብሔር ኤልያስን እንደሚልክና እርሱም የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች እንደሚመልስ መናገሩ

የማቴዎስ ወንጌል

ምዕራፍ ፩፡- የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ መገለጹ

-የድንግል ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስን መፅነስ ያለ ወንድ ዘር በመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ

ምዕራፍ ፪፡- ሰብአ ሰገል በኮከብ መሪነት ለክርስቶስ ለመስገድ እንደመጡ

-ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን ሄዳችሁ ለክርስቶስ ከሰገዳችሁለት በኋላ እኔም እንድሰግደለት ንገሩኝ ማለቱ

-ሰብአ ሰገል ለጌታ እጅ መንሻ እንዳቀረቡለት

-መልአክ ሰብአ ሰገልን በሌላ መንገድ እንዲሄዱ በሕልም መንገሩ

-ሄሮድስ በቤተልሔምና በአውራጃዋ ሁሉ የነበሩትን ሕፃናት እንዳስገደለ

-ዮሴፍ ድንግል ማርያምንና ጌታን ይዞ ወደ ግብፅ እንደተሰደደ

-ሄሮድስ በመሞቱ ዮሴፍ ክርስቶስንና እናቱን ድንግል ማርያምን ወደ እስራኤል መመለሱ

-ክርስቶስ ናዝሬት በምትባል ከተማ እንደኖረ

ምዕራፍ ፫፡- ዮሐንስ መጥምቅ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ እያለ እንደሰበከ

-ዮሐንስ መጥምቅ ፈሪሳውያንን እናንተ የእፉኝት ልጆች ብሎ እንደገሠጻቸው

-ጌታ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ በዮሐንስ መጥምቅ እንደተጠመቀ

-ጌታ ሲጠመቅ በራሱ ላይ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል እንዳረፈበት

ምዕራፍ ፬፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት እንደጾመ

-ጌታ በዲያብሎስ እንደተፈተነና ዲያብሎስን እንዳሳፈረው

-ጌታችን ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ ብሎ እንዳስተማረ

-ጌታ ክርስቶስ ጴጥሮስንና እንድርያስን ዓሣ ከሚያጠምዱበት ሄዶ እንደጠራቸውና እነርሱም መረባቸውን ትተው እንደተከተሉት

-የዘብዴዎስ ልጆች ዮሐንስና ያዕቆብም ታንኳቸውንና አባታቸውን ትተው ክርስቶስን እንደተከተሉት

-ጌታችን ደዌንና ሕማምን እየፈወሰ በመላው ገሊላ ይመላለስ እንደነበር

ምዕራፍ ፭፡- ጌታ አንቀፀ ብፁዓንን እንዳስተማረ

-ጌታ ሐዋርያትን እናንተ የምድር ጨው፣ የዓለም ብርሃን ናችሁ እንዳላቸው

-ጌታ ኦሪትንና ነቢያትን ልሸር አልመጣሁም ብሎ እንዳስተማረ

-ጽድቃችን ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማንገባ

-ጌታ ስድስቱን ቃላተ ወንጌል እንዳስተማረ

ምዕራፍ ፮፡- ጌታ በሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በሰዎች ፊት አታድርጉ እንዳለ

-በምንመጸውት ጊዜ ቀኛችን የሚሠራውን ግራችን ማወቅ እንደማይገባው

-በምንጸልይበት ጊዜ እንደ ግብዞች መሆን እንደማይገባን

-ጌታ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ሥርዓተ ጸሎትን እንዳስተማረን

-ጌታ እንዴት መጾም እንዳለብን ሥርዓተ ጾምን እንዳስተማረን

-ለምንበላውና ለምንለብሰው መጨነቅ እንደማይገባን

-አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁንም መፈለግ እንደሚገባን

ምዕራፍ ፮፡- እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ መባሉ

-የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ እንደተባለ

-ለምኑ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኛላችሁ መባሉ

-የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ከሐሰተኞች ነቢያት መጠበቅ እንዲገባን

-የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ እንዲገባ

ምዕራፍ ፯፡- ጌታ ለምጻሙን እንዳዳነውና ለምጻሙንም ለማንም እንዳይናገር መንገሩ

-ጌታ ለመጻሙን ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ እንዳለው

-ጌታ የመስፍኑን ልጅ፣ የጴጥሮስን አማትና ሌሎችንም መፈወሱ

-ጌታ ማዕበሉን ጸጥ እንዳደረገው

ምዕራፍ ፱፡- ጌታ መጻጉዕን እንደፈወሰው

-ጌታ ኃጢአትን ለማስተሥረይ ሥልጣን እንዳለው መናገሩ

-ጌታ ኃጥኣንን ወደ ንስሓ ለመጥራት እንደመጣ

-አንዲት ሴት የጌታን የልብሱን ዘርፍ በመንካቷ እንደተፈወሰች

-ጌታ ሐመ·ማንን እንደፈወሰ

ምዕራፍ ፲፡- ጌታ ለሐዋርያት ደዌንና ሕማምን ሁሉ ይፈውሱ ዘንድ ሥልጣንን እንደሰጣቸው

-የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም መዘርዘሩ

-ጌታ ሐዋርያትን እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ እንዳለ

-በሐዋርያት መከራ እንደሚደርስባቸው ጌታ እንደነገራቸው

-ጌታ ሥጋችሁን የሚገድሏችሁን አትፍሯቸው ነፍስንም ሥጋንም የሚያጠፋውን ፍሩት ማለቱ

-በጻድቅ ስም ጻድቅን የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል መባሉ

ምዕራፍ ፲፩፡- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐንስ መጥምቅን እንዳመሰገነው

-ሴቶች ከወለዷቸው ወገን ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ እንዳልተነሣ መነገሩ

-ጌታ ክርስቶስ ተአምራት ያደረገባቸውን ከተሞች ንስሓ ስላልገቡ እንደነቀፋቸው

ምዕራፍ ፲፪፡- የሰንበት ጌታዋ የሰው ልጅ እንደሆነ መነገሩ

-መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ ኃጢአቱ አይሠረይለትም መባሉ

-ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን እንደሚሻ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፫፡- ጌታችን የወንጌልን ትምህርት በዘር መስሎ እንደተናገረ

-ጌታ ስለ መንግሥተ ሰማያት በመልካም ዘር፣ በሰናፍጭ ቅንጣት፣ በእርሾ፣ በተቀበረች ወርቅ፣ በዓሣ መረብ መስሎ እንዳስተማረ

ምዕራፍ ፲፬፡- ሄሮድስ ዮሐንስ መጥምቅን እንዳስገደለው

-ጌታችን አምስት እንጀራንና ሁለት ዓሣዎችን አበርክቶ ሕዝቡን እንደመገበ

ምዕራፍ ፲፭፡- አይሁድ ስለወጋቸው የእግዚአብሔርን ቃል ይሽሩ እንደነበር መነገሩ

-ጌታ ሰባት እንጀራንና ጥቂት ዓሣን አበርክቶ ሕዝቡን መመገቡ

ምዕራፍ ፲፮፡- ጌታችን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠበቁ ብሎ እንዳስተማረ

-ጌታ ሐዋርያትን ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል ብሎ እንደጠየቃቸው

-ጴጥሮስ ጌታን አንተ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ እንዳለው

-ክርስቶስ እንደሚሞትና እንደሚነሣ አስቀድሞ ለሐዋርያት መናገሩ

ምዕራፍ ፲፯፡- ጌታ ክብሩን በደብረ ታቦር እንደገለጠ

-አብ በብሩህ ደመና ሆኖ ክርስቶስን የምወደው ልጄ ይህ ነው ማለቱ

ምዕራፍ ፲፰፡- ጌታችን በአንዱ ሕፃን ለደቀመዛሙርቱ ትሕትናን ማስተማሩ

-ማንንም መናቅ እንደማይገባ መነገሩ

-ወንድምን መምከር እንደሚገባ

-ይቅርታን ማድረግ እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፱፡- ጌታችን ብዙ በሽተኞችን እንደፈወሰ

-ጌታ ሕፃናትን እንደባረከ

-ጌታ ፍጹም ልትሆን ብትወድስ ሂድና ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሖች ስጥ ሰማያዊ ሀብትንም ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፭፡- መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ ቦታ ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን እንደምትመስል መነገሩ

-አለቃ መሆን የሚወድ ሎሌ መሆን እንደሚገባው

-የሰው ልጅ ክርስቶስ ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ እንደመጣ

ምዕራፍ ፳፩፡- ጌታ ደቀመዛሙርቱን የታሰረች አህያን ከነውርንጫይቱ አምጡልኝ ማለቱ

-ጌታ በአህያይቱና በውርንጫይቱ ተቀምጦ በመጣ ጊዜ ብዙ ሕዝቡ ልብሱን በመንገድ ላይ እንዳነጠፈ

-ጌታ በቤተ መቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ እንዳባረረ

ምዕራፍ ፳፪፡- መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሠርግ ያደረገ ንጉሥን እንደምትመስል መነገሩ

-የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚገባ

-ሙታን በሚነሡበት ጊዜ በሰማያት እንደ እግዚአብሔር መላእክት ሆነው እንደሚኖሩ

ምዕራፍ ፳፫፡- ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠው የሚያስተምሩትን ማድረግ እንደሚገባና እንደ ተግባራቸው ግን ማድረግ እንደማይገባ መነገሩ

-ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ እንደሚዋረድ ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ደግሞ እንደሚከብር

ምዕራፍ ፳፬፡- ጌታ ለሐዋርያት ስለዳግም ምጽአትና ስለዓለም ፍጻሜ ምልክቶች መንገሩ

-እስከመጨረሻው የሚታገሥ ይድናል መባሉ

-ጌታ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም እንዳለ

ምዕራፍ ፳፭፡- መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ለመቀበል የወጡ ዐሥሩን ደናግል እንደምትመስል

-ስለ ገብር ኄር፣ ስለ ገብር ምእመንና ስለ ገብር ሀሳይ መነገሩ

-የሰው ልጅ በጌትነቱ ቅዱሳን መላእክትን ሁሉ አስከትሎ በሚመጣበት ጊዜ ያን ጊዜ በጌትነቱ ዙፋን እንደሚቀመጥ

-በዕለተ ምጽአት ጻድቃንን ወደእኔ ኑ፣ ኃጥኣንን ከእኔ ሂዱ እንደሚላቸው መናገሩ

ምዕራፍ ፳፮፡- ጌታ እንደሚሰቀል ለሐዋርያት አስቀድሞ መንገሩ

-አንዲት ሴት ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብርሌ ይዛ በጌታ ራስ ላይ እንዳፈሰሰችለት

-ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ ከአይሁድ ጋር በሠላሳ ብር መስማማቱ

-ክርስቶስ ጎብስቱንና ወይኑን ባርኮ ለሐዋርያት እንኩ ይህ ሥጋዬ ነው ይህ ደሜ ነው ብሎ እንደሰጣቸው

-ይሁዳ ጌታን በመሳም ለአይሁድ አሳልፎ እንደሰጠው

-ጴጥሮስ ጌታን አላውቀውም ብሎ ክዶ እንደነበርና በኋላ እንደተጸጸተ

ምዕራፍ ፳፮፡- ይሁዳ ንጹሕ ደምን አሳልፌ የሰጠሁ እኔ በድያለሁ ብሎ ሠላሳ ብሩን እንደመለሰ

-ጌታ በጲላጦስ ፊት እንደቀረበና ሕዝቡ በርባን ይፈታ ክርስቶስ ይሰቀል ማለቱ

-ጭፍሮች በጌታ ላይ እንደተዘባበቱና ጌታን በሁለት ወንበዴዎች መካከል እንደሰቀሉት

-ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ተአምራት እንደተደረጉ

ምዕራፍ ፳፯፡- ስለጌታችን ትንሣኤ መነገሩ

-ጌታ ከሙታን መካከል ተነሥቶ ደቀመዛሙርቱን ሰላም ለእናንተ ይሁን እንዳላቸው

-ጌታ ሐዋርያትን ሂዱ አሕዛብን ሁሉ አስተምራችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው ማለቱ

የማርቆስ ወንጌል

ምዕራፍ ፩፡- ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ስብከትና ጌታን ስለማጥመቁ መነገሩ

-ሐዋርያት ጌታን እንደተከተሉት

-ጌታ ወደ ቅፍርናሆም ሄዶ በምኩራብ እንዳስተማረና ልዩ ልዩ ተአምራትን እንዳደረገ

ምዕራፍ ፪፡- ጌታ ሕመማንን እንደፈወሰ

-አይሁድ ጌታን ስለጾም፣ ስለሰንበት እንደጠየቁት

ምዕራፍ ፫፡- ጌታችን ልዩ ልዩ ተአምራትን እንዳደረገ

-ጌታ አሥራ ሁለት ሐዋርያትን እንደመረጠ

ምዕራፍ ፬፡- ጌታ ለሕዝቡ በምሳሌ እንዳስተማራቸው

ምዕራፍ ፭፡- ጌታ ሌጌዎን ያደረበትን በሽተኛ እንደፈወሰው

-ጌታ አሥራ ሁለት ዓመት ደም ይፈስሳት የነበረችውን ሴት እንደፈወሳት

-ጌታ የምኵራቡን ሹም ልጅ እንደፈወሰ

ምዕራፍ ፮፡- ብዙዎች የጌታን ትምህርት ሰምተው እንዳደነቁ

-ጌታ ያስተምሩ ዘንድ ሐዋርያትን እንደላከ

-ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን እንዳስገደለው

-ጌታ ሁለት ዓሣና አምስት እንጀራዎችን ባርኮ ሕዝቡን እንዳጠገበ

ምዕራፍ ፯፡- ጌታ ፈሪሳውያንን እንደገሠጸ

-ፈሪሳውያን ስለወጋቸው ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሸሩ እንደነበር

-ጌታ ሕመማንን እንደፈወሰ መነገሩ

ምዕራፍ ፰፡- ጌታ ሰባት እንጀራን አበርክቶ አራት ሺ ሰዎችን እንዳጠገበ

-ጌታ ሐዋርያትን ሰዎች ማን ይሉኛል ብሎ በቂሣርያ እንደጠየቃቸው

ምዕራፍ ፱፡- ጌታችን በደብረ ታቦር ለደቀመዛሙርቱ ክብሩን መግለጡ

-ጌታ ጋኔን ይጥለው የነበረውን ሰው እንደፈወሰው

-ለሚያምን ሁሉ ይቻላል መባሉ

-አለቃ ሊሆን የሚወድ ራሱን ለሁሉ ዝቅ ያድርግ እንደተባለ

ምዕራፍ ፲፡- ሚስቱን የሚፈታና ሌላዪቱን የሚያገባ እንዳመነዘረ

-ጌታ ሕፃናትን ወደእኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው እንዳለ

-ጌታን የሚከተል የዘለዓለም ሕይወትን እንደሚያገኝ መነገሩ

-ጌታ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ በርጠሜዎስን እንዳዳነው

ምዕራፍ ፲፩፡- ጌታ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ

-ጌታ በቤተ መቅደስ ይሻሻጡ የነበሩ ሰዎችን እንደገሠጸ

-ሌሎች የበደሉንን በደል ይቅር ማለት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፲፪፡- ጌታ ስለወይኑ ቦታ ምሳሌ እንደነገራቸው

ምዕራፍ ፲፫፡- ጌታ ስለቤተ መቅደስ መፍረስና ስለዓለም ፍጻሜ መናገሩ

-ጌታ ሐዋርያትን ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ እንዳላቸው

ምዕራፍ ፲፬፡- አንዲት ሴት ጌታችንን ሽቱ እንደቀባችው

-ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት በሠላሳ ብር እንደተስማማ

-ጴጥሮስ ጌታን አላውቀውም ብሎ እንደተናገረና በኋላ ግን እንዳለቀሰ

ምዕራፍ ፲፮፡- ጌታን አይሁድ እንደሰቀሉት

ምዕራፍ ፲፯፡- ጌታችን ከሙታን መካከል ተለይቶ እንደተነሣ

-ያመነ የተጠመቀ እንደሚድን መነገሩ

የሉቃስ ወንጌል

ምዕራፍ ፩፡- ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን እንደነበሩ

-ለዘካርያስ መልአኩ ጸሎትህ ተሰምቷል እንዳለው

-ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን እንዳበሰራት

-ኤልሳቤጥ የድንግል ማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ጽንሱ በማኅፀኗ እንደዘለለ

-ኤልሳቤጥ መጥምቁ ዮሐንስን እንደወለደች

ምዕራፍ ፪፡- ድንግል ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደወለደች

-ስለ ግዝረተ ክርስቶስ መነገሩ

-ስለአረጋዊው ስምዖንና ስለነቢይት ሐና መነገሩ

-ክርስቶስን የሰሙት ሁሉ ያደንቁት እንደነበረ

ምዕራፍ ፫፡- ዮሐንስ መጥምቅ እንደሰበከ

-ዮሐንስ ጌታን እንዳጠመቀው

-የጌታችን የትውልድ ሐረግ መገለጹ

ምዕራፍ ፬፡

-ኢየሱስ ክርስቶስ በዲያብሎስ ስለመፈተኑ

-ጌታ ወደ ምኩራብ ገብቶ እንዳነበበ

-ጌታ ዝም በልና ከእርሱ ውጣ ብሎ ሰይጣንን ከታማሚው እንዳስወጣው

ምዕራፍ ፭፡ እነ ስምዖን ጌታ መረባችሁን በቀኝ በኩል ጣሉ ሲላቸው እሺ ብለው ቢጥሉ ብዙ ዓሣዎችን እንደያዙ

-ጌታ በሽተኞችን እንደፈወሰ

-ጌታ ወደ ምድረበዳ እየወጣ ይጸልይ እንደነበር

ምዕራፍ ፮፡ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታዋ እንደሆነ መነገሩ

-ጌታ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እንደመረጠ

-ጌታ በተራራ ላይ አንቀጸ ብፁዓንን እንዳስተማረ

-መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካምን እንደሚያወጣ መነገሩ

ምዕራፍ ፯፡ ጌታ የመስፍኑን ሎሌና የመበለቲቱን ልጅ እንዳዳናቸው

ምዕራፍ ፰፡ ጌታችን በየከተማውና በየመንደሩ ተመላልሶ እንዳስተማረ

-ጌታ በዘር ምሳሌ እንዳስተማረ

-ጌታ ልዩ ልዩ ተአምራትን እንዳደረገ

ምዕራፍ ፱፡ ጌታ ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ድውያንን ይፈውሱ ዘንድ ኃይልንና ሥልጣንን እንደሰጣቸው

-ጌታ ሊፈወሱ የሚሹትን እንዳዳናቸው

-ጴጥሮስ ጌታን አንተ የእግዚአብሔር መሢሕ ነህ እንዳለው

-ጌታ ራሱን ከሁሉ ዝቅ የሚያደርግ እርሱ ታላቅ ይሆናል እንዳለ

ምዕራፍ ፲፡ ጌታ ሌሎች ሰባ ሰዎችን እንደመረጠ

-ጌታ ለሰባው ሰዎች እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፣ እናንተን እንቢ የሚል እኔን እንቢ ይላል እንዳላቸው

-ስለደጉ ሳምራዊ መነገሩ

-ማርያም የማይቀሟትን መልካም እድል እንደመረጠች መነገሩ

ምዕራፍ ፲፩፡ -ሐዋርያት ጌታን ጸሎትን አስተምረን እንዳሉትና እርሱም አቡነ ዘበሰማያትን እንዳስተማራቸው

-እግዚአብሔር ለሚለምኑት መልካሙን ሀብተ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጣቸው መነገሩ

ምዕራፍ ፲፪፥ ጌታ ከፈሪሳውያን እርሾ (ከግብዝነት) ተጠበቁ እንዳለ

-ሰው ገንዘብ በማብዛት እንደማይድን

-ተዘጋጅተን መኖር እንዳለብን መነገሩ

ምዕራፍ ፲፫፥ ጌታ ንስሓ ካልገባችሁ ትጠፋላችሁ እንዳለ

-ጌታ ጎባጣይትን ሴት እንደፈወሳት

-ጌታ መንግሥተ ሰማያትን በእርሾ፣ በሰናፍጭ ቅንጣት መስሎ እንዳስተማረ

ምዕራፍ ፲፬፥ ጌታ ሆዱን የተነፋውን ሰው እንደፈወሰው

-ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሰው እንደሚዋረድና ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ደግሞ ከፍ እንደሚል መነገሩ

-በዓል በምታደርግበት ጊዜ ድኾችንና ጦም አዳሪዎችን መጥራት እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፭፥ ንስሓ ስለሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማያት ፍጹም ደስታ እንደሚሆን መነገሩ

ምዕራፍ ፲፮፥ በጥቂት የታመነ በብዙ እንደሚታመን፣ በጥቂት የሚያምፅ በብዙ እንደሚያምፅ መነገሩ

-በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀ እንደሚሆን

-ስለአንድ ባለጸጋና ስለአልዓዛር መነገሩ

ምዕራፍ ፲፯፥ ለራሳችን መጠንቀቅ እንደሚገባን መነገሩ

-ወንድምህ አንተን ቢበድልህ ብቻህን ምከረው እንደተባለ

-ጌታ አሥሩን ለምጻሞች እንደፈወሰና ከአሥሩ አንዱ ብቻ ተመልሶ እንዳመሰገነው መነገሩ

-ነፍሱን ሊያድናት የሚወድ ይጣላት መባሉ

ምዕራፍ ፲፰፥ አለመሰልቸትና ዘወትር መጸለይ እንደሚገባ መነገሩ

-ሕፃናትን ይባርካቸው ዘንድ ወደጌታ እንዳቀረቡለት

-ጌታ ለሐዋርያት ስለሕማሙና ስለሞቱ እንደነገራቸው

ምዕራፍ ፲፱፥ ዘኬዎስ ጌታን ለማየት ወደፊት ሮጦ ወደሾላ እንደወጣና እንዳየው

ምዕራፍ ፳፥ ፈሪሳውያን ጌታን በማን ሥልጣን ታደርጋለህ ብለው እንደጠየቁት

ምዕራፍ ፳፩፥ አንዲት ድኻ ሁለት መሐለቅ ለእግዚአብሔር መባ እንዳስገባች

-ጌታ ስለኢየሩሳሌምና ስለቤተመቅደስ መፍረስ እንደተናገረ

-በትዕግሥታችሁ ነፍሳችሁን ገንዘብ ታደርጋላችሁ እንደተባለ

-ጌታ በመብልና በመጠጥ፣ በመቀማጠልና የዓለምን ኑሮ በማሰብ ልባችሁን አታደንድኑ እንዳለ

-ጌታ ከሚመጣው ሁሉ በጸሎታችሁ ማምለጥ እንድትችሉ በሰው ልጅ ፊትም እንድትቆሙ ሁልጊዜ ትጉ ማለቱ

ምዕራፍ ፳፪፦ ይሁዳ ጌታን አሳልፎ ለመስጠት ከካህናት አለቆች ጋር እንደተነጋገረ

-ጌታ ወደመከራ እንዳትገቡ ጸልዩ ማለቱ

-አይሁድ በጌታ እንደተዘባበቱ

ምዕራፍ ፳፫፦ አይሁድ ጌታ እንዲሰቀል አብዝተው መጮኻቸው

-ጌታ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው እንዳለ

ምዕራፍ ፳፬፦ ጌታ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ

-ጌታ በኤማሁስ መንገድ ለሚሄዱ ሁለት ሰዎች እንደተገለጠ

-ጌታ እንዳረገ መነገሩ

-ሐዋርያት በቤተ መቅደስ ዘወትር እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያገለገሉ እንደኖሩ መነገሩ

የዮሐንስ ወንጌል

ምዕራፍ ፩፡- በመጀመሪያ ቃል እንደነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበርና ቃልም እግዚአብሔር እንደነበር መነገሩ

-ሁሉ በቃል እንደሆነና ያለእርሱ ምንም ምን የሆነ እንደሌለና ሕይወት በእርሱ እንደነበረ

-ቃል ሥጋ እንደሆነ

-ዮሐንስ ስለክርስቶስ ከእኔ አስቀድሞ ነበረ ብሎ እንደመሰከረ

-በአባቱ እቅፍ ያለ ልጁ ገለጠልን እንጂ እግዚአብሔርን ከቶ ያየው እንደሌለ

-ዮሐንስ ጌታን የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እንዳለው

-ዮሐንስ ስለክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እኔ ምስክሩ ነኝ እንዳለ

-ጌታ ናትናኤልን ገና ፊልጶስ ሳይጠራህ በበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ አይቼሀለሁ እንዳለው

ምዕራፍ ፪፡- ጌታ በቃና ዘገሊላ በተደረገ ሰርግ ከእናቱና ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደተገኘ

-ጌታ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ እንደለወጠው

-ጌታ ክርስቶስ በቤተመቅደስ የነበረውን ንግድ እንዲቆም መከልከሉ

-ክርስቶስ ሞቶ በሦስተኛው ቀን እንደሚነሣ ለሐዋርያት መንገሩ

ምዕራፍ ፫፡- ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደጌታ እየመጣ ይማር እንደነበር

-ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ መንግሥተ ሰማያት እንደማይገባ መነገሩ

-እግዚአብሔር የላከው ስለእግዚአብሔር እንደሚናገር

-በወልድ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት እንዳለው መነገሩ

ምዕራፍ ፬፡- ጌታ ሳምራዊትን ሴት ውሃ አጠጪኝ እንዳላትና የሕይወት ውሃን የሚሰጥ መሆኑን እንደገለጸላት

-እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነ መነገሩ

-ጌታ ነቢይ በሀገሩ አይከብርም ብሎ እንደተናገረ

ምዕራፍ ፭፡- ጌታ ሠላሳ ስምንት ዓመት ሙሉ በሽተኛ የነበረውን ሰው እንዳዳነው

-ጌታ መፃጉዕን ከፈወሰው በኋላ ከዚህ የባሰ እንዳያገኝህ ዳግመኛ እንዳትበድል እንዳለው

-ጌታ ኢየሱስ አባቴ እስከዛሬ ይሠራል እኔም እሠራለሁ እንዳለ

-ወልድን የማያከብር የላከውን አብንም እንደማያከብር መነገሩ

ምዕራፍ ፮፡- ጌታ አምስት እንጀራንና ሁለት ዓሣን ባርኮ ለሕዝቡ እንደሰጣቸው

-ጌታ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ብሎ እንዳስተማረ

-ጌታ የላከኝ አብ ካልሳበው በቀር ወደእኔ መምጣት የሚችል የለም እንዳለ

-ጌታ ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው እንዳለ

ምዕራፍ ፯፡- አይሁድ ሳይማር እንዴት ያውቃል ብለው ስለክርስቶስ መናገራቸው

-ጌታ የተጠማ ወደእኔ ይምጣና ይጠጣ እንዳለ

ምዕራፍ ፰፡- ጌታ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ እንዳለ

-ኃጢአትን የሚሠራ ሁሉ የኃጢአት ባርያ እንደሆነ

-ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚሰማ መነገሩ

ምዕራፍ ፱፡- ጌታ በምራቁ ጭቃ አድርጎ ዓይነ ስውር ሰውን እንዳዳነ

ምዕራፍ ፲፡- ክርስቶስ የበጎች በር እኔ ነኝ እንዳለ

-ጌታ ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ ቸር ጠባቂ ስለበጎቹ ነፍሱን ይሰጣል እንዳለ

-ክርስቶስ እኔና አብ አንድ ነን እንዳለ

ምዕራፍ ፲፩፡- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ እንዳለ

-ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት እንዳስነሣ

-ቀያፋ ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል እንዳለ

-የካህናት አለቆች ክርስቶስን ሊገድሉት እንደተማከሩ

ምዕራፍ ፲፪፡- ማርያም እጎተ አልዓዛር ጌታን ሽቱ እንደቀባችው

-ብዙ ሰዎች የዘንባባ ዛፍ ይዘው ጌታን ሆሣዕና በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የእስራኤልም ንጉሥ ቡሩክ ነው እንዳሉት

-ፈሪሳውያን ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር እንደወደዱ መነገሩ

-ጌታ በእኔ የሚያምን በላከኝም ነው እንጂ በእኔ ብቻ የሚያምን አይደለም እንዳለ

ምዕራፍ ፲፫፡- ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር እንዳጠበ

-ጌታ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው መናገሩ

-ጌታ እኔ እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ ብሎ እንደተናገረ

ምዕራፍ ፲፬፡- ጌታ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔም እመኑ ብሎ እንደተናገረ

-ጌታ የእውነትና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ እንዳለ

-ጌታ እኔን ያየ አብን አየ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ ማለቱ

-ጌታ የሚወደኝ ቃሌን ይጠብቃል እንዳለ

ምዕራፍ ፲፭፡- ጌታ እውነተኛ የወይን ሐረግ እኔ ነኝ እንዳለ

-ጌታ እኔን የሚጠላ አባቴን ይጠላል እንዳለ

-ጳራቅሊጦስ ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፮፡- ለሐዋርያት የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት እንደሚመራቸው መነገሩ

-ክርስቶስ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ብሎ እንዳስተማረ

-ክርስቶስ ከአብ ወጣሁ ወደ ዓለምም መጣሁ ብሎ እንደተናገረ

-ሐዋርያት ጌታን ሁሉን እንደምታውቅ ዐወቅን ማለታቸው

ምዕራፍ ፲፯፡- ክርስቶስ አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፲፰፡- ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ጆሮ እንደቆረጠ

-ጴጥሮስ ጌታን አላውቀውም እንዳለ

ምዕራፍ ፲፱፡- ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዞ እንደገረፈው

-ጌታችንን የእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ እንደደፉበት

-አይሁድ ጌታችንን ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ በጥፊ እንደመቱት

-አይሁድ ክርስቶስን እንደሰቀሉት

-ከጌታ ጋር ሁለት ወንበዴዎችን አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ እንደሰቀሉ

-ጌታ በመስቀል ላይ ሆኖ ሳለ ተጠማሁ እንዳለ

ምዕራፍ ፳፡- ጌታ ከሙታን መካከል እንደተነሣና ለማርያም መግደላዊት እንደተገለጸላት

-ጌታ በተቆለፈ ቤት ገብቶ ደቀመዛሙርቱን ሰላም ለእናንተ ይሁን እንዳላቸው

-ጌታ ለሐዋርያት ኃጢአታችሁን ይቅር ያላችሁላቸው ይሰረይላቸዋል ይቅር ያላላችሁላቸው ግን አይሰረይላቸውም እንዳላቸው

-ቶማስ የጌታን ትንሣኤ ካላየሁ አላምንም ብሎ እንደነበርና የጌታን ጎን ዳስሶ እንዳመነ

ምዕራፍ ፳፩፡- ጌታ ከትንሣኤው በኋላ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀመዛሙርቱ እንደተገለጸላቸው

-ጌታ ጴጥሮስን በጎቼን ጠብቅ እንዳለው

የሐዋርያት ሥራ

ምዕራፍ ፩፡ ጌታ ከትንሣኤ በኋላ ብዙ ተአምራትን በማሳየት አርባ ቀን ሙሉ ለሐዋርያት እየተገለጠላቸው እንደነበርና ስለእግዚአብሔር መንግሥት እንዳስተማራቸው

-መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ጊዜ ኃይልን እንደሚቀበሉ ለሐዋርያት መነገሩ

-ጌታችን ወደ ሰማይ እንዳረገ

-ሐዋርያት፣ ድንግል ማርያምና ሌሎችም ሴቶች ለጸሎት ይተጉ እንደነበረ

-በይሁዳ ምትክ ማትያስ እንደተሾመ

ምዕራፍ ፪፦ በአምሳኛው ቀን ሐዋርያትና ሌሎችም መንፈስ ቅዱስን እንደተሞሉ

-የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ እንደሚድን

-ጴጥሮስ 3000 ሰዎችን አሳምኖ እንዳጠመቀ

ምዕራፍ ፫፦ ጴጥሮስና ዮሐንስ ዘጠኝ ሰዓት ለጸሎት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ እንደነበር

-ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ እግሩ ሽባ የነበረን ሰው ጴጥሮስ እንደፈወሰው

-ኃጢአታችሁ ይሠረይላችሁ ዘንድ ንስሓ ግቡ መባሉ

ምዕራፍ ፬፦ ሊቃነ ካህናትና የቤተ መቅደስ ሹሞች ሐዋርያት በመስበካቸው እንደተናደዱና እንደያዟቸው

-በጴጥሮስ ስብከት 5000 ሰዎች ማመናቸው

-እግዚአብሔርን መስማት እንደሚገባ

-ያመኑት ሁሉ አንድ ልብና አንዲት ነፍስ ሆነው ይኖሩ እንደነበር

ምዕራፍ ፭፦ ሐናንያና ሰጲራ በማታለላቸው እንደሞቱ

-በሐዋርያት እጅ ብዙ ተአምራት ይደረግ እንደነበር

-ሊቃነ ካህናትና ሰዱቃውያን ሐዋርያትን ወደ ወኅኒ ቤት እንዳስገቧቸው

-ሐዋርያት ለሰው ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባል እንዳሉ

-በቀድሞ ዘመን ቴዎዳስና ይሁዳ ዘገሊላ የሚባሉ ክፉ ሰዎች ተነሥተው እንደነበር ገማልያል መግለጹ

ምዕራፍ ፮፦ ሐዋርያት ሰባቱን ዲያቆናት እንደሾሙ

-የእግዚአብሔር ቃል ከፍ ከፍ እንዳለና ከካህናትም ብዙዎች እንዳመኑ

ምዕራፍ ፯፦ እስጢፋኖስ ከአሪት ጀምሮ እየጠቀሰ እንዳስተማረ

-እስጢፋኖስ ስለገዳዮቹ እንደጸለየ

ምዕራፍ ፰፡ በቤተክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት እንደመጣ

-ሳውል ቤተክርስቲያንን ያሳድድ እንደነበረ

-የተበተኑት እየተዘዋወሩ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሰበኩ

-ሲሞን የሚባል ሥራየኛ ሰውን ያስት እንደነበር

-ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በፊልጶስ አማካኝነት አምኖ እንደተጠመቀ

ምዕረፍ ፱፡ ከሰማይ መብረቅ ብልጭ ስላለበት ሳውል እንደወደቀና እንደታወረ

-ሐናንያ የጳውሎስን ዓይን እንደፈወሰለትና እንዳጠመቀው

-ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማሩ

-ቅዱስ ጴጥሮስ ኤንያን እንደፈወሰና ጣቢታን ደግሞ ከሞት እንዳስነሣት

ምዕራፍ ፲፡ ቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ እንደተጠመቀ

ምዕራፍ ፲፩፡ ጴጥሮስን ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሰዎች እንደተቃወሙት

-ደቀመዛሙርት መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተብለው እንደተጠሩ

-አጋቦስ በዓለም ሁሉ ጽኑ ረኃብ እንደሚመጣ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት እንደተናገረ

ምዕራፍ ፲፪፡ ሄሮድስ የቤተክርስቲያንን ሹሞች እንደያዛቸውና መከራም እንዳፀናባቸው የዮሐንስን ወንድም ያዕቆብንም በሰይፍ እንደገደለው

-መልአኩ ጴጥሮስን ከእስር ቤት እንዳወጣው

-ሄሮድስ ለእግዚአብሔር ክብር ስላልሰጠ ተቀሥፎ እንደሞተ

ምዕራፍ ፲፫፡ በርናባስና ሳውል ለስብከተ ወንጌል እንደተመረጡ

ምዕራፍ ፲፬፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሽባውን እንደፈወሰ

-እግዚአብሔር ራሱን ያለምስክር እንዳልተወ መነገሩ

ምዕራፍ ፲፭፡ ቢጽ ሐሳውያን እንደ ሙሴ ሕግ ካልተገረዛችሁ ልትድኑ አትችሉም እያሉ ማስተማራቸው

-ወደ እግዚአብሔር በተመለሱ አሕዛብ ላይ ሥርዐት ማክበድ እንደማይገባ መገለጹ

-ለጣዖት የተሠዋን፣ ሞቶ የተገኘን፣ ደምን መብላት እንደማይገባ መገለጹ

-በራሳችሁ የምትጠሉትን በወንድሞቻችሁ ላይ አታድርጉ መባሉ

ምዕራፍ ፲፮፡ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከእናት ከአባቱ ለይቶ ይዞት እንደሄደ

-ልድያ ጳውሎስ የሚያስተምረውን ትምህርት ታዳምጥ እንደነበር

-በመንፈ*ቀ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ እንደጸለዩና እግዚአብሔርንም እንዳመሰገኑ

-ጳውሎስና ሲላስ የታሰሩበትን የወኅኒ ቤቱን ጠባቂ አሳምነው እንዳጠመቁት

ምዕራፍ ፲፯፡ ጳውሎስ ስለክርስቶስ እንዳስተማረ

-ጳውሎስ በአርዮስ ፋጎስ ቆሞ ለግሪክ ሰዎች እንዳስተማረ

ምዕራፍ ፲፰፡ ጳውሎስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እየመሰከረ ቃሉን ለማስተማር ይተጋ እንደነበር

-ጳውሎስ ስእለት ስለነበረበት በክንክራኦስ ራሱን እንደተላጨ

-አጵሎስ የእግዚአብሔርን መንገድ የተማረ እንደነበርና ስለኢየሱስ ክርስቶስም ሊያስተምርና ሊመሰክር ከልቡ የሚተጋ እንደነበር

ምዕራፍ ፲፱፡ የጳውሎስ የልብሱ ዘርፍና መጠምጠሚያው ሕመማንን ይፈውስ እንደነበር

-የኤፌሶን ሰዎች አርጤምስ ለምትባለዋ ጣዖታቸው ጥብቅና እንደቆሙ

ምዕራፍ ፳፡ ቅዱስ ጳውሎስ ብዙ ትምህርትን እንዳስተማረ

-እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያንን መጠበቅ እንደሚገባ መነገሩ

ምዕራፍ ፳፩፡ ጳውሎስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመሞት የቆረጥኩ ነኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፳፪፡ ጳውሎስ ስለመጠራቱ ለሕዝቡ እንዳብራራ

ምዕራፍ ፳፫፡ ጳውሎስ በመልካም ኅሊና ሁሉ እግዚአብሔርን ሳገለግል ኖሬያለሁ እንዳለ

-ጳውሎስ ከሳሾቹ እኩሉ ሰዱቃውያን እኩሉ ፈሪሳውያን እንደሆኑ አውቆ ፈሪሳዊ ነኝ በማለቱ እርስ በእርሳቸው እንደተለያዩለትና ከመከራ እንደተረፈ

ምዕራፍ ፳፬፡ ጳውሎስን ከሳሾች እንደከሰሱት

ምዕራፍ ፳፭፡ አይሁድ ጳውሎስን በፊስጦስ ፊት እንደከሰሱት

-ጳውሎስ ወደ ቄሣር ይግባኝ እንዳለ

ምዕራፍ ፳፮፡ ንጉሥ አግሪጳ ጳውሎስ ስለራሱ እንዲናገር እንደፈቀደለትና ጳውሎስም ለአግሪጳ ምስጋና አቅርቦ ንግግር እንዳደረገ

ምዕራፍ ፳፯፦ ጳውሎስ በመርከብ ወደ ሮሜ እንደሄደና በመርከብ ሳሉም ማዕበል እንዳስቸገራቸው

ምዕራፍ ፳፰፦ ጳውሎስን እፉኝት እንደነደፈችውና ምንም ጉዳት ግን እንዳላገኘው

-ጳውሎስ በኔሮን ቄሣር ዘመነ መንግሥት በሰይፍ ተመትቶ ሰማዕት እንደሆነ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች

ምዕራፍ ፩፡- ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሰላምታን እንዳቀረበ

-የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ የፈጠረውን ፍጥረት በመመርመር እንደሚታወቅ

-እግዚአብሔር ለዘለዓለም ቡሩክ አምላክ እንደሆነ

-እግዚአብሔር በክፉዎች መቅሠፍትን እንዳመጣባቸው

ምዕራፍ ፪፡- በሌላ ላይ አይተን የምንጠላውንና የምንነቅፈውን እኛ ራሳችን ስንሠራው መገኘት እንደሌለብን

-እግዚአብሔር በእውነተኛ ፍርዱ ለሁሉ እንደ ሥራው እንደሚከፍለው

-በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉ እንደሚጸድቁ

-መገዘር ሕገ ኦሪት እንደነበረ በሐዲስ ግን ኃጢአትም ጽድቅም እንዳልሆነ

ምዕራፍ ፫፡- ጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት ያለዋጋ በእርሱ ቸርነት እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡- አብርሃም በእግዚአብሔር እንዳመነና ጽድቅ ሆኖም እንደተቆጠረለት

-ኃጢአታቸው የተሠረየላቸውና እግዚአብሔር በደላቸውን የማይቆጥርባቸው ብፁዓን እንደሆኑ

ምዕራፍ ፭፡- በመከራ ተስፋ እንደሚገኝ

-ክርስቶስ እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን ስለኃጢአታችን ይሞት ዘንድ ዘመኑ ሲደርስ እንደመጣ

ምዕራፍ ፮፡- ክርስቶስን በሞቱ ከመሰልነው በትንሣኤውም እንደምንመሰለው

-ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር በሕይወት እንደምንኖር

-የኃጢአት ትርፏ ሞት እንደሆነ

ምዕራፍ ፯፡- ሴት ባሏ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ እንደምትሆን

-ኦሪት መልካሙን ከክፉ ልትለይ እንደተሠራች

ምዕራፍ ፰፡- የሥጋ አሳብ ሞትን እንደሚያመጣብን የመንፈስ አሳብ ግን ሰላምንና ሕይወትን እንደሚሰጥ

-ለመንፈሳዊ ሕግ እንጂ ለሥጋችን ፈቃድ የምንሠራ እንዳንሆን

-ሰውነትን ከኃጢአት ሥራ መለየት እንደሚያስፈልግ

-በመንፈሳዊ ሥራ የሥጋችንን ፈቃድ ብንገድል ለዘለዓለም በሕይወት እንደምንኖር

-ክርስቶስን በመከራ ከመሰልነው በክበር እንደምንመስለው

-የዚህ ዓለም መከራ ለእኛ ሊገለጥ ካለው ክብር ጋር እንደማይተካከል

-እግዚአብሔር ልባችን የሚያስበውን እንደሚያውቅ

-እግዚአብሔር የሚወዱትን ምርጦቹን በበጎ ምግባር ሁሉ እንደሚረዳቸው

-ከክርስቶስ ፍቅር ማንምና ምንም እንደማይለየን

ምዕራፍ ፱፡- ክርስቶስ ከእስራኤላውያን በሥጋ እንደተወለደና ዘለዓለማዊ አምላክ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ቃል እንደማይታበል

ምዕራፍ ፲፡- የኦሪት ጽድቅ ፍጻሜ በክርስቶስ ማመን እንደሆነ

-ከሰማይ የወረደውና ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ክርስቶስ እንደሆነ

-ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ መመስከር እንደሚገባ

-የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ እንደሚድን

-ማመን ከመስማት፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፩፡- የእግዚአብሔር ባለጠግነት ጥበብና ዕውቀት ጥልቅ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፪፡- ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ሕያውና ቅዱስ ደስ የሚያሰኝም መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ እንደሚገባን

-ይህንን ዓለም መምሰል እንደማይገባ

-ሁላችን ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል እንደሆንን

-ፍቅራችን ያለ ግብዝነት እንዲሆን

-በአገልግሎት መትጋት፣ በማስተማር መትጋት እንደሚገባ

-እርስ በእርስ መከባበር እንደሚገባ መነገሩ

-እንግዳ መቀበልን ማዘውተር እንደሚገባ

-ደስ ከሚለው ጋር ደስ እንዲለን ከሚያለቅስ ጋር እንድናለቅስ መነገሩ

-ክፉን በመልካም ሥራ ድል መንሣት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፲፫፡- ለባለሥልጣኖች መገዛት እንደሚገባ፣ ግብር ለሚገባው ግብር መስጠት እንደሚገባ

-ዐሥራት ለሚገባው ዐሥራት መስጠት እንደሚገባ

-ክብር የሚገባውን ማክበር እንደሚገባ

-ባልንጀራውን የወደደ ሕግን ሁሉ እንደፈጸመ

-ባልንጀራውን የሚወድ በባልንጀራው ላይ ክፉ ሥራን እንደማይሠራ

ምዕራፍ ፲፬፡- እምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው መታገሥ እንደሚገባ

-ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን ሁሉን ይብላ መባሉ

-የሚበላ የማይበላውን፣ የማይበላው የሚባለውን መንቀፍ እንደማይገባ

-ሁላችን በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት እንደምንቆም

-ሁላችን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደምንመረመር

-እርስ በእርሳችን መነቃቀፍ እንደማይገባን

-የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፭፡- በእውነትና በመልካም ሥራ ይታነጽ ዘንድ ለባልንጀራችን ማድላት እንደሚገባ

-መጻሕፍት እኛ ልንማርባቸው እንደተጻፉ

-ጳውሎስ ወንጌልን ለማስተማር እንደተጋ

ምዕራፍ ፲፮፡- ጳውሎስ ምእመናንን እንዳመሰገነ

-እርስ በእርሳችን በተቀደሰ ሰላምታ ሰላም መባባል እንደሚገባ

-መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን እንድናውቅባቸው መነገሩ

አንደኛ ቆሮንቶስ

ምዕራፍ ፩፡- ከሰዎች ጋር አንድ ሐሳብና አንድ ልብ ሆኖ መኖር እንደሚገባ

-የመስቀሉ ነገር በሚጠፉ ሰዎች ዘንድ ስንፍና ለምንድነው ለእኛ ግን የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ

ምዕራፍ ፪፡ ማመናችን በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን መነገሩ

-መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምሥጢር እንደሚያውቅ

-መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ሁሉን እንደሚመረምር

ምዕራፍ ፫፡ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ እያልን መከፋፈል እንደሌለብን

-እኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆንን

-የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተባለ ሰውነታችንን ማርከስ እንደማይገባ

ምዕራፍ ፬፡ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ቤዛችሁ ነኝ እንዳላቸው

-ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ወልጃችኋለሁ እንዳላቸው

ምዕራፍ ፭፡ አዲስ ቡሆ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ ከእናንተ አርቁ መባሉ

-ከክፉ ሰዎች ጋር አንድ መሆን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፮፡ ቅዱሳን በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ

-ዐመፀኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ሌቦች፣ ጣዖትን አምላኪዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ

- ሁሉ ቢፈቀድልንም ሁሉ ግን እንደማይጠቅም

-ሥጋችን የክርስቶስ አካል እንደሆነ

-ከዝሙት መሸሽ እንደሚገባ

-በሥጋችን እግዚአብሔርን ማክበር እንደሚገባን

ምዕራፍ ፯፡ ባል ለሚስቱ የሚገባትን እንዲያደርግላት ሚስትም ለባሏ እንዲሁ እንድታደርግ መነገሩ

-በምኞት ከመቃጠል ማግባት እንደሚሻል

-ራሱን መግዛት ያልቻለ እንዲያገባ

-በሐዲስ ኪዳን መገረዝም አለመገረዝም ሕግ እንዳልሆነ

ምዕራፍ ፰፡ ፍቅር እንደሚያንጽ

-ሌላው ከሚሰናከል የተፈቀደልንንም መተው እንደሚገባ

ምዕራፍ ፱፡- ጳውሎስ ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ ብሎ እንደተናገረ

-ጳውሎስ አይሁድን ለመሳብ እንደ አይሁዳዊ እንደሆነ፣ ሕግ ያለው ሲሆን ሕግ እንደሌላቸው እንደሆነ

-ታገኙ ዘንድ ሩጡ እንደተባለ

ምዕራፍ ፲፡- እስራኤላውያን ከጥም አውጥቶ ያረካ መንፈሳዊ ዓለት ክርስቶስ እንደሆነ መነገሩ

-እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ መባሉ

-እግዚአብሔር ከሚቻለን በላይ እንደማይፈትነን

-ጣዖትን ከማምለክ መሸሽ እንደሚገባ

-የባልንጀራችንን ጥቅም እንጂ የራሳችንን ጥቅም ብቻ በመፈለግ እንዳንኖር

-የምናደርገውን ሁሉ ስለእግዚአብሔር ክብር ማድረግ እንዲገባን

ምዕራፍ ፲፩፡- ጳውሎስ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ እንዳለ

-ወንድ ልጅ ራሱን ተከናንቦ መጸለይ እንደማይገባው

-ሴት ስትጸልይ ራሷን መሸፈን እንደሚገባት

-ሴት ራሷን ባትሸፍን ጸጉራን ትቆረጥ መባሉ

-ወንድ ጸጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንደሚሆንበት

-ሳይገባው የክርስቶስን ሥጋና ደም የተቀበለ ፍዳ እንዳለበት

ምዕራፍ ፲፪፡- በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ኢየሱስ ጌታ ነው የሚል እንደሌለ

-መንፈስ አንድ ቢሆንም ጸጋ ግን ልዩ ልዩ እንደሆነ

-ሁላችንም የክርስቶስ አካል እንደሆንን

ምዕራፍ ፲፫፡- እምነት ሁሉ ኖሮን ፍቅር ከሌለን ከንቱ እንደሆንን

-ፍቅር እንደሚታገሥ፣ ቸርነትን እንደሚያደርግ፣ እንደማያስቀና፣ እንደማያስመካ፣ በደልን እንደማይቆጥር፣ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ከዐመፃ ጋር ደስ እንደማይለው፣ ለዘወትር እንደማይወድቅ

-እምነት፣ ፍቅር፣ ተስፋ ጸንተው ይኖራሉ መባሉ

ምዕራፍ ፲፬፡ በልሳን ስለመናገር መገለጹ

-ለክፋት ነገር እንደ ሕፃናት መሆን በአእምሮ ግን መብሰል እንደሚገባ መነገሩ

-እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ እንዳልሆነ

-ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ መባሉ

-ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር እንደሆነ

-ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን እንደተባለ

ምዕራፍ ፲፭፡ ጳውሎስ ራሱን ጭንጋፍ ማለቱ

-ስለክርስቶስ ትንሣኤ መነገሩ

-ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን እንደተነሣ

-ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል እንደሚያጠፋ

-ሞት ድል በመነሣት እንደተዋጠ

-ስለ ትንሣኤ ሙታን መነገሩ

ምዕራፍ ፲፮፡ ለቅዱሳን (ለምእመናን) ገንዘብ ማዋጣት እንደሚገባ

-ንቁ በሃይማኖት ቁሙ፣ ጎልምሱ፣ ጠንክሩ መባሉ

-ሁሉ በፍቅር ይሁን መባሉ

-በተቀደሰ አሳሳም እርስ በእርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ እንደተባለ

ሁለተኛ ቆሮንቶስ

ምዕራፍ ፩፡ የክርስቶስ መከራ በእኛ ላይ ሲበዛ መጽናናታችንም በክርስቶስ እንደሚበዛ መነገሩ

-እግዚአብሔር የታመነ እንደሆነ

ምዕራፍ ፪፡ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሥርዓት አላጸናባችሁም እንዳላቸው

ምዕራፍ ፫፡ ኃይላችን ከእግዚአብሔር ስለሆነ ከእኛ ከራሳችን እንደሆነ አድርገን ምንም ልናስብ እንደማይገባን

-የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት ነጻነት አለ መባሉ

ምዕራፍ ፬፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ ነው ብለን እንደምንሰብክ

-ጳውሎስ መከራን እንቀበላለን ግን አንጨነቅም፣ እንናቃለን ግን ተስፋ አንቆርጥም፣ እንወድቃለን ግን አንጠፋም ብሎ እንደተናገረ

-ዘወትር የክርስቶስን ሞት በሥጋ መሸከም እንደሚገባ

ምዕራፍ ፭፡ በሰማይ የሰው እጅ ያልሠራው ዘለዓለማዊ ቤት እንዳለ መነገሩ

-ሁልጊዜ እመኑ፣ ጨክኑም እንደተባለ

-ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት እንደምንቆም

-በክርስቶስ የሆነው ሁሉ አዲስ ፍጥረት ነው እንደተባለ

ምዕራፍ ፮፡ ራሳችንን አቅንተን የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንሁን መባሉ

-ተጠራጣሪዎች አትሁኑ መባሉ

ምዕራፍ ፯፡ ራሳችንን ማንጻት፣ ሥጋችንን አለማርከስ፣ ነፍሳችንን አለማሳደፍ እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን በመፍራት የምንቀደስበትን መሥራት እንደሚገባን

-ስለእግዚአብሔር ተብሎ የሚደረግ ነዘን የዘለዓለም ሕይወትን የሚያሰጥ ንስሓ እንደሆነ

ምዕራፍ ፰፡ በእርሱ ድህነት እኛ ባለጸጎች እንሆን ዘንድ ክርስቶስ ስለእኛ ራሱን ድሃ እንዳደረገ

ምዕራፍ ፱፡ እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን እንደሚወድ

ምዕራፍ ፲፡ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ መባሉ

-እግዚአብሔር ያከበረው እንደሚከብር መነገሩ

ምዕራፍ ፲፩፡ ሰይጣን የብርሃን መልአክ እንደሚመስል

-ቅዱስ ጳውሎስ ልዩ ልዩ መከራ እንደደረሰበት መናገሩ

ምዕራፍ ፲፪፡ ጳውሎስ ራእይ እንዳየ መናገሩ

ምዕራፍ ፲፫፡ በሃይማኖት ጸንታችሁ እንደሆነ ራሳችሁን መርምሩ እንደተባለ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች

ምዕራፍ ፩፡ ጳውሎስ እኛ ካስተማረናችሁ ወንጌል ሌላ መልአክም ቢሆን ቢሰብክላችሁ የተወገዘ ይሁን እንዳለ

-ጳውሎስ ያስተማርኳችሁን ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ ገለጠልኝ እንጂ ከሰው አልተቀበልኩትም እንዳለ

ምዕራፍ ፪፦ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንደማያዳላ

ምዕራፍ ፫፦ አብርሃም በእግዚአብሔር እንዳመነና ጽድቅም ሆኖ እንደተቆጠረለት

-ተስፋ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንደሆነ

-ኦሪት ወደ ክርስቶስ መሪ እንደሆነችን

ምዕራፍ ፬፦ ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን እንደላከውና ከሴትም እንደተወለደ

-ልጆች ከሆንን በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሾች እንደሆንን

-ለመልካም ሥራ መቅናት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፭፦ ጸንተን መቆምና በባርነት ቀንበር መኖር እንደማይገባን

-ለወንድሞቻችሁ በፍቅር ተገዙ መባሉ

-በመንፈስ መኖር እንጂ የሥጋን ፈቃድ ማድረግ እንደማይገባ

-የሥጋ ሥራዎችና የመንፈስ ሥራዎች እንደተገለጹ

-እርስ በእርስ መተማማት እንደማይገባ

-የሥጋ ሥራዎችን የሚያደርግ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማያይ

ምዕራፍ ፮፦ የተሳሳተ ሰው ቢኖር ቅንነት ባለው ልቡና አጽኑት መባሉ

-እያንዳንዱ የባልንጀራውን ሸክም ይሸከም መባሉ

-በጎ ሥራ መሥራትን ቸል ማለት እንደማይገባ

-ሳለን ለሁሉ መልካም ማድረግ እንደሚገባን

-ጳውሎስ ዓለሙ በእኔ ዘንድ የሞተ ነው፣ እኔም በዓለሙ ዘንድ የሞትኩ ነኝ እንዳለ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን

ምዕራፍ ፩፦ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካሉና በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ እንደሆነች

ምዕራፍ ፪፦ ድኅነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ

-ክርስቶስ ሰላማችን እንደሆነ

-ክርስቶስ ጥልን በመስቀሉ እንደገደለ

-በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ እንደታነጽን

ምዕራፍ ፫፦ የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ መበርታት እንደሚገባ

ምዕራፍ ፬፦ እርስ በእርሳችን በፍቅር መታገሥ እንዲገባ

-አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ አንድ ጌታ እንዳለ

-በአእምሯችን መንፈስ መታደስ እንደሚገባ

-ውሸትን አስወግደን ከባልንጀሮቻችን ጋር እውነትን መነጋገር እንደሚገባ

-ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ እንደተባለ

-በቁጣችሁ ፀሐይ አይግባ እንደተባለ

-ከአፋችሁ በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል አይውጣ እንደተባለ

-መራርነት፣ ንዴት፣ ቁጣ፣ ጩኸት፣ መሳደብ፣ ክፋት ከእናንተ ይወገዱ እንደተባለ

-እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኅ ሁኑ መባሉ

ምዕራፍ ፭፦ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ተከተሉ መባሉ

-በፍቅር መመላለስ እንደሚገባ

-የሚያሳፍር ነገር፣ የስንፍና ንግግርና ዋዛ እንደማይገባ

-አመንዝራና ጣዖትን የሚያመልክ በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት እንደሌለው

-ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ እንደተባለ

-ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ እንደተባለ

-የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ መባሉ

-ለጌታ በልባችን መቀኘትና መዘመር እንደሚገባ

-ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት እንደሚገባቸው ባሎችም ሚስቶቻቸውን መውደድ እንደሚገባቸው

-ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ባልም ሚስቱን እንደራሱ ይውደዳት መባሉ

ምዕራፍ ፮፦ ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ እንደሚገባቸው

-እናትና አባቶች ልጆቻቸውን ማስቆጣት እንደማይገባቸውና በተግሣጽ ማሳደግ እንደሚገባ

-ባሮች ለጌቶቻቸው በልብ ቅንነት መገዛት እንደሚገባቸው ጌቶችም ባሮችን በፍቅር እንዲንከባከቧቸው

-የዲያብሎስን ሽንገላ ለመቃወም የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር መልበስ እንደሚገባ

-ሁልጊዜ መጸለይ እንደሚገባ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ

ምዕራፍ ፩፦ ፍቅራችን በዕውቀትና በማስተዋል ሊሆን እንደሚገባ

-ከሁሉ ይልቅ ከክርስቶስ ጋር መኖር እንደሚሻል

-ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ መባሉ

ምዕራፍ ፪፦ እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንደሚሻል (አስቦ) በትሕትና መኖር እንደሚገባ

-ሰው የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የባልንጀራውንም ጥቅም መመልከት እንደሚገባው

-የክርስቶስ ስም ከስም ሁሉ የሚበልጥ ስም እንደሆነ

-በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ የራሳችንን መዳን መፈጸም እንደሚገባን

ምዕራፍ ፫፦ በጌታ ደስ ሊለን እንደሚገባ

-ከክፉዎች ሰዎች መጠበቅ እንዲገባን

-እኛ ሀገራችን በሰማይ ነው እንደተባለ

ምዕራፍ ፬፦ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ እንደተባለ

-ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ መባሉ

-ጌታ ቅርብ እንደሆነ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ቈላስይስ

ምዕራፍ ፩፦ በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ በማፍራት ማደግ እንደሚገባ

-ክርስቶስ የማይታይ አምላክ ምሳሌ እንደሆነ

-በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በክርስቶስ እንደተፈጠሩ

-ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነ

-ክርስቶስ በሞቱ በኩል እንዳስታረቀን

ምዕራፍ ፪፦ በሃይማኖት መጽናት፣ በክርስቶስ መታነጽ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፫፦ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም እንደተባለ

-ክርስቶስ ሕይወታችን እንደሆነ

-ከአፋችን ስድብንና የሚያሳፍርን ንግግር ማስወገድ እንዲገባ

-ውሸትን መነጋገር እንደማይገባ

-ምሕረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግሥትን፣ ፍቅርን መልበስ እንደሚገባ

-በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ መባሉ

-ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት እንደሚገባቸው፣ ባሎችም ሚስቶቻቸውን እንዲወዱና መራራ እንዳይሆኑባቸው

-ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ እንደሚገባቸው

-አባቶች ልጆቻቸውን ማበሳጨት እንደማይገባቸው

ምዕራፍ ፬፦ ጌቶች ባሮቻቸውን በጽድቅና በቅንነት ያዝዟቸው ዘንድ እንዲገባ

-ንግግራችን ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ሊሆን እንደሚገባ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ፩ኛ

ምዕራፍ ፩፦ ወንጌል በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንደመጣ

-የተሰሎንቄ ሰዎች በአካይያና በመቄዶንያ ለሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ እንደሆኗቸው

ምዕራፍ ፪፦ ጳውሎስ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለንም እንዳለ

-ሐዋርያት ክብርን ከሰው እንዳልፈለጉ

ምዕራፍ ፫፦ ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ እንደተላከ

ምዕራፍ ፬፦ ከዝሙት መራቅ እንደሚገባና በቅድስና መኖር እንደሚገባ መገለጹ

-እግዚአብሔር ለርኵሰት ሳይሆን ለቅድስና እንደጠራን

-በዳግም ምጽአተ ክርስቶስ ጊዜ ሙታን እንደሚነሡ

ምዕራፍ ፭፦ የጌታ መምጫ ቀን እንደማይታወቅ መገለጹ

-የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደራስ ቁር እየለበስን በመጠን መኖር እንደሚገባን

-ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ክርስቶስ ስለእኛ እንደሞተ

-እርስ በእርስ መመካከር እንደሚገባና አንዱ ሌላውን ሊያንጸው እንደሚገባ

-ያለሥርዓት የሚሄዱትን መገሠጽ እንደሚገባ

-ለደካሞች መትጋት እንደሚገባና ሁሉን መታገሥ እንደሚገባ

-በክፉ ፋንታ ክፉ መመለስ እንደማይገባና ለሁሉ መልካም ለማድረግ መትጋት እንደሚገባ

-ሁልጊዜ ደስ ሊለን እንደሚገባ

-በሁሉ ማመስገን፣ ሳያቋርጡ መጸለይ እንደሚገባ

-ሁሉን መፈተንና መልካሙን መያዝ እንደሚገባ

-ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር መራቅ እንደሚገባ

ሁለተኛ ተሰሎንቄ ፪ኛ

ምዕራፍ ፩፦ ጌታ በዳግም ምጽአት ጊዜ እርሱን የማያውቁትንና ለወንጌሉ የማይታዘዙትን እንደሚፈርድባቸው

ምዕራፍ ፪፦ የጥፋት ሰውና የዐመፅ ልጅ ሳይገለጥ ምጽአት እንደማይሆን፣ ይህ የዐመፅ ልጅም እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደሚል

-ስለሐሳዊ መሢሕ ምንነት መገለጹ

-ጸንተን መቆምና የተማርነውን ወግ መያዝ እንደሚገባን

ምዕራፍ ፫፦ ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም መለየት እንደሚገባ

-ሁሉም እየሠራ የገዛ እንጀራውን መብላት እንደሚገባው

አንደኛ ጢሞቴዎስ

ምዕራፍ ፩፦ የትእዛዝ ፍጻሜ ከንጹሕ ልብና ከበጎ ኅሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር እንደሆነ

-ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ሊያድን ወደ ዓለም እንደመጣ

ምዕራፍ ፪፦ እግዚአብሔርን በመምሰል በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን መኖር እንደሚገባን

-ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ መካከለኛ እንደሆነ

-ክርስቶስ ራሱን ለሁሉ ቤዛ እንዳደረገ

-ያለቁጣና ያለ ክፉ ሐሳብ የተቀደሱትን እጆች አንሥቶ መጸለይ እንደሚገባ

-ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትኑር መባሉ

-ሴት በዝግታ ልትኖር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን እንደማይገባ

ምዕራፍ ፫፡ ኤጲስ ቆጶስ የማይነቀፍ፣ ራሱን የሚገዛ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ገንዘብን የማይወድ እንዲሆን

-ዲያቆናት ጭምቶች፣ በሁለት ቃል የማይናገሩ፣ በንጹሕ ኅሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ እንደሚገባቸው

-ሴቶች ጭምቶች፣ የማያሙ፣ ልከኞች፣ በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለጥርጥር ታላቅ እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡ በኋለኞች ዘመናት ብዙዎች የሚያስቱ መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ እንደሚስቱ

-እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነና ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ስለሚቀደስ የሚጣል ምንም እንደሌለ

-እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ እንደሚገባ

-እግዚአብሔርን መምሰል የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ እንደሚጠቅም

-በቃልና በኑሮ፣ በፍቅርም፣ በእምነትም፣ በንጽሕናም ለሚያምኑት ምሳሌ መሆን እንደሚገባ

-የተሰጠንን ጸጋ ቸል ማለት እንደማይገባ

ምዕራፍ ፭፡ ሽማግሌዎችን እንደ አባት፣ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፣ የሸመገሉትን ሴቶች እንደ እናት፣ ቆነጃጅቶችን ሴቶች እንደ እኅት ማየት እንደሚገባ

-በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር እንደሚገባቸው

-በሌሎች ኃጢአት አለመተባበርና ራስንም በንጽሕና መጠበቅ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፮፡ እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ እንደሆነ

-ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር እንደሆነ

-መልካሙን የእምነት ገድል መጋደል እንደሚገባ

-ያለእድፍና ያለነቀፋ ሆነን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ እንደሚገባን

-በሚያልፍ ባለጠግነት ተስፋ ማድረግ እንደማይገባ

-የተሰጠንን አደራ መጠበቅ እንደሚገባን

ሁለተኛ ጢሞቴዎስ

ምዕራፍ ፩፦ እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሀት መንፈስን እንዳልሰጠን

-ስለወንጌል መከራን መቀበል እንደሚገባ

-ክርስቶስ ሞትን እንደሻረ

-መልካሙን አደራ በመንፈስ ቅዱስ መጠበቅ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፪፦ ኢየሱስ ክርስቶስን ማሰብ እንደሚገባ

-ራስን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ መትጋት እንደሚገባ

-ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ መራቅ እንደሚገባ

-የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዐመፅ መራቅ እንደሚገባው

-ከክፉ የኅልማሳነት ምኞት መሸሽ እንደሚገባ

ምዕራፍ ፫፦ በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ራስ ወዳድ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ወዘተ እንደሚሆኑ

-ቅዱሳት መጻሕፍት መዳን የሚገኝበትን ጥበብ እንደሚሰጡ

-የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት እንደሚጠቅም

ምዕራፍ ፬፦ በጊዜውም አለጊዜውም መጽናት እንደሚገባ

-ነገርን ሁሉ በልክ ማድረግ እንደሚገባ

-የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ ማድረግ እንደሚገባ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ

ምዕራፍ ፩፦ የማይዋሽ እግዚአብሔር ተስፋን እንደሰጠ

-ኤጲስ ቆጶስ የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ መሆን እንደሚገባው

-ኤጲስ ቆጶስ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ጻድቅ፣ ቅዱስ፣ ራሱን የሚገዛ እንዲሆን

-ለንጹሖች ሁሉ ንጹሕ እንደሆነ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም ነገር እንደሌለ

ምዕራፍ ፪፦ ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን መናገር እንደሚገባ

-ሽማግሌዎች ልከኞች፣ ጭምቶች፣ ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ መነገሩ

-አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የተገባ፣ የማያሙ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ሊሆኑ እንደሚገባ

-ቆነጃጅት ባሎቻቸውን የሚወዱ፣ ልጆቻቸውን የሚወዱ፣ ራሳቸውን የሚገዙ፣ ንጹሖች ሊሆኑ እንደሚገባ

-መልካምን በማድረግ ምሳሌ መሆን እንደሚገባ

-ባሮች በታማኝነት ማገልገል እንደሚገባቸው

-ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርን መምሰል እንደሚገባን

ምዕራፍ ፫፦ ለገዦችና ለባለሥልጣኖች መታዘዝና መገዛት እንደሚገባ

-የእግዚአብሔር ቸርነት ሰውን በመውደዱ እንደተገለጠ

-ጠማማን ሰው አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ከገሠጽነው በኋላ ካልተመለሰ መራቅ እንደሚገባ

-በመልካም ሥራ ለመጽናት መማር እንደሚገባ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና

-ፊልሞና የቀድሞ አገልጋዩን አናሲሞስን በፍቅር እንዲቀበለው ቅዱስ ጳውሎስ መጻፉ

የጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን

ምዕራፍ ፩፦ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና በነቢያት አድሮ እንደተናገረ

-እግዚአብሔር በኋላ ዘመን ሁሉን ወራሽ ባደረገው ልጁ እንደነገረን

-ክርስቶስ የአብ የባሕርዩ ምሳሌና የክብሩ ነጸብራቅ እንደሆነ

-ክርስቶስ ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን እንደወረሰ

-መላእክት ሰው ሁሉ መዳንን ይወርስ ዘንድ የሚያገለግሉ እንደሆኑ

ምዕራፍ ፪፡ አብ ለክርስቶስ እንደመሰከረለት

-አብ ለክርስቶስ ሁሉን አስገዛለት እንደተባለ

-ክርስቶስ የአብርሃምን ዘር እንጂ የመላእክትን እንዳልያዘ

-ክርስቶስ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን (ሐዋርያትን) እንደመሰለ

ምዕራፍ ፫፡ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን መመልከት እንደሚገባ

-ሁሉን ያዘጋጀ እግዚአብሔር እንደሆነ

-በእያንዳንዱ ቀን እርስበእርስ መመካከር እንደሚገባ

ምዕራፍ ፬፡ ያመንን ሰዎች ወደ ዕረፍቱ እንደምንገባ መገለጹ

-የእግዚአብሔር ቃል ሕያው፣ የሚሠራና የልብን ስሜት የሚመረምር እንደሆነ

-በእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ፍጥረት እንደሌለ

-ጸንተን ሃይማኖታችንን መጠበቅ እንደሚገባን

-ክርስቶስ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደእኛ እንደተፈተነ

ምዕራፍ ፭፡ ሊቀ ካህናት ስለኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው የሚመረጥ እንደሆነ

-ክርስቶስ በሥጋው ወራት ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን እንዳቀረበ

-ክርስቶስ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘለዓለም መዳን ምክንያት እንደሆነላቸው

ምዕራፍ ፮፡ በእምነትና በትዕግሥት የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን መምሰል እንደሚገባ

-ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ሊቀ ካህናት እንደሆነና ስለእኛ ቀዳሚ ሆኖ እንደገባ

ምዕራፍ ፯፡ ስለመልከ ጼዴቅ መነገሩ

-ታናሽ በታላቅ እንደሚባረክ

-ኦሪት ስላልጠቀመች እንደተሻረች

-የክርስቶስ የማይለወጥ ክህነት እንዳለው

ምዕራፍ ፰፡ የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ

ምዕራፍ ፱፦ የኦሪታ ቤተ መቅደስ አገልግሎት ምን ይመስል እንደነበረ መገለጹ

-የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት በፍየሎችና በሌሎችም እንስሳት ደም እንዳልሆነ

-የክርስቶስ ደም ኀሊናን እንደሚያነጻ

-ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ እንደሆነ

-ክርስቶስ አንድ ጊዜ ተሠውቶ የሚያድን መሥዋዕት እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፦ ክርስቶስ አንድን መሥዋዕት ለዘለዓለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደተቀመጠ

-ለፍቅርና ለመልካም ሥራ መነቃቃት እንደሚገባ

-በእግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ እንደሆነ

-ጻድቅ በእምነት እንደሚኖር

ምዕራፍ ፲፩፦ እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ እንደሆነ

-ዓለም በእግዚአብሔር እንደተዘጋጀ በእምነት እንደምናውቅ

-ያለእምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል

-በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበው በእምነት እንዴት እንደተጠቀሙ መገለጹ

ምዕራፍ ፲፪፦ እግዚአብሔር ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን እንደሚቀጣን

-በማክበርና በፍርሀት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደሚገባን

-አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፫፦ እንግዶችን መቀበል እንደሚገባ

-እንደታሰረ ሆነን እስረኞችን ማሰብ፣ እንደተጨነቀ ሆነን የተጨነቁትን ማሰብ እንደሚገባ

-መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር፣ መኝታውም ንጹሕ እንደሆነ

-በሴሰኞችና በአመንዝሮች እግዚአብሔር እንደሚፈርድባቸው

-ገንዘብን መውደድ እንደማይገባ

-የእግዚአብሔርን ቃል የነገሩንን ዋኖቻችንን ማሰብ እንደሚገባን

-ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለም ያው እንደሆነ

-ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕትን ማቅረብ እንደሚገባን

-መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈል እንደሚገባ

አንደኛ ጴጥሮስ

ምዕራፍ ፩፦ ለሰው ልጆች ሰለሚሰጠው የመዳን ጸጋ ነቢያት በትንቢት ተግተው እንደመረመሩ

-በክቡሩ የክርስቶስ ደም እንደተዋጀን

-እርስ በእርሳችን ከልባችን መዋደድ እንደሚገባን

-ዳግመኛ የተወለድነው ከሚጠፋ ዘር እንዳልሆነና በሕያውና ለዘለዓለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር እንደሆነ

ምዕራፍ ፪፦ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ግብዝነትን፣ ቅንዐትን፣ ሐሜትን ማስወገድ እንደሚገባን

-ክርስቶስ ሕያው ድንጋይ እንደተባለ

-ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ማቅረብ እንደሚገባ

-መንፈሳዊ ቤት ለመሆን መሠራት እንደሚገባ

-ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት መራቅ እንደሚገባ

-በአሕዛብ መካከል ኑሯችሁ መልካም ይሁን መባሉ

-ሁሉን ማክበር፣ ወንድምን መውደድ፣ እግዚአብሔርን መፍራት እንደሚገባ

-በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኀዘንን ቢታገሥ ምስጋና እንደሚገባው

-ክርስቶስ ሲሰድቡት መልሶ እንዳልተሳደበ፣ መከራን ሲቀበልም እንዳልዛተ

-ክርስቶስ ስለእኛ መከራን እንደተቀበለ

-ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ መኖር እንደሚገባን

ምዕራፍ ፫፦ ሴቶች ከሥጋዊ ልብስ ይልቅ መንፈሳዊ ልብስን ገንዘብ ማድረግ እንደሚገባቸው

-ሣራ ለአብርሃም ጌታ እያለች እንደተገዛችለት

-ባሎች ከሚስቶቻቸው ጋር በማስተዋል አብረው እንዲኖሩ መታዘዙ

-ርኅሩኅና ትሑት መሆን እንደሚገባ

-ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፋንታ መመለስ እንደማይገባ

-ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኮልን ከመናገር መከልከል እንደሚገባው

-የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን እንደሆኑ

-ስለጽድቅ መከራን መቀበል ብፁዕነት እንደሆነ

-ለሚጠይቁን መልስ ለመስጠት የተዘጋጀን መሆን እንደሚገባን

-ክርስቶስ በሥጋ እንደሞተና በመንፈስ ሕያው እንደሆነ

ምዕራፍ ፬፡ ክርስቶስ ስለእኛ በሥጋ መከራን እንደተቀበለ

-እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት መኖር እንደማይገባ

-ፍቅር የኃጢአትን ብዛት እንደሚሸፍን

-ስለክርስቶስ ስም ብንነቀፍ የክብር መንፈስ በእኛ ላይ እንደሚያርፍ

ምዕራፍ ፭፡ ትሕትናን እንደ ልብስ መታጠቅ እንደሚገባ

-እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወምና ለትሑታን ጸጋን እንደሚሰጥ

-እግዚአብሔር ስለእኛ ስለሚያስብ የሚያስጨንቀንን ሁሉ በእርሱ ላይ መጣል እንደሚገባን

-በመጠን መኖር እንደሚገባ

-ዲያብሎስን በእምነት ጸንተን መቃወም እንደሚገባ

ሁለተኛ ጴጥሮስ

ምዕራፍ ፩፡ ትጋትን ይዘን በእምነታችን በጎነትን መጨመር እንደሚገባ

-በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም በገዛ ራሱ ሊተረጉመው እንደማይገባ

-ትንቢት በሰው ፈቃድ እንዳልመጣ

ምዕራፍ ፪፡ ሐሰተኛ መምህራን ከቀድሞ ጀምሮ እንደነበሩ

ምዕራፍ ፫፡ በጌታ ዘንድ ሺ ዓመት እንደ አንድ ቀን እንደሆነ

-ጌታ ሁሉ ወደ ንስሓ እንዲጠጋ እንደሚታገሥ

-ክፉ ሰዎች መጻሕፍትን ለራሳቸው እንደሚያጣምሙ

አንደኛ ዮሐንስ

ምዕራፍ ፩፦ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነጻን

-ኃጢአታችንን ብንናዘዝ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚለን

ምዕራፍ ፪፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአታችን ማስተሥረያ እንደሆነ

-እግዚአብሔርን አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዙን ግን የማይጠብቅ ውሸተኛ እንደሆነ

-በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙን የሚጠላ እስካሁን በጨለማ እንዳለ

-ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል መባሉ

-ዓለምንና በዓለም ያሉትን መውደድ እንደማይገባ

-ዓለሙም ምኞቱም እንደሚያልፉ

-የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ለዘለዓለም እንደሚኖር

-ወልድን የሚክድ አብ እንደሌለው፣ በወልድ የሚታመን አብ እንዳለው

ምዕራፍ ፫፦ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን

-በክርስቶስ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን እንደማያደርግ

-ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ እንደሆነ

-የእግዚአብሔር ልጅ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ እንደተገለጠ

-ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን እንደማያደርግ

-ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር እንዳይደለ

-ወንድሙን የማይወድ በሞት እንደሚኖር

-ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ ገዳይ እንደሆነ

-ስለወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን መስጠት እንደሚገባን

-በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት ብቻ መዋደድ እንደማይገባ

-እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያውቅ

ምዕራፍ ፬፦ መንፈስን ሁሉ ማመን እንደማይገባን

-ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን እንደማያውቅ

-እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ

-እርስ በእርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚኖር

-እግዚአብሔርን ያየው ማንም እንደሌለ

-ፍጹም ፍቅር ፍርሀትን አውጥቶ እንደሚጥል

-እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ እንደሆነ

ምዕራፍ ፫፦ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን እንደሚያሸንፍ

-የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት እንደሌለው

-ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት እንደሆነ

-ራሳችንን ከጣዖታት መጠበቅ እንደሚገባን

ሁለተኛ ዮሐንስ

-ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ የማያምኑ አሳቾች እንደሆኑ

-የሠራነውን እንዳናጠፋ ለራሳችን መጠንቀቅ እንደሚገባን

-በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ እንደሌለው

ሦስተኛ ዮሐንስ

-በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን መምሰል እንደማይገባ

-በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር እንደሆነ

መልእክተ ያዕቆብ

ምዕራፍ ፩፦ በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ እንደሆነ

-እግዚአብሔር በክፉ እንደማይፈትን

-ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን እንደምትወልድ፣ ኃጢአትም ሞትን እንደምትወልድ

-ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ ይሁን መባሉ

ምዕራፍ ፪፦ ለሰው ፊት ማድላት ኃጢአት እንደሆነ

-ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ እንደሚሆን

-ክነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ እንደሆነ

ምዕራፍ ፫፦ ቅንዐትና አድመኝነት ባሉበት ቦታ ክፉ ሥራና ሑከት እንደሚኖሩ

ምዕራፍ ፬፦ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት እንደሚሆን

-እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወምና ለትሑታን ደግሞ ጸጋን እንደሚሰጥ

-ለእግዚአብሔር መገዛትና ዲያብሎስን ደግሞ መቃወም እንደሚገባ

-በጌታ ፊት ራስን ማዋረድ እንደሚገባ

-ሕይወታችን ጥቂት ጊዜ ታይቶ የሚጠፋ እንደሆነ

-ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት እንደሚገባ

-በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት እንደሆነ

ምዕራፍ ፭፦ ጌታ እስኪመጣ ድረስ መታገሥ እንደሚገባ

-የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን መመልከት እንደሚገባ

-በትዕግሥት የጸኑት ብፁዓን እንደሚባሉ

-መከራን የሚቀበል እንዲጸልይ፣ ደስ ያለው እንዲዘምር

-የታመመ ቢኖር ቀሳውስትን ዘይት ቀብተው እንዲጸልዩለት መጥራት እንዲገባው

-የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል እንደምታደርግ

-እርስ በእርስ ኃጢአትን መናዘዝ እንደሚገባ

መልእክተ ይሁዳ

-ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠ ሃይማኖት መጋደል እንደሚገባ

-የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስድብን እንዳልተናገረ

-በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችንን መጠበቅ እንደሚገባ

የዮሐንስ ራእይ

ምዕራፍ ፩፦ የዚህን መጽሐፍ የትንቢት ቃል የሚሰሙትና በውስጡም የተጻፈውን የሚጠብቁ ብፁዓን እንደሆኑ

-ክርስቶስ እንደወደደንና ከኃጢአታችንም በደሙ እንዳጠበን

-ክርስቶስ በሰማይ ደመና እንደሚመጣና የወጉት ሁሉ እንደሚመለከቱት

-ዮሐንስ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በመጽሐፍ ጽፎ መልእክት እንደላከ

-ዮሐንስ በሰባት መቅረዞች መካከል የሰው ልጅ የሚመስልን እንዳየ

ምዕራፍ ፪፡- ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን አለቃ ስለተላከ መልእክት

-ስለክርስቶስ ስም ብለን መታገሥ እንደሚገባን

-ንስሓ መግባት እንደሚገባ

-እስከ ሞት ድረስ መታመን እንደሚገባና በዚህም የሕይወት አክሊል እንደሚሰጥ

ምዕራፍ ፫፡- ሊሞቱ የደረሱትን ማጽናናት እንደሚገባ

-ድል ለነሣ ስሙ ከሕይወት መጽሐፍ እንደማይደመሰስ

-አክሊላችንን የሚወስድብን እንዳይኖር ያለንን አጽንተን መያዝ እንደሚገባን

ምዕራፍ ፬፡- ዮሐንስ ሰማያዊ ዙፋንን እንዳየና በዙሪያውም ኻያ አራት ወንበሮችና በእነዚያ የተቀመጡ ኻያ አራት አለቆች ተቀምጠው እንደነበር፣ በዙፋኑ ዙሪያ ደግሞ አራት እንስሶች እንዳየና እነዚህም ለእግዚአብሔር ምስጋናን ሲሰጡ እንዳየ

ምዕራፍ ፭፡- ዮሐንስ በራእዩ በሰማያዊው ዙፋን መካከል የታረደ በግ የሚመስል እንዳየ

ምዕራፍ ፮፡- ዮሐንስ ሰባት ማኅተሞች ሲፈቱ እንዳየ

-ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የተገደሉት ሰዎች ነፍሳት ስለደማችን ተበቀል ብለው ጌታን እንደለመኑት

ምዕራፍ ፯፡- ዮሐንስ በራእዩ አራት መላእክትን ማኅተም ይዘው እንዳየ

-ቅዱሳን እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑ

ምዕራፍ ፰፡- ዮሐንስ በራእዩ ሰባት መላእክትን በእግዚአብሔር ፊት ቆመው እንዳየ

-ሰባቱ መላእክት ቀንደ መለከት ይዘው በየተራ እንደነፉ

ምዕራፍ ፱፡- ዮሐንስ በራእዩ የተለያዩ መቅሠፍቶች እንደሚደርሱ ማየቱ

ምዕራፍ ፲፡- ዮሐንስ በራእዩ መጽሐፍ የጨበጠ መልአክ እንዳየ

ምዕራፍ ፲፩፡- አውሬው ሁለቱን ነቢያት እንደሚገድላቸው መነገሩ

-ኻያ አራቱ ካህናተ ሰማይ በግንባራቸው ወድቀው ለእግዚአብሔር እንደሰገዱ

-የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት በመቅደስ እንደታየች

ምዕራፍ ፲፪፡- ዮሐንስ በራእዩ ታላቅ ምልክት በሰማይ እንዳየ

-በሰማይ ሰልፍ እንደሆነና ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን እንደተዋጉት

-ሰይጣን እንደተጣለ

-ሰይጣንን ምእመናን በበጉ ደም የተነሣና ከምስክራቸው ቃል የተነሣ ድል እንደነሡት

ምዕራፍ ፲፫፡- ዮሐንስ ዐሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች የነበሩት አውሬን በራእዩ እንዳየ

-አውሬው በእግዚአብሔርና በስሙ ላይ በማደሪያውም ላይ፣ በሰማይ በሚኖሩት ላይም የስድብን ቃል ይናገር ዘንድ አፉን እንደከፈተ

-ብዙዎች ለአውሬው እንደሚሰግዱለት መነገሩ

ምዕራፍ ፲፬፡- ዮሐንስ በጉ በጽዮን ተራራ ላይ ቆሞ እንዳየ

-ስለእግዚአብሔር የሚሞቱ ብፁዓን እንደሆኑ

ምዕራፍ ፲፭፡- ቅዱሳን እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት

ምዕራፍ ፲፮፡- ዮሐንስ ሰባት መቅሠፍቶችን በራእዩ እንዳየ

-የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅን እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፯፡- ዮሐንስ ስለአንዲት ሴት ራእይ እንዳየ

-በጉ የጌቶች ጌታ፣ የንጉሦችም ንጉሥ እንደሆነ

ምዕራፍ ፲፰፡- ስለባቢሎን ውድቀት መነገሩ

ምዕራፍ ፲፱፡- ማዳንና ክብር ኃይልም ለአምላካችን እንደሆነ መነገሩ

ምዕራፍ ፳፡- ለአውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱት፣ በግንባራቸውና በእጃቸው ላይ ምልክቱን ያልጻፉት ከክርስቶስ ጋር ሺህ ዓመት ኖረው እንደሚነግሡ

ምዕራፍ ፳፩፡- ዮሐንስ በራእዩ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን እንዳየ

-የክፉ ሰዎች ፍጻሜያቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ውስጥ እንደሆነ

-ስለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ዮሐንስ በራእይ ማየቱ

ምዕራፍ ፳፪፡- ዮሐንስ በራእዩ የሕይወት ወንዝና የሕይወት ዛፍን እንዳየ

-እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደሥራው መጠን እንደሚከፍለው መናገሩ

-ክርስቶስ የሚያበራ የአጥቢያ ኮከብ እንደተባለ